# ይስማዕከ ወርቁ

# ዴር ጋዳ




ልቦለድ

፲፱፻፺፱ ዓ.ም
አዲስ አበባ

All Rights Reserved to Yismake worku.

✍ ዘፈለጠ ወዘሠረቀ በስልጣነ ክ.ን ወጥበብ ውጉዘ ለይኩን። © ይስማዕከ ወርቁ-፳፻፰

# DERTOGADA

A Novel by Yismake Worku

የመጀመሪያ ዕትም ሚያዝያ ፳፻፰ ዓ.ም

ሁለተኛ ዕትም ሰኔ ፳፻፰ ዓ.ም

ሦስተኛ ዕትም ሐምሌ ፳፻፰ ዓ.ም

አራተኛ ዕትም ነሐሴ ፳፻፰ ዓ.ም

አምስተኛ ዕትም ጥቅምት ፳፻፱ ዓ.ም

ስድስተኛ ዕትም ህዳር ፳፻፱ ዓ.ም

ሰባተኛ ዕትም ታህሣስ ፳፻፱ ዓ.ም

ስምንተኛ ዕትም ታህሣስ ፳፻፱ ዓ.ም

ዘጠነኛ ዕትም ሚያዝያ ፳፻፱ ዓ.ም

**ዋና አከፋፋይ ፡- አይናለም መጻፍት ቤት**

**አድራሻ፡-ከብሔራዊ ቴአትር ቤት ጀርባ**

**☎ 011 550 58 44/011 550 58 45**

የሽፋንና የውስጥ ዲዛይን፡-ይስማዕከ ወርቁ
ኮምፒዩተር ትየባ፡- መላኩ ኃ/ሚካኤል

**E-mail: ramatohara@gmail.com**

## መግለጫ

በዚህ በተራቀቀና በህዋ ቅርምት (space exploration) ዘመን በአማርኛ ተፅፎ ለመነበብ በቂ ብቃት ያለው ፊር ቀዳጅ ልቦለድ እነሆላችሁ።

ሀ) ቋንቋው እስከነ ታሪክ አወቃቀሩ እንከን አይወጣለትም፤ ከዚያም ጋር ከማንም ሌላ ፀሐፊ የሚለየው ይስማዕከ የራሱ «እንትን» አለው (style)።

ለ)ብዙ ሳይንስ ፊክሽን አንብቤም በሲኒማ አይቼም አውቃለሁ፤ ይሄ የምታነቡት ፀሐፊውንና እንዲፅፍ ቀስቀሰው ያስቀጠሉትን ሁኔታዎች ከግምት በማስገባት ስናነበው፣ ከማንኛቸውም ይስተካከላል።

ሐ) ትረካውን ከምዕራፍ ወደ ምዕራፍ ስንከተለው ልብ አንጠልጣል ነው፣ አንድ ነጠላ ታሪክ ይዞ ችክ አይልብንም፣ የብዙ ውስብስብ ታሪኮች ጭማቂ ሆኖ አንድ ገፅ ስንገለብጥ አዲስ ነገር እናገኛለን፤ በድርጊት የተሞላ ነው (ፍጥነቱ)።

መ) ሳይንስ፣ ስለላ፣ ሮማንቲክ፣ ታሪካዊ ልቦለድም ጭምር ነው….ከዚህ አንፃር፣ ትስስሮሻቸው እስካሁን ያልታዩንን የተለያዩ ክስተቶች አቀራኝቶ አቅርቦልናል። ትናንትን፣ ዛሬንና ነገን ያስተሳሰረ ተሻጋሪ ልቦለድ ነው።

ሠ) ይሄ የመጨረሻው ነጥብማ….ከሚያውጠነጥናቸው ሀሳቦች አንዱዋ ብቻ እቻት። ለቁሳዊ ሀብትና ለአዕምሮአዊ ሀብት ስለሚደረግ ትንቅንቅ። ደም ሀገር ወዳድነት… ማን ለራሱ ሲል ምን ተከፍሎት ማንን ወይስ ምንን ይሸጣል? ማንስ ለሀገሩ «እስከመጨረሻዋ ደም ጠብታ» ይፋለማል? ወዘተ… የተቀረውን አንባቢ ከወዘተ ጋር ቢወያይበት ይመረጣል።

ደራሲ ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር

## ምስጋና

የሁሉም ነገር አባቴ ዓለሙ ቢያድጊ ጌታሁን ...ያንተን ታላቅ አባትነት መመስከሪያ ቃል ካላቸው ገና ከዘመናዊው ትምህርት ጋር በደንብ ሳልተዋወቅ ጀምሮ የገዛሁልኝ መጻሕፍት ይመሰክሩልኝ፡፡ እነሆ የልጅ ቡራኬ፡፡

ደራሲ ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር (አቦይ) የዚህ መጽሐፍ ረቂቅ በኔ ቢረቀቅም ባንተ ደምቋል፡፡ በየትኛውም ዘመን ውስጥ ከየትኛውም ትውልድ ጋር መኖር የመቻልህ ምስጢር ይህ አንዱ ፈርጁ ነው፡፡ አዲስ ዘመን፣ አዲስ ትውልድና አዲስ እሳቤ አንተን አያስፈሩም፡፡ ያለፈኝን ዘመን ባንተ ኖሬያለሁና እነሆ ስብሐት ለአብ!

ጋሼ የሻው ተሰማ (ደራሲና ሀያሲ) በሌላ ቅንፍ ውስጥ የኮተቤው ወጌሻ....በጥበብ እጅ ሲታሽ የማይጠገን የስነፅሁፍ ውልቃት፣ የማይጠግግ ወለምታ እንደሌለ አይቻለሁና እነሆ ብዕሬን ለምስጋና አነሳለሁ፡፡ ደራሲና ገጣሚ በዕውቀቱ ስዩም፣ ዶ/ር ዮፍታሄ ስዩም፣ ደራሲና ገጣሚ እንዳለጌታ ከበደ፣ ደራሲና ገጣሚ ዘላለም ጌታቸው፣ ዶ/ር ከፈለኝ፣ አሜሪካዊው ደራሲ ዳንኤል ጆንሰን ሁላችሁንም ከጥበብ ማዕድ አይለይብኝ፡፡

ገጣሚ በለው ገበየሁ በቅንፍ ውስጥ የኔ ገማልያል... እነሆ የተዋረስነው ጋኔን ስሙ ሥነ ጽሁፍ ነውና በጠበልም በመገረፍም በስቅላትም አይለቅም፡፡ ብንሞትም አብሮን አይሞትም፡፡ እንግዳ ወርቅ ሀብቴ በቅንፍ ውስጥ የኔ ቤተ መጻህፍት... ያነበብከውን ሁሉ ለማዳመጥ መቃብራችን እስኪቆፈር ያቆየናል፡፡ ታድለን!

ፀጋ እንዳርጌ....ለዛ ሁሉ ልፋት ምስጋና በቂ ነው ወይ? ከሆነ እነሆ እስከ መጨረሻው ጊዜ የሚያቆይ ምርቃት ጀባ ብያለሁ፡፡ መላኩ ኃ/ሚካኤል፣ እመቤት እንዳለ፣ ብሩክ ተስፋዬ፣ቃልኪዳን ጌታቸው፣ ትዕግስት ሰለሞን፣ ፋሲካ ጌታቸው፣ ናርዶስ ፀጋዬ፣ መ/ር አላዛር ጌታቸው፣ አቶ ደረጀ ዋለ፣ ጌትነት ዳናና ድልዓለም አዩ መርቄያለሁና...አሜን በሉ፡፡



## መግለቢያ

ከላይኛው ደራሲ ዘንድ የተላከ ታላቅ መልእክ በመንፈቀ ሌሊት በሬን በርግዶ ገብቶ ከእንቅልፌ አባነነኝ፡፡ ራሴን ጎዝጉዤ በራሴ ላይ ተኛቼ ነበር፡፡ ከወርቃማ ክንፉ ላይ አንድ ላባ ነቅሎ ብዕር ቀርፆ ሰጠኝ፡፡ በታላቅ ሰሌዳ ላይም «ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ» ብሎህ ጻፍ አለኝ፡፡ ከነገረኝ ቃል አንዳች ባጎድል ከህይወት መፅሐፍ ላይ እንደሚሰርዘኝም አስጠነቀቀኝ፡፡

በሰጠኝ ብዕር ከላቤ ወዝ ቀለም እየጠቀስኩ ስከትብ የነገረኝን ቃል የሚናገሩ ገፀ ባህርያት (አምሳለ ሰብዓት) ከዘመኔ ጨለፍኩ፡፡ የፈጠርኳቸው ጥቂት አምሳለ ሰብዓት በዘመኔ ከማውቃቸውና የላይኛው ደራሲ ከፈጠራቸው ገፀ ባህርያት ጋር በሥጋ በነፍስ ተዛመዱ፡፡ በ'ርግጥ እግዜር የፈጠራቸው ገፀ ባህርያት የተሠሩት ከጭቃ ሲሆን እኔ መፍጠርን ከፈጠረኝ ተምሬ የፈጠርኳቸው አምሳለ

ሰብዓት ግን የተጨለፉት ከሰው ላይ ነው፡፡ ከ'ኔና ከመሰሎቼ ግዘፍ ነስተው፣ ከሰው ሥጋ ሥጋን፣ ከሰው ምኞት ምኞትን፣ ከሰው ህልም ህልምን...... ወስደው ፍፁም ሰው ፍፁም እነሱን ሆነው ተፈጠሩ፡፡

ሆኖም እኔ በፈጠርኳቸውና የላይኛው ደራሲ በፈጠራቸው አምሳለ ሰብዓት መካከል አንድ ልዩነት አለ፡፡ የላይኛው ደራሲ የፈጠራቸውን ገፀ ባህርያት ይገድላቸዋል፡፡ እኔ ግን አልገድልም፤ አላድንምም፡፡ ከሞቱም 'ራሳቸው ይሞታሉ እንጂ! ከዳኑም ራሳቸው ይድናሉ እንጂ፡፡ እኔም ከእነሱ ያልተሻልኩ ነኝና፡፡ ለመሞታቸውም ለመትረፋቸውም ተጠያቂ አለመሆኔን ስነግራቸው ፈነጠዙ፡፡ እንዲህም አልኳቸው፡፡ «እኔ ብዕር እንጂ ሰይፍ የለኝም፡፡ አልጠብቃችሁም፡፡ ለጉስቁልናችሁ....ለመደወያችሁ ሁሉ ማንም ተጠያቂ አይሆንም፡፡ ራሳችሁን እድኑ፡፡ ሁላችንም የራሳችን በሽተኞችና የራሳችን ዶክተሮች ነን፡፡ እኔ ራሴ የራሴ ታማሚ የራሴ አስታማሚ የራሴ ዶክተር የሆንኩ የላይኛው ደራሲ የፈጠረኝ እስተኔ ገፀ ባህርይ ነኝ፡፡ ሁላችንም የላይኛው ደራሲ የፈጠረን ገፀ ባህርያት ነን፡፡ አዎ፤ በእርግጥ ...እኔ ፈጣሪያችሁ ነኝ፡፡ ስለናንተ ሐጢአት ግን በመስቀል ላይ አልቸነከርም፡፡...... ስለእናንተም ከእናንተ በላይ አላውቅም፡፡...እኔ ከላይኛው ደራሲ የምለይበት አንድ ሌላ ነገር... ብትሞቱብኝ በእኔ ዘንድ የማወርሳችሁ ገሀነምና መንግሥተ ሰማያት አለመኖሩ ነው፡፡ ገሀነሙም መንግሥተ ሰማያቱም ያለው ከእናንተ ውስጥ ነው፡፡ በምድር ላይ ኃጥዕና ጻድቅ እኩይና ሰናይ ገፀ ባህርይ የለም፡፡ ከእናንተ በተቃራኒ የቆመ ኃይል እኩይ ሲላችሁ እናንተ ደግሞ መልሳችሁ እኩይ ትሉታላችሁ፡፡ ሁሉም ለራሱ ሰናይ ገፀ ባህሪ ነውና፡፡ ሰናይ እኩ ስል አላዳላም፡፡ ደረስኳችሁ እንጂ አልደርስባችሁም» ብዬ ስነግራቸው ሁላቸውም ተደሰቱ፡፡ የላይኛው ደራሲ ከፈጠራቸው ገፀ ባህሪያትም ጋር ተቀላቀሉ፡፡ ከአምሳለ ሰቦቼና

የላይኛው ደራሲ ከፈጠራቸው ገፀ ባህርያት ከህይወታቸው እየጨለፍኩ ይህን መጽሀፍ ጽፌ ስጨርስ ከተኛሁበት የቀሰቀሰኝ መልአክ ቀሪውን የህይወታቸውን ምስጢር እንዳልናገርባቸው ፍም በመሰለ ነበልባላዊ ሰይፉ ከንፈሮቼን አተማቸው። አስቀጥሎም ‹‹ዕቀብ ቃለ ተነብዮቱ ለዝንቱ መጽሐፍ እስመ በፅሐ ዘመኑ›› ብሎ በጥንታዊዉ የግዕዝ ቋንቋ ተናግሮኝ ክንፉን እያማታ ወደ መጣበት ተመለሰ። ‹‹ዘመኑ ቀርቦአልና የዚህን መጽሐፍ የትንቢት ቃል ጠብቀው›› ማለቱ ነው። የላይኛው ደራሲ ‹‹የፈጠርኩትን ላባ የት አባህ ጥለኸው መጣህ!?›› ብሎ እንዳይቆጣው የፈራ ይመስል ከወርቃማ ክንፉ ላይ ነቅሎ የሰጠኝን ላባም መልሶ ክንፉ ላይ ተክሎት ነበር የበረረው።

✍ ይስማዕከ ወርቁ



# ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ

ለሳይንቲስት ኢንጂነር ዶ/ር ቅጣው እጅጉ



# ቅድመ ታሪክ

**አሜሪካ፡-** በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1989 ዓ.ም። በአሜሪካ አየር ኃይል ቢሮ ውስጥ የተቀመጠውን ጥቁር መዝገብ የክፍሉ ዋና አዛዥ ሲያገላብጡት ከቆዩ በኋላ ሰፊው ጠረጴዛ ላይ በብስጭት ወረወሩት። የአሜሪካ አየር ኃይል አባል የነበረው ጌራ ከተልዕኮው እስከዛሬ አልተመለሰም። ባለክንፉ ፓይለት በመባል ይወደስ የነበረው ጌራ ከተሰወረ ጊዜ ጀምሮ የአሜሪካ አየር ኃይል አባላትና የጦር መኮንኖች ስሙን ሳያነሱት ውለው አያውቁም። ይህ ኢትዮ - አሜሪካዊ ወጣት ፓይለት ከመሰወሩ በፊት በአሜሪካ የህዋ ምርምር ማዕከል ናሳ ውስጥ ስሙ ከገነነው እውቁ ኢትዮጵያዊ ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝ እጅጉ ጋር በተደጋጋሚ አብሮ ታይቷል ይባላል። ከመሰወሩ በኋላ የአሜሪካ መንግሥት ኢንጂነር ሻጊዝን መርምሮት ነበር። እሱ ግን ስለጉዳዩ እንደማያውቅ ተናግሮ ድርቅ አለ። በአነስተኛዋ የጦር አውሮፕላን ወደ አፍሪካ እንደበረረ የሚጠረጠረው ጌራ ግን እስከ አሁን ሊገኝ አልቻለም።

ይህ ከሆነ ከሁለት አመት በኋላ እውቁ የሚሳዬል ባለሙያ ኢትዮ-አሜሪካዊዉ ሳይንቲስት ኮሎኔል ፍስሐ ስለረጅም ርቀት ቲወንጫፊ ሚሳዬል የጀመረውን ቀመር በጅምሩ ጠረጴዛው ላይ ትቶ ተሰወረ። "ኢትዮጵያ" በሚል ቅጽል ስም የሚጠሩት የሥራ ባልደረቦቹ ደርቀው ቀሩ። ስለ ኢትዮጵያ በስሜታዊነት ሲናገር ይቀልዱበት ነበር። አንዳንዴም «....አንተ ሰው!..... ወይ መንግሥቱ ኃይለማርያም ነህ! ወይም መንግሥቱ ኃይለማርያምን ውጠኸዋል!...." እያሉ ሲቀልዱበት ስቆ ዝም ይል ነበር። ይህ ኢትዮ-አሜሪካዊ የሚሳዬል ሳይንቲስት ከጭንቅላቱ በቀር ይዞት የጠፋው ቤሳ ቤስቲን የለም እቱባለ ቢወራም ሀብቱን ግን ከመሰወሩ በፊት ወደ ኢትዮጵያ እንዳሸሸ የአሜሪካ የመረጃ ሰዎች ደርሰውበታል ይባላል። ይህ ሰው በጠፋ በሶስተኛው ቀን የናሳው ሻጊዝ እጅጉ ከአንተ ጋር አብሮ ታይቷል በሚል ተመርምሮ ነበር። እሱ ግን "...አሁንስ ከኢትዮጵያ ያመጣችሁት ዶሮ ካለ እሱም ቢጠፋባችሁ እኔ ዘንድ እንዳትመጡ ስጋሁ" ሲል ተሳለቀ።

**እስራኤል፡-** መጋቢት 1990 ዓ.ም። በቴልአቪብ አቅራቢያ ምድር ውስጥ በተገነባው ህቡዕ የምርምር ጣቢያ ውስጥ በሥራ ከተጠመዱት ሳይንቲስቶች መሀል ሁለቱ ኢትዮጵያውያን ሳይንቲስቶች ሳይታሰብ የውሃ ሽታ ሆኑ። እነዚህን ሳይንቲስቶች ለመያዝ የእስራኤል ኮማንዶዎች ያልመነቀሩት ጉዋዳ ጎድጉዋዳ የለም ነበር። ነገር ግን እስከ አሁን ሊያገኙዋቸው አልቻሉም።

**ሰሜን ኮሪያ፡-** መስከረም 1991 ዓ.ም። የኮሪያ ዘማች ከነበሩትና ኮሪያ ከቀሩት ኢትዮጵያዊ አባቱ እና ከአንዲት ኮሪያዊት የተወለደው ኢትዮ-ኮሪያዊው ሳይንቲስት በሮቦቶች ከሚታገዘው ህቡዕ

የኒውክለር ማብላያ ጣቢያ መሰወሩ በምስጢር እንዲያዝ ተደረገ። ፍለጋው እስከ አሁን ቀጥሎ ነበር.... የበላው ጅብ ሊሙህ አልቻለም እንጂ።

**ህንድ፡-** ነሐሴ 1992 ዓ.ም። እውቁ የኮምፒዩተር ሳይንስ ሊቅ ግርማቸው ዘለቀ የሂማሊያ ተራራዎችን ለመጎብኘት እንደሄደ እስከዛሬ አልተመለሰም። በሄሊኮፕተር የታገዘው የህንድ ፖሊሶች ሀሰሳ መና ሆኖ ቀረ። በሂማሊያ ተራራዎች መሃል ቀልጦ የቀረው ግርማቸው ለህንድ አስፈላጊ ሰው ነበር ይባላል።

**ሩሲያ፡-** ጥቅምት1994 ዓ.ም። ወደ ቀድሞዋ ሶቭዬት ህብረት ለትምህርት ከተላኩት ኢትዮጵያውያን መካከል አንዱ ከመሔዱ በፊት "አሞራው" በሚል ቅጽል ስም ይጠራ ነበር። ባለብሩህ አዕምሮ ከመሆኑም በላይ ራሺያ ያየችበት ልዩ ተሰጥኦው በቀላሉ እንዳትለቀው ግድ አላት። ነገር ግን የራዳር ቴክኖሎጂ ሳይንቲስቱ "አሞራው" ከሩሲያ እጅ ከወጣ ከአራት አመት በኂላ አንድ የሩሲያ ጋዜጣ የመጥፋቱን ዜና አተመው።

**ቻይና፡-** ታህሣሥ 1995 ዓ.ም ኢንጂነር ሻጊዝ በምስጢር ወደቻይና በሮ ነበር። ባልታወቀ ምክንያት ድርድሩ አልሰመረም። እውቁ የናሳው ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝ እጅጉ ለቻይና የህዋ ምርምር ተቅዋም እንዲሠራ ቻይና ያቀረበችለትን ረብጣ ገንዘብ ረግጦ ሆንግ ኮንግን በለቀቀ ማግስት በቻይና የህዋ ምርምር ውስጥ ተቀጥሮ ይሠራ የነበረው ኢንጂነር ኢዩኤል አጥናፉ መሰወሩ ከቻይና የደህንነት ሰዎች ጆሮ ደረሰ።...... አንዲት ድምጽ አልባ አውሮፕላን ከቤቱ ጀርባ በድቅድቅ ጨለማ ስታርፍ ኢዩኤል ያለውን ሀብት በሙሉ በባንክ ወደ ኢትዮጵያ ለአንድ መነኩሴ አዛውሮ መመለሱ ነበር። መነኩሴው ደውለው ገንዘቡ እንደደረሳቸው ከነገሩት ከአርባ ደቂቃ በኂላ ከቤቱ ጀርባ ባረፈችው ድምጽ አልባ አውሮፕላን ቻይናን ለቆ ወጣ። ሆንግ ኮንግ በቻይና ኮማንዶዎች ብትታመስም ኢትዮጵያዊዉ የቻይና የህዋ ሳይንቲስቶች ባልደረባ የትም ሊገኝ አልቻለም። የቻይና የደህንነት ሰዎች የኢዩኤልን መሰወር ከኢንጂነር ሻጊዝ ወደ ቻይና መጥቶ መመለስ ጋር ቢያያዙትም እስካሁን ግን የተረጋገጠ ነገር አልተገኘም።

**ኩባ፡-** ጥር 1995 ዓ.ም። ፊደል ካስትሮ አንድ መርዶ ተነገራቸው። መርዶውን እንደሰሙ ወዲያው ላልተወሰነ ጊዜ ከኩባ ማንም እንዳይወጣ አዘዙ። የኩባ ኬላዎች በሙሉ ተዘጉ። የኩባ አውሮፕላኖችም ላልተወሰነ ጊዜ ከበረራ ታገዱ። በዛች ቀን ያልተፈተሸ ነገር ቢኖር የፊደል ካስትሮ ኪስ ብቻ ነውም ተብሎ ተቀልዷል። ተራ የህዝብ ማመለሻዎችና የቤት መኪናዎች በየመንገዱ በሰልፍ ተፈተሹ። ከሰማይ ጠቅስ ፎቆች እስከ ደሳሳ ጎጆዎች ተመነቀሩ። ኩባ ደብቃ ያኖረችው ኢትዮጵያዊ የሜድካል ላቦራቶሪ ሳይንቲስት ግን የትም ሊገኝ አልቻለም። የትም!



## አመክንዮ

**ኢትዮጵያ፡-** 1961 ዓመተ ምህረት። ጀምበር በአዲስ አበባ ሰማይ ላይ ልትጠልቅ አቅላልታ ነበር። አንድ የተበሳጨ መነኩሴ በብስጭት የምንኩስና ቆቡን ከራሱ ላይ መነጨቀው። ከራሱ ላይ የመነጨቀውን የምንኩስና ቀይ አስኬማ ከአዲስ አበባ እምብርት አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ግርጌ ወርውሮ ሲጥለው በዛ የሚያልፉ መንገደኞች በትንግርት እየተመለከቱት ነበር።

ከአራዳው ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን በታች ወደሚገኙት መሸታ ቤቶች እየተገላመጠ ወርዶ አማርጦ ገባ። ሲጠጣ ቢያመሽም ሸንቱ ከመምጣቱ በቀር ፍንክች አላለም ነበር። አሁንም ብቻውን እየተበሳጨ ከማንም ጋር ታንቲራ ሳይገጥም የጠጣበትን ሸኸሬታ ከፍሎ ሲወጣ በምናምንቴ የተወጠቀችውን ከረጢቱን በጉያው አጥብቆ ይዞ ነበር። "ወይኔ ዲዲሞስ!" ይላል በየደቂቃው። "ከአሁን ወዲህ ማንም አባ ዲዲሞስ ብሎ እንዳይጠራኝ! ማንም! .....እኔ አያሌው በላይሁን ነኝ። አያሌው በላይሁን! .....አያሌው በላይሁን ነኝ!.... አያሌው ጀግናው! .....ጀግናው አያሌው እንደ ዝንጆሮ ጭሮ ያደገው! ....ማንም ከአሁን በኂላ አባ ዲዲሞስ ብሎ እንዳይጠራኝ!..ማንሽም አባ እንዳትይኝ! አባሽን ፈልጊ!....." እያለ ወደ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ተመለሰ። ሸንቱ ፊኛውን እንደ ንፋፊት እንደ ወጠረው ነበር።

ከአቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ላይ ሸንቱን በረጅሙ እያንፎለፎለ "አንተ ድንጋይ! አሸናብሃለሁ!..." ሲል ባካባቢው የሚያልፉት ሰዎች መንገዳቸውን ገተው መሳቅ ዠመሩ።

"አንተ ድንጋይ! ...... አሸናብሃለሁ። ....ይኸው እኔ ግን አለሁ ..... እንቁልልጭ! አንተ ግን ድንጋይ ሆነሃል .....ድንጋይ ሆነህ ቀረህ። ተው ብየህ አልነበረም?..... አንተ ድንጋይ!..... ክፉ ቀንን ማለፊያ ጥበብ አልነገርኩህም ነበር?.... አንተ ድንጋይ!..... ሆን ብለህ ነው!...... ሆን ብለህ !....ክፉ ቀንን በጥበብ ከማለፍ በላይ ጥበብ የለም! ...አንት ድንጋይ! ....ይህንም ነግሬህ ነበር። ይህቺ ደም መላስ የለመደች ሀገር የምትለወጥ መስሎሃል! .....ቴዎድሮስን በላች! አልተለወጠችም።......ገብርዬን በላች! አልተለወጠችም። ....ምኒልክ ደከመላት!..አልተለወጠችም።...... ፋሲልን...በላች! አልተለወጠችም። አሉላን በላች! አልተለዉጠችም! አንተንም በላች አልተለወጠችም!...... የበላይን ደም ጠጣች! ይኸው አልጠረቃችም። ስንት ጀግኖች ሞቱላት.........አልተለወጠችም። አልነገርኩህም?! .....ጴጥሮስ! አልነገርኩህም?! ....አትሰማም። ወይኔ ዲዲሞስ! ወይኔ አያሌው በላይነህ! ...አንተ ብትኖር ኖሮ ይሄኔ አቡነ ዲዲሞስ እባል ነበር። የዚህች ሀገር ዕጣፋንታ በእጃችን ይወድቅ ነበር። እንለውጣት ነበር። ግን ሞትክ! ተው እያልኩህ ሞትክ! ጵጵስና ሳትሾመኝ ሞትክ።

ይኸው እኒህኛው ጳጳስ የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም አበምኔት እንኳ ያድርጉኝ ብላቸው ከለከሉኝ። አባ ዝንበሩን ሾሙት። አንተ ብትኖር ግን ወንበዴዎች ጳጳስ ሆነው አይሾሙም ነበር። እኔና አንተ የምናውቀው የዚህች ሀገር ውድ ምስጢር በወንበዴዎች እጅ አይገባም ነበር። አፈር ብላ!....አፈርስ በልተሃል አንተ ድንጋይ! እሸናብሃለሁ። አንተ ድንጋይ ስልጣን ፈልጌ እንዳይመስልህ! አበምኔትነት ስልጣን አለመሆኑን ታውቃለህ። ጵጵስናም ተራ ነገር መሆኑን አታጣውም። ለምን ስልጣኑን ሳትሰጠኝ ሞትክ? ለግሌ እንዳልሆነ እያወቅ! ለዚህች ሀገር ታላቅ ሥራ ልንሠራ ተስማምተን ከዳኸኝ አንተ ድንጋይ። እሸናብሃለሁ። ...አንት ድንጋይ! ጓደኞችህ ተመችቷቸው በማርቼዲስ ሲንሸራሸሩ ይኸው አንተ ድንጋይ ሆነህ ቀረህ። ድንጋይ! እሸናብሃለሁ..." እያለ ሲለፈልፍ አንድ ወጣት "ድንጋይ አይደለም! ....ድንጋይ አይደለም!..." እያለ በደም ፍላት ዘሎ ግብግብ ገጠመው።

"ድንጋይ ነው!" ሐውልቱ ላይ ሲሸናበት የነበረውን ፅቃውን አራግፎ ወደ ሱሪው ሰገሰገው። "ድንጋይ ነው!"

"ድንጋይ አይደለም!" እድሜው በግምት ወደ ሃያ አምስት አመት የሚጠጋው ወጣት ተንተገተገ። ወጣቱን ያውቀዋል። በዛ ወቅት አለ የሚባል ገጣሚ መሆኑን ያውቃል። ይህን ወጣት እዛው አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት አጠገብ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ስብሰባ ሲገባ በጊዜ አይቶት ነበር። ወጣቱ ከስብሰባው ሲወጣ ጠብቆ ሐውልቱ ላይ ሽንቱን መሽናቱ....... ከወጣቱ ጋር ግብግብ መግጠሙ ሁሉ ወጥመዱን በትክክል ማጥመዱንና ወጥመዱም በጊዜ መያዙን እያረጋገጠለት ነበር። አንገት ላንገት ተናነቁ። በቡጢ ሲቃመሱ ያ ወጣት በትክክል ፀጋዬ ገብረ መድህን መሆኑን እያጤነ ነበር። ማስታወቂያ ሚኒስቴር ተሰብስበው የነበሩት ሰዎች ገላገሏቸው፡

ወጣቱ ገጣሚ እየተበሳጨ ቤቱ ሲገባ በቅርብ ርቀት ሰውዬው እየተከተለው ነበር። ፀጋዬ ሌሊቱን አልተኛም፤ ሲፅፍ አደረ። ‹‹ጴጥሮስ ያችን ሰዓት›› የተሰኘውን ቴአትር በዛች ሌሊት ፅፎ እንዳገባደደ በደረቀው ሌሊት የሚፅፍበት ቤት በር ተንኳኳ። በሩ እደተከፈተ ሰውዬ ዘው ብሎ ወደ ውስጥ ገባ። ያኔ ፀጋዬ እየተንቀጠቀጠ ነበር። በሁዋላ ግን ሊያጠቃው እንዳልመጣ ተገነዘበ።

እንዲያውም በዛች ሌሊት የፃፈውን የቴአትር ረቂቅ አንስቶ ወረቀቶቹን እያተረማመሰ "እኮራብሃለሁ። ገና....ገና....ዓለም ሳታስበው ታከብርሃለች። ብዕርህን ወደ ሰገባው እዳትመልሰው። እየህ...ይህች አገር ህዝብ አላት ሰው ግን የላትም። እንጨት ብቻውን



ቆሞ ቤት አይሠራም። ማገር ያስፈልገዋል። ህዝብም ብቻውን ሀገር አይሆንም። አንድነቱን የሚጠብቁ ካስማዎች ያስፈልጉታል። የዚህች ሀገር አንድነት ካስማዎች እነ ቴዎድሮስ እነ ምኒልክ...... አሁን የሉም። አንተ እነሱን መሆን አትችልም። ራዕያቸውን ብትጋራ ግን እነሱን ትተካቸዋለህ። እነሱን ለመተካት ደግሞ ግዴታ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መሆን አይጠበቅብህም።" ንግግሩን አቁሞ ቅንድቡን ዓይኑ አፋፍ ድረስ አንጠለጠለና የፀጋዬን ዓይነ ውሀ ጠልቆ መረመረው። ፀጋዬ ምንም መልስ አልሰጠውም። ባግራሞት እየተመለከተ ዝም አለው።

በምናምንቴ ነገሮች ከተወጠቀችው ከረጢቱ ውስጥ አንድ ሰፊ ብራና መዝረጠና ጠረጴዛው ላይ ዘረጋው። የነተበው ጥንታዊው የብራና ገፅ ላይ በቀይ ቀለም የተቀረፀ ካርታ ይታያል። ፅሑፉ በጥንታዊው የግዕዝ ቋንቋ የተፃፈ ነው። የወሰል ምንጣፍ በሚያክለው የብራና ገፅ ላይ በጥቁር ቀለም ፲፱ የሚል ቁጥር ከላይኛው ህዳግ ላይ ይታያል።

"ማልልኝ!" አለው የፀጋዬን። "በኢትዮጵያ አምላክ ማልልኝ!" አለው እንደገና መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቀይ ቀለም የኢትዮጵያ ካርታ የሳለበትን ገፅ እያወጣ። ፀጋዬ እጁን እመፅሐፉ ላይ ሳያቅማማ አሳረፈ።

"ቴአትሩን ፅፈህ ጨርሰኸዋል?" አለው ስልቻው ውስጥ እጁን ልኮ ሌላ ነገር እየበረበረ።

"በግርድፉ......." ፀጋዬ መለሰለት።

"ጥሩ። ይህ ደግሞ ለቴአትሩ መዝጊያ የገጠምከው ግጥም ነው!" ፀጋዬ ለጴጥሮስ ያችን ሰዓት ቴአትር መዝጊያ የፃፈውንና «ሰቆቃወ ጴጥሮስ» የሚል ርዕስ የሰጠውን ግጥም አንስቶ ሰውየው ድምፁን ዘለግ አርጎ አነበበው። ድምፁ እንደ ሐምሌ ነጎድጓድ አስገምጋሚ ነው። "ገጣሚ በሆን!" አለ ፀጋዬ በልቡ አነባበቡ ደስ ብሎት።

ግጥሙን አንብቦ እንደጨረሰ "ግሩም ነው! .....ይበል ነው! ....ጨብጠኝ!" አለ ሰውየው። በደስታ ሰክሮ ሲጨብጠው መዳፉ አንበሳ የሚሰባብር ያህል ጠንከረበት። ጨብጦ ሲነቀንቀው እጁን ለመንቀል የሚታገል መሰለው። አጥብቆ ቢመታው ኖሮ በአንድ ስንዘራ ህቅ እንደ ሚያደርገው አመነ ፀጋዬ። ከዛም ሁሉም ነገር ገባው።

"ነገር ፈልጎኝ ነው ለካ።"

"መልካም! አሁን ነገሩ ተለወጠ ማለት ነው።አንድ ሥራ ላዝህ ነበር። ከባድ ሥራ። አሁን ግን በቀላሉ ሥራውን እንዲህ

ነው" አለ ሚራዥ ግንባሩን በመዳፉ አሻሽቶ:: "ከ1969 ዓመተ ምህረት ጀምሮ በደረሰብህ የልብ ህመም ምክንያት ብዙ ጊዜ የልብ ቀዶ ጥገና ተደርጎልሃል። ከዛም ወዲህ በየሁለት ወሩ ቀዶ ጥገና ይደረግልሃል። በየሁለት ሳምንቱም በሃኪም የመታየት ግዴታ አለብህ። ያሰቅቃል!" ዶ/ር ሚራዥ በማያውቀው ስሜት ራሱን ነቀነቀ።

"ለመሆኑ አንተ ማነህ?" ሲል ዶክተሩን በጥሞና እየተመለከተ ጠየቀው ሻጊዝ። "እንዴት እንድታክመኝ ፈቀዱልህ?"

"እዎ.....እክሜህ አላውቅም። የህክምናህን ጉዳይ ግን ብዙ ጊዜ እከታተል ነበር። ይህን ጊዜም ስናፍቅ ነበር። ያገኘኋቸውን መረጃዎች ላካፍልህ ስጠብቅ ነበር። ይኸኛውን ቀዶ ጥገና ብቻዬን አይደለም ያደረኩልህ። ከሌሎች ዶክተሮች ጋር በመሆን ነው። ቀዶ ጥገናውን በበላይነት እንዲመራ የተወከለው ሐኪም ዶ/ር ሉስ ካን ባልታወቀ ጉዳይ ወደ ሌላ ሆስፒታል በመዛወሩና ተረኛም ስለነበርኩ ተክቼው እንድሠራ ተደርጓል። በእርግጥ እስካሁን እኔን አታውቀኝም። አሁን ተዋውቀናል። የሀገርህ ሰው በመሆኔ ብቻም ሳይሆን የሙያ ግዴታዬና ህሊናዬ የሚጠይቀኝ በመሆኑ ነው የጤንነትህን ጉዳይ በጥብቅ መከታተል የጀመርኩት" በረጅሙ ተንፍሶ ንግግሩን ቀጠለ።...........“አንተ እኔን ባታውቀኝ አይገርምም። የሚገርመው እኔ አንተን ባላውቅህ ነው። በእርግጥ ኢትዮጵያውያን ስላንተ ማወቅ ,ጀመሩት በቅርቡ ነው።.... በቅርቡ። ስላንተ በጣም የሚታወቀው በሰለጠነው ዓለም አካባቢ ነው። ስላንተ ብዙም ባይሆን በጥቂቱ ለማወቅ ችያለሁ። ከመገናኛ ብዙሃንና ከሰዎች አንደበት ብዙ ሰምቻለሁ። በህዋ ምርምር ዓለማችን ካፈራቻቸው እውቅ ሳይንቲስቶች መሃል ግዙፍ ስም ያለህ ሳይንቲስት መሆንህን አውቃለሁ። በዚህ አጋጣሚ እንደምኮራብህ ልነግርህ እወዳለሁ። ልኮራብህም ይገባል። ኢትዮጵያም ልትኮራብህ ይገባል። በህዋ ምርምር አንቱ የተባለ አንድ ኢትዮጵያዊ ሳይንቲስት ማግኘት ቀላል አይደለም። ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጅ ነህ። ኢትዮጵያ እንዳንተ ያለ ሰው ለማፍራትና ለማሰልጠን ብዙ ቢሊዮን ዶላር ማፍሰስ ባስፈለጋት ነበር። ብቻህን ታግለህ እዚህ ደረጃ መድረስህ ለብዙ የሀገርህ ልጆች አርአያነቱ ላቅ ያለ ነው። ከዲፕሎማ ተነስተህ የአለማችን ታላቅ የህዋ ሳይንቲስት መሆንህ ለሀገርህ ሰዎች ታላቅ መነሳሳትን ይፈጥራል። ኢትዮጵያውያን አትንኩኝ ባዮች ብቻ ሳይሆኑ እድሉን ካገኙ መሰልጠንና መበልፀግ የሚችል አዕምሮ ያላቸው እንደሆኑ ለዓለም ታላቅ ምስክር ሆነሃል።"

"ለመሆኑ ሰነዱ በእጅህ ይገኛል?" ኢንጂነር ሻጊዝ በመደመም ጠየቀው። እሱ አቅቶት የተወውን ነገር ይህ ሰው እንዴት ሊደርስበት እንደቻለ ተደንቆ።

"ሙሉ አይደለም" አለ ዶ/ር ሚራዥ ትንሽ ትክዝ ብሎ።



"በእጅህ ስላለው.........." ኢንጂነር ሻጊዝ ሰውነቱ ላይ በተተካከሉት የህክምና መሣሪያዎች እንደተተበተበ ሳይነቃነቅ ጥቃቅን አይኖቹን ብቻ እያንቀዋለለ የዶክተሩን መልስ መጠባበቅ ጀመረ።

ዶክተር ሚራዥ የተረጋጋ መንፈስ አይታይበትም። ብዙ ጊዜም በር በሩን ይመለከታል። "ብቻ ግን አንድ ነገር አለ" ሚራዥ ቅጭም ብሎ በእጁ የያዛቸውን ወረቀቶች አርገፈገፋቸው።

"እዎ አውቃለሁ፤ አሁን ማወቅ የምፈልገው የደረስክበት ምስጢር ካለ ያንን ነው" ሻጊዝ በጥያቄ መልክ የግንባሩን ቆዳ ሸበሸበው።

"ነገሩ በቀላሉ የሚገባና ግልፅ የሆነ ነገር አይደለም። ሰነዱ ላይ ያለው ሪፖርት በትክክል የልብህን በሽታ ምንነት አይገልፅም። ብቻ የመጀመሪያው የልብ ቀዶ ጥገናህ ላይ የሆነ ጉዳይ ሳይኖር አይቀርም። ያሁኑ የልብ ቀዶ ጥገናህ ሲደረግ ያየሁትና..... የተደረገው ሌላ ሪፖርቱ የሚለው ሌላ። አሁንም ቢሆን የተፃፈው ሪፖርት ከበሽታህ ጋር የማይገናኝ ነው። የ.ማ.ይ.ገና.ኝ!» ተቁነጠነጠ።

«የሆስፒታሉን ዳይሬክተር ለማናገር ገብቼ ነበር። ያገኘሁት ምላሽ ምን እንደሚል ታውቃለህ? ‹አያገባህም አርፈህ ሥራህን ሥራ› ነበር ያሉኝ። እንዲያውም ይህን ክትትሌን ካላቆምኩ በሰዓታት ውስጥ ከሆስፒታሉ እንደሚያሰናብቱኝ በጥብቅ አስጠንቅቀውኛል። እኔ ደግሞ እንደዚህ አይነት ነገሮችን መጋፈጥ ደስ ይለኛል። ይህን ጉዳይ አንተ ቻል ብትለው እንኳ መጋፈጤን አላቆምም። አሜሪካ እንደምትፈልግህና እንደምታስፈልጋትም አውቃለሁ። ግን በዚህ መልኩ መሆን የለበትም። ነፃነትህንና ሰብአዊ መብትህን ከዚህም በላይ በህይወት የመኖር መብትህን መጋፋት ታላቅ ወንጀል ነው። የተደረገልህ ቀዶ ጥገና የተለየና በየትኛውም ከአሜሪካ ውጭ ያለ ሀገር ሊሰጥ የማይችል ነው..." ዶ/ር ሚራዥ ለማስረዳት ግራ ተጋብቷል።

"እሱንማ...... አውቃለሁ።......ከአሜሪካ ውጭ መታከም ስለማልችል አይደል እንዴ የዚህች ሀገር እስረኛ ሆኜ የቀረሁት?! እሱንማ አውቃለሁ» አለ ተስፋ በቆረጠ ድምፅ። "ይልቅ የተለየ የደረስክበት ምስጢር ካለ ንገረኝ። እርዳታህን እሻለሁ። የፈለከውን ያህል ለመክፈልም ዝግጁ ነኝ" አለ ሻጊዝ በተማፅኖ።

«እኔንም ይህ ጉዳይ ይመለከተኛል። አንተኮ ለሀገርህ ብቸኛ ሰው ነህ። አንተን በረዳ ረድቻት የማላውቃትን ሀገሬን መርዳት ቻልኩ ማለት ነበር። ግን እንዴት አድርጌ? በጣም በጥብቅ የተያዘ ምስጢር ይመስለኛል። ብቻ እግዚአብሔር ከረዳኝ ባደርግልህ ደስታውን አልችለውም ነበር።" ዶ/ር ሚራዥ አፍንጫው ላይ የተሰካውን ነጭ መነፅሩን አንስቶ ከነጭ ጋዋኑ

ኪስ ባወጣው መሐረቡ የአይኑን ሥር እየጠራረገ ተነስቶ ጠረጴዛው ላይ ያስቀመጠውን ላፕቶፕ ኮምፒዩተር ቁልፎች መነካካት ጀመረ፡፡

ኢንጂነር ሻጊዝ ግንባሩን ወደላይ እንደሸበሸበ ዶ/ር ሚራዥን በጥያቄ ይከታተለዋል፡፡ ከዕውቅናውና ከስኬቱ ጀርባ ውጣ ውረድ የበዛበት የህይወቱ ጉዞ ከአዕምሮው ተሰነቀረ፡፡

ጠፈርን ገዝተዋል ከሚባሉት እውቅ የህዋ ሳይንቲስቶች አንዱ የሆነው ኢንጂነር ሻጊዝ ለአሜሪካ የህዋ ምርምር ተቋም ናሳ ያበረከተው ግኝት ገና በ43 አመቱ በአሜሪካ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ማህበረሰብ ዘንድ እውቅናን አስገኝቶለታል፡፡

በናሳ ውስጥ የመንኮራኩር ሲስተም ዲዛይን ኢንጂነር ሆኖ ጨረቃ ላይ በመውጣት ሁለተኛ ሰው ከሆነው የአፖሎ ጠፈተኛ ቡዝ አልድሪን ጋር በመሆን ሁለት የህዋ መንኮራኩሮችን ዲዛይን አድርጓል፡፡ የጁፒተር፣ የሳተርን በተለይም በቀጣይ ለአሜሪካና ለዓለማችን ህያላን ሀገራት ማረፊያነት ተስፋ የተጣለባት ፕላኔት ማርስን ውስጣዊና ውጫዊ አካል የሚያጠናውን ልዩ የሳይንቲስቶች ቡድን መሪ በመሆን ለጠፈር ምርምር ያደረገው አስተዋፅኦ ቀላል እንዳልሆነ ይነገራል፡፡ በዚህ ወቅት የመሬትን ውስጣዊና ውጫዊ ሀብት ከመመርመሩም ባሻገር ስለ ሳተላይቶችና ራዳሮችም የጠለቀ እውቀት ካላቸው ሳይንቲስቶች ግንባር ቀደሙ ሳይንቲስት ነው፡፡

ይህ ሰው ወደ አሜሪካ ካገባ ጊዜ ጀምሮ በሠራው አስደናቂ ሥራ ምክንያት ከአንድ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት እጅ በጣም ጥቂቶች ብቻ የሚያገኙትን ሽልማት ተቀዳጅቷል፡፡ በተራቀቁ ላቦራቶሪዎችና በአሜሪካ ምስጢራዊ የቴክኖሎጂ ተቋማት ውስጥ በያዛቸው ጥብቅ የቴክኖሎጂ ምስጢሮች ምክንያት አንድም ቀን አንዲትም ደቂቃ ከጥበቃና ከክትትል ውጪ ሆኖ አያውቅም፡፡ እንዲያውም ወደ ኢትዮጵያ ከመጣበት ጊዜ ቀደም ብሎ ኢትዮጵያ የገባው የሲ.አይ.ኤ ቡድን ለደህንነቱ ሥጋት የሆኑ ነገሮችን ካጠናና ካስወገደ በኋላ ነበር አሜሪካ የፈቀደችለት፡፡ ኢትዮጵያ በመጣበት ጊዜ ይደረግለት የነበረው ጥበቃም አንድ አሜሪካዊ ባለስልጣን ከሚደረግለት ጥበቃ በላይ ነበር ይባላል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይቀርም ለተፈቀደለት ጊዜ ብቻ የሚያቆይ ምስጢራዊ ህክምና እንደተሰጠው እሱ ብቻ ነው የሚያውቀው፡፡ ፊጥኖ የተመለሰበትም ምክንያት ይህ ነበር፡፡ በግልፅ ከተቀጠሩለት እስከ አፍንጫቸው ከታጠቁ አጃቢዎቹ በተጨማሪ በዙሪያው የሚያንዣብቡ የሲ.አይ.ኤ ሰዎች በዓይነ ቁራኛ ይጠባበቁታል፡፡ ወደሚንቀሳቀስበት ቦታ ሁሉ እየተንቀሳቀሱ በጥብቅ ይጠብቁታል፡፡ ጠፈርን የገዛ የአሜሪካ



የጠፈር ምርምር ሳይንቲስት መሆኑ ብቻም ሳይሆን የቋጠረው የአሜሪካ የቴክኖሎጂ ምስጢር የበለጠ ጥበቃውን አክሮታል፡፡

ቻይና፣ ጃፓን፣ ኢራን፣ ህንድ፣ ፓኪስታን፣ ሰሜንኮርያ፣ እስራኤልና ሩሲያ ይህንን ሳይንቲስት በእጃቸው ለማስገባት ጥያቄያቸውን በምስጢር ሲያቀርቡለት ረብጣ ገንዘብም በመቋጠር ነበር፡፡ እስራኤልም ከነዚህ ሀገራት ጋር ያረገውን ግንኙነት ስታነፈንፍ ከኖረች በኋላ ጥያቄዋን አለመቀበሉን ስትረዳ ከእሷ በቀር ወደ የትኛውም ሌላ ሀገር እንዳይሄድ በተለይም በአረብ ሀገራት እጅ እንዳይገባ በስለላ ድርጅቷ ሞሳድ በኩል ጥብቅ ክትትል ለማድረግ ከሲ.አይ.ኤ ጋር ተቀላቅላለች፡፡ ከአሜሪካ መንጋጋ ፈልቅቀው ለመውሰድ የሚኳትኑትን ሀገራት አሻፈረኝ ቢላቸውም ክትትላቸውን ግን አላቋረጡም፡፡ በነዚህ ሀገራት ክትትል ምክንያትም ሞሳድና ሲ.አይ.ኤ የበለጠ ጥበቃቸውን እንዲያጠናክሩ አድርጓቸዋል፡፡ ይህንን ሳይንቲስት ሁሉም የዓለም ሀገራት ይፈልጉታል...ከኢትዮጵያ በቀር፡፡

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ቤቱ ከተከበበ ሶስተኛ ቀኑ ነው፡፡ ሽጉጡን ጭንቅላቱ ላይ እንደ ደቀነው በሩ በኃይል ተንኳኳ፡፡ «ገዳዮቼ እያንኳኩ ነው» ሲል ለራሱ ተናገረ፡፡ የኢንጂነሩ የቅርብ ሰው ለመሆን በመቻሉ ጉዳዩን እሱ ይዞት ቢቆይም ከባለፈው ስብሰባ ወዲህ ግን ሌላ ሁለት ደህንነቶች እንዲከታተሉት ተቀይረው መጥተዋል፡፡ የኢንጂነሩን መወገድ በሚቃወሙና በሚደግፉ ጎራዎች በተከፈለው በዛ ስብሰባ ላይ ያንፀባረቀው ሀሳብ ጉባኤውን ለሁለት ከገመሰው ወዲህ እሱ ራሱም ታዳኝ ሆኗል፡፡ ዋሽንግተን ነው ሲሉት ደንቨር እየታየ እስካሁን ያጋበሳቸውን መረጃዎችና ሰነዶች ጠራርጎ ይዞ ሲሸሽ ከርሞ ከሶስት ቀናት በፊት ነው ካሊፎርኒያ ውስጥ አሁን ባለበት ሁኔታ የተያዘው፡፡ ሲገቡ በርና መስኮቱን መሰባበር ሲጀምሩ ሽጉጡን ወደ ሽንጡ መልሶ በፍጥነት ሰነዶቹን ጠራርጎ በእሳት አያያዛቸው፡፡ ቤቱ በወረቀቶቹ ቃጠሎ ጢስ እንደታፈነ በድምፅና በምስል የተቀዱ መረጃዎችን እየሰባበረ ከጥቅም ውጭ አደረጋቸው፡፡ ባንዲት ብጣቂ ወረቀት ላይ አንድ ቃል ካሰፈረ በሁዋላ መልሶ ሽጉጡን ጭንቅላቱ ላይ ደቀነው፡፡.......

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ሻጊዝ ገና በልጅነቱ ነበር የተለያዩ ማሽኖችን የመፍታትና የመገጣጠም ፍቅር ያደረበት፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ቦንጋ ከቀሩት ጣሊያኖች የኤሌክትሪክ ሱቅ ጀምሮ፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ በወቅቱ በሩሲያውያን በሚተዳደረው የባህር ዳር ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ በሜካኒካል ኢንጂነሪንግ ዘርፍ የእርሻ ቴክኖሎጂን አጠና፡፡ ከባህር ዳር ፖሊቴክኒክ ተቋም በማዕረግ የተመረቀም ሲሆን ውጤቱም በተቋሙ ታሪክ ሁለተኛው ከፍተኛ ውጤት ነው፡፡

በኋላ ደግሞ በኢትዮጵያ የአውቶሞቲቭ ሰርቪስና ሴልስ ኩባንያ የቴክኒካል ዋና አማካሪ ማናጀር በመሆን ለሁለት አመታት ሠርቷል፡፡ በ1964 ዓ.ም በጃፓን ኦቨርሲስ ማህበር ባገኘው ነፃ የትምህርት ዕድል ወደ ጃፓን አመራ፡፡ በጃፓን ሄሮሺማ ዩኒቨርስቲ ኢንዱስትሪና ኦቶሞቲቭ ኢንጂነሪግን አጠና፡፡ በኦሳካ ዩኒቨርስቲም የጃፓኖችን የቴክኖሎጂ ምስጢር ለመረዳት ሲል ጃፓንኛ ቋንቋ ለመማር አላቅማማም፡፡ ከጃፓን ወደ አሜሪካ ሲያመራ በጠፈር ምርምር የመሳተፍ ህልሙን እውን ለማድረግ በመቋመጥ ነበር፡፡

አሜሪካም ከጃፓን የመጣውን ባለ ብሩህ አዕምሮ የቴክኖሎጂ ሰው እጁን ስማ ተቀበለችው፡፡ ወደ አሜሪካ ከገባ ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ የኤሮስፔስ ኩባንያዎች ሲሰራ ቆይቶ በ1969 ዓ.ም በአሜሪካ የጠፈር ምርምር ማዕከል ናሳ (NASA) ተቀጠረ፡፡

በናሳ ቆይታው የመንኮራኩር ሲስተም ዲዛይን ኢንጂነር በመሆን መንኮራኩሮችን ዲዛይን ማድረግ፣ መሥራትና መገጣጠም፡ መሞከርና ማምጠቅ...ተግባሩ ሆነ፡፡ በዚህ ወቅት ዝናው እየናኘ አውሮፓ ደረሰ፡፡ ለአውሮፓ ስፔስ ኤጀንሲም በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፡፡

በስፔስ ሲስተም ክፍል የበረራ ዳይናሚክ ሲሙሌተር እና 'ኔክስት ጀነሬሽን' ተብሎ የሚጠራው 'ግሎባል ፖዚሽን ሳተላይት ሲስተም' የፈጠራ ባለቤት ሳይንቲስት ከመሆኑም ባሻገር 'ስታር ዋርስ' ተብሎ የሚጠራውን የመከላከያ ሲስተም ቴክኖሎጂ ለማጎልበት የሳይንቲስቶችና የኢንጂነሮች ቡድን መሪ በመሆን ሠርቷል፡፡

ከእስራኤል አሜሪካዊት ባለቤቱ ሶስት ልጆች ቢወልድም ትዳሩ የሠመረ አልነበረም፡፡ የልጆቹን የአሳዳጊነት መብት ለማግኘት በፍርድ ቤት ለመከራከር ሕግ ማጥናቱ ብዙዎችን አስገርሟል፡፡ ብዙዎች ‹ለያንዳንዱ ችግሩ ዩኒቨርስቲ ገብቶ የሚማር ብቸኛው ሰው ሻጊዝ እጅጉ ነው› ይላሉ፡፡ በጠፈር ሲስተምና በኤሮኖቲካል ምህንድስና በከፍተኛ ውጤት በዶክትሬት ዲግሪ ከመመረቁም በተጨማሪ በቢዝነስ አድሚንስትሬሽንም የማስተርስ ዲግሪ አለው፡፡

ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝ በ1969 ዓ.ም በአሜሪካ የጠፈር ምርምር ማዕከል ናሳ ውስጥ ከተቀጠረ በኋላ በአሜሪካ የቴክኖሎጂ ማህበረሰብ ውስጥ ስሙ የገነነው በአጭር ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ግን ብዙም ሳይቆይ የልብ በሽተኛ ሆነ፡፡ ከዚያም በየሁለት ወሩ የልብ ቀዶ ጥገና ማድረጉን ቀጠለ፡፡ ከዚህ ቀዶ ጥገና በስተጀርባ ያለውን ምስጢር እሱም ቢሆን በውል አያውቀውም፡፡



በልቡ ህመም ምክንያት ከተወሰነ የአየር ክልል በላይ መውጣትና መብረር ባለመቻሉ የተነሳ እንጂ ጨረቃ ላይ በማረፍ የመደመሪያው ጥቁር መሆን ይችል እንደነበር ሁልጊዜም ይናገራል፡፡

ፊቱን ወደ አፍሪካ ማዞሩና በተለይም የሀገሩን ማዕድንና እምቅ የተፈጥሮ ሀብት የተማሩ ኢትዮጵያውያንን በማሰባሰብ በሳይንሳዊ ጥበብና በተራቀቀ ቴክኖሎጂ አማካኝነት አውጥቶ ሀገሩን ከድህነት አዘቅት ቶሎ መንጥቆ ለማውጣት በተነሳባት በዚህ ወቅት ክትትሉ ከቀን ወደቀን እየጠነከረበት መጥቷል፡፡ ብዙዎች እንደሚሉት ወደዚች ደሀ ሀገሩ ቢሄድ በሌሎች ሀገራት እጅ ላለመውደቁ አሜሪካ ማረጋገጫ የላትም፡፡ እስራኤልም ቢሆን ይህ ሳይንቲስት በአረብ ሀገራትና ፀረ እስራኤልና አሜሪካ አቋም ባላቸው ሀገራት እጅ እንዳይገባ ክትትሏን አጠናክራለች፡፡ ይህ ሰው የዓለማችንን ራዳሮች ሳተላይቶችና የመገናኛ አውታሮች በፈለገው ጊዜ መዝጋት የሚችል አእምሮያለው ሰው ነው፡፡

በፕላኔታችን ሰማይ ላይ የተበተኑት ጥቁር ሳጥን ወይም በምህፃረ ቃል ‹‹ሳሞስ›› በሚል ምስጢራዊ ስም የሚጠሩት ፀረ-ሚሳዬል መመልከቻ ሳተላይት ስልቶችና ሌሎች በየዘጠና ደቂቃው መሬትን እየዞሩ ሃምሳ ሺህ ወታደሮች በዓመት ውስጥ ከሚሰበስቡት መረጃ እጥፍ የሚበልጥ ጉዳይ የሚሰበስቡትን ሳተላይቶች ቢዘጋቸው የሚከተለውን መገመት ቀላል ነው፡፡ ከዚህም በላይ በብሩህ አእምሮው የሰበሰበውን ምስጢር በምንም መልኩ ለጠላቶቻቸው አሳልፎ ቢሰጥ አሜሪካም ሆነች እስራኤል እንኳን በንብ የጫነ አውሮፕላን ማንም ተራ ወንበዴ አሸመድምዶ የሚያፈራርሳቸው ተራ መንደሮች እንደሚሆኑ ያውቁታል፡፡ የአሜሪካን የቴክኖሎጂ ምስጢር እንደውሃ የጠጣው ይህ ሳይንቲስት ጠላቶቻቸው ምድርን የሚንጡ ተምዘግዛጊ ሚሳዬሎች ባለቤት በሆኑበት በዚህ ወቅት በጠላቶቻቸው እጅ ቢገባ የሚከፍሉትን ዋጋ ያውቁታል፡፡ በመሆኑም ይህንን ሳይንቲስት ከጥበቃው ባሻገር ከአሜሪካ የማያስወጣው ቢወጣ እንኳ ከሁለት ወር በኋላ እያጣደፈ የሚያመጣው የልቡ ጉዳይ ነው፡፡ ......................

ዶ/ር ሚራዥ የኮምፒውተሩን ቁልፎች ሲነካካ ከቆየ በኋላ ተመልሶ ወንበሩን ኢንጂነር ሻጊዝ ወደተኛበት አልጋ አስጠግቶ ተቀመጠ፡፡ ኢንጂነር ሻጊዝም አንዳች መላ ያገኘ መስሎት አይኖቹን በልጥጦ አፍ አፉን ተመለከተው፡፡

"ግዴለህም፡፡ ለዚህ ጉዳይ ጊዜ ስጠኝ፡፡ በየጊዜው የደረስኩበትን ሁኔታ ሪፖርት አደርግልሃለሁ፡፡ ጊዜና ጥብቅ ምርምር የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን ምስጢር እስከምንጨ ማወቅ ይገባናል" አለ ዶ/ር ሚራዥ አንድ ጣቱን ከንፈሩ ላይ ጣል አድርጎ፡፡

"ግን ቶሎ መሆን አለበት። የልቤ ጉዳይ ከተስተካከለ ...." አዕምሮው ወደ አፍሪካ ገሠገሠ........ ወደ ኢትዮጵያ።

"ሌላ ጥያቄ የሆነብኝ ነገር......" አለ ዶ/ር ሚራኸ አሁንም ጣቱን ከንፈሩ ላይ ጣል አድርጎ እያሰላሰለ ብድግ ብሎ። "ጀርባህ ላይ ያለውን ንቅሣት ልብ ብለሸው ታውቃለህ?" ሲል ጠየቀው፡፡ ‹‹ዴርቶጋዳ›› የሚለውን የጀርባው ንቅሣቱን ፅሁፍ ከጀርባው ዞሮ እየተመለከተ፡፡

"ንቅሣት?"

"አዎ..." አለው ሚራኸ። ‹‹ዶርቶጋዳ.....ስለ ሚለው ንቅሳትህ።፡››

"በወጣትነቴ ነው የተነቀሥኩት" አለ ኢንጂነር ሻጊዝ የወጣትነቱን ዘመን እያስታወሰ።

"ማነው የነቀሰህ?"'

"ማን ነበሩ? አዎ፡፡ አለቃ አያሌው ናቸው! አለቃ አያሌው፡፡"

"አለቃ አያሌው ማን ናቸው?" አለ ሚራኸ በጉጉት፡፡

"አያሌውን የማውቃቸው በልጅነቴ ቦንጋ እያለሁ ነው። ቦንጋ የከፋ ጠቅላይ ግዛት ከተማ ናት...ኢትዮጵያ ውስጥ" ኢንጂነር ሻጊዝ አለቃ እያሌውን በደንብ ለማስታወስ እየጣረ።

"በልጅነቴ አለቃ አያሌው ወደዚያች ከተማ ሲመጡ አስታውሳለሁ። በጣም ጎበዝ ተረትና ታሪክ አዋቂ ነበሩ። እኔ እንዲያውም አባቴ ካስተማሩኝ ተረት በላይ የነገሩኝ አለቃ አያሌው ናቸው። በተለይ በጣሊያን ጊዜ ስለነበረው የኢትዮጵያ ሁኔታ አብጠርጥረው የሚያውቁ ሰው ናቸው። እርሳቸው እንደነገሩኝ ከሆነ ከኢጣሊያ ጦር ጋር ተደባልቀው የውስጥ አርበኛ ሆነው ተዋግተው ነበር። ጣሊያን ሲባረር የንጉሡን መምጣት ተከትሎ ወደ ቦንጋ ከተማ መጡ። ቦንጋ የመጡበትን ምክንያት ማንም በውል የሚያውቅ የለም። ብቻ ቦንጋ ከቀሩ የጣሊያን ቤተሰቦች ጋር የሚኖር አንድ ዲምላ የሚባል ልጃቸውን ለመጠየቅ ከባህር ዳር ከተማ ተነስተው እንደመጡ ነግረውኛል። ጣሊያኖችን ሲያዩ ይደበቁ ነበር። ከልጃቸው ጋር ስለ ማይስማሙ ከእኔ ጋር ነበር ብዙ ጊዜ የሚያሳልፉት። ታሪክ ማውራት ይወዳሉ። ስለማዳምጣቸውም ይወዱኝ ነበር። በተለይ ከጣሊያኖች ጋር ስለምቀራረብና በኤሌክትሪክ ሱቃቸው ውስጥ እውል ስለነበር የልጃቸውን ሁኔታ እየተከታተልኩ እናግራቸውም ነበር። አባቴም በኢጣሊያ-ኢትዮጵያ ጦርነት ወቅት በፀረ ፋሽሽት ዘመቻ ጀብዱ የሠራ ወታደር ስለነበር ስለጦር ሜዳ ውሎው ይተርክልኝ ነበር። እሳቸውም የአባቴን አይነት ታሪክ ነበር የሚነግሩኝ። በጣም የተማሩ ሰው እንደነበሩ ተረድቻለሁ። የቤተክህነት ትምህርት በጣም ያውቁ ነበር። እንዲያውም የቤተ ክህነት ትምህርት እንድማር ይገፋፉኝም ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ



እንዳነብና ከእያንዳንዱ ስራዬ በፊት እግዚአብሔርን እንዳስቀድም ብሩን የከፈቱልኝ እርሳቸው ናቸው። ከጣሊያኖችም ጋር ብዙ ሞያ እንደቀሰሙ ነግረውኛል።" ኢንጂነር ሻጊዝ ለኒህ ሰው ልዩ ፍቅር ነበረው።

"እና ለምን ነበር ንቅሳቱን የነቀሱህ?"

"በህይወትህ ውስጥ ሊጠቅምህ የሚችል ከባድ ነገር ነው ብለው ነበር የነቀሱኝ። ለልጃቸው ማድረግ የፈለጉትን ነገር ከልጃቸው ጋር ስለማይስማሙ ለእኔ አደረጉልኝ። በወቅቱም ተማሪ ስለነበርኩ እንዲያውም ትምህርትን የሚገልፅ መድሃኒት መስሎኝ ነበር።"

"ትርጉሙን አልነገሩህም?"

"ትርጉሙ..." አለቃ አያሌው ትውስ አሉት .. ተናግረው የማይደክማቸው ሰው ነበሩ። ትርጉሙን ነግረውት ነበር። ግን ትኩረቱ ትርጉሙ ላይ አልነበረም። መድኃኒትነቱ ላይ እንጂ። የትምህርት መድኃኒት መስሎት ነበር......ዘኢያገድፍ። የማስታወስ ብቃትን የሚጨምር መድኃኒት።

"....‹ዶርቶጋዳ› ማለት ምን ማለት ነው?" ብሎ ሲጠይቃቸው ፈገግ ብለው "እንዲያ ነው ልጄ። እንዲያ ነው። ሚጠየቅ ያደርጋል ሊቅ። ጎበዝ ልጅ! ጉንዳኖች ውሃ ሲሻገሩ አይተህ ታውቃለህ?" ብለው መልሰው ጠየቁትና "ጉንዳኖች ውሃ ሲሻገሩ አይተህ ታውቅ ከሆነ በውሃው ላይ ተያይዘው ተያይዘው ይቆማሉ። ጉንዳኖች ተያይዘው በወንዝ ላይ በሚሠሩት መንገድ ሌሎች ብዙ ጉንዳኖች ይሻገራሉ። ተያይዘው ይሻገራሉ። ተደጋግፈው አስፈሪውን ወንዝ ይሻገሩታል። ባይያያዙና ባይደጋገፉ ግን አይቻላቸውም። አንዲት ጠብታ ዝናብ ለአንድ ጉንዳን ውቅያኖስ ብትሆንም ብዙ ጉንዳኖች አንድ ላይ ከተያያዙ ግን ውቅያኖስ መሻገር ይችላሉ። በመሆኑም ዶርቶጋዳ ማለት......" እስከዚህ የነገሩትን ነግሮት ሌላውን ግን ሊነግረው አልፈለገም። ይህን እሱ ብቻ ሊያውቀው የሚፈልገው ጉዳይ ነው።

"ትርጉሙን ሲነግሩኝ በትክክል አላዳመጥኳቸውም መሰለኝ። ትኩረቴ..... አዩህ..... የመሰለኝ የትምህርት መድሃኒት ነበር። ብዙ ነገር የማወቅ ጉጉት ስለነበረኝ መማር ነበር የዛ ወቅት ታላቁ ፍላጎቴ። ለረጅም አመታትም አእምሮዬ ንቅሳቱን በመድኃኒትነት ተቀብሎት ነበር። ልዩ ኃይል አእምሮዬ ውስጥ እንደሚሰራ በማመኔ በራስ መተማመኔን ከፍ አድርጎልኛል። ሁሉን ነገር ማድረግ እችላለሁ ለማለት እዳፈር ነበር። በውስጤ አንድ አጋዥ ኃይል አለ ብዬ በማመኔም በትምህርቴ አለም የተሳካልኝ ሰው እንድሆን አድርጎልኛል። ከባህር ዳር ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ከዲፕሎማ ተነስቼ ያለ ማጋነን ለሳተርን.....ለመሬት ... ለማርስና

ለጁፒተር ፕላኔቶች ምርምር የሳይንቲስቶች ቡድን መሪ ለመሆን ችያለሁ። ታላቅ የዳበረ ሥነ ልቦናም ነበረኝ።"

"አሁንም በዚህ ኃይል ታምናለህ?" ዶ/ር ሚራዥ ተገረመ።

"ማመንም አለማመንም አልችልም አሁን። በዚህ ጉዳይ ያደረኩት ሳይንሳዊ ጥናት የለም። በደፈናው ይሄ ነገር ውሸት ነው ማለት ደግሞ ኢሳይንሳዊ ነው። ያረጋገጥኩት ነገር እስከ አሁን የለም። ሥነ - ልቦናዊ ተፅዕኖው ግን ቀላል አልነበረም።" ኢንጂነር ሻጊዝ አለቃ አያሌው ከጀርባው የነቀሱትን ንቅሳት በመስታወት ካልሆነ በቀር ዞሮ ማየት ስለማይቻል ከ1960ዎቹ ወዲህ ብዙም ትኩረት ሰጥቶት አያውቅም። ረስቶታል ማለት ግን አይቻልም።

'ድግምት አሰርቶ ነው ጎበዝ ተማሪ የሆነው' ላለመባል ብዙ ጊዜ ጀርባውን ለማንም አያሳይም ነበር። እርሱ ግን ‹እኔ በተፈጥሮዬም ጎበዝ ነኝ። ይህ ንቅሳት በርግጥ ልዩ ኃይል ሊያጎናፅፈኝ ይችላል። ሰይጣናዊ ግን ሊሆን አይችልም። ሰይጣን እንዴት እውቀትን ሊገልፅልኝ ይችላል? ሰይጣን የሰውን ልጅ ትንሣኤና ስልጣኔ የሚደግፍ ከሆነ ሰይጣንነቱ ምን ላይ ነው? አእምሮን ብሩህ አድርጎ የሰዎችን የማስታወስ ችሎታ የሚያበለፅግ ሰይጣን ካለ እሱ እንዴት ጠላቴ ሊሆን ይችላል? ይልቅስ ጥበብ የእግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ጥበቡን ጥበብን ለሚፈልጉት ያድላል። አለቃ አያሌው ደግሞ ፈሪሐ እግዚአብሔር ያደረባቸው ሰው ናቸው። እሳቸው የሰይጣን ወዳጅ ከሆኑማ እኛ ሰይጣኖች ነን ማለት ነው። ሰው መጠበብ ሲያቅተው ጥበበኞችን ያጥላላል። ክፉ ስምም ይቀባል። ጠንቋይ ይላል። የኛ ሀገር ጥበበኞች ጠንቋይ እየተባሉ ሲወገዙ የፈረንሳይ ብልጣ ብልጦች የኛን ሀገር የጥበብ መፃሕፍት ወስደው በላቦራቶሪ ፈትሸው ዶ/ር ይባላሉ። ሰው መደንቆር ሲጀምር ጆሮውን ትርፍ ነሳ ይላል። ቢሆንም ሰው በራሱ ምስል ነው። እግዚአብሔር እኔን ለድንቁርና አልፈጠረኝም። አለቃ አያሌው በንቅሳት አእምሮ የሚከፍቷውን መድኃኒት ባይነቅሱኝም እኔ ብሩህ አእምሮ የተሰጠኝ ሰው ነኝ። አለቃ አያሌው ይህን ያደረጉልኝ ስለሚወዱኝ ነው። ሰው መደንቆር ሲጀምር ወሬኛና ሁሉንም ነገር ተቺ ይሆናል። ወሪያም ሁሉ!" ይላል ስለንቅሳቱ ሲያስብ። መልሶ ደሞ "ምን ይሆን?" ይላል።

ዶ/ር ሚራዥ ከኢንጂነር ሻጊዝ ጀርባ ላይ ያለውን ንቅሳት ያየው ቀዶ ጥገናውን በሚያደርግለት ወቅት ነበር። በጊዜው ልዩ ስሜት ተሰምቶታል። ንቅሳቱን ሲያይ። ረጅም ሰአታት የወሰደው የኢንጂነሩ የልብ ቀዶ ጥገና ከመጀመሩ ከአንድ ደቂቃ በፊት ለምርምራ የቀዶ ጥገናው ጠረጴዛ ላይ ሲያገላብጠው ነበር ከጀርባው ላይ ካለው ንቅሳት ጋር የተፋጠጠው። ቀዶ ጥገናው ካለቀ በኋላም ስለንቅሳቱ ሲያስብ ነበር። ኢንጂነሩ ከሰመመኑ ሙሉ በሙሉ ነቅቶ እስኪያናግረው ትዕግስቱ ቢያልቅም መጠበቅ ግን ግዴታው ሆኖ



ነበር። አሁን ከኢንጂነሩ ጋር ስለዚህ ጉዳይ መነጋገር ከመጀመሩ በጥቂት ቆይታ ውስጥ መግባባታቸው ስለ ንቅሳቱ ለሚጠይቀው ማንኛውም ጥያቄ መልስ እንደሚሰጠው ተስፋ አድርጓል። ከኢንጂነሩ ጀርባ ላይ ያለው "ዶርቶጋዳ" የሚለው የቆየ ንቅሳት ደብዘዝ ቢልም በደንብ ይለያል። ከጀርባው በኩል ትንሽ ገልበጥ አድርጎ ንቅሳቱን በደምብ ተመለከተው።

"ዶርቶጋዳ" ከሚለው የንቅሳቱ ጽሁፍ መሀል ያለው ‹ቶ› ፊደል በባለ ጉጥ መስቀል ቅርፅ የተሠራ ነው። በ‹ቶ› ፊደል የእናት ቀለበት ውስጥ በቀጭኑ የተፃፉ ቁጥሮች ይታያሉ። $54_{4}$ $9_{5}$ $10_{6}$ $29_{23}$ $77_{5}$ $30_{456}$ $52_{7}$ $33_{2}$ ፬፪፬ $97_{5}$ ከሚለው ትንሽና ትልቅ ሆኖ ከተፃፈው ቁጥር ቀጥሎ "ኦርያ ኢትዮጵያ" የሚል በቀጭኑ የተቀረፀ ቃል አለ። ከዚሁ ቀለበት ውስጥም $98_{123}$ $9_{6}$ $10_{67}$ $40_{567}$ $88_{123456}$ የሚል ቁጥር ይታያል። ከባለ ጉጡ መስቀል መስቀልያ ላይ "ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ" የሚል ቃል የተቀረፀበት ሲሆን በክንፍና በክንፉ መጨረሻ የአበባ ዕምቡጥ ከሚመስሉት የመስቀሉ ጫፎች ላይ "ቀጠሮ ቃል" እና "መራራ ክንፍ" የሚሉና ግራ የሚያጋቡ ቃላት ሰፍረዋል። ከታች ከመስቀሉ ግርጌ ደግሞ ቁልፍ ይመስላል። መልህቅ ከሚመስለው ጫፍ ሥር ደሞ "ዶርቶጋዳ" ይላል።

‹‹የእነዚህን ቃላት ትርጉም አላውቅም ነው የምትለኝ ታዲያ ኢንጂነር ሻጊዝ?›› ሚራዥ ተደምሟል፡

"የጥንት ወፍ ጠባቂዎች፣ እረኞች ሰብላቸውን የሚያወድም ግሪሳ አዝመራቸው ላይ ሲያርፍ በወንጭፍ ድንጋይ ከመወርወራቸው በፊት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ‹ኦርያ!› ይሉታል። ድምፃቸውን ሰምቶ ያልተነሳውን ተባይ ይወነጭፉበታል። በድንጋይም ክንፉን ይሰብሩታል። ስለሆነም ኦርያ ኢትዮጵያ ማለት 'የኢትዮጵያ ተባዮች ተነሱ' የሚል የማስጠንቀቂያ ቃል ነው። ‹ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ› የሚለው ደግሞ **‹ምርኮ ፈጠነ ብዝበዛ ቸኮለ!›** ማለት ነው። ኦርያ! ...**ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ**..... የኢትዮጵያ ተባዮች ተነሱ.... ምርኮ ፈጥኗል...ብዝበዛ ቸኩሏል። ማለት ነው።...ይህ ለምን እኔ ጀርባ ላይ ተነቀሰ? መልሴ አላውቅም ነው። ግን ለምን ይህን ያህል ትኩረት ሰጠኸው? ከዚህ የበለጠ በንቅሣት የሚዥጎረጎሩ ሰዎች በሞሉበት አሜርካ ውስጥ ተቀምጠህ የእኔ የደበዘዘ ቅንሣት እንዴት ይህን ያህል ሳበህ?" ሲል መልሶ ጠየቀው ሻጊዝ።

"የገረመኝ ይሄ አይደል!" አለ ዶ/ር ሚራዥ። "ካንተ ጀርባ ላይ ያለው ንቅሣት በተመሳሳይ መልኩ እኔ ጀርባ ላይም አለ። ተመልከት!" ነጭ ጋወኑን እና ሸሚዙን አውልቆ ጀርባውን አዞረለት። ሻጊዝ በመገረም የሚራዥን ተመሣሣይ ንቅሣት ከጀርባው ላይ አነበበው። "ዶርቶጋዳ...ኦርያ ኢትዮጵያ...ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ።"

"እንዴት ተመሳሳይ ነገር ሊኖረን ቻለ?"

“ከአሁን ቀደም እንተዋወቅ ነበር?” አለ ኢንጂነር ሻጊዝ፡፡

“በፍፁም ከአሁን ቀደም የጋራ ምስጢር እስኪኖረን ድረስ ልንተዋወቅ አንችልም፡፡ በፍፁም፡፡ በተለያዩ አለማት የኖርን ሰዎች ነን፡፡ እኔ ቅድም እንደነገርኩህ የማውቅህ ባነበብኩትና በሰማሁት ነው፡፡ በአካል ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁህ ከቀናት በፊት ይህን ቀዶ ጥገና ሳደርግልህ ነው፡፡ ከዚህ በተረፈ ግን እኔና አንተን ሊያገናኘን የሚችል አንዳችም መንገድ አልነበረም፡፡ አንዳችም መስመር!”

“የት ነው ተወልደህ ያደከው?”

“የተወለድኩበትን አላውቅም፡፡ ያደኩት ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ነው፡፡ ጣና ሐይቅ ውስጥ በሚገኝ አንድ ደሴት ላይ፡፡”

“ጣና ሐይቅ ውስጥ ..... የትኛው ደሴት ላይ?”

“ክብራን ደሴት ላይ፡፡ ከባህር ዳር ከተማ በጥቂት ኪሎ ሜትር ርቀው ጣና ሐይቅ ውስጥ ከሚገኙት እንጦንስና ክብራን በመባል በሚታወቁት መንታ ደሴቶች ላይ ነው ያደኩት፡፡ እስክጎረምስ የሴቶች ገዳም በሆነው በእንጦንስ ደሴት...ከጎረመስኩ በኋላ ደግሞ የወንዶች ገዳም በሆነው በክብራን ደሴት ላይ ነው ያደኩት አንተ ደግሞ ከፋ!.....ምን አገናኘን?” አለ ዶ/ር ሚራዥ፡፡

ወዲያው በሩ በኃይል ተበርግዶ ሶስት ሰዎች ወደ ክፍሉ ተንደርድረው ገቡ፡፡ ሁለቱ ነጭ ጋወን የለበሱ ዶክተሮች ሲሆኑ የአንደኛው ማንነት ግን አይታወቅም፡፡

“ዳይሬክተሩ በአስቸካይ ይፈልጉሃል ዶ/ር ሚራዥ?” አለው አንደኛው ዶክተር፡፡ “ባስቸኳይ!” ከዚህ ቀደም አይቶት የማያውቀው ሰውዬ ጠረጴዛው ላይ ያስቀመጣቸውንና የኢንጂነር ሻጊዝን የህክምና መረጃ የያዙትን ወረቀቶች ላፕቶፕ ኮምፒውተሩንም አንስቶ ሊወጣ ሲል ሚራዥ ጎትቶ ወለሉ ላይ ዘረገፈው፡፡ ሰውዬው በፍጥነት ተነስቶ ፈገግ አለ በደረቁ፡፡ “ቀዩ መስመር ውስጥ ከገባህ ቆይተሀል፡፡” ሽጉጡን መኸርርጦ ከሚራዥ ጭንቅላት ላይ አነጣጠረበት፡፡ “ቀጥል!.....ዲታላ!”

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

በሩን በርግደው ተከታትለው ሲገቡ ጭንቅላቱ ላይ የደቀነውን ሽጉጥ ምላጭ ሳበው፡፡ ከተቀመጠበት ወንበር ጀርባ ያለው ነጭ ግድግዳ በደሙ ፍንጣቂ ተጨማለቀ፡፡ በጢስ በታፈነው ሳሎን ውስጥ እየተጨናበሱና እያሳሉ አይተው ራሱን ባጠፋው ደህንነት በድን ላይ በብሽቀት ጥይት አርከፈከፉበት፡፡ አንደኛው ደህንነት ያገኘውን እቃ እየጠለዘ ሲበሳጭ አንደኛው ደግሞ የሰነዱን አመድ ዘግኖ በብሽቀት ሳቀ፡፡ በመጨረሻ ከጻፈው አንድ ቃል በስተቀር አንዳችም መረጃ አላስቀረም፡፡.......ሁለቱም ብጣቂው ፅሁፍ ላይ አፈጠጡ፡፡.....«ዴርቶጋዳ?.......ምን!?».....ተያዩ፡፡

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ሚራዥ የህክምና ክፍሉን ለቆ ወጥቶ ወደ ዳይሬክተሩ ቢሮ ከመሄዱ



በፊት ለመጨረሻ ጊዜ ኢንጂነር ሻጊዝን ፍዝዝ ብሎ ተመለከተው፡፡ ሻጊዝም ሚራዥን በዓይኑ አነጋገረው፡፡ በቀዶ ህክምናው ክፍል ውስጥ የተተከሉት ስውር ካሜራዎች የሚቀርፁትን ምስልና ድምፅ ኮምፒውተራቸው ላይ የሚከታተሉት የሆስፒታሉ ዳይሬክተር ዶ/ር ሚራዥና ኢንጂነር ሻጊዝ የተነጋገሩአቸውን የአማርኛ ቃላት ወደ እንግሊዘኛ የሚተረጉመውን ማሽን የዘጉት ዶ/ር ሚራዥ ወደ ቢሮአቸው ሲገባ ብቻ ነበር፡፡ ምንም ቃል ሳይተነፍሱ አንድ ገፅ ወረቀት ጠረጴዛው ላይ አንስተው ለዶ/ር ሚራዥ ሰጡት፡፡ ከሥራ መባረሩን የሚገልፅ፡፡ “ለምን?” አለ ዶ/ር ሚራዥ፡፡ ምንም ምላሽ አልሰጡትም ዳይሬክተሩ፡፡ “ውጣልኝ አሁን ሥራ ላይ ነኝ፡፡”

## ፬

### ቴልአቪቭ : እስራኤል

"በውድ ዋጋ ነው አይደል የተገረዝሽው?" አላት አይኖቹን አጥቦ እየተጠጋት። ሲለምናት ቢኖርም ፍንክች ብላለት አታውቅም።

"አትጠጋኝ" አለችው ውስጧ እያረረ።

"በእውነት ያንቺን ያህል እግዚአብሔርን ብለምነው ሶስት መቶ ሚስቶች ሰጥቶ ሰማኒያ እቁባቶች ይመርቀኝ ነበር" አሁንም እየተጠጋት።

"አትጠጋኝ" አለችው አሁንም ወደኋላ እያፈገፈገች። ቋጥኝ የሚያክል ራሱን እንደ ክር የቀጠነ አንገቱ እስኪቀነጠስ በአሉታ ወዘወዘው። የበለጠ ዓይኑን እያጠበበ ተጠጋት። ቤቷ ውስጥ ባይሆን ኖሮ የያዘችውን የብርጭቆ ውሃ ላዩ ላይ ከልላበት ባስወጣችው ነበር። ደግሞም አብረው የሚያከናውኑት አንድ የጋራ ጉዳይ አላቸው ።

"ደጋግሜ እንደነገርኩህ አጉል ጊዜህን ባታባክን ይሻላል" ንዴቷን ከውሃው ጋር እየዋጠች ዝም አለችው።

ደረቷ ላይ ተጠጋግተው ከተወጠሩትና ቀጥ ቀጥ ብለው እንደ አምባ ተራራ የቆሙ ጡቶቿ ላይ አይኖቹን ተክሎ በምላሱ ከንፈሩን አረጠበ። በጧት በመምጣቱና የሚቋምጥለት አካሏን በውስጥ ልብስ በማየቱ በጧቱ የቀሰቀሰውን መልአክ አመሰገነው። ተራራ የሚያክል ራሱን እንደ ክር በቀጠነ አንገቱ ላይ አንጠልጥሎ ያቀረቀረ መሰለና ገላዋን ወደ ላይ በደፈረሱ ጥቃቅን ዓይኖቹ እንደ ሸንኩርት መላጥ ጀመረ። እንደ ወርቅ የሚያንፀባርቁ የእግር ጥፍሮቿን ቃኝቶ ሽቅብ ቃተተ። የውስጥ ገላዋን በሚያሳይ ነጭ ስስ የሌሊት ልብሷ ውስጥ የቆመለትን ማራኪ ገላዋን በዓይኖቹ ሽቅብ ሲጠባ ፊት ለፊት ገጥመው የሴትነት መለያዋን የሸፈኑ ጭኖቿ ጠሩት። ‹መሀላችን ግባ ዘግተን የያዝነው ልዩ ዕቃ በመካከላችን አለ› አሉት። ከጎን ሰፋ ያለው ዳሌዋ ከቀጭን ወገቧ ሥር ውሏል። የተቀነበበ እምብርቷን አልፎ ደረቷ አልበቃቸው እንዳለ ተጠጋግተው የተኮፈሱ ትላልቅ ጡቶቿ ከአድማስ ጥግ እንደሚታዩ ተራሮች አልታለፍ አሉት። ከመቃ አንገቷ ላይ የማይለየውንና በትልቅ ሀብል ያሰረችውን በ‹ቶ› ቅርፅ የተሠራ ባለጉጥ ግማደ መስቀል ላይ ሲደርስም ይጥገበኝ ብላ



የቆመች ይመስል ስታየው ቆይታ ፈገግ አለች። የጎመራ የወይን ፍሬ የሚመስሉ ከንፍሮቿ መሀል ችምችም ያሉ ነጫጭ ገጻይ ጥርሶቿን እንደምንም ሲያልፍ የወሲብን ቆሌ የሚጠሩ አይኖቿ ጋር ተጋጭቶ ቆመ። አይቷት የማያውቅ አዲስ ፍጡር አዲስ መስላ ታየችው። ቡዝዝ....ፍዝዝ እንዳለ በማያውቀው ኃይል ተገፍትሮ ከንፈሯ ላይ ሊያሳርፍ የላከው ከንፈሩ በፍጥነት ፊቷን ስታዞር ጆሮ ግንዷ ላይ አረፈ። ወዲያው በአይበሉባዋ የሚያቃጥል ጥፊ ስታሳርፍበት ወደኋላ ተንገዳግዶ ቆመ።

የማይታገላት አደገኛ ሴት ሆነችበት እንጂ ከጭኖችዋ መሀል ገብቶ ለዓመታት የቋመጠለትን ሲሳይ በግዳጅም ቢሆን ሊቋደስ ልቡ ቆርጦ ነበር። ግን ብዙዎችን ያንበረከከችና የሞሳድ ባልደረቦቿ ‹‹አቦ'ሸማኔዋ›› እያሉ የሚያመካሹአት ሲጻራ ናት።

ለእስራኤል የስለላ ድርጅት ሞሳድ በአባልነት የመለመላትም የህክምና ምርመራዋን የሰራውም ራሱ ነው። ከሁሉም በፊት ያጠመደው ውበቷ። እሱም ውበቷንና እሷን ማጥመድ ጀመረ። ዛሬ ደግሞ ለጋራ የሚያጠምዱት ወጥመድ አላቸው። የእስራኤልን አንድ ወጥመድ በጋራ አጥምደው አሽከላቸው ውስጥ የሚገባውን ታዳኝ አንቀው ለእስራኤል መስጠት አለባቸው። ይህ ተልእኮ የወደቀው በነዚህ ሁለት አይሁዶች ጫንቃ ላይ ነው።

ሲጻራ አናንያን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየችው ‹‹ዘመቻ ሙሴ›› በተሰኘው እስራኤል የኢትዮጵያ ፈላሻዎችን በሱዳን በኩል አስኮብልላ ወደ እስራኤል በወሰደችበት ጊዜ ነው።

ዶ/ር አናንያ ከወጣትነቱ ጊዜ ጀምሮ የሞሳድ የህክምና ክፍል አባልና ተመራማሪ ሆኖ ሲሰራ አንድም ቀን ስለፍቅሩና ስለግል ህይወቱ መደላደል አስቦ አያውቅም። የፅዮናዊነት መዝሙር ሲያዜም አደገ። አይሁድነት በደሙ ውስጥ ሲዘዋወር ኖረ። የዘወትር ንግግሩ ማሳረጊያ "እስራኤል ለዘለአለም ትኑር!" ሆነ። ሲጻራን ካያት ጊዜ ጀምሮ የግሉ እንደምትሆን እርግጠኛ ሆኖ ኑሮ ነበር። በተለይ በዚህ ወቅት ፍላጎቱ ንሮበታል። አማላይ ገላዋ አቅበዝብዞታል።

ጥፊውን ወደ ውስጡ ውጦ በቀጭን አንገቱ ቋጥኝ የሚያክል ራሱን ከግራ ወደቀኝ ቀጫ አድርጎ በተለሳለሰ መንፈስ ልመናውን እንደገና ሊጀምር ሲል"አናንያ! እኔና አንተ የተወከልነው ለሀገራዊ ተልእኮ ብቻ ነው። ደግሞ ብቻዬንም ቢሆን እንደምወጣው ታውቃለህ። እመነኝ ....የከፈልኩትን ያህል መስዋዕትነት ከፍዬ ኢንጂነር ሻጊዝን አንቄ ለእስራኤል አስረክባታለሁ። እንዲያውም አንተ የመጀመሪያውንና ተገቢውን ሥራ ሰርተህ ጨርሰሃል። የቀረውን ለእኔ ተወው" እያገለለችው ነው። ዶ/ር አናንያ ግን በዚህ አፕሬሽን ምክንያት ከእሷ ጋር አብሮ በመሳተፉ ግንኙነታቸውን

ሚራዥ ዘሎ ሐይቁ ውስጥ ገብቶ በዋና ጀልባውን መከተል ጀመረ። በጀልባውና በእሱ መካከል ያለው ርቀት የአድማስ ዳርቻ ያህል ሲርቀው ሆዱን ባር ባር ብሎት ዕንባ ባነቀው ድምፅ ለመጨረሻ ጊዜ ተጣራ። "ሲጳራ…ሲጳ……ሲ……ሲ……ሲ……" ተስፋ የከዳው የሰለለ ድምፁ ለእሱም አልሰማው አለ። የእሷም ድምፅ እየሰለለ እየመነመነ በጣና ማዕበል ተዋጠ። ውሃውን ጨብጦ ወደ ሄደችበት በትኖ እየተነፋረቀ በሁለቱ ደሴቶች መካከል ፈዞ ቀረ።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

በኋላ አራት መነኮሳት ሚራዥን ይዘውት ወደ ገዳሙ ጀልባ ከተቱትና ወደ ነበረበት ክብራን የወንዶች ገዳም አሻገሩት። ሁሉም በሀዘን ተውጠዋል። እማሆይ ወለተ ኪሮስ በመሞታቸው ብቻም ሳይሆን በሚራዥ መውደቅ ምክንያት። በሚራዥና በሲጳራ መካከል ስለተፈጠረው ነገር ብዙዎች መነኮሳት የሰሙት ሚራዥ ወደነበረበት ወደ ክብራን የወንዶች ገዳም ከተመለሰ በኋላ ነበር። ከእማሆይ ወለተ ኪሮስ ሥጋዊ ሞት በላይ አሳዛኝ የሆነው የሚራዥ የቁም ሞት ነበር። መነኮሳቱ ለስንት ነገር ይደርሳል ያሉት ብላቴና የቤተክርስቲያን አገልጋይ በሰይጣን ወጥመድ ገብቶባቸዋልና አዘኑ።

በተለይ የክብራን ገዳም አበምኔት የሚሉት ጠፍቶባቸው ከንፈራቸው እየተንቀጠቀጠ "መታሰር አለበህ። ሰይጣንን ልትዋጋው ይገባል" ብለው መነኩሴ ሲተላለፍ እንደሚደረገው ሁለት ቀዳዳዎች ባሉት ግዙፍ ግንድ ሁለት እግሮቹን በቀዳዳዎቹ ውስጥ አሾልከው በእግረ ሙቅ አሰሩት። የእግረሙቁን ቁልፍ ማህደራቸው ውስጥ ከተው እየተበሳጩ ሳያናግሩት ባዶው ቤት ውስጥ ጥለውት ሄዱ።

ከሰዓታት ቆይታ በኋላ መለፍለፍ ጀመረ። "ፍቱኝ! ..አትለዩኝ!….. ሰይጣን አይደለም….." ማንም የሚመልስለት የለም።

ሁሉም መነኮሳት በደንጋዩ ደወል ተጠርተው ከተሰበሰቡ በኋላ እንዲፀልዩለት አበምኔቱ አሳስበው አሰናበቱአቸው። በክብራን ገዳም ውስጥ ሁለት የድንጋይ ደወሎች አሉ። ትልቁ የድንጋይ ደወል መነኮሳቱን መሰብሰቢያ ሲሆን ትንሹ ደግሞ ስብሰባውን መበተኛ ነው። በመሆኑም በትልቁ የድንጋይ ደወል የተሰበሰቡት መነኮሳት በትንሹ የድንጋይ ደወል ድምፅ ሲበተኑ ጀምረው ሁሉም ለሚራዥ ፀሎት ማድረስ ጀመሩ።

"እናንተ ሽማግሌዎች! የማታውቁትን ለምን ታደርጋላችሁ? ፍቅርንና ሰይጣንን ለይታችሁ ማወቅ ለምን ተሳናችሁ?…. ፍቱኝ! …አላበዛችሁትም? …..ጥላኝ ሄደች!…. ፍቱኝ…..አፍነው ወሰዷት። ላስጥላት ፍቱኝ። ስለራሳችሁ ፀልዩ። እኔ ጤነኛ ነኝ። ጤና ያጣችሁ እናንተ ናችሁ።……." ሚራዥን የሚያዳምጥ ጆሮ ግን አልነበረም።



አርባ ቀን ሙሉ ታስሮ ሲለፈልፍ ከረመ። አልተሻለውም። መለፍለፉ ሲታገስለት የተመለሰ መስሏቸው በፈቱት ማግስት በአሮጌ ታንኳ እየቀዘፈ ሁለቱን መንታ ደሴቶችና ገዳማት ጥሏቸው ሸሸ።

ባህርዳር ከተማ ሲደርስ ሁሉም ነገር ተደነጋገረው። የማያውቀው ዓለም።…. መኪና። ……ግርግር። ……ሱሪ ያጠለቁና ዳሌያቸውን የሚወዘውዙ ሴቶች። ጭናቸውንና እምብርታቸውን የሚያሳዩ ልብሶች የለበሱ ልጃገረዶች። ስንቷን ሴት እያየ ሲጳራ መሆን አለመሆንዋን መለየት ይቻላል? አፍጥጦ ሲያያቸው "እህ! ይህ ደሞ ምኑ ባላገር ነው ከእብዶች ሆስፒታል የተለቀቀ መሆን አለበት። ምን እንደ ቡዳ አፍጦ ያያል? …" እያሉ ገላምጠውት ይሄዳሉ። እሱ ግን ሲጳራን ከዚህ ሁሉ ሴት መሀል እንደማያጣት እርግጠኛ ነበር። አቅጣጫ እንደሳተ የተገለጠለት ቆይቶ ነው።

በቀጣይ ምን ማድረግ እንዳለበት እያሰላሰለ ከባህር ዳር ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን በረንዳ ላይ እየተኛ ሲዋትት ሰነበተ።

አንድ ቀን ከተኛበት በረንዳ አንድ ሰው ሲቀሰቅሰው ተሰማው። ቀና ሲል ሞተሩን ያላጠፋ የጭነት መኪና ቆሞ ሸራው ውስጥ ሰዎች እየገቡ ተመለከተ። ሁለት ኮማንዶዎች ወርደው ክንድና ክንዱን ይዘው መኪናው ውስጥ ጫኑት። ከብዙ ጉዞ በኋላ ለውትድርና ከታፈሱት ሰዎች ጋር አንድ በረሀ ውስጥ አብሮ ተራገፈ። "ግራ ቀኝ!…ቀኝ ግራ!…..ወደኋላ ዙር! ….ወደፊት! …እናት ሀገር" ምናምን። ጊዜው ወታደራዊዉ የደርግ መንግስት የሞት ሽረት ትግል በሰሜኑ አካባቢ የሚያደርግበት ወቅት በመሆኑ የዚህ ጦርነት ተሳታፊ ሆኖ ራሱን ያገኘውና የሰሜኑን ጦር የተቀላቀለው ከአድካሚ ስልጠና በኋላ ነበር።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

እነ ሲጳራ ሲነጋጋ ጎርጎራ ወደብ ደረሱ። ጀልባዋን እዛው ትተው ወደ ሰሜኑ አቅጣጫ ረጅም የእግር ጉዞ ካደረጉ በኋላ አንድ ቀጥቃጮችና አንጥረኞች ከበዙበት መንደር ደረሱ። ማንም አይነጋገርም። ዝም ብሎ መጓዝ። ከዚህ መንደርም ብዙ ሰዎች ጎዛቸውን እየጠቀለሉ ተከተሏቸው።

ከቀናት ጉዞ በኋላ የጎንደርን ከተማ ወደጎን ትተው ወደ ሰሜን ተራራ ተጓዙ። ተጓዦችም እየበረከቱ መጡ። ከሚያገኙት መንደር ሁሉ የሚጨመር ተጓዥ አለ።

"ቆይ…. ወደየት እየተጓዝን ነው?" አለች ሲጳራ አንድ ትልቅ ዋርካ ሥር ለእረፍት እንደተቀመጡ።

"ወደ ተቀደሰችዋ ምድር" አሉ አባ ፊንሐስ የሰሜንን ተራራ አንጋጠው እያዩ። ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያናግሯት ነው።

"ማን ናት የተቀደሰችዋ ምድር?" እሷም በላዩ ላይ ባዘቶ የመሰለ ጉም የሸፈነውን የራስ ዳሽንን ተራራ አሻቅባ እያየች አባፊንሐስን መልሳ ጠየቀቻቸው።
"የተቀደሰችዋ ምድርማ እግዚያብሔር ለአባቶቻችን ቃል ኪዳን የገባላቸው እስራኤል ናት- ኢየሩሳሌም"አሏት። ስለ ኢየሩሳሌም ታውቃለች። በመፅሐፍ ቅዱስ።

አባ ማቴምስ ፊንጠር ብሎ ከሚገኘው ጉብታ ላይ አርባጣ አፈር እየቆፈሩ ከማህደራቸው ሲከቱ ሌሎች ከሩቅ ይሳሳቁባቸዋል።

አባ ፊንሐስ.....ቀጠሉ...እየተልጎመጎሙ...እተቁነጠነጡ..."እየሽ ልጄ ሲጻራ.... አንቺ የማታውቂው ብዙ ነገር አለ። በመጀመሪያ ...አባትሽ እኔ መሆኔን ልነግርሽ እወዳለሁ።"

ካቀረቀረችበት ቀና አለች ግራ ተጋብታ። "ምን?!" ቅንድቧን በጥያቄ መልክ ሸብሸባ።

"አዎ ልጄ። ወደ ሴቶች ገዳም ያስገባሁሽ ወድጄ አይደለም። ደኸየሁ። እናትሽንም ሞት ነጠቀኝ። አዝዬሽ በልመና ላሳድግሽ ተንከራተትኩ" የለበሱትን ወይባ አቡጀዴ ሰብስበው ግራ እጃቸውን ገልጠው አሳዩአት። ክንዳቸው በጥይት ተቦትርፎ በተሰበሰበ ግንድ መሰሏል። "እዩውልሽ ልጄ። እኔ አባ ዠንበሩና አባ ዲዲሞስ አንድ የጋራ ጉዳይ ስላለን..... ተይው ይህን ሌላ ቀን ነው የምነግርሽ። ጣና ሐይቅ ላይ በጣሊያን ጊዜ የመርከብ..... ለካ ሌላ ቀን እነግርሻለሁ ብያለሁ። አሁን አይደለም።»

ሚራዥ ካሰረላት በ"ቶ" ቅርፅ ከተሰራው ባለ ጉጥ መስቀል ላይ አይናቸውን አልነቀሉም። ለምን ይህን ያህል ገዜ አፍጥጠው እንደሚያዩት ግን አልገባትም። ባለፈው እንድትሰጣቸው ጠይቀዋት እምቢ ብላቸው ነበር።

«እየውልሽ ልጄ....» አገጫቸውን አሹለው ወደ ሰሜን ተራራም ሲያዩ እሷም ተራራዎችን ተመለከተቻቸው። "ከምታይው ተራራ ግርጌ ነበር እኔና እናትሽ በአንጥረኝነትና ብረት በመቀጥቀጥ ስንተዳደር የነበር። ማረሻ ሽጠን የምናገኘው ገቢ እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም። ሆኖም ተስፋ ያስቆረጠኝ የምወዳት እናትሽ አንቺንና እኔን ጥላ ስትሞትብኝ ነበር። እዚህ አስቸጋሪ ቦታ ላይ አንቺን ማሳደግ ተሳነኝ። ቤተ እስራኤላዊና የአይሁድ እምነት ተከታይ ብሆንም ቀን እስኪወጣ ብዬ እምነቴን በልቤ እንደያዝኩ አንቺን ላሳድግ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ገባሁ። አንቺን በእንጦንስ ደሴት ለሴቶች ገዳም ሰጥቼ እኔ ደሞ በዳጋ እስጢፋኖስ የወንዶች ገዳም ውስጥ መኖር ጀመርኩ። አሁን ግን ዘመዶቻችን ሊወስዱን መጡ።"

ከተንገዦች መሃል በአህያ ላይ ተጭኖ የሚጓዘውንና ፊቱን በጥቁር የዋልካ ጭቃ ቀብቶ ከሐበሻ ጥቁር አይሁዶች ጋር የተመሳሰለውን ፈረንጅ እያሳዩአት።



ፊቱን በዋልካ ጭቃ የተለቀለቀው ፈረንጅ ፎቶ ያነሳል፣ ቪዲዮ ይቀርፃል፣ አባ ፊንሐስንም ቃለ መጠይቅ አድርጎ ቃላቸውን በቴፕ ሲቀርፅና ፎቶም ሲያነሳቸው አይታ ነበር። እሱዋንም ትኩር ብሎ ይመለከታታል። ዓይኑዋን ካልሰበረች ዓይኑን አይሰብርም። ከሁዋላ ስትቀር ወደሁዋላ ይዞራል። ከፊት ስታልፍ እየገሰገሰ ይደርስባታል።

"...ይሄ ነው ዘመዳችን?.... .ነዉ ሰውዬ? .....እንዴት ሆኖ?" ግራ ገባት። "እነማን ናቸው ዘመዶቻችን?" ራሱን ተላጭቶ ፊቱን የዋልካ ጭቃ ተለቅልቆ ከሸማግሌዎች ጋር ቆሞ የሚነጋገረውን ወዘ ልውጥ እያየች።

"እስራኤላውያን ናቸው ወገኖቻችን። ከዚህ የመከራ ኑሮ ሊያላቅቁን መጥተዋል። አንገታችን ደፍተን፣ አፈር ለብሰን ነበር። አሁን ግን ደረሱልን። እግዚአብሔር ለአባቶቻችን ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ ቃል ወደገባላቸው ማርና ወተት ወደምታፈሰው ከነአን ሊወስዱን መጡ" ልቧን አማለው ሚራዥራን ሊያስረሷት መሰሏቸው ነበር። የእሷ ልብ ግን ከሚራዥ ጋር እንደተቆራኘ ነበር።

"እና ምነ ሚራዥ አብሮን ቢሄድ? ለምን ጥላችሁብኝ መጣችሁ? አባ... እሱን እኮ አሁን እያሰቃዩት ነው የሚሆን! ክህነቱን ያፈረሰ ይመስላቸዋል እኮ!...... ግን ምንም አላደረግንም አባ.... እባክዎ ሂደን እናምጣው?" ዓይናቸው ላይ እየተቁለጨለጨች ተማፀነቻቸው።

"ይሄማ የማይሆን ነገር ነው። እየውልሽ ልጄ የማታውቂው ይህንን ነው። እኛ ቤተ እስራኤላውያን ነን። የእግዚያብሔር ህዝቦች ። በእግዚያብሔር የተመረጠውን ዘር ከሌላ ዘር እንደባልቅም።"

"እንዴ! ሙሴ ኢትዮጵያዊቷን አግብቶ የለ? እኤስ ለምን......" አቋረጧት።

"እነዚህ የሚወስዱን ሰዎች ሁሉን ነገር አጥንተው ጨርሰዋል። እስራኤላዊ ያልሆነን ማንንም አይወስዱም" አሉ ወደ ጠጉረ ልውጡ ሰውዬ እያማተሩ።

"እኔ ግን እሱን ትቼ ንቅንቅ አልልም" አለች ወደ መጣችበት አቅጣጫ ፊቷን አዙራ። አልመለሱላትም። ሦእረፍት ሰዓት ሰላበቃ ሁሉም ጓዙን እየጠቀለለ ተነሳ። በቀኝ እጃቸው እጇን ይዘው እየጎተቱ ከሚጥመለመለው ተጓዥ ጋር ተደባለቁ።

ከትከሻቸው ዱላ ቅል ቃንቁራቸውን ሰካክተው ያንጠለጠሉ፣ ማረሻ ማጭድ፣ ጉራዴ፣ ሰይፍ፣ ጦር፣ አንካሴ፣ መቆፈሪያ፣ መጥረቢያ፣ አካፋ፣ ዶማ እና ሌሎችም ዝከንትሉችን አንጠልጥለው ይጓዛሉ። ከወዘ ልውጡ ሰውዬ ጋር በእብራይስጥ ቋንቋ ከሚነጋገሩት ሽማግሌዎች ጋር ህፃናት፣ ጓዝ የተጫኑና በድርቁ

የሚቀምሱት አጥተው በአጥንታቸው የሚሄዱ አህዮች ይጋፋሉ። ይጓዛሉ።

ከጎንደርና አካባቢዋ፣ ከወለቃ፣ ከሩፋኤል፣ ከሲልቀት፣ ከጎርጎራ፣ ከጭልጋ፣ ከቋራ፣ ከጃኖራ፣ ከእንከኮሻሽሊት፣ ከአርማጭሆ፣ ከብልባሆ፣ ከጠዳ፣ ከደንቀዝ እየመጡ ጉዞውን ተቀላቀሉ። ከወገራ አውራጃ ዳግሞ ከዳባት፣ ከሰላምጌ፣ ከጉራሬ፣ ከዋርዋ፣ ከብራ ኢየሱስ፣ ከአምባ ጊዮርጊስ፣ ከደርጋጅ፣ ከጫርቢጣ እየመጡ ተደባለቁ። ሲደባለቁ የሚያወጡት አንድ ቃል ብቻ ነው። «ሻሎም።»

ከጎጃም ደግሞ ከባህር ዳር፣ ከቡሬ፣ ከደብረማርቆስ፣ ከዲማ፣ ከይስማላ ጎዮርጊስ፣ ከአዴት፣ ከዱር ቤቴ፣ ከቁንዝላ፣ ከግብግቢት ቀድመው ደርሰዋል። ከበጌ ምድርም ከወረታ፣ ከሐሙሲት፣ ከፎገራ፣ ከደብረታቦር፣ ከአፈረዋናት፣ ከእስቴ፣ ከፋርጣ፣ ከውዶ፣ ከኩርያ ማርያም፣ ከመነጉዘር፣ ከአሞራ ገደል የመጡትም ከኋላ ደረሱባቸው። ከደቡብ ኢትዮጵያ ፣ ከምእራብ ኢትዮጵያ፣ ከምስራቅ ኢትዮጵያም መጥተዋል።

ወቅቱ ኢትዮጵያ በእርስ በእርስ ጦርነት የምትታመስበት በመሆኑ ሁሉም ባተሌ ነበር። በሽምቅ ተዋጊዎች ጦር በአራቱም አቅጣጫ የሚንቦጀቦጀው የደርግ መንግስት በጦርነት በመማገዱና የሚይዝ የሚጨብጠውን በማጣቱ ቤተ እስራኤላውያኑን ወደ እስራኤል ለማጓጓዝ «ዘመቻ ሙሴ» ለተሰኘው የእስራኤል ኦፐሬሽን ተፈፃሚነት አመቺ ወቅት ነበር። በሱዳን በኩል ሰርገው ለገቡትና ለዓመታት ለሰለጠኑት የእስራኤል ሰላዮችም ወርቃማ ጊዜ ነበር።

ቤተ እስራኤላዊያኑ በኢትዮጵያ በተለይም በሰሜን ምዕራብ የጎንደር ክፍለ ሀገር ተበታትነው ሲኖሩ ለሁለት ምዕት አመታት ያህል ወደ እስራኤል ለመመለስ ምኞት የነበራቸው ቢሆንም ይሁዲ መሆናቸው የተረጋገጠው ከረጅም ጥናት በሁዋላ "ፈላሻዎች በማያጠራጥር ሁኔታ የዳን ነገዶች ናቸው" ተብሎ በመታወጁና ይህም በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዛሬው ደቡባዊ የአረቢያ ልሳነ ምድር ይኖሩ እንደነበር ተረጋግጧል በመባሉ ነው።

የእስራኤሉ የስለላ ድርጅት ሞሳድ ፈላሻዎችን ከኢትዮጵያ በምስጢር ለማስኮብለል የተሳካለት ወቅትም ኢትዮጵያ በጦርነት ውዥንብር ውስጥ በገባችበት ወቅት ነበር። ፈላሻዎችን የማጓጓዙ ተግባር በቀጠለበት በዚህ ወቅትም የወቅቱ የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስተር ሺሞን ፔሬዝ "ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ከኢትዮጵያ በደህና ወደ ሀገራቸው እስኪመለሱ ድረስ ዕረፍት አይኖረንም" ያሉት የረሃብተኛ ፈላሻዎች ሁኔታ በተባባሰበት በነፋሻማው የሀደይ ወቅት ነበር።



ጉዞው ቀጥሏል ። ጥምልምሉ። በኋላ ጉዞው ከቀን ወደ ሌሊት ተዛወረ። በአውራ ጎዳናዎች የሚነጉደውን ረጅም ተጓዥ በመቆራረጥ በየጥሻው በድብቅ ማስጓዝ ነበር አዋጭ ሆኖ የተገኘው።

ሲጻራ በህይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜ ያደረገችውን ረጅም ጉዞ መቋቋም አልቻለችም። ጭብጥ ከምታህል ድንክየ ደሴት ነው ያደገችው። ልቧን እስኪደክማት እንኳ ሮጣ አታውቅም። በጣና ሐይቅ ላይ ግን ልቧን እስኪደክማት ዋኝታ ታውቃለች። አሁን ደም የባሰ ልቧ ወደኋላ በፍቅር ገመድ እየተጎተተ ነው። በአካል ተገዳ ብትጓዝም በመንፈሷ ከሚራኘ ጋር ቀርታለች። እግሮቿ ደም በደም ሆነዋል። የጭኗ ጠባብቅ ተገሽላልጧል። ከንፈሮቿ ተቆራርሰዋል። ውበቷ ጠውልጓል። ከአያሌ ቀናት ጉዞ በኋላ የደባርቅን ከተማ አለፉ። ከጎንደር ከተማ በኋላ ከመቶ ሀላሣ ሁለት ኪሎ ሜትር በላይ ተጉዘዋል። ወደተራራው እንጋጣ አስገራሚውን ትርኢት ጨለፈችው።

የሾሉ ተራሮች.... የምድር ቀንዶች መስለው ቆመዋል። ተፈጥሮ በአለቶች ላይ ያነፀቻቸው እነዚህ ተራሮች ቆመው እንደጅረት የሚፈሰውን ትውልድ ይታዘባሉ። በተራሮች ጫፍ ላይ አስገራሚው ትርዒት ይታያል....ቲያትር። የሚደባደቡ ዝንጀሮዎች። የሚባዝኑ ወፎች። የሚያላዝኑ ቀበሮዎች። ከረጃጅም አለቶች ላይ ኈልቀው በአለቶች ላይ በቀጭኑ ብትን ብለው ለሚወርዱት ፏፏቴዎች ከሁሉም ተራራዎች በላይ ሰማዩን እየቡዋጠጠ የተኮፈሰው ራስ ዳሽን ተራራ ይቀኝላቸዋል።

ሲጻራ ራስዳሽንን ወደላይ አንጋጣ አይታ ጫፉ ላይ እግዚአብሔር የተቀመጠበት መሰላት። በራስ ዳሽን አናት ላይ የሚጥመለመለው ዳመናና ጉም የጠመጠመ የቅኔ መርጌታ አስመስሎታል። መርጌታ ራስዳሽን ወደ ሰማይ ተጠግቶ ለእግዚአብሔር በጆሮው ይቀኝለታል። መወድሱን ያወርድለታል። እግዚአብሔርም ለመርጌታ ራስ ዳሽን የደመና ጥምጣም የደመና ኩታ ይሸልመዋል። ከተራሮች ሁሉ መርጦ ራስ ዳሽንን እድሜ ስላደለው የበረዶ ሽበት ጣል ጣል አድርጎበታል-ከደመና ጥምጣሙ ሥር። ራስ ዳሽንን ያዩ ጤና ያጣ ካልሆነ በቀር ተራራ ነው አይልም። ግዑዝ የድንጋዮችና የአለቶች ጥርቅም አይመስለውም። ነገር ያረገዘ ህያው አካል ይመስላል እንጂ። የሰሜን ተራሮች ከስሩ ጉባዔ ቃና እየተቀኙ በያሬድ ዜማ ያሸበሽቡለታል። ራስ ዳሽን ከላይ ተከፍሶ ያዳምጣቸዋል።

በዘጠኝ ሺህ ጫማ ከፍታ ቁመቱ ልክ ቆሞ ሰማዩን ይጠባል - ራስ ዳሽን። ይህን ተራራ ቤተ እስራኤላውያን ሙጭጭ ያሉበት ምክንያት ግልፅ ነው። በንጉስ ሀብታህ ዘመን ክርስቶስ ከመወለዱ በፊት በ2300 ዓመተ ዓለም አካባቢ ወደ ኢትዮጵያ

ጠዋት በሰሜን ተራሮች ጫፍ ፀሐይ እግሯን ስትሰድ ሳትረግማት አልቀረችም። ቀሚሷ በደም ተዘፍዝፏል። የተኛችበት ምድር ተከፍቶ ቢውጣት መርጣ ነበር።

አባፊንሐስ ተነስተው ልጃቸው ላይ ሲያማትሩ በድንጋጤ ታቅፈው አነሷትና እጇን ፈትተው በቅርብ ወደሚገኘው ወንዝ ይዘዋት ወረዱ። ወንዙ ውስጥ እስከልብሷ ገብታ ልብሷን ላይዋ ላይ እጥባ ብትወጣም ከጥቂት ቆይታ በኂላ መልሶ ተጨማለቀ።

ማታ የምሽት ፀሎቱን የመሩት ሽማግሌ የአይሁድ ካህን እየተጣደፉ መጡና በቁጣ "እንዴት የአባቶቻችንን ሥርዓት ትጥሳላችሁ? እንዴትስ ሰባት ቀን ሳይሞላት የመንፃት ሥርዓት ታደርጋላችሁ። እናንተ ቤተ እስራኤላውያን ነን አላላችሁም? ከሆናችሁ እንዴት የመርገም ጎጆ ያለበትን አትጠይቁነም......" ሊገባት አልቻለም።

"በይ ተነሺ!......."

ወደ አንዲት ከመንደሩ ርቃ ወዳለች ደሳሳ ጎጆ ቤት ይዘዋት ሄዱና "ግቢ! ከሰባት ቀን በኂላ የመንፃት ሥርዓት ይደረግልሻል" ብለዋት ጎጆዋን ከውጭ ዘግተውባት ወደመጡበት መንደር ተመለሱ።

አባ ፊንሐስም ከጎጆዋ በር ላይ ተቀምጠው አቀርቅረው ከቆዩ በኂላ ወደ ወንዙ ወርደው በመታጠብ የመንፃት ሥርዓት አደረጉ። መርገሟ የመጣባትን ሴት ስለነኩ።

እምነቱን አጅግ አጥባቂ የሆነው ቤተ እስራኤላዊ አይሁድ ገበያ ወጥቶ ሲመለስ እንኳ ከቤቱ ከመግባቱ በፊት ወንዝ ወርዶ ታጥቦ መንፃት አለበት። የቤተ እስራኤላውያን ወገን የሆነ ሰው ከክርስቲያኖች ወይም ከሙስሊሞች ጋር እህል አብሮ ቢቀምስ ወይም አብሮ ከጠጣ በድርጊቱ ተፀፅቶ ንስሐ ገብቶ ለተወሰነ ጊዜ የመንፃት ሥርዓት ካልፈፀመ በስተቀር ወደ ቤተ እስራኤላውያን የስግደት ቦታ እንዳይገባ ይከላከላል። የመንፃቱን ሥርዓት የሚፈፅም ሰው ጥሬ ሽንብራ እየቆረጠመ ለሰባት ቀናት መፆም አለበት። የፆሙ ጊዜ ሲያበቃ የንሥሐ ፀሎት ከዳዊት መዝሙር ተደግሞ ፀጉሩን ተላጭቶ በውሃ ታጥቦ መንፃት አለበት።

አባ ፊንሐስም ከማህደራቸው የዳዊትን የመዝሙር መፅሐፍ አውጥተው ‹ተሰአለኒ እግዚኦ› የሚለውን ደግመው ከወንዙ ውሃ ሰባት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ካሉ በኂላ የመንፃት ሥርዓቱን ፈፅመው ወጡ።

ሲፃራ አንዲት ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ቤተ እስራኤላዊት ልጃገረድ የወር አበባዋ በሚታያት ጊዜ እንደምታደርገው ለሰባት ቀናት ከመርገሟ ጎጆ ከሰነበተች በኂላ ወደ ወንዝ ወርዳ ሰባት ጊዜ ወንዙ ውስጥ ጠልማ ወጣች። በዚህ አላበቃችም። የፀሐይ



መጥለቂያ ሰዓት ደርሶ ጭልምልም እስከሚል እዚያው መዋል ነበረባት።

በዚህ ጥብቅ ሥርዓት ውስጥ እንዴት መኖር እንደምትችል ግራ ገብቷታል። ለሁሉም ነገር የመንፃት ሥርዓት አይቀሬ ነው። ከቤተ እስራኤላውያኑ አንዱ ገበያ ወጥቶ የቤተ እስራኤላውያን ወገን ካልሆኑ ሰዎች ጋር ሲገበያይ ቢነካካ ወደ ቤቱ ከመመለሱ በፊት ወንዝ ወርዶ በውሃ ታጥቦ መንፃት አለበት። በገበያው ውስጥ የተጠቀመባቸውን ቁሳቁሶች፤አቁማዳ፣መጫኛ፤ አጎዛ፣ ጆንዲ፣ ቁርበት እንኳ ማጠብ አለበት።

ሲፃራ ወንድ ልጅም ብትሆን ኖሮ የመንፃቱ ሥርዓት አይቀርላትም ነበር። ወንድ ልጅ ለአቅመ አዳም ደርሶ ሌሊት በህልሙ ከብልቱ ነባዘር ቢፈስበት ማለዳ ሲነሳ የተኛበትን ምንጣፍና የለበሰውን ልብስ ጠቅልሎ ወንዝ ወርዶ ማጠብ አለበት። ይህ በሚደርስበት ጊዜ በቋራኛ ቋንቋ "ሰርክ ተነካ" ይባላል። ሰውነቱንም ወንዝ ውስጥ በመጥለም ማንፃት አለበት። እድሜው ሃያ አመት ሲሞላም ሚስት ማግባት ግዴታው ነው። ከሚስቱ ጋር ሌሊት ግብረ ሥጋ ግንኙነት ከፈፀሙም በበነጋታው ከሚስቱ ጋር ወንዝ ወርደው ሁለቱም ተጣጥበው መንፃት አለባቸው። የኢትዮጵያ ቤተ እስራኤላውያን ይህን ሥርዓታቸውን ከቅድመ አሪት ጀምረው ጠብቀው የኖሩበትን ምድር ለቀው ወደ ኢየሩሳሌም ሊሄዱ በአውራ ጣታቸው ከቆሙ ሰነበቱ። እስራኤል ሀገር ውስጥ ካላቸው የምኩራብ ቁጥር በላይ ምኩራቦች የሰሩባትን ምድር ኢትዮጵያን ለቀው ለመሄድ ከመላው ኢትዮጵያ ተጠራርተው ነቅለው ወጥተዋል።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ከቀናት በኂላ ጉዞው ተጀመረ......................ወደ ሱዳን። ተጓዦቹ ጓዛቸውን በአህያና በትከሻቸው ጭነዋል። በማዳበሪያና በአቁማዳ፣ በስልቻና በሸክላ ራሳቸው ላይ አቁረው የበረሃውን ጉዞ ተያያዙት።

ሱዳን በረሃ ከመድረሳቸው ብዙዎች ህፃናትና አዛውንቶች የበረሃ ሲሳይ ሆኑ። በረሃብና በውሃ ጥም እየተሰቃዩ አለቁ። አንዳንዶች ደግሞ ያሳደገን መሬት ይበላን ብለው ወደ ነበሩበት ተመለሱ።

በእባብና በጊንጥ እየተነደፉ በሱዳን በረሃ ውስጥ የወደቁትም ብዙ ናቸው። ሲፃራ በዚህ ጉዞ ያየችውን ስቃይ ገሃነም ውስጥ ብትገባ እንኳ የምታገኘው አልመሰላትም። ከሱዳን የስደተኞች ካምፕ ለመድረስ ከሁለት ወራት በላይ አስቸጋሪና አድካሚ የእግር ጉዞ አደረገች።

ከሱዳን የስደተኞች መጠለያ ለመድረስ ሁለት ማይልስ ርቀት ሲቀራቸው ደግሞ አባ ፊንሐስ በእባብ ተነድፈው ወደቁ። የእባቡ መርዝ በሰውነታቸው ለመሰራጨት አፍታ አልፈጀበትም። አባ ማቴዎስ የዕባቡን መርዝ የሚያረክስ መድሃኒት የሚቀመሙባቸው እፅዋቶችን ፍለጋ ቢንከራተቱም ዝቅ ሲሉ አሸዋ ቀና ሲሉ የሚያቃጥል ሰማይ በሚታይበት የሱዳን በረሀ ውስጥ ሊያገኙ አልቻሉም።

አባ ፊንሐስ በጣረ ሞት እየተንዘፈዘፉ ሲጳራ ያሰረችውን ባለጉጥ መስቀል ጨምድደው ይዘው «ል....ጂ እ....አሁን ወደሁዋላ እንዳትመለሽ ከጊዜ በሁዋላ ግን በዚህ መስቀል.........» ያሉት ሳይገባት ሁሉ ነገር ተጠናቀቀ። ሲጳራ ስቅስቅ ብላ እንድታለቅስ ያደረጋት አባትነታቸው ሳይሆን ከስደተኞች ጣቢያ ለመድረስ ጥቂት ሲቀራቸው በመሞታቸው ነበር። ግን አንድ የተናገሯት ቃል በጆሮዋ ደጋግሞ አቃጨለባት። "ወደኂላ እንዳትመለሽ!!......ወደኂላ እንዳትመለሽ............"

"አዎን! ከእንግዴህማ ልመለስ ብልስ በየት ብየ እመለሳለሁ? በቃ ይሄበህይወቴ ሊያጋጥመኝ የታቀደ ነገር ነው።" አለች በልቧ። "ወደ ኂላ አልመለስም።"

እለቱ ዕለተ ሰንበት በመሆኑ አባ ፊንሐስ አልተቀበሩም። በአይሁዳውያን ሥርዓት መሠረት በዕለተ ሰንበት፣ በቅዳሜ ቀን የሞተ ሰው አይቀበርም። የተቀበሩት በነጋታው ከሱዳን የስደተኞች ካምፕ አቅራቢያ ባለ አሸዋማ ቦታነው። እንደ ትክክለኛው የአይሁድ ሥርዓት ከሆነ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ጥቁር አይሁድ ሥርዓት የአባፊንሐስ የመቃብር ጉድጓድ አራት ማዕዘን ተደርጎ በአምስት ሜትር ጥልቀት መቆፈር ነበረበት። የአስከሬኑ እራስና እግር በሚያርፍበት ወገን "መርገብ" የሚባለው ጠፍጣፋ ድንጋይም መጣል ነበረበት። ጉድጓዱ ተቆፍሮ ሲያልቅና "መርገቡ" ከሥፍራው ሲደረግ ከበላይም ከበታችም ባዶ ይሆናል። መርገቡ በሁለት በኩል በጫፍና በጫፉ ብቻ ጉድጋዱ መካከል ተይዞ ይንጠለጠላል። ይህ የሚደረገው በድንኑን የያዘው ሬሳ ሳጥንም ሆነ ሌላ መጠቅለያ መሬቷን ነክቶ እንዳያረክሳት ነው። አስከሬኑ ወደ መጨረሻ ማረፊያው ከመግባቱ በፊትም ካህናቱ መቃብሩን እያጠኑ ይኸው ‹‹ቤትህ፤ ከእንግዲህ ከዚህ መመለስ የለም›› ብለው መሰናበት ነበረባቸው። በሶስተኛውም ቀን ጠጉሯ፣ ቀንዶቿና ጥፍሮቿ ባካሏ ሁሉ ትክክል የሆነች እንከን የሌላት ቀይ ጊደር ታርዳ ደምዋና የተቆራረጠ አካሏ በወይራ ወይም በግራር ፍልጥ በሚነድ እሳት ተቃጥሎ አመዱን በአዲስ ሸክላ እቃ ካህናቱ መከፋፈል ነበረባቸው። አመዱም በውሃ ተበጥብጦ ሬሳ በነካውና በቀረበው ሰው ላይ ሁሉ መረጨት ነበረበት። የጊደሪቱ



አመድ እርኩስ ነገር የነካ ሰውን ያነፃል ተብሎ ስለሚታመን። ለአባ ፊንሐስ ግን ከዚህ ሁሉ ሥርዓት አንዱም አልተፈፀመም።

ሲጳራ በዚህ የሱዳን ስደተኞች ካምፕ ከአባ ማቴዎስ ጋር እየተዘዋወረች አሰቃቂውን ጉስቁልና ተመልክታለች። በረሃብ የሞገጉት ህፃናትና አዛውንቶች አጥንታቸው ይቆጠራል። የተቦተራረፈ ጋቢ የለበሱ በሽተኞች ሞት ሞት ከሚሸቱት ከቀይ መስቀል ድንኳኖች ውስጥ እየሞቱ ይወጣሉ። ነጫጭ ጋወን የለበሱት ነጫጭ ዶክተሮች በሽተኛ የሚወጉበት መርፌ በመልአከ ሞት የተሞላ ይመስል የሚያክሙት ሁሉ እጃቸው ላይ ይሞታል።

ጠኔ ካነጠፋቸው ስደተኞች መሃል አንዲት ጠና ያለች ሴት ከኢትዮጵያ ቋጥራ ያመጣቺውን አርባጫ አፈር ስትበላ ስለታየች ሌሎችም ለመካፈል ከበቧት። ሌላኛው ሽማግሌ ደግሞ ለእሚያን የቋጠሩትን ጤፍ ሲቅሙ ታዩ።

ቀድሞም ምንም ስንቅ ያልያዙት አባ ማቴዎስና ሲጳራ ለመጨረሻ ጊዜ ያገኟትን ቁራሽ የበቆሎ ቂጣ ተገላገሉባት።

"አባ እርስዎ ይብሏት አትበቃንም። "

"ልጄ አንቺ ብያት አትበቃንም።"

"አይሆንም አባ እርስዎ ይትረሷት።"

"ልጄ እባክሽ አንቺ ብይልኝ እኔማ ባይሆን እችለዋለሁ። ብበላውም ጥፍር እንጂ ሰውነት አይሆነኝም።"

ሲገላገሉ አንድ በልቶ የማያውቅ የሚመስል አጥንቱ የገጠጠ ሰው ቁራሿን ቂጣ አንስቶ ከአፉ አደረጋት።

«እርፍ!» አለች ሲጳራ «ግልግል!»

አባ ማቴዎስ ወደ አንዲት የማሽላ ገንፎ ወደ ምታገነፋ ሴት ሲጳራን ይዘው ሄደው "እባክዎ ልጄ ረሃቡን አልቻለችውም" አሏት።

"ታዲያ እኔ ዩኒሴፍ ነኝ? ለራሴ ልጄ ደሜን እየጠባ እያየኹኝ። ይበሉ ወደመጡበት። ቀልደኛ ኖት?"

"ምን ተሻለኝ ልጄ?!" ተሸማቀቁ። ዙሪያ ገባውን ሲያማትሩ ቂጣዋን ከሰለቀጣት ሞጋጋ ሰውዬ ጋር አይን ለአይን ተጋጩ። መልስልኝ አልለው ነገር! አሉ በሆዳቸው።

"ልጄ ቆይ እስከ ነገ የሚበላ እንፈልጋለን። ብናጣ ብናጣ ተነገ ወዲያ አናጣም።" ተስፋ እየሰጧት ነበር። እሷ ግን ለደቂቃ የምትቆይም አልመሰላትም። ከረሃቡ ውሃ ጥሙ ባሰባት።

ትዋኝበት የነበረው የጣና ሐይቅ ትዝ አላት። እየሳቀች የምትንቦራጨቅበት ቀዝቃዛ ውሃ። በሃሳብ ሃይቁ ውስጥ መዋኘት ጀመረች። በሁለቱ መንታ ደሴቶች መሃል ስትዋኝ ታያት። ቀጥሎ ደግሞ ማራኺን አየችው። እየዋኘ መጥቶ በጨለማው ውስጥ አለቱ ላይ ተቀምጠው ጨረቃዋን እያዩ ስለፍቅር ሲዘምሩ። መቃብር ቤቱ

ውስጥ ገብተው ፍቅርን ሲጎራረሱ። መቃብር ቆፋሪዎች መጥተው ሲያስወጧቸው። አባ ፊንሐስ ከሚራኽ ለይተው ጀልባዋ ውስጥ ሲከቷት..........ወይኔ! ብላ ከሐሳቧ አለም ነቃች። ብዙ ደቂቃዎችን በሐሳቧ በመቆየቷ ረሃብና ጥሟን ረስታው ነበር።

አባ ማቴዎስ ፈገግ አሉ። ከማህደራቸው የከተቱት አርባጫ አፈር ትዝ ሲላቸው። አርባጫውን አፈር ከማህደራቸው ዘግነው እንደትበላ ለመኑዋት። «እባክሽ ልጄ ባይሆንለነፍስሽ መያዣ ይሆናል።»

ወዲያው ህፃን ልጇ የሞተባት ሴት ኡኡታዋን ስታቀልጠው ወደ ሴቷ ዞረች። ገንፎ የከለከለቻት ሴት ነበረች። ለልጇ ገንፎውን በስሉ ሳታበላው ሞተ። ጦሙን በባዶ አንጀቱ ፈጅሙን የመንገደ ሰማይ ጉዞ ያለሥንቅ ተያያዘው። ብዙም ሳይቆይ ከድንኳኖቹ ራቅ አድርገው አሸዋውን ቆፍር ቆፍር አርገው ቀበሩላት።

ሴትዮዋ ልጅዋን ቀብራ ስትመለስ ገንፎዋ ተበልቶ ጠበቃት።-"ማነው ገንፎየን የበላብኝ?!" አንባረቀች በሌለ አንጀቷ። እየተመናቀረች መጥታ ሲጳራ ላይ አፈጠጠችባት። ካንገትዋ ሥር የተገታተረው ጅማትዋ ከሩቅ ይቆጠራል።

"አንቺ ነሽ?!" አለቻት። "አሁን ልጠፍጥፍሽ?"

"እረ እኔ አይደለሁም! ማርያምን!" እመቤቴ ቅንጥስ ታርገኝ!" አለች ሲጳራ ከንፈሯ እየተንቀጠቀጠ። አፍዋ በሙሉ ጭቃ ሆኖአል። የምታላምጠው አርባጫ አፈር በከንፈርዋ ዳርዳር ተዝረከርኮአል።

"እሽሽሽ......" አሉ አባ ማቴዎስ የሲጳራን አፍ አፍነው።

"ማርያምን አትጥሪ። አይሁድ ካልሆንሽ አይወስዱሽም"

"አይውሰዱኝ! አላበዙትም? ደግሞ እመቤቴን ማለት አልችልም? እሷን ጠልተው ማንን ሊወዱ ነው?"

"እየውልሽ.... ለእነሱ እኮ ኢየሱስ ገና አልተወለደም። እግዚአብሔር አንድ አምላክ እንጂ አንድም ሦስትም ነው ብለው በስላሴ አያምኑም። ኢየሱስ ክርስቶስ ከማርያም የተወለደ የእግዚያብሔር ልጅ ነው የሚለውን አይቀበሉም። ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን ተሰቅሎ፤ ሞቶ በሦስተኛው ቀን ከሞት ተነሳ፣ከሞት በተነሳ በዓርባኛው ቀን ወደ ሰማይ አረገ የሚለውን ትምህርት አይቀበሉትም፤አያምኑበትም። መሲሑ ገና ከእስራኤል ወገን እንደሚወለድ ነው የሚያምኑት። እግዚአብሔር ፈጣሪ ነውና አይወልድም፤አይወለድም፤አይሞትም፤ይገድላል እንጂ።፡ብለው በፅናት ያምናሉ" አሏት አባ ማቴዎስ ሰው እንዳይሰማቸው በለሆሳስ።

"ለእኔ ግን ኢየሱስ ተወልዶአል። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳም ንዶታል። ሞትን ድል አድርጎ ከሙታን መካከል ተነስቶ በአርባኛው ቀን አርጓል።..... አላዩም?!



......ይህ ሲሆን በስፍራው ያልነበረነው እኛ ስናምን ለምን እነሱ ያዩት አላመኑም?" ጥያቄዋ አይጣል ነው ድሮም።

"...‹ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁአን ናቸው › ተብሎ ተፅፏል ልጄ። ራሱ ኢየሱስም ‹ነቢይ በሀገሩ አይከበርም› ብሏል።"

"እሱማ ልክ ልካቸውን ነግሯቸው ነበር።"

"በቃ ዝም በይ። እሱ ራሱ ያልመለሳቸውን!" ደንቋቸው ፈገግ አሉ። "በቃ ልጄ ዝም በይ። ባካባቢያችን ያሉት ከሰሙን ያቃጥሩብናል። እዚህ በረሃ ውስጥ ጥለውን ከሄዱ ደግሞ መድረሻ የለንም ሀገራችንንም ጥለናት መጥተናል። ተይ! ‹ጅብ እስኪይዝ ያነክስ› ብለዋል አበው። ብቻ ኢየሩሳሌም እግባ እንጂ በሰሌሆም ወንዝ አቅራቢያ ከሚገኘው ንጉሥ ሰሎሞን ለንግሥተ ሳባ ከተናዘዘላት የርስት ቦታ ላይ ካለው ዴር ሡልጣን ገዳማችን ገብተን እንቀመጣለን። እስከዚያ ግን የልብሽን በልብሽ ያዥው"

አባ ማቴዎስ ምንም እንኳዋ እስራኤላዊ ባይሆኑም ኢየሱስ የተመላለሰባቸውን ቦታዎች ሁሉ ተሳልመው ዴር ሱልጣን ገዳም የመግባት ህልማቸውን እውን ለማድረግ ጉዋጉተዋል። ለዚህም ሲሉ የምንኩስና ቆባቸውን ከራሳቸው አውርደው ልባቸውላይ ደፍተውታል።

ገንፎዋ የተበላባት ሴት የልጇን ሞት ረስታ ረሃቧን ልታስታግስ ከጠረጠረችው ጋር ሀሉ ስትሟገት ሲጳራና አባ ማቴዎስ እየተመለከቱ ምሽቱ እየገፋ ሄደ።

በድንገት በድቅድቁ ጨለማ ውስጥ ሸራ የለበሱ የጭነት መኪናዎች መብራታቸውን እያንቦገቦጉ መጥተው ሲቆሙ የታጠቁ ኮማንዶዎች ከመኪናዎች ወርደው በፍጥነት አካባቢውን ተቆጣጠሩት። በየድንኳኑና በውጭ አሸዋ ላይ የፈሰሱት ፈላሻዎች እየተጋፉ፣ እየተዋከቡ ወደ መኪናዎች ተጫኑ። ፈላሻ ያልሆኑትም ስማቸውን ‹ሙሴ፤ያዕቆብ፣ይስሐቅ› እያሉ እየተመዘገቡ ተጫኑ። አሸዋው ላይ እንቅልፍ እንደ ስጦ ያሰጣቸውም ዓይኖቻቸውን እየሞዠቁ ተነስተው ሰልፉ ውስጥ ተቀላቀሉ።

ሞሳድ ለዘመቻ ሙሴ ያዘጋጃቸው እነዚህ መኪናዎች በአንድ ጊዜ መቶ ሰው ብቻ መጫን የሚችሉ ቢሆንም መኪናው ላይ የሚወጡት ግን ከእጥፍ በላይ ነበሩ። በምግብ እጦትና በበሽታ ሲሰቃዩ በመኖራቸው እንኳንስ በመኪና በሰይጣናት ፈረሶች ላይ ተፈናጠውም ቢሆን ከዚህ ምድራዊ ገሃነም ማምለጥ ይፈልጋሉ።

ፈላሻዎቹ በተዘጋጀላቸው አውሮፕላን ወደ ቴልአቪብ ለመብረር ገና በበረሃው ውስጥ በሞሳድ ወደተዘጋጀው አውሮፕላን ማረፊያ ለመድረስ የስድስት ሰዓት የመኪና ጉዞ ማድረግ አለባቸው።

ሲጳራ ሰልፉ ውስጥ ያለውን ግፊ አልፋ መኪናው ውስጥ ልትገባ ስትል አባ ማቴዎስ ስለጠፉባት ተመልሳ ፍለጋ ስትጀምር

ብትለኝም እወድሃለሁ።» ዓይኖቿ እንባ አንቀረዘዙ፡ ማንፍረቅ አልፈለገችም። ሀሳቧን ወደ ሌላ ለመመለስ «ዣንጊዳ ነክቶት የሚያውቅ ዕቃ አለህ?» አለችው። ቀልቧን ወደ መጀመሪያው ነገር ለመመለስ እየታገለች።

«አዎ» አላት። «እንዲያውም ከወራት በፊት ደጋግሞ ሲያነበው የነበረውንና 'እሳት ወይ አበባ' የሚለውን የሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህንን መፅሐፍ ላምጣልሽ።»

እሳት ወይ አበባ የሚለው መፅሐፍ ውስጥ ጨረር በሚተፋ ብዕር መሰል መሳሪያ ገፆቹን ስትመረምር ከቆየች በኋላ'ሰቆቃወ ጴጥሮስ' የሚለው ግጥም ከተፃፈባቸው ገፆች ላይ የዣንጊዳን አሻራዎች አገኘቻቸው። የተላከውን ባዶ ደብዳቤም በዛው መሳሪያ አሰለችው። ተመሳሳዩን የዣንጊዳን አሻራ አየችና «በዚህ ጉዳይ ውስጥ ዣንጊዳም አለበት።» አለችው።

«ምንድን ነው እየሆነ ያለው?» ራሱንም እሷንም ጠየቀ።

«እኔ ምን አውቄ።» አለች ሜሮዳ። «ብቻ ግን አንድ ምስጢራዊ ነገር እንዳለ እገምታለሁ።»

«ምን አይነት ምስጢር?» አለ ሚራዥ። «በአፋጣኝ ኢንጂነር ሻጊዝን ማግኘት አለብኝ።» ጊታሩን መልሶ እንዳገኘው እየገባጠመ። ቁልፎቹን መልሶ በተሰጡት ቀጥሮች ሲጫናቸው የጊታሩ የድምፅ ሳጥን ተንሸራቶ ተዘጋ። «ሻጊዝን ማግኘት አለብኝ። ቢያንስ አንድ ጊዜ ሳላገኘው ወደ ኢትዮጵያ አልሄድም።» አለ የጊታሩን ክሮች በጣቱ እየነካካ።

«ጊታር ልትጫወትለት ነው?» አለችው። «ሞኝ መነኩሴ ነህ ሚራዥ። ቀሽም ነገር ነህ።»

«እንዴት?»

«እሱን እልፍ ውሾች እንደሚከተሉት አታውቅም? መሞት ትፈልጋለህ? እንደገና ከሲ.አይ.ኤ ጋር መጋፈጥ ትፈልጋለህ?»

«እንደምንም ማግኘት አለብኝ።» ብሎ ተንቀሳቃሽ ስልኩን አንስቶ የኢንጂነር ሻጊዝን የስልክ ቁጥሮች ሲጫን ከእጁ ላይ መነጨቀችው። «ስልክህ መጠለፋን እንኳ አታውቅም» አለችው። «የምታሳዝን ፍጡር።»

እጁን ይዛው ወደ መኝታ ቤት ወሰደችውና በሌላ ስልክ እንዲደውልለት ሰጠችው። ደውሎ ኒውዮርክ ከተባበሩት መንግስታት ህንፃ አቅራቢያ በሚገኝ ባንድ ረጅም ህንፃ ላይ እንዲገናኙ ቀጠረው። ኢንጂነር ሻጊዝም ሊያገኘው እንደሚፈልግ በጥድፊያ ነበር የነገረው።



# ፳

## ኒውዮርክ÷አሜሪካ

ከራሱ በላይ ከደፋው ጥቁር ሞላላ ባርኔጣና ከነጭ ሱፉ ጋር ያነገተው ጊታር ተዳምሮ ምርጥ የሮክ ሙዚቃ አቀንቃኝ አስመስሎታል። ከኢንጂነር ሻጊዝ ጋር ወደ ተቀጣጠሩበት ሰማይ ጠቀስ ህንፃ በአሳንሰሩ ወጥቶ ሲደርስ ሳይንቲስቱን ቀድሞት ነበር።

ከአስራ ሁለተኛው ፎቅ ላይ ሆኖ ቁልቁል ሲመለከት የጥቁሮ አውቶሞቢል በሮች በሁለቱም በኩል ተከፍተው ግምብ ግምብ የሚያካክሉ ጋርዶች ሲወጡ አየ። አካባቢውን ተገላምጠው ከቃኙ በኋላ ሌላ ቀጠን ያለ ሰው ወጥቶ የፊተኛውን በር ከፈተ። ሙሉ ጥቁር ሱፍ የለበሰ ሰው ወጥቶ የተባመመ ከረቫቱን እያስተካከለ ወደ ፎቁ ሽቅብ አንጋጠ ተመለከተ። በጥቁር መደብ ላይ ስሳሽ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ መስመሮች ያረፈበት ከረቫቱን አይቶት ያውቃል ሚራዥ። ከላይ ሆኖ ቁልቁል ሲመለከተው መሃል አናቱ ላይ የሀብታም አውድማ የሚያህል በራው ክብ ራሱ ላይ ታየው። ከግንባሩም በኩል በሁለት አቅጣጫ የሸሸው በራው መሀል ላይ ሾጠጥ ብሎ የገባውን ስስ ፀጉሩን የባህር ወሽመጥ አስመስሎታል። በጆሮዎቹና በማጅራቱ በኩል የቀረው ጥቁር ፀጉሩ በራውን ከቦ ጋሜ የተከረከመች ልጃገረድ እንጂ የ55 ዓመት ጉልማሳ አያስመስለውም።

ዶ/ር ሚራዥ ቁልቁል የሚመለከተው ሰው ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝ መሆኑን ለማወቅ አፍታ አልፈጀበትም። ጋርዶቹ አውቶሞቢሏ ውስጥ ተመልሰው ከገቡ በኋላ በዝግታ ተራምዶ ወደ ህንፃው ገባ። ከአይኑ እስኪጠፋ ተከተለውና ጊታሩን አውልቆ ወንበር ይዞ ተቀመጠ።

ኢንጂነር ሻጊዝና ዶክተር ሚራዥ ተገናኝተው መነጋገር ከመጀመራቸው አራት መኪናዎች ከተለያዩ አቅጣጫዎች ተከታትለው መጥተው ከሰማይ ጠቀሱ ህንፃ ስር ባለው መኪና ማቆሚያ ቆሙ። ከውስጣቸው የወጣ ሰው ግን አልነበረም።

ሚራዥን ስትከታተለው የነበረችው ነጭዋ ካዲላክ መኪና ከሁሉም ቀድማ ነበር የደረሰችው። ነጯን ካዲላክ ሲያይ በድጋሚ ከሲ.አይ.ኤ ጋር መጋፈጡን አረጋግጦ ምን ማድረግ እንዳለበት በውስጡ እያውጠነጠነ ነበር ሚራዥ።

ሁለቱ ዕውቅ የሞሳድ አባሎች ሲ.ዳራና ዶክተር አናንያ፣ከጥቁሩ ቢ.ኤም.ደብልዩ መኪና ውስጥ ተቀምጠው ሰማይ ጠቀሱን ህንጻ በዓይነ ቁራኛ እየተከታተሉት ነው። የናሳውን ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝን እያንዳንዱዋን እንቅስቃሴ በስውር እየተከታተሉ ለበላዮቻቸው ሪፖርት ሲያቀርቡ ቆይተዋል። ሞሳድ

እያወሩ ነው:: ስለ ሐበሻው ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝ:: እያወሩ ያሉት ግን ሰውየውን ወደሀገራቸው ወስደው የቴክኖሎጂ እውቀቱን በዝብዘው ሀገራቸውን የረቀቀ የቴክኖሎጂ ባለቤት ስለማድረግ አይደለም:: ግንባሩን በጥይት ወንፊት ስለ ማድረግ እንጂ:: በዚህ ሰው ላይ ግድያ መፈፀማቸው በግልፅ ቢታወቅ ሀገር ውስጥ የሚቀሰቀሰውን ቁጣና አመፅ በመፍራት ሰውየውን የማስወገዱ ሁኔታ ማንም ሳያውቅ መሆን እንዳለበት ወስነዋል:: በመሆኑም ይህ ጉዳይ በጥቂት ሰዎች እጅ እንጂ በአንዳንድ ሀገር ወዳድ ባለስልጣናት እጅ እንኳ አልገባም:: ይህ ሰው እንኳንስ ጭንቅላቱና ሊቅነቱ አስከሬኑ እንኳ ኢትዮጵያን አይረግጣትም ሲሉም ዝተዋል:: ይህ ግዳጅ የተሰጣቸው ታማኝ የኢትዮጵያ የደህንነት ሰዎች ስለዚህ ሳይንቲስት እያወሩ ሽቅብ አንጋጠው ከሰማይ ጠቀሱ ህንፃ ባስራ ሁለተኛው ፎቅ ላይ ዓይናቸውን ተክለዋል:: ቀድሞ ሲከታተለው የነበረው ደህንነት ሰነዱን ሁሉ አቃጥሎ ራሱን ካጠፋ ወዲህ እነዚህ ሁለት ደህንነቶች ስራቸውን እንደገና አሀዱ ብለው ለመጀመር ተገደዋል::

«ይህ ሰው ከአርበኞች ግንባር ጋር ከሚተባበር ለአባት አርበኞች ምርኩዝ መግዣ ቢልክላቸው ይበጀው ነበር» አለ አንደኛው ፈገግ ብሎ::

«እስኪ እናያለን በንጋን ሲረግጣት?» አለ ሁለተኛው:: ሲጋራውን እያቀጣጠለ::

ዶ/ር ሚራኸ ከተቀመጡበት ህንፃ ሥር መኪና ማቆሚያው ውስጥ ከቆሙት መኪናዎች ውስጥ የወጣ ሰው ባለመኖሩ ተገርሟል:: መኪናዎቹ ሰው አልባ ተሽከርካሪዎች መሰሉት:: መስታወቶቻቸው ወደ ውስጥ ስለማያሳይ ውስጥ ያሉትን ማየት አልቻለም:: ነጩን ካዲላክ ግን አውቋታል:: ሲአይኤዎች ተቀምጠው እንደሚከታተሏቸው ማወቁን ለኢንጂነር ሻጊዝ ነግሮታል:: እንጂነር ሻጊዝም «እኔ ለምጃቸዋለሁ::.....ሁሌም ይከተሉኛል::» ሲለው ሜሮዳ የነገረችው ትዝ አለው:: «እሱን ብዙ ውሾች ይከተሉታል::»

ኢንጂነር ሻጊዝ በእሱ ምክንያት ከሥራ በመፈናቀሉ ሲአይኤዎችም ባደረጉበት የግድያ ሙከራ ማዘኑን ገልፆለታል ለዶክተር ሚራኸ:: የንቅሳት ባለሙያው ከኬጂቢዎች ጋር ግንኙነት እንደነበረው ሜሮዳ የነገረችውን ሲነግረው ሻጊዝ ብዙም አልተደነቀም:: ብዙ የሚከታተሉት ሰዎች እንዳሉ ነገረው:: የሚመጡበት ሁኔታና መንገድ ግን ሁል ጊዜም ይለዋወጥበታል::

ዶ/ር ሚራኸ በጊታሩ የድምፅ ሳጥን ውስጥ ያገኘውን «ዶርቶጋዳ» ስለሚለው ንቅሳታቸው ፍንጭ ማግኘቱን በደፈናው ሲነግረው ፍንጩን እንዴት እንዳገኘ አልጠየቀውም ኢንጂነር ሻጊዝ:: ሻጊዝ በንቅሳቱ ምስጢር ላይ ምንም አይነት ጥያቄ ባለማንሳቱ ሚራኸ ግራ ተጋብቷል:: ምናልባት ምስጢሩን ደርሶበት



ይሆን? ሲል አስቦ «ስለ ዶርቶጋዳ የደረስክበት ነጥብ አለ ወይ?» ብሎ ሊጠይቀው ሲቃጣ ከተቀመጡበት ፎቅ ወዲያ ማዶ ስለሚታየው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ህንፃ አሻግሮ እየተመለከተ ሌላ ወሬ ቀጠለ::

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አደባባይ በአንድ ግንብ ላይ «ሰይፋቸውን ማረሻ፣ ጦራቸውንም ማጭድ ለማድረግ ይቀጠቅጣሉ፤ ህዝብም በህዝብ ላይ ሰይፍ አያነሳም፤ ሰልፍም ከእንግዲህ ወዲህ አይማሩም» በሚል ስለተፃፈ ጥቅስ ኢንጂነር ሻጊዝ ወሬ መዘ ማውራት ጀመሩ::

«ይህ ጥቅስ ደስ አይልም?» አለ ሻጊዝ በግንቡ ላይ የተቀረፀውን ጥቅስ ለሚራኸ ከነገረው በኋላ::

«እጅግ ደስ ይላል እንጂ!» አለው ሚራኸም::

«ከጥቅሱ በታች በ1975 ኢሳይያስ የሚለው ስም እንዲቀረፅ ሳይደረግ በፊት ለአስርት አመታት ያህል የጥቅሱ ምንጭ ሳይገለፅ ቆይቷል» አለ ሻጊዝ:: «የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዓላማ ዓለም አቀፍ ሰላም ማስፈን እንደሆነ ለመስበክ ጥቅሱን የመነጩት በ1945 ድርጅቱን የመሰረቱት ሰዎች ናቸው ይባላል:: ግን ጥቅሱና ድርጅቱ አይጣጣሙም::»

«እንዴት?» አለ ሚራኸ እሱም አሻግሮ ወደተባበሩት መንግስታት ድርጅት ህንፃ እየተመለከተ::

«እስኪ ይግረምህ:: ማነው ሰይፉን ማረሻ ለማድረግ የሚቀጠቅጥ? ዓለም በጥይት ቋንቋ ብቻ መግባባት በሚችሉ ፖለቲከኞች ተሞልታ ማረሻቸውን ሰይፍ ለማድረግ በሚቀጠቅጡበት ወቅት ማንን ለማቄል ነው ሰይፋችሁን ማረሻ አድርጉ ብለው የሚሰብኩት? አየህ....ብዙዎች የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን እንደ በጐ አድራጊ የኃይማኖት ድርጅት ይቆጥሩታል:: ግን የጥቂቶች ክንድ ነው:: እንዲያውም የመንግስታት አምባገነንነት መሰረቱና አርአያቸው ይኸው ድርጅት ነው:: የአምስት አገራት የበላይነት ብቻ የሚንፀባረቅበት ድርጅት:: ዋነኛ ሸሪኮቹ ደግሞ የአፍሪካ አምባገነን መሪዎች ናቸው:: ወደኛ ነገር ስንመለስ......ወንድም ሚራኸ ብዙ ነገሮች ያሳስቡኛል» አለው በደቃቃ የንስር ዓይኖቹ እየተመለከተው::

«ምን አይነት ነገሮች?» አለው ሚራኸ ለመስማት እየተመቻቸ::

«በጥቂቱ ልንገርህ:: የሚከነክነኝን:: አንተ ስለእኔ የምታውቀው አለህ:: በመገናኛ ብዙሃን ወይም በስሚ ስሚ:: ስለ እኔ ማወቅህና አለማወቅህ አያሳስበኝም:: እኔ አንተን በማወቄ ግን እኮራለሁ:: ምክንያቱም ውስጥህ ቅንነትክን አይቻለሁ:: ከዚህ የበለጠ ነገር የለም::» ትኩረቱን ሙሉ በሙሉ ለመሳብ:: «በሲስተም ኢንጂነርነትና በፈጠራ ሳይንቲስትነት በሠራሁባቸው ዓመታት ከሌሎች ሳይንቲስቶች ጋር በመተባበር ለመሬታችንና ለሌሎች

ኘላኔቶችም የምርምር ሳይንስ የሚያገለግሉ መንኮራኩሮችንና ሮኬቶችን ለመፍጠር ችያለሁ። ግን ምን ዋጋ አለው!» ኢንጂነር ሻጊዝ የዶ/ር ሚራዥን ዓይኖች ጠልቆ ተመለከታቸው።

«እንዴት ዋጋ የለውም? አለው እንጂ። ይህ እኮ ለብዙዎች ኩራት የሚሆን ተግባር ነው በተለይም ለጥቁር ህዝቦች» አለው ዶ/ር ሚራዥ።

«ዋጋ እንደሌለው የተረዳሁበትን ምክንያት ልንገርህ ነው። ላለፉት በርካታ ዓመታት ስታር ዋርስ ለሚባለው የመከላከያ ሲስተም ቴክኖሎጂ ለማጐልበት የሳይንቲስቶችና ኢንጂነሮች ቡድን መሪ በመሆን አገለገልኩ። ይህም ከንቱ መሆኑን አወኩ፡ የልዕለ ሀያላኑን ሀገራት መንኮራኩሮች ወደ ህዋ ሳስወነጭፍ ኖርኩ። የሰሜን አሜሪካ የህዋ አስተዳደርና የአውሮጳ የህዋ ማዕከል የሳይንቲስቶች ቡድን መሪ ሆኜ በህዋ ውስጥ ለሚደረግ ተልዕኮ መጠቀሚያ መንኮራኩርና ምድርን እየዞሩ ደሀ ሀገራትን ለብዝበዛ የሚያመቻቹ ሳተላይቶችን እንዲመጥቁ አደረኩ። በጠፈር መንኮራኩር የምድርን ሀብት በተለይም የአፍሪካ አህጉርን የመሬት ውስጥ ሀብት አይቼ በሶስተኛው አለም በረሀብና በስቆቃ የሚሰቃዩ ህፃናትንና አዛውንቶችን ሳስብ ውስጤ ይሰበራል። ከዚህ በላይ ከንቱነት አለ? እኔ የኘላኔቶችን ውስጣዊና ውጫዊ አካል በዩኒቨርስ ውስጥ ለማጥናት ስኳትን ወገኖቼ ግን በረሃብ አለንጋ ይገረፋሉ።» ዓይኖቹ እንባ አቀረሩ።

«እና ከንቱነቱ ምንድን ነው?» አለ ሚራዥ «ማወቁ መልካም አይደለም እንዴ?»

«ባላወኩት ወዳጄ! አየህ ሃያላን ሀገራት መሬትን ወደ ገሃነምነት እየለወጧት ነው። ድሮ በቅኝ ግዛት የአፍሪካን የምድር ሀብት ሞጨለፉና ከበሩ። አሁንም ቀሪውን ለመቀራመት የማይሠሩት ደባ እንደሌለ አውቄያለሁ። መሬት ወደ ገሃነምነት ብትለወጥ ቀዳሚ ተጠቂዎቹ አሁንም የሶስተኛው አለም ደሃዎች ናቸው። የኃይል ሚዛኑ በዚህ ከቀጠለ የመሬት ህልውና የሚያከትምበት ጊዜ በየደቂቃው እየፈጠነ እየቀረበ ነው። በፈጠሩት ገሃነማዊ ሙቀት የምድራችን ውሃ ፈልቶና ተኖ ውቅያኖሶች ላይ አውሎ ነፋስ የሚነሳበትን ጊዜ ለማወቅ አቡሻህር ገልጦ ጠጠር መጣል አያስፈልግም።»

«አልገባኝም ኢንጂነር። እያልከኝ የለኸው ታዲያ ዛፍ እንትከል ነው?»

«የምነግርህ ለምን የመሬትን ሀብት ከመጠን በላይ መቀራመት እንደፈለጉ ነው። መሬትን ተቀራምተዋታል። አሁን እየተቀራመቱ ያሉት ደግሞ ዩኒቨርስን ነው። ለዚህም ነው መንኮራኩሮቻቸውን በየጊዜው የሚያመጥቁት። ሌላ ምቹ የሰው ልጅ መኖሪያ ካገኙ ዜጐቻቸውን ወደዚያ በመንኩራኩር ያጓጉዛሉ።»

ሚራዥ ከት ብሎ ሳቀ።



«እየቀለድኩ አይደለም። አሜሪካውያን ወይም ቻይናውያን ወይንም ሩሲያውያን አልያም ኮርያውያን አለበለዚያም ጃፓናውያን ቀድመው በህዋ ውስጥ በሚገኘው አዲስ ገነት ውስጥ ይሰፍራሉ። በተለይም ለእስራኤላውያን አስፈላጊ ነው። በዚህ የጠበባቸውን ያህል በዚያ ሰፋ አድርገው ለመያዝ። ከጨከኑም ሁሉንም ይዘው በኋላ የሚመጣውን መንኮራኩር በተምዘግዛጊ ሚሳዬል አመድ ሊያደርጉት ይችላሉ። ከዚያም ደሀ ሃገራት መሬት ላይ እየጻሁ ገሃነሙ ውስጥ ተጠራርገው ይገባሉ። አፍሪካ ወደ ገሃነም ሀያላኑ ወደ ሌላ ኘላኔት። ወደ ሌላ ገነት። ይህ ከመሆኑ በፊት የመንኮራኩሮች ግንባታና የኃይል አቅርቦት ሩጫና ፉክክሩ በልዕለ ሃያላኑ ሃገራት እየተሟሟፈ ነው። የኃይል አቅርቦቱን ለማሟላት የመሬትንና የጨረቃን ሀብት በመንኮራኩር በማሰስና በመቃረም ተግባር ላይ ናቸው። ነገሩን አጭር ለማድረግ ያህል ለምሳሌ የኢትዮጵያን የምድር ሃብት ብናይ እንኳንስ ለኢትዮጵያውያን ለአፍሪካ ህዝቦችም የሚበቃ ነው። የምነግርህ ያየሁትን ነው። ሚራዥ። ዩራኒየሙ፣ ኘላቲኒየሙ፣ የከሰል ድንጋዩ፣ መዳቡ፣ ወርቁ፣ ብሩ፣ የነዳጅ ድፍድፉና አልማዙ ሁሉ ያላት ባለፀጋ ሀገር ናት። የብዙ ሃገራት አይን አርፎባት የኖረው ለሌላ ለምንም አይደለም። ኢጣሊያን አስወጥታ እንግሊዝ፣ እንግሊዝን ገዝግዛ አሜሪካ፣ ምናልባት አሁን ደግሞ የአሜሪካን ቦታ ለመያዝ ደፋ ቀና የምትለው ቻይናም....እነዚህ ሁሉ የሚሻኮቱባት ምድር ኢትዮጵያ ያንቀላፋችበት ወቅት ላይ ነን። በአሁኑ ወቅት.....ኢትዮጵያ ለብዝበዛ ተንጋላ የተኛች ሀገር ናት። ይህን ሁሉ ሀብቷን ደብቀው ህዝቧን በእርዳታ ሸባ እያደረጉ ለድህነትና ለጭቆና እየተከፈለን ሳንኖር እየኖርን ያለንበት ወቅት ላይ ነን።» ኢንጂነር ሻጊዝ የሚራዥን ትኩረት ያገኘበትን ቅፅበት ላለማቋረጥ ቀጠለ። «ኢትዮጵያን ለመመንተፍ በኢንቨስተር ስምና በተለያዩ የረድኤት ድርጅቶች የተሰገሰጉ ወንበዴዎች ህዝቡን በስብሰባና በፎረም ቁጭ አድርገው እያንጫጩ እነሱ ሥራቸውን ከሙሰኛ ባለሥልጣኖቻችን ጋር በሽርክና ይሠራሉ። ምናልባት የኢትዮጵያን ጉዳይ ዕለት በዕለት የምትከታተል ከሆነ...»

«አዎ በመጠኑ እከታተላለሁ።» አለው ዶ/ር ሚራዥ።

«የኢትዮጵያ መሪዎች በየቀኑ ብድር ይፈራረማሉ። ባለስልጣናቱ የብድር ሥምምነት ሳይፈራረሙ የሚውሉበት ቀን የለም። ኢትዮጵያ መጭው ትውልድ ከፍሎ የማይጨርሰው ብድር ተበድራለች። እያንዳንዱ ወጣት እያንዳንዱ ታዳጊ የሚወርሰው ሌላ ነገር የለም። ቀጣዩ ትውልድ የሚወርሰው የትየለሌ ዕዳ ብቻ ነው። የገንዘብ ዕዳ፣ የሞራል ዕዳ፣ የደም ዕዳ። ገና የምንከፍለው ብዙ ነገር አለ። ኢትዮጵያውያን ነዳጃቸው ላይ ቆመው እየለመኑ ነው። ኢትዮጵያውያን ዩራኒየማቸው ላይ ቆመው ኃይል አጥሯቸዋል፣ በጨለማ እየኖሩ ነው። የኢትዮጵያ ጥቋቁር አልማዞች ጥቁር አልማዛቸው ላይ ቆመው እየተመፀወቱ ነው። ...ይህን ሁሉ የዘበዘብኩብህ ወድጄ አይደለም። ወንድሜ ሚራዥ?.....እኔና አንተስ

እስከመቼ ዝም እንላለን?» አለው ይበልጥ ወደፊቱ ተጠግቶ በጥያቄ ዓይን፡፡ «ስለዚህ ጉዳይ እስከመቼ ድረስ ዳር እንቆማለን?»

«እስከመቼም!» አለ ሚራዥ ውስጡ ተቃጥሎ፡፡ «እኔ በበኩሌ ከአሁኗ ደቂቃ ጀምሮ ማንኛውንም ተግባር ለመፈፀም ዝግጁ ነኝ፡፡ ግን ምን ማድረግ እችላለሁ? የችግሩ ሰንሰለት ተቆርጦ የማያልቅ ነው፡፡ የሰው ኃይልና በቂ ገንዘብ ይፈልጋል፡፡»

«በቂ ገንዘብ ብቻ አይደለም የሚፈልገው፡፡ ብዙ ህዝብም አይደለም የሚፈልገው፡፡ ልብ ለልብ ከተገናኘንና አብረን ከሰራን እንኳንስ አንዲት ሀገር አለምን መለወጥ የሚያስችል እውቀትና አቅም አለን፡፡ አለማችን የተለወጠችው እጅግ በጣም በጥቂት ሰዎች ነው፡፡ አሥር በማይሞሉ፡፡ አሜሪካን በሁለተኛው የአለም ጦርነት ዋዜማ የአቶሚክ ኢነርጂ ባለቤት ያደረጓት ሳይንቲስቶችን አስብ፡፡ ኤንሪኮ ፈርሚን፣ ሊዎ ስዚላርድን፣ አልበርት አንስታይንን፣ ሩተርፎርድን፣ ቦንን........፡፡ የእነዚህ ሳይንቲስቶች ባንድ የታሪክ አጋጣሚ መገናኘት ነው አሜሪካን ልዕለ ሀያል ሀገር ያደረጋት፡፡ አሜሪካ አዕምሮን እንዴት ማጠብ እንዳለባት ታውቅበታለች፡፡ ገና ምድሯን ሳትረግጥ አሜሪካዊ የሆንህ ያህል እንዲሰማህ የሚያደርጉ ታላላቅ ሰዎች ያሉባት ሀገር ናት፡፡ እኛ ሀገር ደግሞ ባደክበት ቀየ ባደክበት ምድር ወዘ ልውጥ እየተባልክ ትኖራለህ፡፡ ለሀገርህ ባዳ ሆነህ አያገባህም እየተባልክ አፍህን ጠመንጃ ሸብቦት ብታውቅ እንኳዋ እንዳላወክ ሆነህ ትሞታለህ፡፡ እነዚህ አሜሪካን ልዕለ ሀያል ሀገር ያደረጉዋት ሳይንቲስቶች ሁሉ አሜሪካውያን ናቸው፣ አይደሉም፡፡ እምባገነን መሪዎቻቸው ያሳደዷቸው የሌሎች ሀገራት ዜጎች ናቸው፡፡ የኛና የሌሎች ኢትዮጵያውያን ምሁራን እጣ ፋንታም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ የተማረ ሰው አጥታ አይደለም የተማረ ስለማትወድ እንጂ፡፡ ግን ...» አለው ኢንጂነር ሻጊዝ፡፡ «አንድ ነገር ያስፈልጋል፡፡ ለለውጥ ራስን መስጠት፡፡ አሁንም....... ኢትዮጵያ አንድ አብዮት ያስፈልጋታል፡፡ ልጆቿን የማይበላ አብዮት! ራሱን የማይውጥ አብዮት! ሳይንቲፊክ ሪቮሉሽን፡፡ በሳይንስና ቴክኖሎጂ የታገዘ አብዮት፡፡ አየህ ሚራዥ..... ለውጥን የሚጠላ ኢትዮጵያዊ የለም፡፡ ለውጡ ሆዳቸውን ከሚያጉልባቸው ጥቂቶች በቀር፡፡ ችግሩ ግን የለውጡ አካል ለመሆን የሚፈልግ የለም፡፡ በሌሎች ሞትና ደም ለመጠርቃትና ኑሯቸውን ለማደላደል የሚመኙ ብዙ ናቸው፡፡»

«እኔ በበኩሌ» አለ ዶ/ር ሚራዥ፡፡ «በሰቆቃ ውስጥ ያሉት ወገኖቼን ችግር መቅረፍ የምችልበት አቅም ያለኝ ሰው ከሆንኩ ይኸው እንደፈለገህ አድርገኝ፡፡ ግን እንዴት ለውጡን ማምጣት እንችላለን?.... ኢትዮጵያ እያስፈለግሃት አትፈልግህም፡፡ ኢትዮጵያ እንደ ሴተኛ አዳሪ ሴት ተኳኩላ በር ላይ የምትጠብቃቸው የሩቆችን ነው፡፡ ገመናዋን ጉዷን የሚያውቁላትን አታስጠጋም፡፡



ባይኗ ገርፋ ታባርራቸዋለች፡፡ በሰይፏ ትጠርጋቸዋለች፡፡ የተማሩት ይሰደዳሉ፡፡ የሚማሩት ወጣቶችና ታዳጊዎች ከእስር ቤት በማይተናነሱ ትምህርት ቤት ተብየዎች ታጉረው የነቀዘ ቲዎሪ እንዲሸመድዱ አእምሯቸው ነፃነትን እንዳያስብ ተደርገው ይውላሉ፡፡ ከዚህ ሰንሰለት ለማምለጥ የሚጥሩ ሲገኙ በጠላትነት ይፈረጃሉ፡፡ ታዲያ እኔና አንተ በምን አይነት መልኩ ይህን ያህል ችግር መቅረፍ እንችላለን?» ሲል ሚራዥ መልሶ ጠየቀው፡፡

«እንግዲያውስ የያዝከው መንገድ ወደዚያ የሚያደርስህ ነው!» አለው ኢንጂነር ሻጊዝ፡፡

«የትኛው የያዝኩት መንገድ?» ሲል ጠየቀው ሚራዥ

«ወደ ተጠራህበት ያለማቅማማት ተጓዝ፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ሂድ፡፡ አታቅማማ፡፡ በአቅማማህ ቁጥር መንገድክን ትስታለህ፡፡ እስከ አሁን የተጨዋወትነው ሀገራዊ ጥያቄ የሚፈታው በያዝከው ጎዳና ነው፡፡ በድጋሚ የምነግርህ በአቅማማህና ባወላወልክ ቁጥር ተመራጩ ሰው አትሆንም፡፡ ቅድም ያልከው፡፡ ዩራኒየሙ፣ የሰብል ድንጋዩ፣ መዳቡ፣ ወርቁ፣ ፕላቲኒየሙ፣ የነዳጅ ድፍድፍ ገደሎችም ከአንተ አይበልጡም፡፡ ኢትዮጵያ እየጠራችህ ነው፡፡ እነዛኞቹን ርሳቸው፡፡ ዝም ብለህ የራስህን ጉዞ ተጓዝ፡፡» ሲለው ዶ/ር ሚራዥ የማያውቀው የተወሳሰበ ነገር ውስጥ እግሩን ማስገባቱን ተረዳ፡፡ ግን 'ለምን አይነግረኝም ሁሉን ነገር?' ሲል አሰበ፡፡

ሚራዥ ግራ ተጋብቶ ለደቂቃዎች ፀጥ ብሎ ከቆየ በኋላ «ወዴት ነው የምጓዘው?» ሲል ሻጊዝን ጠየቀው፡፡

«ይህን ምስጢር እንዳቀብልህ አልተፈቀደልኝም፡፡ አንድ ምክር ግን ልለግስህ እችላለሁ፡፡ ከሁሉም በላይ ምስጢር ጠባቂነትህን ማረጋገጥ አለብህ፡፡ ቅንጣት የምታህል ስህተት ወደገሃነም እንደምትወረውርህ አስብ፡፡ ላስፈራራህ አይደለም፡፡ አንድ ነገር ግን ላረጋግጥልህ እወዳለሁ፡፡ ጉዞ ጀምረህ መመለስ እንደማትችል፡፡ ካልፈለግህ አሁን ንገረኝና አሁኑኑ ማቆም ትችላለህ፡፡ አርፈህ የግልህን ህይወት መኖር ትችላለህ፡፡»

ዶ/ር ሚራዥ ለረዥም ጊዜ በብቸኝታ ውስጥ ከቆየ በኋላ ቁርጥ ውሳኔ ላይ ደረሰ፡፡ «የመጣው ይምጣ፡፡ አላቅማማም፡፡ አላፈገፍግም» ሲል ነገረው፡፡ «ግን የአንተን የልብ ችግር መፍታት እፈልግ ነበር፡፡»

«የልቤን ችግር ለመፍታት የቻልከውን አድርገሃል፡፡ ከአቅምህ በላይ ነው አሁን፡፡ ስለኔ ብለህ ከሥራ ተፈናቅለሃል፡፡ በህይወትህ ላይ አደጋ እንዲንዣበብ አድርገሃል፡፡ ከዚህ በላይ ልታደርግልኝ የምትችለው ነገር የለም፡፡ ብንችል አንድ ቀን ሀገራችን ውስጥ እንፈታዋለን፡፡ አለበለዚያ ስለ እኔ ለረጅም ጊዜ መኖር አትጨነቅ፡፡ እኔ እልፍ ለመኖር ምኞት የለኝም፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ በየቀኑ በረሃብ ስለሚያልቁ ህፃናት ተጨነቅ፡፡ እኔ ብሞት ኢትዮጵያ ሰው አታጣም፡፡ በየዘመኑ አንዳንድ ሰዎችን አጥታ

አታውቅም:: ደጋጉቹ በክፉዎቹ ብዛት እየተዋጡ እንጂ:: አትጨነቅልኝ:: ይልቅ እኔም አንተም ሞት ሳይቀድመን ወገኖቻችንን ከሞት የምንታደግበት ወቅት ላይ መሆናችንን አስብ:: ኢትዮጵያውያን አንገታቸውን የደፉበት ወቅት ላይ ነን:: በሃፍረት ተሸማቀዋል:: አቀርቅረዋል:: ሴቶች ለአረብ ነጋዴዎች እየተሸጡ ነው:: ወጣቶች በጠረፋማ አካባቢዎች ከሀገር ሲወጡ በጋንጃቸው እየታረዱ ነው:: ኢትዮጵያ ተስፋ በቆረጡ ወጣቶች ተሞልታለች:: ራዕይ ያጡ ህዝቦች ጎተራ ሆናለች:: ራዕይ የሌለው ህዝብ ደግሞ ይጠፋል:: የተስፋው መስኮት መከፈት አለበት:: ኢትዮጵያን ሌላ ሰው መጥቶ አይለውጥልህም:: አንተን ለመለወጥ ሌላ ሰው አይመጣም:: ይህን ሀቅ እወቅ:: ኢትዮጵያ ውስጥ ሺ ብትን የሚሉ ቻይናዎችና አረቦች ሁሉ ለአንተ ብልፅግና ግድ የላቸውም:: ሀገርህን ከቅጥረኞችና ከወሮበሎች የምትታደግበት ጊዜ አሁን ነው::» ሻጊዝ የሚራዥን እጅ ያዘውና የዓይኖቹን ውስጥ ተመለከተ::

«አንድ ጥያቄ እንድጠይቅህ ፍቀድልኝ?» አለው ሚራዥ::

«ጠይቀኝ እስከተፈቀድልኝ እነግርሃለሁ::» አለው ሻጊዝ::

«ወደ ጦር ሜዳ እየላካችሁኝ ነው?»

ሻጊዝ ከት ብሎ ሳቀ:: «የደርግ ወታደር እንደነበርክ አውቃለሁ:: ገዳማዊ እንደ ነበርክም እንዲሁ:: ታዲያ ወታደርና መናኝ ሞት ይፈራል?»

«አይፈራም ይሆናል:: ግን ጦርነት አልወድም:: እናም ከአሁን በኋላ በማንም ሰው ላይ ቃታ አልስብም::»

«እኛም ሰይፍህን እንድታነሳ አንፈልግም:: ስለዚህ እየሄድክ ያለኸው ወደ ጦርነት እንዳልሆነ እወቅ::»

«ታዲያ ወዴት ነው?»

«እሱን ምስጢር እንድነግርህ አልተፈቀደልኝም:: ብዬሃለሁ አይደለም? ሁለት አማራጮች አሉህ አሁን:: ጉዞውን አሁኑኑ በእኔ ፊት ማቆም አንድ! ሳታቅማማ በጊታርህ ዜማ ዘና እያልክ መጓዝ ሁለት:: ከዚህ በተረፈ በማስተዋል መጓዝ:: በጥበብ መጓዝ:: አለቀ::»

«እምንሃለሁ ኢንጂነር::»

«እኛም በረጅም ጊዜ ጥናት ታማኝነትህን ማረጋገጥ ጀምረናል:: አንተም አሁን አረጋግጥልን:: ባለማቅማማት::»

«አላቅማማም:: ግን ዴርቶጋዳ ምንድን ነው?»

«ባላቅማማህ ቁጥር ወደ ዴርቶጋዳ የምትደርስበት መንገድ ቀና ይሆናል:: ዝም ብለህ ወደፊት ተጓዝ:: አሁን የሚመሩህ አሉ:: ሌላ ጊዜ ደግሞ በተራህ የምትመራቸው አሉ:: መጀመሪያ ጥሩ ተመሪ ሁንና ከዚያ ጥሩ መሪ ትሆናለህ::»

ኢንጂነር ሻጊዝና ዶ/ር ሚራዥ ይህን ሲነጋገሩ በነበሩበት ቅፅበት አንዲት ወፍራም ሴትዮ ወደ ህንፃው አሳንሰር ገባች:: ማንም ትኩረት አላደረገባትም:: መኪናዎቹ ውስጥ ያሉት ሰዎች የቆርቆሮ ቢራ እየጠጡ ሽቅብ አንጋጠው እየተመለከቱ ነው::



ወደ ህንፃው የገባችው አሮጊት ሴትዮ እጅግ ወፍራም በመሆንዋ እግሯን ከወገቧ ወገቧን ከአንገቷ ለይቶ ማወቅ አይቻልም:: ክብ ጉጆ ቤት ትመስላለች:: ከጀርባዋ ረጅም ሻንጣ አንግታለች::

ሚራዥ ሴትዮዋ ወደ ውስጥ ከገባች ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በተንቀሳቃሽ ስልኩ መልእክት እንደደረሰው ሻጊዝን ተሰናብቶት ተነስቶ ወደ ህንፃው ሽንት ቤት ገሰገሰ::

ወዲያው ከጥቁሩ ቢ.ኤም.ደብልዩ መኪና ውስጥ ተቀምጠው የነበሩት ሲጳራና ዶ/ር አናንያ ከመኪናዋ ወጥተው ወደ ህንፃው አሳንሰር በፍጥነት ገቡ::

ከቀይዋ ፊያት ውስጥ ያሉት የኬጂቢ ወኪሎች ከነጭዋ ካዲላክ ውስጥ የነበሩት የሲ.አይ.ኤ ሰዎችም ተከታትለው ወጥተው ወደ ህንፃው ገቡ:: ሰዓቱ መድረሱን ተገንዝበዋል:: ከኢንጂነር ሻጊዝ ጋር ያንን ያህል ሰዓት ተቀምጦ ሲያወራ የነበረው ባለጊታር የሚያዝበት::

የሞሳድ ኤጀንቶች ሲጳራና አናንያም ይህን ያህል ጊዜ ከኢንጂነሩ ጋር ተቀምጦ የቆየውን ባለጊታር ማንነት ለማወቅ ብቻም ሳይሆን አንገቱን ለመበጠስ ሽጉጣቸውን አቀባብለው እየጠበቁት ነው::

ኢንጂነር ሻጊዝ በቁጥር አስራ ሁለቱ በር በኩል በሚገኘው አሳንሰር ፎቁን ወርዶ ወደ መኪና ማቆሚያው ሲደርስ ጋርዶቹ ከመኪናው ወጥተው አካባቢውን ተቆጣጠሩትና ከለላ ሰጥተው ወደ መኪናው አስገቡት::

ከጥቂት ጊዜ ቆይታ በኋላ ጉጆ ቤት የምታህለው ወፍራም ሴትዮ ሻንጣዋን ከጀርባዋ እንዳዘለች ሌላ ክብ ከሆነች ወፍራም ሴት አስከትላ ወጣች:: ሁለቱ ወፍራም ሴቶች ተከታትለው ከሩቅ ወደቆመችው የቤት መኪና እንደገቡ መኪናዋ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ህንፃን ወደቀኝ ትታ ከነፈች::

የኢንጂነር ሻጊዝ ተንቀሳቃሽ ስልክ ጠራ:: «ኢንጂነር ሻጊዝ ከህንፃው ወጥቼ ሄጃለሁ:: ደህና ነኝ አሁን:: ስለእኔ ደህንነት አታስብ:: ስለአንተ ደህንነት እንጂ:: አሁን ተንቀሳቀስ ካለህበት:. መልካም ጊዜ:: ቻው::» ስልኩ ተዘጋ:: የዶ/ር ሚራዥ ድምፅ ነበር::

«የኔ አንበሳ» አላት ሚራዥ ሚሮዳን:: «አደንቅሻለሁ::» ኢንጂነር ሻጊዝ ዶ/ር ሚራዥ ምን አይነት ዘዴ ተጠቅሞ ከህንፃው ወጥቶ እንዳመለጠ ባያውቅም ደህና በመውጣቱ ተደሰተ::

የኢንጂነር ሻጊዝ መኪና ከአካባቢው እስከምትሰወር ወደ ህንፃው የገቡት የሞሳድ፣ የሲ.አይ.ኤና የኬጂቢ ሰዎች አልተመለሱም ነበር:: ከኢንጂነር ሻጊዝ ጋር የነበረው ባለጊታር የውሃ ሽታ በመሆኑ በንዴት ጦፈው ተመለሱ::

ከማፍያዎች ጋር ሲቀላቀሉ የራሳቸውን ቡድን የመመስረትና ዶን የመሆን ህልም ሰንቀው ነበር:: ሲሲሊ ውስጥ ለማፍያዎች የሚሰጠውንና ዶን የሚለውን የክብር ስም ለማግኘት ቀላል ባይሆንም እርሳቸው ግን በብልጠት ቀላል አደረጉት:: ቀስ በቀስ ሲሲሊ ሞርሞርዲኖ የሚለውን ስም መስማት ጀመረች:: አስፈሪው ሞርሞርዲኖ የሲሲሊን ማፍያዎች አቻ ለመሆን የተጠቀሙትን ዘዴ እስከዛሬ ማንኛውም ማፍያ የተጠቀመው አልነበረም:: የማፍያዎች አለቃ ሆነው ዶን የሚለውን የክብር ስም ሲጐናፀፉ ጠንካራ የማፍያ ቤተሰብ መሥርተው ነበር:: በዚህ ቤተሰብ ውስጥ ግን አንድም ዘመዳቸው አልነበረም: ከአርባ በላይ ሰዎች ባሉበት ቤተሰብ ውስጥ አንድ ታማኝና አደገኛ ጥቁር ሰው መኖሩንም መላ ሲሲሊ ያውቃል:: ኢትዮጵያዊው ዲምላ የሞርሞርዲኖ ቀኝ እጅ የሆነበትን ምስጢር ግን እሱ ብቻ ነው የሚያውቀው::

ዶን ሞርሞርዲኖ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ ቀርቶ ከነበረው ቤተሰብ ውስጥ የተረፉ ብቸኛው ሰው ናቸው:: ሲሲሊያውያን የሲሲሊ ራስ ይሏቸዋል:: ፓሌርሞም ከመንግሥት ባለስልጣናት ይልቅ ለሞርሞርዲኖ ሰጥ ለበጥ ትላለች:: ሲሲሊ ውስጥ ትክክለኛ ገዢዎች ማፍያዎች ናቸው:: በማፍያዎች ጥበቃ ውስጥ ያልታቀፈ ማንኛውም ቤተሰብ በአንድ ሌሊት ላለመጥፋቱ ዋስትና የለውም:: በማፍያዎች ጥበቃ ውስጥ ሆኖ ለነርሱ የማይገብር ቤተሰብ ይጠፋል::

በዚህ ከፍተኛ ጥበቃ በሚደረግለት የቤታቸው ግቢ ውስጥ ዝር የሚል የለም:: የዛሬውን ደስታ በፈንጠዝያ ለማጀብ ከምድር በታች በተሰራው ሌላኛው የቤታቸው ክፍል ውስጥ በእሳት መሞቂያው አቅራቢያ ወይን እየተቀዳ በእቁባቶቻቸውና በሚስቶቻቸው የተከበቡት ዶን ሞርሞርዲኖ ሴቶቹ በሚዘምሩት ለእርሳቸው መወድስ ሲባል በተደረሰው መዝሙራቸው እየተደሰቱ፣ የጥንታዊነትና የታላቅነት ስሜት እየተሰማቸው ነው:: ሴቶቹ በቆየ ዘየ ሚዘምሩት የውዳሴ መዝሙርና በወይኑ መጠጥ ስሜታቸው በደስታ ንሯል:: ሳቁና የወይኑ ዱቅዱቅታ አስፈንድቋቸዋል::

«....ጌታ ሞርሞርዲኖ ሞርሞርዲኖ ቡስኪ የሲሲሊው አድባር
አይሞት አያረጅም ፀሐይ ቢጠወልግ ጨረቃ ቢሰበር ......»

ሰምተው አይጠረቁም ይህን መዝሙር:: መዝሙሩን ሲሰሙ ወንድነታቸው ይነቃቃል:: ሁሉም ነገር ወደንረት ያመራል:: ቀንዳቸው ይሾላል:: በወይኑ ሞቅታና ዕርቃናቸውን በዙሪያቸው በሚያሻሿቸው የወሲብ እመቤቶች በሚመስሉ ሴቶች እቶናዊ ገላ በእርካታና በንረት ይስቃሉ:: ምድር ቤቱን የሳቅ ማምረቻ ያስመስሉታል:: በወይኑ ዱቅዱቅታና የእሳቱ ነበልባል በፈጠረው ግለት ከእቁባቶቻቸው መሃል ደስ ያለቻቸውን መርጠው ይወስባሉ:: ሌሎች ሲያሻሿቸው ከፊሎቹ መዝሙሩን ይቀጥላሉ:: የጀመሯት



ካልጣመቻቸው ሌላኛይቱን ጐትተው ጭኗ ሠስጥ ይገባሉ:: እሷም ካልጣመቻቸው ሌላይቱን ከኋላ ማጥቃት ይጀምራሉ::

የዶን ሞርሞርዲኖ ቡስኪ እድሜ እየገፋ በመጣ ቁጥር የእቁባቶቻቸውና የጠባቂዎቻቸው ሀብታቸውን የመቀራመት ሽኩቻም በዛው ልክ እየናረ መጣ:: እሳቸው ግን ፀጉራቸውና ቆዳቸው እንጂ ልባቸው ገና አላረጀም:: ቅንጣት ታህል ዝንጋኤ አይነካካቸውም:: እንዲያውም እያረጁ በመጡ ቁጥር የማስታወስ ብቃታቸው እየበለፀገ መጣ:: በአንድ ወቅት ፈረንሳይ ውስጥ ሾርባ ቀርቦላቸው ከተመገቡ በኋላ ሲከፍሉ አስተናጋጁ አምስት ሱ አጥቶ ያልመለሰላቸውን ሁሉ ሳይቀር እስከ ቀኑ እስከ ሰዓቱ ድረስ ያስታውሱታል::

ጠባቂዎቻቸው በነሀ አዛውንት እድሜ ዘልዛላነት መማረር ጀምረዋል:: የአዛውንቱን ሞት እየተጠባበቁ እርስ በእርሳቸው አሥራ ስምንቱም ሊዔረሱ ሴራ እየተጠማጠሙ ነው::

ከአስራ ስምንቱ ጠባቂዎች ውስጥ ብቸኛው ጥቁር የሆነው ዲምላ አያሌው የሴራው ቅድሚያ ተጠቂ ሆኗል:: በእርግጥ የቀድሞ ስሙ ሽብሩ አያሌው ነበር:: ቀጥሎ ስሙን ፊላ ብሎ ራሱ በመሰየሙ ፊላ አያሌው እየተባለ ይጠራ ነበር:: ከኢትዮጵያ ወደ ጣሊያን ከመሄዱ በፊት በሁለት የኢትዮጵያ ከተሞች ኑሯል:: አንዱ ባህርዳር ከተማ ውስጥ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ቦንጋ ከተማ ውስጥ ነበር። በባህር ዳር ፊላ አያሌው ይባል የነበረውን ወደ ቦንጋ ሲሄድ ደግሞ ሞርሞርዲኖ ባወጡለት ስም ዲምላ አያሌው ተብሎ ይጠራ ነበር:: ቦንጋ ውስጥ ይኖር የነበረው ከኢትዮ ጣሊያን ጦርነት በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ ከቀረው ጣሊያናዊ ቤተሰብ ጋር ነበር:: ይህ ቤተሰብ ኢትዮጵያ ውስጥ የቀረበትን ምክንያት በውል ባያውቅም በምቾት ምክንያት እንዳልሆነ ግን ያውቅ ነበር:: የዚህ ቤተሰብ አባላት በከፊል ወደ ጣሊያን ሲሄዱ አብሮ ወደ ጣሊያን ተጓዘ:: የመርሞርዲኖ ቡኪስ ታማኝ ጠባቂ ሆኖ መኖር ከጀመረ ብዙ ዓመታት ተቆጥረዋል:: የሞርሞርዲኖ ጠባቂዎች ሀብታቸውን ለመቀራመት እርስ በእርስ ሲጠላለፉ እሱን ቀድመው ለመጣል እንደተባበሩበት ገብቶታል:: ክፋታቸውንና ሴራቸውን ቀድሞ ይነቃባቸዋል:: ይህ ወቅት ግን እጅግ የመረረበት ወቅት ነው:: የመረረበት ምክንያትም ከጉልበት በቀር ብዙም እውቀት ለሌለው ነው:: እድሜ ልኩን ዶን መርሞርዲኖን ሲያገለግል የኖረው በጉልበቱ ብቻ ነው:: ታማኝ ጠባቂያቸው ያደረጉት ደደብ በመሆኑና ባለመማሩ መሆኑን በአለቀ ሰዓት ደርሶበታል:: «እርስዎን ለመግደል ሲዘጋጅ ደርሰንበታል» በማለት ሌሎች ጠባቂዎች ስላሴሩበት ጨለማ ክፍል ውስጥ ሲደበደብ ሰንብቶ የወጣው በቅርቡ ነው:: ከዚህ በፊትም ብዙ ጊዜ በዚህ ጨለማ ቤት ውስጥ ተደብድቧል:: በንዴት ዓይኑ የቀላበት ምክንያት የሌሎች ጠባቂዎቻቸውን ሠንጀላ እንደ እውነት ተቀብለው የዱላ ውርጅብኝ ባስወረዱበት ዶን ሞርሞርዲኖ የጭካኔ በትር ምክንያት ነው::

«ምናጠፋሁ ታዲያ ጌታ ሞርሞርዲኖ?» አለ ዲዎላ::

«ምናጠፋሁ ይለኛል ደግሞ ይህ ብስብስ ባሪያ! በለው! አሉ::» አንዱን እንቆ የመጣውን ጋርድ::

«እኮ ምን አጠፋሁ?»

«እንዴት ክንፏን ትቆርጥባታለህ?»

«ስላስቸገራት እኮ ነው ጌታ ሞርሞርዲኖ::» አለ ዲዎላ::

«ይህች እርግብ በዚህ ግቢ ውስጥ ስትኖር አንድም ቀን ስትበር አይቻት አላውቅም:: እዚሁ ትውላለች:: ምግቧን እንሰጣታለን:: እዚሁ ታድራለች:: ታዲያ..... እርግቧ ክንፏን ካልበረረችበት ከትርፍ ገላ በምን ይሻላል?» ሞርሞርዲኖ ከጆሮ ግንዳቸው አካባቢ ለብቻው በቅሎ የተንጠለጠለ ትርፍ ገላ ስላላቸው እሱን በአሽሙር ሲነካቸው ጭምር ነበር::

«እርግቧ ክንፏን ካልተጠቀመችበት ቆርጠን ለእባብ ብንቆጥለው አይሻልም? ሁል ጊዜ በሆዱ እየተሳበ ከሚማቅቅ?» ስለ እባብ በልጅነቱ የሰማውን አፈ ታሪክ ጨለፈላቸው:: «እየውልዎት ጌታ ሞርሞርዲኖ እባብ እንደ ጊደር አራት እግር ነበረው አሉ:: ታዲያ ለአዳምና ለሔዋን በለስን አሳያቸው:: አዳምና ሔዋን እውቀት የሚገልፀውን ዛፍ በሉ:: እነሱ በበሉ እባብ ተረገመ:: ያውም እኮ እውቀት የሚገልፀውን ዛፍ በማሳየቱ ነው:: በእርግማኑ ምክንያትም አራት እግሮቹ ሆዱ ውስጥ ገብተው በደረቱ መሳብ ጀመረ:: የሮም ጳጳሳት እንደሚሰብኩት የአዳምንና የሔዋንን እርግማን ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ሲሽርላቸው ለእባብ ግን እስከ አሁን የተሰቀለለት ክርስቶስ የለም:: የነሱ እርግማን ሲሻር እባብ ግን እስከ አሁን አራት እግሮቹን አጥቶ በደረቱ እየተሳበ ይገኛል:: ጌታ ሞርሞርዲኖ! እርስዎ ፍትሐዊ ነዎት:: አይደለም እንዴ ጌታ መርሞርዲኖ?»

«ነኝ» አሉት:: አውቆ ሲጃጃል እየገረማቸው ሁሌም ያዳምጡታል:: ይህን ብቃቱን ባይነግሩትም እጅግ ያደንቁለታል::

«እኮ! እኔም እርሱን አውቃለሁ:: እርግጠኛ ነኝ እርስዎ ክርስቶስን ቢሆኑ ለእባቡም ይሰቀሉለት ነበር:: ቢያንስ አራት እግሩን ይመልሱለት ነበር:: እስኪ ይታየዎት ጌታ ሞርሞርዲኖ! እንዴት ፈጥሮ በደረቱ እያስጓዘ ያሰቃየዋል?! እሺ ከቀጣም መቅጣት ያለበት የመጀመሪያውን ተንኮለኛ እባብ መሆን በተገባ:: በለሱ ድረስ ወስዶ እንዲበሉ የጋበዛቸውን እባብ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ቢቀጣው ባልከፋ:: እኔም ያለጥፋቴ እየተቀጣሁ ነውና:: ግን አንድ እባብ በበደለ እንዴት የእባብ ዘር በሙሉ ባልሰራው በደል ይቀጣል እንዴት ምድረ እባብ እስከዛሬ መከራውን ያያል?»

«መናገር የፈለከውን ቅልብጭ አድርገህ ተናገር አንት መሸጦ ባሪያ:: ይልቅስ መዛላበድ የዘርህ ነው:: ምን ዙሪያ ጥምጥም



ያስኬድሃል?» አሉት ሞርሞርዲኖ:: አውቀው መነካካታቸው ነው ብዙ እንዲለፈልፍ::

«ይህ እኮ ነው ችግሩ ጌታ ሞርሞርዲኖ! አያት በበደለ ልጅን መቅጣት:: አዎ! አባቴ ዙሪያ ጥምጥም ይጓዝ ነበር:: የሱም አባት ዙሪያ ጥምጥም ሊጓዝ ይችል ይሆናል:: እኔን ግን በእነሱ ዙሪያ ጠምጥመው አይስደቡኝ:: እኔ የርስዎ ቅን አገልጋይ ነኝ:: ነገሬም ቅልብጭ ያለ ነው:: የተናገርኩትም ስለ ፍትሐዊነት ነው:: እርግቧ ክንፏን ካልበረረችበት ተቆርጦ በደረቱ አፈር ድሜ ለሚግጠው እባብ ይሰጠው:: ምናባቷ! ወይም ከጳጳሳት አንዱ ስለእባቦች ኃጢአት ይሰቀልና እባቦች እግሮቻቸው ይመለሱላቸው:: አበቃሁ::»

«አጨብጭቡለት!»አሉ ሞርሞርዲኖ ጳጳሳቱን ስለለከፈላቸው ተደስተው:: ዲዎላ ምን መናገር እንዳለበት ያውቃል::

ዲዎላ የኒህ ሰው ሁነኛ ጠባቂ ነው:: ሐብታቸውን ለመቀራመት ሲሳፈጡ እርሱ ግን ይህ ፍላጐት እስከ አሁን በግልፅ አልተንፀባረቀበትም:: ከሁለት ዓመታት ጀምሮ የሚወስደው ሥልጠና ውስብስብ ሆኖበታል:: ከወሰዳቸው ስልጠናዎች አንዱ የምንኩስና ስልጠና ሲሆን የሚሄድበትን ግዳጅ ለመወጣት የምንኩስናውን ሥልጠና በደንብ ተከታትሏል:: ከግዳጅ በኋላ ስለሚያገኘው ከአገልጋይነት ወደ ጌትነት ስለሚያደርሰው ታላቅ ምስጢርም እያሰላሰለ ነው:: ሁሉን ነገር የግሉ የሚያደርግበትን መንገድም እየቀየሰ ነው:: ይህን ለማሳካትም ብዙ እውቀት ባይኖረውም ድብቅ ብልጠትና ጉልበት አለው:: አጋር ባይኖረውም ብቻውን በምድርና በሰማይ መካከል የቆመ ጠንካራ ምሰሶ አድርጎ ራሱን ይቆጥራል:: ሙሉ ቢጫ የምንኩስና ልብስ ተሰፍቶለታል:: የመነኩሴ ቆብም ተዘጋጅቶለታል:: በዶን ሞርሞርዲኖ የግል አውሮኘላን ወደ ኢትዮጵያ ተጉዞ ባህርዳር ከተማ የሚደርስበት ቀን ተወስኗል:: ከዚያም የሚሄድበትን ከእርሱና ከሞርሞርዲኖ በቀር ማንም አያውቅም::

«እንዴት አይነት ምስጢር?» ሚራዥ ሰፍ ብሎ ጠየቀው::

«መፅሐፉን አንብበኸዋል?»

«አዎን አንብቤዋለሁ::»

«አሁን ያልኩህን ግጥምስ?»

«አንብቤዋለሁ::»

«እሺ 'የግማደ መስቀሌን ጉጥ እታገስበት አላጣም' ማለት ምን ማለት ነው?» አለ ገጣሚው ፈገግ እያለ::

«እኔም አልገባኝም» አለ ሚራዥ በመደናገር:: «እየውልህ ሰውየው በግጥሞቹ ውስጥ አንዳንድ ግራ የሚያጋቡ ስንኞችን ይከታል:: የሥነ ፅሑፍ ሰዎችም ሳይገባቸው ዝም ብለው አጫፍረው ሲተረጉሟቸው ሰምቻለሁ:: አሁን እስኪ 'የግማደ መስቀሌን ጉጥ ምንድን ነው?'» አለው እንደ ገና ወደ ሚራዥ የበለጠ ተጠግቶ:: «ጉጥ ያለው ግማደ መስቀል! ... ጉጥ ያለው ግማደ መስቀል አይተህ ታውቃለህ?»

«ግን እኮ ግጥሙ ስለ አቡነ ጴጥሮስ ነው:: ምናልባት እርሳቸው ...»

«ታዲያ አቡነ ጴጥሮስ ጉጥ ያለው መስቀል መታገሻ ጥግ አያጡም ማለት ምን ማለት ነው? በል ለማንኛውም መሸቶብኛል በጊዜ ልሂድ» ብሎ ገጣሚው ብድግ አለ::

«አንተ የፃፍከውን ግጥም ሳታነብልኝ?» አለው ሚራዥ:: «ስለዚህ ጉዳይስ የምታውቀው ነገር አለ ...ማለቴ ስለ ሎሬቱ ግጥም..... ስለ ሰቆቃወ ጴጥሮስ.....» አብሮት ለመነሳት እየዳዳው::

«መንገደኛ ነኝ:: አንተም መንገደኛ ትመስለኛለህ:: ከተገናኘን ሌላ ጊዜ የእኔን ግጥም አነብልሃለሁ» ብሎት ከቁመቱ የማይተናነስ ጃኬቱን ዚፕ እየዘጋ ሄደ:: ሚራዥ ገጣሚውን በዓይኑ እየሸኘው አፉን ከፍቶ ቀረ::

ከምሽቱ አምስት ሰዓት ተኩል ሲሆን የቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ፀጥ ረጭ አለ:: ከባድ ጨለማ መካነ መቃብሩ ላይ ወድቋል:: ቀን ሲተራመስ የነበረው ህዝብ አሽልቧል::

ኢትዮጵያ ባንዲራዋን አውርዳ ሰንደቋ ላይ አንቀላፍታለች:: ዝንቡም ሰውም ተኝቷል: ወፎችም መብረር አቁመዋል:: ከብቶች በበረት አህዮች በጋጣ ታጉረዋል:: ተራሮች ዝም ብለዋል:: ወንዞች ግን ይፈሳሉ:: የጅቦች ተራ ነው:: ጅቦች በየተራራው በየሸለቆው ይደነፋሉ:: ህዝቦቿም ጥቁር አልማዛቸው ላይ ተኝተው ያልጠረቃ ሆዳቸውን እያከኩ ነው:: «ኢትዮጵያውያን በመብራት የተፈጠሩ ይመስል ፀሐይ ስትጠልቅ አይናቸውም ጭራሮውን ይዘጋል» ብሎ ፈገግ አለ:: ኢትዮጵያ ውስጥ ጀምበር ሲያዘቀዝቅ በይፋ ሰንደቅ አላማ ከተሰቀለበት ወርዶ እንቅልፍ ይለጠጣል:: እንዲያውም የከተማ ሮንዶች ቱልቱላ እየነፉ ሰአት እላፊ መንገድ ላይ የሚያገኙትን ሰው ሁሉ ይደበድባሉ ሲባል የሰማው ትዝ ብሎት



ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ቀን ቀን እንጂ ሌሊት እንደሌለች ተረዳ::

ድቅድቁን ጨለማ በእጅ ባትሪው ብርሃን እያባረረ እንደ ኒውዮርክ ህንፃ የተደረደሩት የመቃብር ሐውልቶች ላይ የተፃፉትን ስሞች እያነበበ ሲዟዟር ሌሊቱን አጋመሰ:: የመቃብራቱን ሐውልቶችና ጌጣጦች ሲያይ 'ኢትዮጵያውያን ከህይወት ይልቅ ለሞት ክብር አላቸው:: ህይወትን ቅጠል ጉዝጉዘው ሲቀበሏት ሞትን ግን መቃብር አስጊጠው ይጠብቁታል:: ከመኖሪያ ቤቶቻቸው ይልቅ የመቃብር ሐውልቶቻቸው ይልቃሉ:: መኖሪያ ቤቶቻቸው ደሳሳ ጐጆዎች ሲሆኑ የመቃብር ሐውልቶቻቸው ግን በውድ ጠብችና ሸክላዎች ያጌጡ ናቸው:: በህይወት ዘመናቸው አበባ ቀጥፎ የሰጣቸው ባይኖርም መቃብራቸው ላይ ግን የማይደርቁ አበቦች የፕላስቲክ አበቦች ለደረቁ በድኖቻቸው ይቀመጣሉ:: ይህ እብደት ነው:: ምናለ በህይወት ዘመናቸው እንደዚህ ቢያምርባቸው' እያለ ብቻውን እያጉረመረመ የመቃብር ሐውልቶችን ስም ሲያነብ ቆይቶ ከአንድ ሐውልት አልባ ልጥፍ መቃብር ላይ ሲደርስ ቆመ:: የሚፈልገው መቃብር እንደ ሌሎቹ መቃብሮች ባለ ግርማ ሞገስ ይሆናል ብሎ ነበር:: ከራስጌው ከሚታየው ጥቁር የብረት መስቀል በቀር መቃብር የሚያስመስለው ነገር የለም:: መሬት ከተነጠፈው ስሚንቶ ላይ «አባ ሲርጋጋ ከ1886 —1996» የሚል ጽሁፍ ተቀርፆበታል:: ፈራ ተባ እያለ ከጀርባው ያዘለውን ረጅም ሻንጣ አውርዶ ከውስጡ ዶማና አካፋ አወጣና መቆፈር ሲጀምር ዝናቡም መዝነብ ጀመረ:: በአፉ የእጅ ባትሪውን ነክሶ መቃብሩን በስሚንቶው ዙሪያ ቆፍሮ ከጨረሰ በኋላ ጠፍጣፋውን ድንጋይ ሲያነሳው ከባዶ ገደል መቃብር ጋር ተፋጠጠ:: መቃብሩ ውስጥ ምንም አስከሬን የለም::

«ምን አይነት ጉድ ነው?» አለ በብሽቀት መቆፈሪያውን ወርውሮ:: «እንዴት ባዶ ምድር ያስቆፍሩኛል? ማነው ግን እንዲህ የሚጫወትብኝ? ቆይ ከእኔ ስቃይ የሚያገኙት ደስታ ምንድን ነው?» ጥቂት ከተነጫነጨ በኋላ የቆፈረውን ባዶ መቃብር አፈር በአካፋው ሲዝቅ አንድ አነስተኛ ክብ ቀይ ድንጋይ በአካፋው ከተዛቀው አፈር ጋር ወጣ:: ቀዩን ክብ ድንጋይ አንስቶ እያገላበጠ ሲያየው ከቆየ በኋላ በልብሱ አፈሩን ሙልጭ አድርጎ ሲጠርገው ላዩ ላይ የተቀረፀ ፅሑፍ አነበበ:: «ዴርቶጋዳ» ኳስ የሚመስለውን ቀይ ድንጋይ በባትሪ እያገላበጠ ካየው በኋላ ያገኘውን ጉጥ ነገር ሲጫነው ድንጋዩ ለሁለት ተገመሰ:: ውስጡ ክፍት ነው:: ድንጋይ አልነበረም:: ከብረት የተሠራ ውስጠ ክፍት አሎሎ ነገር ነበር ለካ:: በነተበ ብራና የተፃፈ አጭር ፅሁፍ ከውስጡ አገኘ::

*«ሊያተርፍህ ሲፈልግ ሀልም ያሳይሃል»* ይላል ፅሁፉ:: ደጋግሞ አነበበው «ሊያተርፍህ ሲፈልግ ሀልም ያሳይሃል:: ....... ሊያተርፍህ ሲፈል ....... ሊያተርፍህ...... »

«እሺ ይህን ለማስተማር ነው ይህን ሁሉ ፍዳ የሚያሳዩኝ? ይህ ታዲያ ምን ምስጢር አለው?» ብሎ በምሬት ቁራጩን ብራና ሲወረውረው በዝናቡ ውሽንፍር ተንሳፎ በጀርባው ተገለበጠና መሬት ላይ አረፈ:: በጀርበው የሆነ ነገር አየ:: ወደ ወደቀበት ጉንበስ ብሎ በጥቃቅን የተፃፈውን ነገር አነበበው:: «ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ከሳላት የቅድስት ማርያም ስዕል ጀርባ ቀጣዩ መልእክት ተቀምጦልሃል» ይላል:: ትንፋሹን ሰብስቦ በረጅሙ ተነፈሰ:: «ወንጌላዊው ሉቃስ የሳላት የማርያም ስዕል የት ናት...?» ራሱን ጠየቀ:: ያለችበትን ቦታ ለማስታወስ በትዝታ ወደኋላ ሸመጠጠ::

ያገኘውን መልዕክት እያምሰለሰለ ቀዩን ድንጋይ ወደ ሻንጣው አስገብቶ የቆፈረውን አፈር ወደ መቃብሩ መለሰው:: መቃብሩን ሊዘጋ ጠፍጣፋውን ሀውልት ወደነበረበት ሲጉትት ኮሽታ ሰምቶ ወደ ኋላው ዞረ:: እርፍ የማያክል ዱላ የያዘ ሰው «ማነህ?» አለ ዱላውን ሊያሳርፍበት እንደተንጠራራ:: «አንተ ሰው በላ! እለቅህ መስሎሃል:: አስከሬኑን በላኸው! አስከሬኑን ሳላስተፋህ አለቅህም::» ዱላውን ሲጥልበት ወደ ጉን ተስፈንጥሮ አመለጠ:: ዱላው መሬት ላይ አረፈ::

«ይኸው! እየው ጥሩንባዬን!» በአንገቱ ያንገተውን ጡሩንባ አሳየው:: «ይህን ጥሩንባ ነፍቼ ሀገር ይሰበስባል:: ከዚህ መቃብር ፈንቅለህ አስከሬን በመብላትህ ይፈርድብሃል:: በላኸው! የአባ ሲርጋጋን አስከሬን በላኸው! እነፋለሁ! እነፋለሁ! ይህን ጉድ አገር ይስማ!»

«አልበላሁም!» አለ ሚራዥ:: «አባ ሲርጋጋ መቃብሩ ውስጥ የሉም:: እኔ አስከሬን...»

አቋረጡት «ዝም በል! በቀር በላሁ ልትል ነው? ይልቅስ ማንነትህን ንገረኝ:: ይህን ጥሩንባ ነፍቼ አገር ጉድ ሳይል?»

«ልጃቸው ነኝ::» አለ ሚራዥ ሌላ ውሸት እንደሌለው ሲረዳ:: «የአባቴ መቃብር ላይ ሀውልት መሥራት አልችልም? አባቴን! እንዴት የአባቴን መቃብር? ለመሆኑ አንተ ማን ነህ? ማነህ ከአባቴ መቃብር መጥተህ የምትደበድበኝ? ንፋ! እንዲያውም ጥሩንባውን ንፋ! ከሥራህ ነገ ጠዋት ትባረራለህ!» የሚራዥ አእምሮ በፍጥነት አሰበለት::

«አንተ የአባ ሲርጋጋ ልጅ ነህ?» በምፀት ሳቀ ሰውየው:: «አዎ! እንዲያውም ከፈለግህ ሻንጣዬ ውስጥ ከአባቴ ጋር የተነሳሁትን ፎቶ ላሳይህ እችላለሁ» ወደ ሻንጣው ተራምዶ ሻንጣውን ሙሉ በሙሉ በእጁ መያዙን ሲያረጋግጥ እግሬ አውጭኝ በጨለማው ውስጥ ሻንጣውን ነጥቆ ተፈተለከ:: ብዙ ርቀት ከሮጠ በኋላ ወደ ኋላ ዞሮ ሲያይ የተከተለው ማንም አልነበረም::



# ፲፩

ከአሉሚኒየም ብረት ወደ ተሠራችው የሞተር ጀልባ ሲገባ ጣና ሆቴል ውስጥ ጥሎት የመጣው እንቅልፉ ተከትሎ እያዳፋው ነበር:: ጉርብጥብጥ ጉዝጉዞ የተኛ ይመስል ከምቹው የጣና ሆቴል አልጋ ላይ ሲገላበጥ ነበር ያደረ:: ሀሳብ ሲያገላብጠው::

ወንጌላዊው ሉቃስ ስሏታል የምትባለውን ቅድስት ማርያም ስዕል የት እንደሚያገኛት ቢያውቅም ከጀርባዋ ያለውን መልእክት እንዴት አድርጎ መውሰድ እንደሚችል ግራ ገብቶታል:: ቢሆንም ወደዚያው እየሄደ ነው:: በልጅነቱ ሲያስጉበኛት ነበር:: አሁን ግን ሊጎበኛት እየሄደ ነው:: ወደነበረበት እየተመለሰ:: በልጅነቱ ወዳደገበት ገዳም:: ወደ ወንዶች ገዳም:: ወደ ክብራን::

ወጣቱ የጀልባዋ ካፒቴን አስጉብኚ ሊፈልግለት ቢሞክርም ዶ/ር ሚራዥ ግን አስጉብኚ እንደማይፈልግ ነግሮት ሁለቱ ብቻ ናቸው በትንሽዋ ጀልባ የጣናን ሐይቅ ሊሰነጥቁት በጠዋቱ ዘመናዊዋ ጀልባ ውስጥ የተቀመጡት:: በምሥራቁ የጣና ሰማይ ጥግ ጀምበር እግሯን ስትሰድ ወጣቱ ካፒቴን ሞተሯን ገመዱን ስቦ ሲያስነሳው ጀልባዋ እያጓራች ጣናን መሰንጠቅ ጀመረች:: ይህ ሲሆን ብጣና ሐይቅ ላይ በባህር ዳር ባህር ትራንዚት ወደብ የቆሙ አሮጌ የአሸዋና የህዝብ ጀልባዎች ሞተራቸውን እያሞቁ ነበር:: ሚራዥ አሮጌዎቹ መርከቦች ላይ ዓይኑን ተክሎት ቀረ:: ያው ናቸው፤ ከስንት ዘመን በኋላም አልተለወጡም::

ከባህር ዳር ተነስታ ጐርጐራ ለመድረስ ሁለት ቀን የጣናን ሐይቅ ስትዋኝ የምትሰነብተው የጣናነሽ ጀልባ ሞተሯን እያሞቀች ተመለከታት:: መንፈሱ በትዝታ ቢዋጥም በነገሮች አለመለዋወጥ ውስጥ የታሪክ ዝግመትን ተመለከተ::

የጣናነሽ ጀልባ በጣና ሐይቅ ላይ ከሚጓጓዙት ጀልባዎች ሁሉ በመጠኗ ሰፊና ትልቅ ስትሆን ባለሁለት ሞተርም ናት:: ይህች ጀልባ በስድስት መቶ ሊትር ነዳጅ አንድ ሺህ ኩንታል ጭና መጓዝ ትችላለች:: ከባህር ዳር ተነስታ ዘጌ፣ ጉረር፣ ቁንዝባ፣ አስፋደብር፣ ዳልጊ ደርሳ ጐርጐራ ትገባለች:: ከዚያም በሄደችበት ዝክንትሏን ሰብስባ ትመለሳለች::

ፋሲለደስና ድል በትግል የሚባሉት ጀልባዎችም ቆመው ታዩት:: ከሀንጋሪ ተገዝታ የመጣችው ዳህላክ የምትባለው ጀልባና ከሆላንድ የተገዛችው የካቲት የምትሰኘዋ ጀልባ በፀጥታ ቆመዋል:: የኢጣልያ ጦር ከኢትዮጵያ ሲባረር በአንጋሬ ደሴት አስጥሟቸው በኋላ ቡስኪ በተባለ ጣሊያናዊ ከሐይቁ የወጡት አፈር የፈጃቸውና የወየቡ የአሸዋ ጀልባዎችም ሊንቀሳቀሱ ሞተራቸውን እንደ ሰሀል ወፍጮ እያንገራገጩ ነበር::

ሚራዥ ዓይኑን መርከቦቹ ላይ ነቅሎ ሐይቁ ላይ ወረወረው:: የጣና ሐይቅ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት ሐይቆች መካከል በትልቅነት የሚስተካከለው የለም:: ሶስት ሺህ ስድስት መቶ ስኩዌር ኪሎ ሜትር አጠቃላይ ስፋት ሲኖረው አቀማመጡም ከሰሜን እስከ ደቡብ ሰባ አምስት ኪሎ ሜትር ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ደግሞ ስድሳ ኪሎ ሜትር ርዝመት አለው:: የጣና ሐይቅ ከባህር ወለል በላይ በሺ ስምንት መቶ ሰላሳ ሜትር ወይም ስድስት ሺህ ጫማ ከፍታ ላይ የተንጣለለ ምስጢራዊ ሐይቅ ነው:: ከያዘው አራት ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ የውሃ ይዘት በላይ በብዙ ምስጢሮች የታመቀ ኃይቅ ነው:: ጣና ሁሌም እርጥብ ነው:: ዳር ደንበሩን ከዘጌ እስከ ጎርጎራ ከጎርጎራ እስከ ፎገራ የሸበቡትን ዓይናማ ድንጋዮች ታከው 'ርብ'ና 'ጉማራ'ን ጨምሮ ከሰላሳ የማያንሱ የጉንደርና የጉጃም ወንዞች ይገብሩለታል:: ውሃ፣ ታሪክ፣ አፈር፣ አዕም፣ እንጨት፣ ህይወት:: ሆኖም ጣና በቃኝ አይልም:: ሲጠግብ በምሥራቃዊ ዳርቻው መተንፈሻ አለው.....ዓባይ:: ጣና በክረምቱ ማብቂያ መስከረም ሲጠባ ከሐይቁ በአባይ አበጋዝነት የሚወጣው ውሃ በሰከንድ አራት መቶ ሜትር ኪዩብ ያህል ያማክላል:: በታህሳስ በሰከንድ ወደ መቶ ሜትር ኪዩብ ያህል ያማክልና በግንቦት ደግሞ በሰከንድ አስር ሜትር ኪዩብ ደርሶ ሲቀበል ይከርማል:: ሲያምጥ ይከርማል:: መስከረም ላይ በግዮኑ መልአክ ተራዳኢነት ጭንቁን ይገላገላል:: ያንቀላፉት ኢትዮጵያኑን እስከ እንቅልፋቸው ትቶ አባይ በእንቁላል ቅርፊት ሲቀዳባቸው ለሚንገበገቡለትና ነቅተው ለሚጠብቁት ግብፃውያን ይደርስላቸዋል::

የነሚራዥ ጀልባም ደህና አረንጓዴ ሐይቅ እየቀዘፈች ከባህር ዳር ከተማ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ለአርባ አምስት ደቂቃ ያህል ከተጓዘች በኋላ ከመንታዎቹ ደሴቶች መሀል ደረሰች:: ሁለቱም ደሴቶች የሚገኙት ማራኪ በሆነ ተፈጥሯዊ የመሬት አቀማመጥ ባለውና በደን በተሸፈነ ከረብታማ ስፍራ ነው:: ከጣና ደረት ላይ ያጉጠጉጡ ልጃገረድ ጡቶች ይመስላሉ:: አሞራዎች ይጠቧቸዋል:: ማዕበሉ ይጋጫቸዋል:: የመናንያኑ ፀሎትና የወፎች ዝማሬ ያለመልማቸው ይመስል በጋ ከክረምት ደረቅ ነገር በነዚህ ደሴቶች ላይ አይታይም::

ጀልባዋ ከወንዶች ገዳም ወደብ ሥር መልህቋን ስትጥል ዶ/ር ሚራዥ ወደ ሴቶች ገዳም ዞሮ አይኖቹን እንጦንስ ደሴት ላይ ወርውሯቸው ነበር:: ሲጸራና ትዝታዋ ከቀዝቃዛው የጣና ሐይቅ አየር ጋር ዘልቀው ሰረሰሩት:: ሲጸራና እሱ ፍቅርን የተቋደሱባቸው መንታ ደሴቶች መንታ ሕይወት ውስጥ ሲከቱት ተሰማው:: ትዝታ ጥፍሩን አሹሎ ቁስሉን ያከከ መሰሎ አቆሰለበት:: መንፈሱና አካሉ ሁሉ ሲጸራን ተጣራ:: «ምን አዙሪት መልሶ አመጣኝ?» ብሎ ራሱን ቅጭም እንዳደረገ ካኘቴኑን ጀልባዋ ላይ ትቶት ብቻውን ወደኮረብታው ወጣ::



ከብራን ገብርኤል ደሴት ላይ ሲወጣ እንጦንስን አሻግሮ የሚያይበት የእሸ ዛፍ እስከ ግርማ ሞገሱ ተገትሯል:: ይቀድስበት የነበረው ቤተ መቅደስ መጋረጃዎች እንኳ ያው ናቸው:: የእጣኑና የማዕጠንቱ መአዛም አልተለወጠም:: የሚያስጉበኙት መነኩሲ የተናገሩትን ታሪክ አንዱንም አልሰማቸውም:: ያሳደገው ታሪክ ነው:: አእምሮው እየተራወጠ ሁሉን ነገር ሲደቅንበት አይኖቹ በእንባ ተሞሉ:: ድምፅ አውጥቶ ማልቀስ ነበር የቀረው:: ለምን እንደሆነ ግን ሊገባው አልቻለም:: ዘመናዊው አለም ውስጡ እየሟሟ ሲያልቅ እየተሰማው ነው:: ሐኪምነቱም ሲተን:: ራሱን ማዳን ራሱን ከትዝታው መፈወስ ተሳነው::

ቀልቡን ወደ መጣበት ጉዳይ ለመሰብሰብ ተሳነው:: የሚያስጉበኙት መነኩሴ «ይህች ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ የሳላት የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ስዕል ናት::» ሲሉት ብቻ ነቃ::

«ይቅርታ አባቴ ስዕሏን ለመሳለም እፈልጋለሁ» ብሎ ወደ ስዕሏ ሲቀርብ ፈገግ አሉ መነኩሲው::

«ብፅአት አለብኝ:: እመቤቴ በሰላም ወደ ሀገሬ ከመለሰችኝ ወንጌላዊው ሉቃስ በሳላት ስዕሏ ስር ፀሎተ ማርያም ለማድረስ ስዕለት አለብኝ:: ፈቃድዎ ቢሆን አባቴ::» መነኩሴው ጢማቸውን በግራ እጃቸው ጉተት ጎተት እያደረጉ ለጥቂት ጊዜ ካዩት በኋላ በቀኝ እጃቸው በያዙት የእጅ መስቀላቸው ወደ ስዕሏ እንዲጠጋ ጋበዙት::

ተንበርክኮ ፀሎተ ማርያም እያደረሰ በቀኝ እጁ ከስዕሏ ጀርባ ይዳብስ ጀመር:: ፀሎቱን ሲያደርስ ከልቡ አልነበረም ህሊናው ከስዕሏ ጀርባ ስለተቀመጠለት መልዕክት መገኘት አለመገኘትና ምንነት እያወጣ እያወረደ ነው:: መነኩሴው የማያዩ መስለው እየተከታተሉት ነው::

ከስዕሏም ጀርባ ሲዳብስ ቢቆይም ሊያገኝ የቻለው አንዳች ነገር አልነበረም:: ሀሞቱ ፈሰሰ:: ያስቀመጡለት መልዕክት የለም:: ካጣው ደግሞ ሁሉንም ነገር ትቶ ህይወቱን ወደሰጠለት ተልዕኮ የመድረሻው መንገድ ጨለማ ዋጠው ማለት ነው:: አንዱን መልእክት ሳይዝ ወደ ሚቀጥለው መጓዝ አይችልም:: የሚቀጥለውን መንገድ ለመርገጥ ይህኛውን መመሪያ መጨበጥ አለበት:: ግን አጣው:: ፀሎቱን አቋርጦ ተነሳ:: ወደኋላ ሊመለስ? 'ባቅማማህ ቁጥር መንገድክን ትስታለህ' ሲል ኢንጂነር ሻጊዝ የነገረው ታወሰው:: ለይስሙላ በቻ መነኩሴው እንዳይታዘቡት ስዕሏን ስሞ ደንዝዞ ቆመ:: እየተርበተበተ::

«ምንድን ነው እያደረክ ያለኸው?» አሉት መነኩሴው በቁጣ:: «ውጣ ከዚህ አሁን!» የእቃ ቤቱን በር ይዘው ወደ ውጭ እንዲወጣ በዓይናቸው ገፉት:: ድንጋጤ ወረረው::

«አባ .... ማለት ...እዚህ ...»

«አዎን አባቴ::» አላቸው ሚራዥ:: የሚነፍሰው ቀዝቃዛ አየር የጋለ ሰውነቱን ሰከን አድርጎታል:: ከረዣዥም ብሉይ ዛፎች ላይ እየተነሱ ወደ ጣና ሐይቅ እየተጯጯሁ ከሚምዘገዘጉ ባለረጃጅም ክንፍ አሞራዎች ድምፅና ከማዕበሉ ሞገድ በስተቀር የሚሰማ አንዳች ነገር የለም::

ዕድሜ የጠገቡትንና ረጃጅሞቹን የቤተ ክርስቲያኑን የእንጨት ሳንቃዎች እየከፈቱ በቤተ መቅደሱ ግድግዳ ላይ የተሳሉትን ጥንታዊ ስዕሎች ካስጐበኙት በኋላ አራት ማዕዘን ቅርፅ ካለው ቤተክርስቲያን ተመልሰው በገቡበት በሮቹን እየዘጉ ወጡ::

መነኩሴው እንደተቀደደ ከበሮ በሚነፋነፍ ዝቅተኛ ድምፃቸው ስለገዳሙ እየተረኩለት ወደ እቃ ቤቱ ይዘውት ሄዱ:: «ይህን ቅዱስ ቦታ በመርገጥህ እግዚአብሔርን ልታመሰግነው ይገባል:: የእግዚአብሔር የክብሩ ዙፋን የሆነችው ታቦተ ፅዮን ያረፈችበት ቅዱስ ቦታ ነው:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲወለድ ሕፃኑን ለመግደል ሄሮድስ ሲፈልገው እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ግብፅ ይዛው ከተሰደደች በኋላ ከግብፅም ወደ ኢትዮጵያ ጉዞዋን ቀጥላ እዚህ ቅዱስ ቦታ መጥታ ስለመቆየቷ ድርሳነ ኡራኤል የተባለው ጥንታዊ መጽሐፍ ላይ በሰፊው ተጽፎ ይገኛል:: በዚህ ገዳም ውስጥ ብቻ በሚገኘው ድርሳነ ማርያም በተባለ መጽሐፍ ውስጥ የጌታ ስደትና የእመቤታችን ቆይታ ሙሉ ታሪክ ተጽፎ ይገኛል:: ቅድስት ድንግል ማርያም የጌታችን እናት በዚህ ቦታ ሦስት ወር ከአስር ቀን ቆይታለች::»

መነኩሴው እቃ ቤቱን እየከፈቱም ትረካቸውን አላቋረጡም:: «እመቤታችን በዚህ ገዳም ሳለች ይመራት የነበረው መልአክ ለዮሴፍ በህልም ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ሂድ ሲለው ዮሴፍ ወደሕጻኑ ቀርቦ «ፀእና በደመና - በደመና ጫናት» ብሎ ተማፅኖ በማቅረቡ ከዛ ወዲህ የገዳሙ ስም «ጣና ቂርቆስ» የሐይቁ ስም ደግሞ «ጣና» ተብሎ ቀረ:: ለዚህም የጽሑፍም የቁስም ማስረጃዎችን ማየት ትችላለህ::» ብለው ጥንታዊውን እቃ ቤት ከፍተው ወደውስጥ ጋበዙት:: መነኩሴው በጥንቃቄ እየተመለከቱት ነው:: ከእግር እስከራሱ እየመረመሩት::

በእቃ ቤቱ ውስጥ የመጀመሪያው ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ፣ መጽሐፈ ሔኖክ፣ መፅሐፈ ሐዊ፣ የቅዱስ ያሬድ የእጅ መስቀል፣ ካባው፣ በራሱ እጅ የጻፈው ምልክት አልባው የድጓ መፅሐፍ፣ የወርቅና የብር እቃዎች፣ አንድ ሺህ አመት የሞላቸው ጥንታዊ ስዕሎች፣ እና ሌሎችን ለዓይን የሚታክቱ ቅርሶችን አስጎበኙት:: በዚህ ዕቃ ቤት ውስጥ ያሉት ቅርሶች ከመጨናነቃቸው የተነሳ ከአይጥ ለመከላከል ሲሉ ከጣሪያው ማገር ጋር መጻህፍቶችን በገመድ በአየር ላይ አንጠልጥለው ያሰሩትን ሲያይ ተገረመ:: አይጦቹ በማገሩ ላይ በመሔድ ገመዱን እየበጠሱ ቅርሶቹን እንደሚያወድሙባቸው ሲነግሩት እያዘነ ወጣ::

መነኩሴው ግራና ቀኙ በእሾህማ ቁጥቋጦዎች በተሞላ ቀጭን የእግር መንገድ እየመሩ ወሰዱት:: በጠባቡ መወጣጫ ደረጃ



ወጥተው በደሴቱ ላይ በሚገኝ ሜዳማ ቦታ አደረሱት:: በዚህም ታቦተ ጽዮንን ወደ ደሴቱ ይዘዋት የመጡት ካህናት የደም መስዋዕት ይሰዉበት የነበረውን መሰዊያ አሳዩት:: በኦሪት ዘሌዋውያን ውስጥ ካነበበው ጋር የሚገጥም ነገር በማየቱ ከሶስት መቶ አመታት በላይ ታቦተ ጽዮን በዚህ እንደነበረች የሚያውቀውን ለማመን ተገደደ:: ቢሆንም የመጣበት ዓላማ ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ ሳይሆን የቀጣይ ጉዞውን ጠቋሚ መልእክት ለማግኘት መሆኑን አረሳም::

የተቀመጠለትን መልእክት በመሰዊያው ስር እየተሿሿረ ሲፈልግ መነኩሴው ትተውት ወደ ጫካው ገቡ:: ለብዙ ጎብኚዎች ግልጽ ሆነው የማይነገሩትን ድብቅ የሆኑ ነገሮች እንዳሉ በልጅነቱ የሰማው ትዝ ብሎታል:: ለእርሱ ብቻ ይህ ነገር መደረጉ አንድ ነገር ከጀርባው እንዳለውም ገብቶታል:: በመሰዊያው ስር ያገኘውን አራት ማዕዘን ድንጋይ አንስቶ እያገላበጠ ካየው በኋላ እፍ እፍ ብሎ አፈሩን ሲያስለቅቀው በላዩ ላይ የተቀረጹ ጽሑፎች ብቅ ብቅ አሉ:: ድንጋዩ ከመሰዊያው ድንጋይ ለየት ያለና ቀይ ሲሆን ለእርሱ የተቀመጠለት መልእክትም ይህ ለመሆኑ አልተጠራጠረም:: በድንጋዩ ላይ ከተቀረጹት ፅሑፎች ጋር ስሙን ስላገኘው ለእርሱ የተቀመጠ ድንጋይ ለመሆኑ እርግጠኛ ሆነ:: በድንጋዩ ላይ ከተቀረጹት ፅሑፎች አንደኛው «ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ» ይላል::

ጊታሩንና የጉዞ እቃዎቹን የያዘበትን ረጅም ሻንጣ ከጀርባው አውርዶ መፅሐፍ ቅዱስ ካወጣ በኋላ የኢሳያስን የትንቢት መጽሐፍ አውጥቶ ምእራፍ ስምንት ቁጥር አንድ ላይ ያለውን ጽሑፍ አነበበው:: «እግዚአብሔርም:- ታላቅ ሰሌዳ ወስደህ፣ ምርኮ ፈጠነ፣ ብዝበዛ ቸኮለ፣ ብለህ በሰው ፊደል ጻፍበት:: የታመኑትን ሰዎች ካህኑን ኦርዮንና የበራክዩን ልጅ ዘካርያስን ምስክሮች አድርግልኝ አለኝ» ይላል የኢሳያስ መፅሐፍ::

ኢንጂነር ሻጊዝ የነገረው ትርጉምም ትክክል እንደነበር አረጋገጠ:: እንደ ኢሳያስ «ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ» የሚለው ቃል ትርጉም «ምርኮ ፈጠነ፣ ብዝበዛ ቸኮለ» ማለት መሆኑን ቢያገናዝብም ይህ ቃል ለምን ለእሱ በመልእክትነት እንደተቀመጠለት ስላልገባው በተለያየ አቅጣጫ መተርጎም ጀመረ::

የተጠራበት ጉዳይ ሀገራዊ በመሆኑም ቃሉን ከሀገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታ ጋር አገናዘበው:: «እዎ» አለ ሚራዥ ቀዩን ድንጋይ እንደያዘ:: «ምርኮ ፈጥኖአል:: ብዝበዛም ቸኩሎአል:: ሀገሪቱ በቅጥረኞችና በአድርባዮች እየተበዘበዘች ነው:: ሕዝቦቿ የበላይ ተመልካች ሆነዋል:: ተስፋ በቆረጠ ትውልድ ተሞልታለች:: ወጣቶቿ እንጀራ ፍለጋ በባዕዳን ሀገር ሲሰደዱ በጋንጃቸው እየታረዱ ነው:: ሴት ልጆቿ የአረብ ገረዶች እየሆኑ ነው:: ማምለጫ ያጡትም በጥቁር አልማዛቸው ላይ ተኝተው እየለመኑ ነው:: አዎ ጥቂቶች እየበዘበዙ ነው:: ብዙዎችም እየተበዘበዙ:: ኢትዮጵያን የተሰበረ መንፈስ ወሯታል:: ምርኮ ፈጥኗል:: ብዝበዛም ቸኩሏል::»

ቆም ለጥ ያለውን የጣናን ሐይቅና አረንጓዴውን የፎገራን ምድር ሲያይ ከቆየ በኋላ «ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ» ብሎ

«በፃድቁ ተራዳኢነት እንኳን ደህና መጣችሁ::» አሉ አንደኛው መነኩሴ:: ሽማግሌው መነኩሲ ወደ ጫካው ከገቡ በኋላ:: «ምነዋ ከመሼ?» አሉ ሁለተኛው ጥቁር ጉርፌ ጢም ያላቸው መነኩሴ:: ከሪዛቸው ውስጥ ብልጭ ያለው ነጭ ፍንጭት ጥርሳቸው መልሶ ተከደነ::
«ማዕበሉ አስመሽቶብን ነው::» አለ ሚራዥ የመነኩሴውን ፊት እያነበበ::

ካፕቴኑ ወደ ሚራዥ ተጠግቶ «መሄዴ ነው::» አለ::

«በዚህ ጨለማ?» ሚራዥ ደንገጥ ብሎ::

«ነገ ወደዚህ ገዳም ለጉብኝት የሚመጡ ባሊያናውያንን እንዳመጣ ድርጅቴ አዞኛል:: በፈለከኝ ሰዓት ብትደውልልኝ መጥቼ እወስድሃለሁ::» በብጣቂ ወረቀት የተንቀሳቃሽ ስልኩን ቁጥር ፅፎ ሰጠው::

«ኧረ መሽቷል ተው?»

«ነገርኩህ እኮ ጣልያናውያኑን ይዤ በጧት ወደዚህ ገዳም እንድመጣ ታዝዣለሁ:: የሥራ ጉዳይ ነው:: ብትደውልልኝ በማንኛውም ጊዜ እመጣልሃለሁ::» ካፕቴኑ የጀልባዋን ሞተር አስነስቶ ወደ ባህር ዳር ከነፈ::

ሚራዥ በሁለቱ መነኮሳት መሪነት ደሴቱ በር ሲደርስ ወደገዳሙ መግቢያ ከተተከለ ሰሌዳ ላይ «ዳጋ ቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም» የሚል ፅሁፍ አየ:: በጉን በኩል ደግሞ ሴቶች ወደ ገዳሙ እንዳይገቡና ማንም ሰው የጦር መሳሪያ ይዞ እንዳይገባ የሚከለክለውን ፅሁፍ አነበበ::

ጥቅጥቅ ባለው ደን ውስጥ እንደ ክር በቀጠነችው መንገድ እየመሩ ሲወስዱት ሚራዥ በሚያያቸው ሀገር በቀል ዛፎች ልምላሜ ተመስጦ ነበር:: ከሀያ ሰባት በላይ በሌላ የምድራችን ገፃ ላይ ያልበቀሉ ሀገር በቀል ዛፎች በዳጋ እስጢፋኖስ ደሴት እንደሚገኙ ያነበበው ጥናታዊ ፅሁፍ ትውስ አለው:: ፀደዩን በፍካት ሊቀበሉ ከእንቡጣቸው የተሽለቀቁ አበቦች መአዛ ሲያውደው የተሽበሸበ መንፈሱ መዘረጋጋት ጀመረ:: ከገዳሙ መግቢያ ወደ ውስጥ ገባ ብሎ የገዳሙ ተግባር ቤትና የዕህል ወፍጮ ቤት ይገኛል:: የሞተር ወፍጮውን ለዚህ ገዳም ያስተከለው የቀድሞው ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለ ማርያም መሆኑን ሲነግሩት ተገረመ:: ፕሬዝዳንቱ በመጨረሻው ሰዓት አካባቢ በዚህ ገዳም ውስጥ የተወሰኑ ቀናትን እንዳሳለፈና በገዳሙ ውስጥ ያለው የአንድነት መንፈስ አስደብቶት ብዙ ድጋፍ አድርጎ እንደ ነበር ጨምረው ነገሩት::

በዚህ ገዳም ውስጥ እስከ ሶስት መቶ የሚጠጉ መነኮሳት እንደሚኖሩ ቢገመትም ከአእዋፋቱ ዝማሬና ከጣና ሐይቅ የማዕበል ድንፋታ በቀር የሚሰማ ድምፅ የለም:: የደሴቱን ጥቋቁር አለቶች ከሚጋጨው የጣና ማዕበል ጋር የሚቀላቀለው የእንቁራሪቶችና የጉርጦች ድምፅ ቀስ ብሎ በሚነፍሰው ነፋስ እየተቀመረ በጆሮው



ሲንቆረቆር እውቅ የሙዚቃ አቀናባሪ የተጠበበበት ረቂቅ ሙዚቃ መሰለው:: የተኮፋተረ ፊቱ ሲፍታታ ተሰማው:: የተጨናነቀች ነፍሱ በእፎይታ ተነፈሰች:: ከየት እንደመጣ ባላወቀው ምክንያት አልባ ደስታ ነፍሱ ተንፈራገጠች:: ምናልባት በዚህ ደሴት ውስጥ ከጉመሩት የፀደይ መግቢያ አበቦች መአዛ የተቀመመ ደስታን የሚሰጥ ቅመም እንዳለ ጠረጠረ:: እንጂማ እሱን የማያፍነከንክ ደስታ ሌላ ከወዴት ይመጣል? «ሳፊንግ ጋዝ ባፍንጫየ ገብቶ መሆን አለበት» አለ በሆዱ:: «ሳቅ ቀስቃሽ ንጥረ ነገር ሽቶኝ መሆን አለበት::»

ቀጭኗን መንገድ ተከትለው ጥቂት ከተጓዙ በኋላ ሁለቱ መነኮሳት ወደ አንድ ሌላ መነኩሴ ቀርበው እጅ ነሱ:: ጥቂት ተነጋግረው ወደ ሚራዥ ተመለሱ:: «የገዳሙ መጋቢ በገዳሙ ውስጥ እንዲያድሩ ፈቅደዋል::» አሉ ጠይሙ ጢማም መነኩሴ:: ያለገዳሙ ኃላፊዎች ፈቃድ በገዳሙ ውስጥ ማደር እንደማይቻል ያውቃል:: ሰገድ ብሎ ለመልካም ፈቃዳቸው ምስጋና አቀረበ::

የምሽቱን ፀሎት ሊያደርሱ በየበእታቸው የገቡት መነኮሳት መውጣት ጀምረዋል:: ሁሉም እየመጡ ለሚራዥ ሰላምታ ሰጡት::

ሰላምታቸው ለየት ያለ ነው:: ገና ከሩቅ ሰላም ሊሉት ሲመጡ እስከ መሬት አጐንበሰው እየተንደረደሩ ይመጡና ከእሱ ሲደርሱ እጅ በመንሳት የበለጠ ከወገባቸው ሰግደው ትከሻውን ይስሙታል::

ከርቀት እስከመሬት አንገታቸውን ደፍተው እየተንደረደሩ ሲመጡ ለውጊያ የሚሽከረከሩ አውራ በጎችን ይመስላሉ:: የበለጠ እስከመሬት የተጐነበሰ የበለጠ ትህትናና አክብሮት መግለጡን ያመለክታል:: መነኮሳቱ ይህን የሰላምታ ዘይቤ ለዘመናት ይዘውት ኑረዋል:: በየቀኑ ከፀሎት በኋላ ሲገናኙ እርስ በእርሳቸው ይህንን አድካሚ ሊባል የሚችል ሰላምታ ሳይሰለቹ ይለዋወጣሉ:: ትህትናና ፍቅረ ቢፅ ዋናው አብሮ ለመኖር ያስተሳሰራቸው ሰንሰለት ነው:: ጮኾ መናገር፣ ጓደኛን ማንጓጠጥ፣ አለመታዘዝ፣ አብዝቶ መብላት፣ ፆም መሻር የመሳሰሉት ጉዳዮች በጥብቅ የተከለከሉ ናቸው::

ዶ/ር ሚራዥ ፍፁም የሆነውን የወንድማማችነት ድባብ ሲያይ የልጅነት ዘመኑ ውል ብሎ ታየው:: ክብራን:: የዳጋ ገዳምም እንደ ገዳም ክብራን የወንዶች ገዳም በመሆኑ የተቀራረበ ባህልና ትውፊት አለው:: እንዲያውም በጣና ሐይቅ ላይ ባሉ ደሴቶች ውስጥ ያሉ ገዳማት እርስ በእርስ እንደሚቀራረቡ ያውቃል:: ክብራን፣ ዳጋና ሐይቅ እስጢፋኖስ የበለጠ ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው ገዳማት መሆናቸውንም ያውቃል::

በልጅነቱም አባ ዝንበሩ ከክብራን ገዳም አምጥተው የዳጋ ቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳምን እንዳስጐበኙት ያስታውሳል:: በመሆኑም ባህሉንና ትውፊቱን ለመላመድ የሚያደርገው ጥረት አይኖርም:: ሰላምታቸውም አዲስ አልሆነበትም:: እሱም እንደነሱ እስከመሬት ለጥ ብሎ እጅ መንሳት አልተሳነውም:: ሁለቱ መነኮሳት ፈንጠር

ብሎ ብቻውን ወደተሰራው የእንግዳ ቤት ይዘውት ሄዱ:: የእንግዳ ቤቱ ክብ የሳር ጉጆ ነው:: መደቦቹ ላይ ከሰሌን በእጅ የተሠሩ ምንጣፎች ተነጥፈዋል፡ ከግድግዳው ላይ ያለው ቀንዲል ተለኩሷል:: ጭል ጭል የሚለው የቀንዲሉ መብራት ወጋገን በደሳሳው ጉጆ ውስጥ ያለውን ጨለማ ወደ ውጭ ይገፋል:: ከእንጨት ጥርብ የተሠራው የሳንቃ ንቃቃት በሚወጡት የቀንዲሉ ብርሃን ጨረሮች ፍንጣቂ ዙሪያ ትንኞች ይተራመሳሉ፤ ያሳዝናሉ:: በቀንዲሉ ብርሃን መፅሐፍ ክንፋቸው ላይ ዘርግተው ያነቡ ይመስል በብርሃኑ ጨረር ዙሪያ ይሽከረከራሉ:: ያነበንባሉ:: ትንኞቹ:: ሚራዥ በሁለቱ መነኮሳት ታጅቦ ወደ ጉጆዋ ሲገባ ከተነጠፉት የሰሌን ምንጣፎች አንደኛው ላይ የተቀመጡት መነኩሴ ተነስተው ቆሙ::

«እርሳቸውም እንደ እርስዎ እንግዳ ናቸው» አሉ ጠይሙ ጢማም መነኩሴ:: «አብራችሁ ተጫዋወቱ:: መጋቢው መጥተው ይጉበኙችኋል::» ሁለቱ መነኮሳት የእንግዳ ቤቱን ሳንቃ የኋሊት ዘግተውት ሄዱ::

ሚራዥ እንደ እሱ እንግዳ የሆኑትን መነኩሴ እጅ ነስቶ ተቀመጠ:: በግድግዳው ዙሪያ ማዶና ማዶ በተሰሩት መደቦች ላይ የተቀመጡት ሁለቱ እንግዶች ሳይነጋገሩ በዝምታ ተውጠው ቆዩ:: እንግዳው መነኩሴ የለበሱትን ቢጫ የምንኩስና ቀሚስ በፈርጣማ አካላቸው ተወጣጥሮ እርጉዝ ሴት አስመስሏቸዋል:: የደረቡት መጉናፀፊያ ተንሸራቶ መሬት እየላሰ ነው:: ጥቁር ፀጉራቸው ላይ የደፉት ቆብ ራሳቸውን በከፊል ያሳያል:: ጥቁር ፊታቸው ከፀጉራቸው ጋር ሊመሳሰል ምንም አልቀረውም:: በጩቤ የተሸረካከተ መሆኑን የሚያሳብቀው ፊታቸው ሰድሜ ልካቸውን ሲደባደቡ የኖሩ አስመስሏቸዋል:: የተሠበረ ቀንድ የሚመስለው ጉራዳ አፍንጫቸው በላልዟል:: አገጫቸው ላይ የበቀለው ፀጉር ጥቁር ግንድ ላይ የሚርመሰመስ ጉንዳን ይመስላል::

ሚራዥ እንግዳውን ለረጅም ጊዜ እያጮለቀ ሲመለከታቸው ከእስር ቤት ያመለጠ አደገኛ ወንበዴ መስለው ተቀረፁበት:: መነኩሴ ቀርቶ ምንኩስና የሚባል ነገር የሰሙ አይመስሉም:: የምንኩስና ልብሳቸውን በሥርዓቱ ካለመልበሳቸውም በላይ ከሰውነታቸው ጋር ባልተዋሃደው ቀሚስና መጉናፀፊያ ዝርክርክ ብለዋል:: ደሞ ጠብደል ናቸው:: በየቀኑ በሬ እስከቀንዱ ሲውጡ የኖሩ እንጂ በፆምና በስግደት ሲመጠመጡ የኖሩ አይመስሉም:: የፊት ጥርሳቸውን በሙሉ ያጡ መሆናቸውን ያረጋገጠው አፋቸውን እስከጆሯቸው መልግደው ሲያዛጉ ነው:: የተከፈተ አፋቸውን በመዳፋቸው እየከመከሙ «ስምህ ማነው?» አሉት:: አንተ ብለው በመጥራታቸው የሚቀነስ ክብር ባይኖረውም ለስርዓተ ገዳም አዲስ መሆናቸውን ፍንጭ ሰጠው:: ማን እንዳመነኮሳቸው እግዜር ይወቀው እሰ በሆዱ:: ለነገሩማ እሱንስ ማን አመነኮሰው ልበስ የተባለውን ልብሰ ምንኩስና ገላው ላይ ቢጭንም ነፍሱ እንዳልመነኮሰች ግን ልቡ ያውቃል:: አፉን መከርከም እንዳለበት አምኖ «ሚራዥ



እባላለሁ::» ብሎ ዝም አለ:: መልሰው ደግሞ እርስዎ አሉት:: ረስተውት ነበር ለካ::

«አባ ሚራዥ ከወዴት መጥተው ነው?» ድምፃቸው ጆሮ የሚቆረቁር ለዛቢስ ነው:: ጮክ ብለው በመናገራቸው ሰቀጠጠው:: ጥያቄያቸው ደግሞ ትክክል አይደለም:: በኢትዮጵያ ገዳማት ውስጥ የቆዩ ቢሆኑ ኑሮ ከወዴት መጣህ ብለው አይጠይቁም ነበር:: በኢትዮጵያ ገዳማት የሚመጣ ማንኛውም መናኝ ሀገሩ፣ ዘሩ፣ ሐብቱ፣ ስልጣኑ፣ አይጠየቅም፡ እግዚአብሔር ...ርቶት ከመጣ መጣ ነው በቃ:: ከዚህ ውጪ የገዳሙን ስርዓት አክብሮ እስከኖረ ድረስ ራሱ ፈቅዶ ካልተናገረ በስተቀር «እስራኤላዊ ነህ? ኢትዮጵያዊ ነህ? ግብፃዊ ነህ? አማራ ነህ? ኦሮሞ ነህ? ትግሬ ነህ? ገለመሌ ነህ?» ተብሎ አይጠየቅም:: ቢጠየቅም እንኳ መነኩሴ ትክክለኛ ማንነቱን አይናገርም:: ማንነቱን ማጣራት ቢገባ እንኳ ማጣራትና መጠየቅ የሚገባው የገዳሙ ኃላፊ የሆነ መነኩሴ ነው:: የገዳሙ አበምኔት ወይም መጋቢ ወይንም ሌላ ኃላፊ::

«ከዋልድባ ገዳም ነው የመጣሁት::» ሲል የምሽቱን ታላቅ ውሸት ዋሸ ሚራዥ:: «ዋልድባ ገዳም ወዴት ነው?» አሉ ጠብደሉ መነኩሴ::

«ዋልድባን የማያውቅ መነኩሴም አለ እንዴ?»

«ይኸው እኔ አለሁ::» ጥቁር ከንፈራቸውን ብልጥጥ ሲያደርጉት ጥርስ አልባው ቀይ ድዳቸው ከከሰል ጫፍ ላይ ያለ ፍም መሰለ::

«ዋልድባ ሲባል ሰምተው አያውቁም?»

«አረ ስቀልድ ነው......... ዋልድባን የማያውቅ መነኩሴ እንዴት ይኖራል?» በዚህ መሀል አባ ዲምላ እባላለሁ ብለው ስማቸውን በስህተት ሊያስተዋዉቁት ለጥቂት መልሰው ዋጡት:: አባ ዲምላ ይህን ይበሉ እንጂ ከሲሲሊ ደሴት በዶን ሞርሞርዲኖ የግል አውሮኘላን ከቀናት በፊት ኢትዮጵያ መግባታቸውን ልባቸው ያውቃል:: ለመጠብት ልዩና ምስጢራዊ ተልእኮ የሚበጁቸውን ምርጥ ምርጥ ውሸቶችና የሀሰት ሽፋኖች ካልተጠቀሙ ከዚህ ገዳም ተባረው ተልእኳቸው ከንቱ እንዳይሆን ሰግተዋል::
ወዲያው መጋቢው ወደ እንግዳ ቤቱ ገቡ:: ረዥም ሰላምታ ለሁለቱም ሰጥተው ተቀመጡ:: ጥቂት አቀርቅረው ከቆዩ በኋላ «እዚህ ለመኖር ነው?» ሲሉ ሁለቱንም ጠየቁ:: እንዳቀረቀሩ::

«አዎን እዚሁ ለመኖር ነው» አባ ዲምላ ፈጠን ብለው መለሱ::

«የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን::» አባ ሚራዥ አንገታቸውን ሰበር አድርገው ለስለስ ባለ ድምጽ::

«ያው ...መቼም በሌላ ገዳም የቆያችሁ ከሆናችሁ ታውቁታላችሁ ስለገዳም ሥርዓት እናንተን ማስተማር ድፍረት ይሆንብኛል:: ውሃ ሽቅብ አይፈስም:: በመዘውር ካልሆነ በቀር::»

ወጥ ከደራሽ የጉርፍ ውሃ ተቀድቶ የመጣ መሰላቸው:: «ይህን እየተመገቡ ነው ዘለአለም የሚኖሩት? የማይታመን:: መንግሥተ ሰማያት ሲያንሳቸው ነው:: የሰው ልጅ ግን ለምን ራሱን ያሰቃያል? ቆይ ይሄ መንግስተ ሰማያት ግን ምንድን ነው? እንዴት ሰው የተሰጠውን አለም ንቆ ገና ያልተሰጠውንና የማያውቀውን አለም ያፈቅራል? ኧረ እኔስ ዓለሜን አልንቅም:: ከፈለጋችሁ ለምን እንጦርጦስ አትገቡም:: ማንም አውደልዳይ በዓለም አልሳካለት ሲል ሌላ አለም እስኪመጣ ይጠባበቃል:: ኧረ እዛው! እኔ ዲምላ ኢየሱስም ይምጣ ሞርሞርዲኖ ለእኔ ያው ናቸው:: ኢየሱስ መንግሥተ ሰማያትን አወርስሃለሁ ሲል ሞርሞርዲኖ ደግሞ ሲሲሊን እሰጥሃለሁ ይለኛል:: ሁለቱም አንድ ናቸው:: የሰውን ልጅ በጥቅም ለመደለል:: በምን ሒሳብ ነው መንግስሥትህ ትምጣ ብዬ የምፀልይለት? በዚህኛው መንግሥት ምን ተጠቀምኩ መጀመሪያ! ኢየሱስና መንግስቱ እዛው በሰማይ ይቆዩልኝ:: ሞርሞርዲኖን ጌታዬ ስል በኖርኩበት አፌ ደሞ ኢየሱስን ጌታዬ ልል? ጌታዬ ስል እንድኖር ከፈጠረኝ ተሳስቷል:: እኔ የራሴን መንግሥተ ሰማያት አዘጋጃለሁ:: መንግሥተ ዲምላ ቀርባለችና ሁላችሁም ገደል ግቡ:: አለም ከኔ በተቃራኒ ቆማ ነበር:: አሁን ግን በኔ ቁጥጥር ስር የምትውልበት ጊዜ በየሰከንዱ እየቀረበ ነው:: መንግሥተ ዲምላ እየቀረበች ነው::» አባ ዲምላ ይሄን እያሰላሰሉ ምግቡን ማቆማቸውን ዘንግተውት ነበር::

«ይቅመሱ እንጂ አባ?» መጋቢው በሀሳብ ባህር የሰጠሙትን አባ ዲምላን አባነኗቸው:: «እየበላሁ ነው:: እየበላሁ ነው ...ታምሜ ነበር የከረምኩት:: ትንሽ የምግብ ፍላጐቴ ቀንሷል:: ቀስ እያልኩ እስቲ እንግዲህ እበላለሁ:: ለአሁኑ ግን በቃኝ::»

አባ ሚራኝ የተሰጣቸውን መቁነን ጨርሰው «ስብሐት ለአብ» ብለው አመስግነው ማዕዳቸውን ከፍ አደረጉ::

መጋቢው ማዕዱ ከፍ ካለ በኋላ ስርዓተ ገዳሙን የሚመለከተውን ንግግራቸውን ቀጠሉ:: «.....ቅድም እንዳልኩት ምንኩስና በወንጌል የተገኘ ጥበብ ነው:: የምንና አብነታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: መነኮሳት በምድር ያሉ መላእክት ናቸው:: ለስጋቸው አይኖሩም:: መነኩሴ ማለት «ምውት ዘተፈልጠ እምአለም» ማለት ነው:: ቢሰድቡት የማይሳደብ፣ ቢመቱት የማይማታ በልቡ ክፉ ነገርና ቂም በቀል የማያስብ ነው:: ምውት ዘተፈልጠ እምአለም....ከዓለም በሞት የተለየ:: .....በዓለም ሆኖ የሚራብ እሱ መነኩሴ አይደለም ሰነፍ ነው:: መነኩሴ የሚራብ ግን እያለው ነው:: ዘመድ አዝማዱን አይናፍቅም:: በአቱን ለቆ አይወጣም:: ተቀምጦ አይፈርድም:: የመነኩሴ ሰይፉ ፀሎቱ ነው:: ሰይፍ አያነሳም:: አይቆጣም:: በቁጡ ሰው መንፈስ ቅዱስ አያድርበትምና:: ቁጡ ሰው የሰይጣን ደቀ መዝሙር ነው::» ቀና ብለው ሁለቱንም አዩአቸውና ቀጠሉ::



«ሰው ስጋዊ ወመንፈሳዊ ነው:: ሰው ፈቃደ ስጋና ፈቃደ ነፍስ የሚዋጉበት የጦርነት አውድማ ነው:: በመሆኑም ከወንድሞቻችሁ አንዳቸው በፈቃደ ስጋ ቢወድቁ መሰናከል አይገባም:: ስጋዊ ወመንፈሳዊ መሆናቸውን ካወቃችሁ በቂ ነው:: የነገሩትን ሳያስተውል ፈጥኖ የሚያምን ሰው ልበ ቀሊል ነው:: በገዳሙ ውስጥ የምታዩት ደስ የማያሰኝ ነገር ካለ ለአበምኔቱ መንገር እንጂ ባያችሁት ነገር መሰናከል የለባችሁም:: ወደ ገዳሙ ማህበር ከተቀላቀላችሁ ወዲህ በገዳሙ ውስጥ ካሉ ወንድሞች ጋር አብራችሁ ችግሩንም ደስታውንም መካፈል፣ በፀሎት ጊዜ መገኘት፣ በተለይ በተለይ ደግሞ ወሳኙ ነገር ፍቅረ ቢፅ ነው:: እርስ በእርስ መዋደድ:: የገዳሙ ማህበር ለገዳሙ ስራ ካልሳካችሁ በቀር ወደ ከተማ መውጣት በጥብቅ የተከለከለ ነው:: አንዴ ንቃችሁት ወደ መጣችሁበት ዓለም መመለስ የለባችሁም::»

«ኧረ እኔስ የናኩት አለም የለኝም:: አለም ንቃው የመጣ መነኩሴ ሁላ አለምን ንቄ መጣሁ ቢል አይደንቀኝም::» አባ ዲምላ በውስጣቸው አፌዙ::

መጋቢው መነኩሴ «.....የገዳሙ አበምኔት አባ ዝንበሩ የተረፈውን ይነግሯችኋል:: ነገ ጠዋት::» ብለው እጅ ነስተው ወጡ::

# ፲፪

አባ ሚራዥ ከደሴቱ ላይ ባለው ኮረብታ የገዳሙ ደወል ድምፅ ሲያስተጋባ ነቅተው እይናቸውን ሞዠርቀው ሲቃኙ በእንግዳ ቤቱ ውስጥ ማንም የለም ነበር:: አባ ዲዖላ የተኙበት መደብ ባዶ ነው:: የንጋቷ ፀሐይ እግሮች በቤቱ ግድግዳ ንቃቃቶች ሰርገው ገብተዋል::

ከጀርባቸው የማይለየውን ረጅም ሻንጣ እንደ ልጅ አዝለው ወደ ወደቡ ወረዱ:: አባ ዲዖላ በጣና ዳር በወደቀው እይናማ ድንጋይ ላይ ተቀምጠው እየተጣጠቡ ነበር:: አባ ሚራዥ ከአባ ዲዖላ ጥግ በሚገኝ ሌላ ትልቅ ድንጋይ ላይ ተቀምጠው በማዕበል ግፊት ከድንጋዩ እየተጋጨ በሚመለሰው የጣና ሐይቅ ውሃ ያደረ ፊታቸውን አለቃለቁት::

አባ ዲዖላ ወደ ጫካው ሮጠው ገቡና ኪሳቸው ውስጥ የተንፈራፈረውን ተንቀሳቃሽ ስልክ እናግረው ከመመለሳቸው ሰባት ሰዎችን የጫነች ዘመናዊ ጀልባ እየተንደቀደቀች ከተፍ አለች:: በውስጧ ጣሊያናዊው የማፍያ አለቃ ሞርሞርዲኖ ቡስኪ ከአራት አጃቢዎችና ከአስተርጓሚዎች ጋር ጀልባዋ ላይ ተቀምጠዋል::

ጀልባዋ ወደ ወደቡ እንደተጠጋች አራቱ አጃቢዎች ከጀልባዋ ወጥተው አካባቢውን ተቆጣጠሩት:: ዶን ሞርሞርዲኖ ሐበሻው አስጐብኚ ወጣት የሚለፈልፈውን አንድም ሳይሰሙ የገዳሙን በር ወደ ግራ ትተው ኮረብታው ላይ ወደታነፀው ቤተክርስቲያንና ሙዚየም የሚያደርሰውን ቀጭን መንገድ ተያያዙት::

ዲዖላና ሚራዥም ከጐብኚዎች ኋላ እየተከተሉ ወደ ኮረብታው ወጡ:: ከኮረብታው ወገብ ላይ የፃድቃን ማረፊያ የምተባለው ቦታ ሲደርሱ ከፊት የሚመሯቸው መነኩሴ እረፍት እንዲያደርጉ ጋበዟቸው:: የፃድቃን ማረፊያ ላይ ሳያርፍ ማንም ሰው ወደ ቤተክርስቲያኑ አይሄድም:: ነጭ ላብ የሚያስለበው አቀበት የዶን ሞርሞርዲኖን ሳንባ ከደረታቸው ወትሮት ስለነበር ማረፉን አልጠሉትም:: አባ ዲዖላም ፍየል ፍየል እየሸተቱ ነበር::

የፃድቃን ማረፊያ የዲጋ ቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳምን የመሠረቱት ፃድቁ አቡነ ሂሩተ አምላክ ወደ ደሴቱ ሲመጡ በጣና ሐይቅ ላይ እንደ ጀልባ አድርገው በላዩ ላይ ተቀምጠው እየቀዘፉ የመጡበት ተአምራዊ ድንጋይ የተቀመጠበት ቦታ ነው:: ሐበሻው አስጐብኚ ወጣት ወደ ዶን ሞርሞርዲኖ ዞሮ «ይህ የምታዩት ጠፍጣፋ ጥቁር ድንጋይ ገዳሙን የመሠረቱት አቡነ ሂሩተ አምላክ በ1268 ዓመተ ምህረት በጣና ሐይቅ ላይ እየተንሳፈፉ የመጡበት የድንጋይ ታንኳ ነው::» አለ:: ስሜት አልሰጣቸውም:: ሊናገሩ ያሉትን ቃል መልሰው ዋጡት:: «ይህ ሲሲሊ አይደለም::» አለ ውስጣቸው:: ሲሲሊ ውስጥ የፈለጉትን የመናገር አቅም ብቻ ሳይሆን



የፈለጉትን ባለስልጣን የመፈንቀልም ስልጣን በእጃቸው ነው:: ለዶን ሞርሞርዲኖ በምድር ላይ ሁሉንም ነገር የማድረግ ተአምር የተቀበረው ገንዘብ ውስጥ ነው:: እንደእርሳቸው ድምዳሜ ስልጣን የገንዘብ ነው:: መብት የገንዘብ ነው:: ኃይልም ገንዘብ ነው:: አቡነ ሂሩተ አምላክ ምናልባት በቅድስና ድንጋይ በውሃ ላይ ማንሳፈፍ ችለው ቢጋልቡ ግድ አይሰጣቸውም:: ዶን ሞርሞርዲኖ ሲሲሊና ህዝቦቿን ሜዲትራንያን ባህር ላይ እድሜ ልካቸውን ሲጋልቡ ኑረዋል:: «ቅድስና ድንጋይ ሲያስጋልብ ገንዘብ ደግሞ ህዝብ ያስጋልባል::» አሉ በውስጣቸው ሞርሞርዲኖ:: ለዶን ሞርሞርዲኖ ታላቁ የምድራችን ባለ ስልጣን ገንዘብ ነው:: ቅድስና አይደለም:: ለእሳቸው በጣና ሐይቅ ላይ የተንሳፈፈው ተአምራዊው የአባ ሂሩተ አምላክ ድንጋይ ቅንጣት ታህል ስሜት አልሰጣቸውም:: እድሜ ልካቸውን ሲመኙት የኖሩትና ለአባታቸው ቡስኪ ከአቅም በላይ የሆነው ምስጢር ነው ስሜት ሊሰጣቸው የሚችል:: የሩቁን አቅርቦ በሚያሳይ መነጽራቸው በደሴቱ ዳርቻ ደቡባዊ ምሥራቅ በኩል ያለውን ጣሊያን የሠራውን ወደብና በደሴቱ በኩል ለሚያልፉ መርከቦች ምልክት እንዲሆን የተከለውን የመብራት ማማ እየተመለከቱ ነበር ወደ ደሴቱ የሰሜኑ ወደብ የተጠጉት:: ጣሊያናዊው ከበርቴ ሞርሞርዲኖ ቡስኪ በዳጋና በደቅ ደሴት መካከል በምትገኝ አነስተኛ ደሴት ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ከከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናት ጋር ስምምነት የተፈራረሙት ከሁለት ቀናት በፊት ነው:: ይህንን የኢንቨስትመንት ስምምነት ፊርማ የመፈራረማቸው ዜና እንዲህ ዓይነት ዜናዎች በየቀኑ ስለሚደመጡ ማንም ትኩረት አልሰጠውም እንጂ በሀገሪቷ ቴሌቭዥንና ሬድዮ ተላልፏል:: የጣና ሐይቅ አርጀኖዎች ፀሐይ መሞቂያ በሆነችውና የደሀ ሰው መዳፍ በምታህለው ብጣቂ ደሴት ላይ ለምን ዓይናቸውን እንደጣሉ ከእርሳቸውና ከአንድ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣን በቀር ማንም አያውቅም:: ግሩ ሲል የምስጢሩ ጫፍ የተያዘው በአባ ዲዖላ ነው:: አባ ዲዖላ ወደ ዳጋ የመጡበት ጉዳይ በእርሳቸውና በዶን ሞርሞርዲኖ የተያዘ ከፍተኛ ምስጢር ነው:: በርግጥ በብጣቂዋ ሰው አልባ ደሴት ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ስምምነት ተፈራረሙ እንጂ ምን ኢንቨስት እንደሚያደርጉ በውል የሚታወቅ ነገር የለም:: የተዘገበ ነገር ቢኖር አንድ ጣሊያናዊ ባለሃብት በአማራ ክልል ኢንቨስት ለማድረግ ስምምነት መፈራረማቸው ብቻ ነው:: በአነስተኛዋ ሰው አልባ ደሴት ላይ የሰፈሩት የሞርሞርዲኖ ሰዎችም በዛች ደሴት ላይ ምን እንደሚሰሩ አያውቁም:: ለስንቅ ማመላለሻ ተብላ ከሲሲሊ ተጭና መጥታ የተገጣጠመችው ዘመናዊ ጀልባ ደሴቱን ልታህል ምንም አልቀራትም:: በተተከሉት ታላላቅ አረንጓዴ ድንኳኖች ውስጥ የተቀመጡት የሞርሞርዲኖ ሰዎች እስከ አፍንጫቸው ታጥቀው ትዕዛዝ በመጠባበቅ ላይ ናቸው:: ይህ ከሆነ በኋላ ነበር ዳጋ ገዳምን ሊጐበኙ የተንቀሳቀሱት:: በእቅዱ መሠረት ጉብኝቱ ተጀምሯል::

«ኃይል እንጠቀም?» አሉ ጌታ ሞርሞርዲኖ፡

«አንችልም!»

«እንዴት?»

«እዚህ ሁሉም ሞት የጠማው ነው። መነኩሴ አጥብቆ የሚፈልገው ነገር ቢኖር እረፍተ ሞቱን ነው። መነኩሴ የሚሆንም አስቀድሞ የሞተ ሰው ነው። እኛ ሳንገድላቸው አስቀድመው የሞቱ ናቸው። እንዲያውም በሰማዕትነት ለመሞት የሚሳል መነኩሴ ብዙ ነው። መነኮሳት ከዚህኛው አለም ይልቅ ለዛኛው አለም ጥልቅ ፍቅር አላቸው። ሞት ለመነኮሳት ወደ ዘለአለማዊነት መሸጋገሪያ ድልድይ ነው። ሞት በዚህ ደሴት ውስጥ ከዛፍ ጥላ አይበልጥም። ጌጥ ነው። ሞት ለነዚህ መነኮሳት ደስ የሚል ዕረፍት ነው። አይሰጡንም። ፍንክች ቢሉ አይሰጡንም። ለመስረቅ እንዳልሞክር ደሞ የሚሰረቀው ነገር የት እንደተቀመጠ አላውቅም። ለማሞኘትም አይመቹም።»

«እየውልህ ባሪያው! ፍቅር ያልፈታውን ገንዘብ ይፈታዋል። ገንዘብ ያልፈታውን ኃይል ይፈታዋል። በፍቅርና በገንዘብ አልሆን ካለን ኃይል ከመጠቀም ወደኋላ አንልም። ኃይል መጠቀም የመጨረሻው አማራጭ ነው።»

«ተሳስተዋል ጌታ ሞርሞርዲኖ። ኃይል ለመጠቀም አቅማችን አይፈቅድም።»

«እንዴት ነው የማንችለው? እኔ እኮ ሞርሞርዲኖ ነኝ! እንኳንስ አንድ ኋላ ቀር ደሴት እነ ሳልባቶሪ ጁሊያኖ፣ እነ አሞሪ አድሪኖ.......... እነ....እነ... እነዛ ሁሉ ጀግኖች ነግሠው የኖሩባት ሲሲሊን ያንቀጠቀጥኩ ጀግና መሆኔን ረስተኸው ነው አንት ባሪያ! ይህን ደሴት ከፈለግሁ በግራ እጄ ገፍትሬ ጣና ሐይቅ ውስጥ ማስጠም አልችልም? ባሪየው! እስከ አሁን አላወከኝም ማለት ነው።»

«መለኮታዊ ጥበቃ የሚደረግለት ገዳም መሆኑንስ ልብ ብለውታል?»

«መለኮታዊ? ሃ! ሃ! ሃ!.........» ሞርሞርዲኖ በለበጣ እንደ እህል ወፍጮ ተንደቀደቁ። «እየህ ባሪያው...... መለኮት በእንደዚህ ዓይነት ትግሎች ውስጥ እጁን አያስገባም። በትግል ህግ መሠረት ያሸነፈ ይገባዋል። እናሸንፋለን-ይገባናል። መለኮት ፍትሐዊ ከሆነ በማንኛውም ትግል ውስጥ ጣልቃ መግባት የለበትም። አንበሳ ጎሽ አድቅቆ ሲበላ መለኮት ጣልቃ አይገባም። ጅብም አህያን አራሩጦ አንጀቱን ሲመዘው መለኮት ጣልቃ አይገባም። የዓለም ዋነኛው ህግ በልቶ መበላት ነው። ያም ተባይ ያም ተባይ! መለኮት ለማን ሊያግዝ ይችላል? ሰውም እንስሳትን አርዶ ይበላል። እንዲያውስ ሐበሻ ጥሬ ስጋ እየዘለዘለ ሲበላ ዝም የሚል መለኮት ከሞርሞርዲኖ በተቀራኒ ይቆማል ብለህ ታስባለህ? እኔ ጥሬ ሥጋ አልበላም»



«ጠብሰው ይበሉ አይደል እንዴ ታዲያ!? ጠብሰውም በሉት ጥሬውን ያው ነው። ይልቅስ ትዝ አያስብሉኝ ጥብስ ሥጋ እየበላን ወይን የተጎነጨንበትን ወቅት። ያም ሆነ ይህ ገዳሙ በመለኮታዊ ጥበቃ ብቻ አይደለም የሚጠበቀው። የቀድሞ ወታደሮችና ጄነራሎች የነበሩ መነኮሳት መኖራቸውን ደርሼበታለሁ። ከዚህም ሌላ በዚህ ገዳም ውስጥ ብዙ የታሪክ ተመራማሪዎች፣ ፈላስፋዎች፣ኢንጂነሮችና ዶክተሮችም አሉ። እንዲያውም ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ኢንጂነሮችና ዶክተሮች የላቁ ዶክተሮችና ኢንጂነሮች እዚህ ዳጋ ገዳም ውስጥ አሉ። እዚህ ምን እንደሚሠሩ አላውቅም። የዋዛ እንዳይመስሉዎት! እነዚህን ሰዎች መጋፈጥ የአድዋውን ድል መልሰው እንዲቀዳጁ እድል መስጠት ነው።»

ከት ብለው ሳቁ ሞርሞርዲኖ። «አድዋ?....... የአድዋ ድል? እኛ አፈገፈግን እንጂ አድዋ ላይ አልተሸነፍንም። ለአርባ አመታት በሠራነው ሥራ ተመልሰን መጥተን ድል አድርገናል። ኤርትራን የገነጠላችሁበት ምክንያት ምኒልክ ጦርነቱን ጨርሰው ጣሊያንን ከቀይ ባህር ስላላሻገሩት ነው? ምኒልክ ያልጨረሱት ጦርነት ካለ ይህ ከሳቸው የተሻለኩ ነኝ የሚለው ትውልድ ጦርነቱን መጨረስ አይገባውም ነበር? አቅም የለማ! ጣሊያን ኤርትራ ውስጥ ያቋቋመችው ፋብሪካዎችንና ካምፓኒዎችን የወረሱ ለቃቃሚዎች ባቋቋሚቸው ወንበዴዎች የተደረገው ግንጠላ አንዱ የኛ አሸናፊነት ማረጋገጫ ነው። እየህ ሐበሻን በሆዱ እንጂ በጦር በጎራዴ አታሸንፈውም። ከዚህ በላይ ሽንፈት አለ እንዴ? ተውማ ብዙ አታናግረኝ ....መቾም አፍንጫውን የተያዘ ለጊዜውም ቢሆን በአፋ መተንፈሱ አይቀርም። የኢትዮጵያ አፍንጫ ቀይ ባህር ነበር። አሁን እሱ አፍንጫዋ ተቆርጧል። ለዛም ነው አድዋ አድዋ እያላችሁ የምትነፋነፉት። አይገባህም እንጂ እያልኩህ ያለሁት ዓድዋ ላይ ድል አደረግን ማለት አትችሉም የተዋጋችሁለት መሬት አሁን የለምና። ዓድዋ አልከኝ..... አይ ባሪያው! ያም ሆነ ይህ የዓድዋ ድል አንተን አያካትትም። ሲሉ ሰምተሀል! አህያ! ......የእኔና ያንተ ራስ ምታትም ይህ አይደለም። የኤርትራና የኢትዮጵያ መሪዎች የሚቆምሩትን ቁማር እዛው ለእነሱ እንተወውና እኔና አንተ የራሳችንን ቁማር እንጫዎት። አለም ቁማሩን የማያሸንፉትን አታስተናግድም። ለመሆኑ ገዳሙ ውስጥ መሣሪያ የታጠቁ አሉ?»

«...እ....እገምታለሁ» አለ ዲምላ በተቆራረጠ ድምፅ።

«እገምታለሁ!?» በንዴት ጦፉ ሞርሞርዲኖ።

«እንዲያውም አረጋግጫለሁ።............ የማይሆን ነገር ነው ጌታ ሞርሞርዲኖ። አጉል ነው በረሃብ የምስቃዩው። ከጉሮሮ የማይወርደውን ዳቤ የሚባል ቀፋፊ ምግብ መቋቋም አልቻልኩም። በዛ ላይ ሰገራው! ውይ..ውይ...ውይ! እዚህ ገዳም ውስጥ

«ወይን አልጠጣም በቃኝ» አለች ሲጻራ እጇን እንደተማረከ ወታደር ወደ ላይ አንስታ።

«ጠጪ እንጂ የኔ ቆንጆ....» አፉ እየተሳሰረ ነበር። ፊቱም ረተቀቀለ ሳምባ መስሏል። «.. ....ባይሆን የጀመርሽውን ብርጭቆ ጨርሽው። ገዳችን እንዳይበላሽ። ነገ ሳይንቲስት ሻጊዝን አንቀን ወደ ቴልአቪብ የምንወስድበት ቀን መሆኑን ረሳሽው የኔ ቆንጆ ገዳችን ይመር እንጂ። ችርስ በይኝ ይልቅ እንደ ገና» ብርጭቆውን አንስቶ ወደ ፊቷ አቀረበው።

ብርጭቆዋን አንስታ ከብርጭቆው ጋር አጋጭታለት ወደ ከንፈሯ በምትወስድበት ቅፅበት ጠረጴዛው ላይ ከነጠበች ርሚጥ ቡናማ ዱቄት ላይ አፈጠጠች።

«ሺት!ይህች አውሬ» አፍንጫው ላይ ላቡ ተንቆረዘዘ።

«ከዚህ መውጣት አለብን» አለች በፍጥነት እንደ ጥንቸል በርግጋ። «አደጋ ውስጥ ነን።»

«የምን አደጋ?»

«መጠጤ ተመርዟል።»

«ምን?»

«ይህን ሆቴል መልቀቅ አለብን አልኩህ በቃ።»

የመኪናዋን በር ከፍታ ገብታ በፍጥነት ሆቴሉን ስትለቅ አንዳች ነገር እያንዘፈዘፋት ነበር። አናንያ ከሁዋላ ወንበር ተቀምጧል።

ለጊዜው ከተከራየችበት አፓርታማ የመኪና ማቆሚያ መኪናዋን አቁማ ወደቤትዋ ይዛው ገባች። የንዴት ሲቃ እየተናነቃት ሽጉጧን ከሽንጧ መዥርጣ ከአናንያ አንገት ሥር ሸጉጠችው።

«አሁን ይህንን ሲባጉ አንገትህን በጥሼ ልጣለው?»

«ምን ነካሽ የኔ ቆንጆ....እ....» አለ ወደ ላይ እንዳንጋጠጠ አይኖቹን ዘቅዝቆ።

«ያደረከውን ልትክድ ነው?»

«ምንድን ነው ያ...ያ..ያደረኩት? »

በብሽቀት ሳቅ ተንፈቀፈቀች። «ለምንድን ነው መጠጤን መመረዝ ያስፈለገህ?»

«አልመረዝኩትም ሲጻራ።»

«የምትበልጠኝ ይመስልሃል። ደደብ! ቢገባህ..... ደደብነትን ካለማወቅ የበለጠ ደደብነት የለም። ጭቃ ራስ! ሁሉንም ነገር ተከታትየዋለሁ። ልትክደኝ አትምክር። ተልኮህ ምን እንደሆነ ብቻ ንገረኝ። ከጠላቴ ጋር ከዚህ በላይ መጓዝ አልፈልግም።»

«አልመረዝኩትም አልኩሽ። በእርግጥ.....» ቋጥኝ የሚያህል ራሱን በቀጭን አንገቱ ላይ ቀጫ አደረገው። «በ...በበ...በእርግጥ ዱቄቱን የጨመርኩት እኔ ነኝ። በማንም ተልኬ ሳይሆን እምቢታሽን



ለደቂቃዎች ለመስበር ነው። የላከኝ ፍቅርሽ ነው። በፍፁም አንችን ልጉዳሽ አልነበረም። ህይወትሽን የሚያቆም ነገርም አልነበረም። ትንሽ እንደ እንቅልፍ ሽልብ የሚያደርግ......» ተልመጠመጠ። መጠጡ አቅመ ቢስ እንዳደረገው ተገነዘበ። ቤቷ ውስጥ ከቋሚው ብረት ጋር በሰንሰለት ግጥም አድርጋ ስታስረው አልተቃወማትም ነበር። ጥላው ወጣች። የመኪናዋ ሞተር ሲጮህ ተሰማው።

ከደቂቃዎች በኋላ ስትመለስ ብቻዋን አልነበረችም። አስከትላት ያመጣቻት ጭራቅ የምትመስል ነጭ ሴትዮ ወደታሰረበት ቋሚ ብረት ተጠጋች።

«እሄ ነው እንዴ ጅላጅሉ ሚስስ ሲጻራ?» ጥርሷ የሻንፓዬር ዓይነት መሆኑን ያየው ደረቅ ፈገግታ እስከ አይኑ ቀርባ ስታሳየው ነው። አልኮል ያጠነፈፈው ትንፋሽዋ ሲገርፈው ሆዱ ተገለባበጠ። «እኔም እንዳንተው የቀነዘረብኝ ጅላጅል ቢጤ ነኝ። አብረን ሌሊቱን እናቀነዝረዋለን።» ከቦርሳዋ መርፌ አውጥታ ሲሪንጁን የሞላውን ፈሳሽ በሙሉ ከደሙ ጋር ቀላቀለችው። ብዥ ......ብዥ....ብዥዥዥዥ......ድንቅዝቅዝ.....ቅዝዝዝዝ...።....የታቹ ወደላይ ሲሆንበት ታየው። ቆይቶ ደግሞ የሚነዝር ስሜት አጥለቀለቀው። ወደብልቱ ሲንዶሉዶል......። በዝብርቅርቅ ሰመመን ውስጥ ሆኖ ሲጻራን በአይኑ ተማፀናት። ሽጉጧን ይዛ ቆማለች።

«ወሲብ አይደል የፈለከው?» አለች ሲጻራ «እሱትልህ።»

«አዎ.... ብቃትክን ማዬት እፈልጋለሁ»አለች ጭራቅ የምትመስለዋ ሴትዮ ሱሪውንና ሙታንቲውን እኩል እያወለቀች።

«እንደዚህ!....አዎ።» ብልቱን እየሸቀሸቀች። «ትንሿ ብልትህ ወደ ዋሻዋ ተመልሳ እንዳትገባ ተዪ በላት።»

ሲጻራ ሁለት እጆቹ የታሰሩበትን ሰንሰለት ፈትታ አንድ እጁን ከቋሚው ብረት ጋር ጠርንፋ አሰረችና አንድ እጁን ነፃ አወጣችለት።

«አመሰግናለሁ ሚስስ ሲጻራ!» አለች ሴትዮዋ። «ለእሱ የማደርግለትን ለእኔም እንዲያደርግልኝ እፈልጋለሁ።»

«አዎ።» አለች ሴትዮዋ። «ሚጢጢየዋን ብልትህን በማቆም ስለተባበርከኝ አመሰግናለሁ። ካጠነከርካት ልትበቃኝ ትችላለች።»

አናንያ ሴትዮዋን ከኋላዋ ማጥቃት ጀመረ። በግዱ። ትለፈልፋለች። ድምጧ ያስጠላል። ሰቀጠጠው። ጨረሰ።

«ውይ!» አለች ሴትዮዋ። «ከምኔው? »

እንደገና ተጀመረ። መፈጠሩን እስኪጠላ። ሲጻራ ፊቷን አዙራ ቆማለች።

«ቅድም ቶሎ የጨረስክበትን ምክንያት ተረድቼልሃለው። አሁን ግን እኔ እስክጨርስ መቆየት አለብህ። አትጨማለቅ።»

«በቃኝ! የተረገምሽ!» አለ አናንያ በምሬት። «አልፈልግም!»

«እኔ እፈልጋለሁዋ!» አለች ሴትዮዋ በደረቁ አስጠሊታ ፈገግታዋ አግጥጣ። «ቡል ሺት!» እንግሊዝኛዋ የደቡብ አሜሪካውያን ቅላፄ ያለበትና ቀፋፊ ቃና ያለው ነው። «ኡኡ» ሲል ምንም አልቀረውም። እንደዚህ የተሰቃየበትን ቀን አያስታውስም። እንደገና መርፌውን አወጣች።............ቀይታ ረጅም ምላሷን በከንፈሯዙሪያ እያሽከረከረች ቀረበችው። ጥርሷ መቶ ሰላሳ ሆነበት። ብዥዥዥታ። ብልቱን ቁልቁል ሲመለከተው ብዙ ሆኖ ታየው። አርባ.....ሃምሳ..... ከዛ ምን እንዳደረገ አያውቅም።

ጠዋት ዘግናኟ ሴትዮ ከወጣች ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሲጻራ ሻንጣዋን ጠቅልላ ስትወጣ  አናንያ ከቋሚው ብረት ጋር እንደ ታሰረ ከሰመመኑ ነቅቶ ነበር። ሲጻራን በበቀል ዓይን ተጉረጥርጦ ተመለከታት።

«ይህን ነበር አይደል የፈለከው?» አለችው ሲጻራ ሻንጣዋን እንደተሸከመች። «ከአሁን በኋላ ከኔ ጋር አብሮ የመስራት አጋጣሚ አይኖረንም። የሳይንቲስት ሻጊዝን ጉዳይ ለእኔ ተወው። በክንፋም አውሮኘላን ጭኜ ቴልአቪቭ ባላደርሰው ምን አለች በለኝ። አታውቀኝም ለካ።»

«አይደለም... ሲጻ....»

«ቻው!» ወጣች።

«ሲጻራ.... ሲጻራ.....ሲጻ....» የመኪናዋ ሞተር እስኪያጓራ ድረስ ስሟን እየጠራ ነበር። እንደታሰረ። ከእኩለ ቀን በኋላ በሁለት የእስራኤል ኮማንዶዎች ታጅቦ ወደ ቴሌአቪቭ በረረ። የሞሳድ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ሰብሳቢ ከሆኑት ወግ አጥባቂ አይሁዳዊ ጋር ሲነዛነዝ ከርሞ በከፍተኛ ማስጠንቀቂያ ታለፈ። ዶ/ር አናንያ በሞሳድ ውስጥ ያለ እውቅ የቀዶ ህክምና ባለሙያ ባይሆን ኖሮ መሰናበቱ ባልቀረለትም ነበር።

ሲጻራ ያደረገችው በየደቂቃው ትዝ እያለው ሽንፈት አጥንቱን ዘልቆ ሰረሰረው። ረመረመው። ከዛ ጊዜ ጀምሮ በሲጻራ ላይ ጥርሱን ነከሰ። ደሙ በጥላቻ ሲሰወስ ታወቀው።

ዶ/C አናንያ ከሞሳድ ዋና መስሪያ ቤት በታች ባለው የምድር ውስጥ የህክምና ጣቢያ ስራውን ተመልሶ ሲጀምርም በጥላቻ ተሞልቶ ነበር። ሲጻራን የሚበቀልበትን ማንኛውንም ስልት መንደፍ ጀመረ። በቀል ውስጡን ሲያርመጠምጠውና አጥንቱን ሲግጠው ይሰማዋል።



# ፲፰

## ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም፣ ኢትዮጵያ

ራሳቸውን ያመነኮሱት አባ ዲምላ በወጣትነት ዘመናቸው የሠሩት አንድ ስህተት በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ውስጥ የሚኳትኑለትን ክባድ ምስጢር በቀላሉ እንዳያገኙ ሳንካ ሆኖባቸዋል። ስህተቱንም የፈፀሙት በአባታቸው በአለቃ አያሌው ወይም በአባ ዲዲሞስ ላይ ነበር።

የወጣትነት ዘመናቸው ውል ብሎ ሲታያቸው በአሁኑ አባ ዲምላ ውስጥ የነበረው ወጣቱ ዲምላ ተከሰተላቸው። ወጣቱ ዲምላ ለምንም ነገር ደንታ የሌለው ነበር። የበለጠ ብልጥ ሆንኩ ሲል ራሱን የበለጠ ሞኝ ሆኖ ያገኘውም ነበር። ሰፍነግ ፈሳሽ ነገሮችን መርጦ እንደሚመጥ ሁሉ ክፉ ነገሮችን መርጦ የሚመጥ አእምሮው ውስጡ በጥላቻና በበቀል እንዲሞላ አድርጉታል። ደስታ የሚሰጠው አንዳች ነገር የለም ነበር። ሁሉንም ያማርራል። ዲምላን የማይኮሰኩሰው ነገር ምን ነበር? ምንም።

ምናልባት ከአባቱ ጋር አለማደጉ ለዚህ ጠባይ ሳይዳርገው አልቀረም ይባላል። አባቱ ከኢጣሊያና ከኢትዮጵያ ጦርነት በኋላ የት እንደደረሱ ለብዙ ጊዜ ሳይታምቅ ቆዩ። አልቃሻ እናቱም ሳያለቅሱ የዋሉበትና ያደሩበትን ጊዜ አያስታውስም። ቡተለይ በተለይ በኢጣሊያ ወረራ ወቅት በየጦር ግንባሩና በየሰፈሩ የወዳደቁ የሰው ሥጋዎችንና እጅና እግሮቹን እየዘነጠሉ የሚያመጡ ውሾች ዘንጥለው የሚያመጡት እጅ የባለቤታቸው  የአያሌው እጅ እየመሰላቸው እዬዩ ይሉ ነበር። ውሾችን አስጥለውም ክፋይ አካሉን ያዩና «ይሄማ የባለቤቴ እጅ አይደለም። የአያሌውን እጅ አውቀዋለሁ። ጣቶቹንም አልረሳቸውም።» ብለው ሲያነፈርቁ ዲምላ አንዳችም ዘለላ ዕንባ ጠብ አይለውም ነበር። ዝም። ዲምላ በባህር ዳር ከተማ ዳርቻ ባለች ቆሻሻ ሰፈር ውስጥ ሲያድግ... ከሰፈሩ ልጆች ጋር ሲጣላ «የጋለሞታ ልጅ» የሚለውን ስድብ ሳይቀምስ ውሎ አያውቅም ነበር።

በአንድ ወቅት አባ ፊንሐስ የሚባሉ ሽማግሌ እንጦረኛ በዛች ቆሻሻ ሰፈር ውስጥ ታዩ። ከነዲምላ  ቤት ጥግ ባለ የተንጣለለ ግቢ ውስጥ የሚኖሩትን ጣሊያናውያን ለምን እንደሚደበቁ ግን አይገባውም ነበር። ጣሊያናውያኑ ከኢትዮ-ጣሊያን የአምስት አመታት ጦርነት በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ የቀሩ ቤተሰቦች ነበሩ።

እንጥረኛው አባ ፊንሐስ በተለይ ቡስኪ የተባለውን የጣሊያናውያኑን ቤተሰብ አለቃ ሲያዩ ይፈረጥጡ ነበር። አንዳንዴም ቡስኪ በአካባቢው ሲያልፍ ዘለው ከነዲምላ ቤት ይገባሉ። እንጥረኛው ፊንሐስ ከዲምላ እናት ጋርም ሲጨቃጨቁ ይሰማ ነበር።

«ባልሽ ግማደ መስቀሉን ይዞ የት እንደተሰወረ ካልነገርሽኝ በዚህ ጉጠት ነው አይንሽን የምመነግለው» ሲሉ ይሰማል።

«አላውቅም። በየቀኑ ሳለቅስ የምኖረው እኔስ ስላጣሁት አይደልም?» ይላሉ እናቱ።

«አውቀሽ ነው አንች ከሐዲ እንደባልሽ እየካድሽኝ ነው።» እጥረኛው ያንባርቃሉ።

እንዲህ ሲነዛነዙ ከኖሩ በኋላ አንድ ቀን ሌሊት ዲምላ እና እናቱ ወደ ተቀመጡባት ደሳሳ ጉጆ ዘው ብለው ገቡ።

«ባልሽ ያለበትን ትነግሪኛለሽ አትነግሪኝም?»

«ስንቴ አላውቅም ልበልም። አላውቅም!»

ቤቱን ዘግተው ዙሪያውን በእሳት እያያዙት። መስኮት አልባው ደሳሳ ጉጆ ዥው ብሎ በፍጥነት ነዶ ዲምላ ሰውነቱ ተጠባብሶ ሲወጣ እናቱ እዛው ነደው ቀሩ። ከአልጋው ጋር እንዳሰሯቸው ያወቀው በኋላ ነበር። ደማቸው ሲንጨቀጨቅ ሥጋቸው ሲንፈቀፈቅ አጥንታቸው እሳቱ ውስጥ ሲከሰከስ ቆሞ ከማየት ውጭ ሊፈይድ የቻለው ነገር አልነበረም ነበር ህፃኑ ዲምላ። ለመጀመሪያ ጊዜ ዕንባ ጠብ ያለው ያኔ ነበር። ቆሻሻዋ ሰፈር በመንፈቀ ሌሊት በእናቱ የሥጋ ሽታ ስትታጠን የወጡት መንደርተኞች የደረሱት ሁሉም ነገር ሲጠናቀቅ ነበር።

የእናቱ ኡኡታና ዋይታ በህፃኑ ዲምላ አእምሮ ውስጥ ታትሞ ቀረ። ከዛን ጊዜ ጀምሮ ሰው የተባለን ሁሉ ጠላ። የእኔ የሚለው አንዳች ነገር የሌለው ዲምላ ከእናቱ ሞት በኋላ በዛ ቆሻሻ ባጥለቀለቀው ሰፈር ሲንከራተት ኖረ። ከባህር ዳር ከተማ ተጭነው መጥተው ከሚጣሉ ቆሻሻዎች ውስጥ በቆሻሻ ተጨማልቆ በቆሻሻ የተጨማለቁ የዳቦ ቁራሾችን ከውሾች ጋር ተሻምቷል።

አንድ ቀን ከተቃጠለው የእናቱ ቤት አቅራቢያ ካሉት ጣሊያውያን ቤተሰቦች ግቢ ውስጥ ዘው ብሎ ገባ። ለጣልያናውያኑ እየተላላከ ኑሮውን መግፋት ሲጀምር ቢያንስ ቢያንስ ከጣሊያውያኑ ውሾች በጥቂት ያነሰ ኑሮ መኖር ቻለ።

የጣሊያናዊው ቡስኪ ቤተሰብ ባልታወቀ ምክንያት ለሁለት ተከፍሎ ከፊሉ ወደ ከፋ ሲሄድ እሱም አብሮ ተጓዘ። በቦንጋ ከተማ ውስጥ ከሰፈረው የጣሊያን ቤተሰብ ጋር ተቆራኝቶ ከመኖር ውጭ ሌላ አማራጭ አልታየውም ነበር። በቦንጋ ከተማ የሰፈረው ጣሊያናዊ ቤተሰብ ውስጥ ዋነኛ ባው የነበረው ጉልማሳው ሞርሞርዲኖ ቡስኪ ነበር። ሞርሞርዲኖ ቡስኪም ከውሻው ቀጥሎ



ይንከባከበው የነበረው ሰው ቢኖር ዲምላ አያሌውን ነበር። ዲምላ ከሞርሞርዲኖ ጋር ኮከቡ ከገጠመለት ጊዜ ጀምሮ የተሻለ ህይወት መምራት ቻለ። ሞርሞርዲኖን ላቡ ጠብ እስኪል ቢያገለግልም የተበዘበዘ መስሎ አይሰማውም ነበር።

በዚህ መሀል አባቱ አለቃ አያሌው ቦንጋ ደረሱ። ከየት እንደመጡ ማንም አላወቀም። ዲምላን «አባትህ ነኝ» ሲሉት አንዳች የጥላቻ ስሜት እንደምች ሽው አለው። የጋለሞታ ልጅ ሲባል የኖረው ትዝ አለው። በእሳት እንደቋንጣ የተጠበሱ እናቱ ታወሱት። የመንፈቀ ሌሊቱ የእሳት ነበልባል።

«የት ነበርክ?» አለ ዲምላ ተጉረጥርጦ። «ከደካማዋ እናቴ ጋር በችግር ስንጠበስ የት ነበርክ? በለቅሶና በዋይታ ኑሮአችን በዕንባችን ስናጥብ የት ነበርክ? እናቴ በቁም ስትለበለብ የት ነበርክ? እኔ ቁራሽ ዳቦ ከቆሻሻ ገንዳ ውስጥ ስጉረጉር የት ነበርክ?»

«እየውልህ ልጄ እኔ.....» የአለቃ አያሌው አይኖች በዕንባ እየወረዙ።

አላስጨረሳቸውም። «አትንገረኝ! ምንም አይነት ይቅርታ ልቤ ላይ አይወድቅም ወደ መጣህበት ተመለስ። ያንን የሰቆቃ ጊዜ በየቀኑ እንድታስታውሰኝ አልፈቅድልህም።»

«ልጄ» አሉ አለቃ አያሌው። «ይቅርታ ልብ ላይ እንጂ መሬት ላይ አይወድቅም። በእርግጥ የመጣሁት ይቅርታን ልለምንህ አይደለም። የእኔ ውጣ ውረድ ስለማይገባህ ያንተን የሰቆቃ ጊዜ ሽረህ ይቅርታ እንደማታደርግልኝ አውቃለሁ። ሁሉንም የደረሰባችሁን ነገር ሰምቻለሁ። አሁን የመጣሁት ግን ልክስህ ነው። ልብ ካለህ ትጠቀምበታለህ።»

«ምንድን ነው እሱ?»

«አሁን አልነግርህም። ጥቂት ጊዜ ያስፈልገናል። ረጅም ነው ታሪኩ። እዚሁ እሰነብታለሁ።»

«አልፈልግም። ረጅም ነገር ያስጠላኛል። ከነገርከኝ ባጭሩ ነግረኸኝ ወደ መጣህበት ተመለስ።»

«እንዲህ ባጭሩ የሚነገር ነገር አይደለም ልጄ ጊዜ ያስፈልገዋል።»

አለቃ አያሌው በዛው በቦንጋ ውስጥ ለብዙ ጊዜ ቢቆዩም የዲምላን ትኩረት ሊያገኙ አልቻሉም። አያዳምጣቸውም፤ገና ሊያነጋግሩት ወዳለበት ሲሄዱ ይሸሻቸዋል፤ይደበቃቸዋል።

ከዲምላ ይልቅ ወደ ጣሊያኖች የኤሌክትሪክ ሱቅ መምጣት የሚያዘወትረው ወጣቱ ሻጊዝ እጅጉ ይቀርባቸው ነበር። ብዙም ነገር ይነግሩታል። የሻጊዝን እስተዋይነትና ብሩህ አእምሮ የተገነዘቡት አለቃ አያሌው ለልጃቸው ሊያስተላልፉት የነበረውን ምስጢር ለሻጊዝ ሊያቀብሉት ወሰኑ። ምስጢሩን ከመዘርገፋቸው በፊት ግን

የምስጢሩን ቁልፍ ከጀርባው በንቅሣት አስቀመጡለት። ሙሉ በሙሉ እንዳልተረዳቸው ግን እርግጠኛ ነበሩ። አንድ ቀን ግን እንደሚደርስበት አልተጠራጠሩም።

አለቃ አያሌው ዲምላን ቀስ በቀስ እየቀረቡ አንዳንድ ታሪኮችን ይነግሩታል። እሱ ግን አይገባውም። በአብዛኛው የሚነግሩት ስለ ኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪክ ነበር። ባያዳምጣቸውም ዝም ብለው ይተርኩለታል።

«የኢትዮጵያ መሪዎች ከጥንት ጀምሮ ለሥልጣናቸው ሰፍሳፋዎች ናቸው» ይሉታል።

«እና እኔ ምን አገባኝ? ይንሰፍሰፉዋ! ድሮ ለሥልጣን ካልተንሰፈሰፉ ለምን ሊንሰፈሰፉ ነው?» ይበሳጫል ዲምላ። አለቃ አያሌው እንደሁ አንዴ መተረክ ከጀመሩ ማቆሚያ የላቸውም።

«እናም አየውልህ ልጄ......ለሥልጣናቸው ቀናኢ በመሆናቸውም ለሥልጣናቸው ህልውና ሲሉ የማያደርጉት ነገር የለም ነበር። በዓለም ላይ ታላላቅ በሆኑ አስማተኞችና ጥበበኞች ራሳቸውን ከግድያ ለመከላከል የሚያሰሩት ብዙ ድግምት ነበር። ለምሳሌ ስለ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ልንገርህ።»

«አትንገረኝ!»ይላል ዲምላ። «ደክሞኛል። ስልችት ብለኸኛል።»

አለቃ አያሌው ግን ይቀጥላሉ። አባ ዲዲሞስ ትረካቸውን አያቆሙም።

«ንጉሥ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ኢትዮጵያን ለሰለሣ አራት በላይ አመታት ገዝቷል። መንበረ መንግሥቱም በሸዋ ነበር። በአክሱም ያሉ ጠላቶቹ ስለበዙ የደብረ ብርሃንን ከተማ ቆረቆረና በዚያ አንድ ትልቅ ቤተ መንግሥት አሠራ።»

«ኧረ በፈጠረህ አታድርቀኝ? ምንም የሚያገባኝ ነገር የለም ስለሱ!»

«አፄ ዘርዓ ያዕቆብ በእርግጥ ጥበበኛ ሰው ነበር። ደራሲም ነበር። ብዙ መጻህፍትን ደርሷል። መጽሀፈ ብርሃንና መጽሀፈ ንግሥ የሚባሉ መጻህፍቱ የሚጠቀሱ ናቸው። በዘመኑ የነበሩትን ደራስያን በመደገፍ ስለመጻሕፍት ምርመራ ያለውን ዝንባሌና ችሎታ አሳይቷል።»

«ቅድም ስለ አስማት አሁን ስለድርሰት። ተው ተው ግን አታድርቀኝ? በምን ቀን መጣህብኝ ልበል!»

«አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ለምን ከሕዝብ እይታ መደበቅ እንደሚያዘወትር ታውቃለህ?»

«ባላውቅ ይሻላል። ማወቅም አልፈልግም።»

«ከቤተ መንግሥቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄድም ሆነ ሲመለስ ማንም ሰው አያየውም ነበር። ከቤተ መንግስቱ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ የሚወስደው መንገድ ግራናቀኙ በረዥም ግንብ የተከለለ



ስለነበር። "ጠላቶቼ ሥራይ ያደርጉብኛል" በማለት ከምሽት እስከ ንጋት ካህናት ቤተ መንግስቱን እየዞሩ እየፀለዩ እንዲያድሩ ያደርግ ነበር። ካህናቱም ቤተ መንግሥቱን እየዞሩ ጠበል እየረጩ፣ ክህደተ ሳይጣንና መዝሙረ ዳዊት እየደገሙ ያድሩ ነበር። በኋላ ላይ ግን ወጣ ወጣ ማለት ጀምሮ ነበር። ለምን ይመስልሃል?»

«ለምንም አይመስለኝም። ባትነግረኝ እመርጣለሁ።»

«አንድ ትልቅ ጥበብ አሰራ!... ማንኛውም የጦር መሣሪያ የዘርዓ ያዕቆብን ገላ መውጋት እንዳይችል የሚያደርግ ጥበብ በታላላቅ የአለማችን ጥበበኞች አሠራ።» ዲምላ ጆሮውን አቆመ እዚህ ላይ።

«አርዌ በድላይ የተባለ የአዳል ባላባት ማመፁንና ግብር መከልከሉን ከዚህም በላይ ለጦርነት መሰናዳቱን ሰምቶ ሲዘምት የተከተሉት ጥቂት ወታደሮች ብቻ ነበሩ። ከአረዌ በድላይ ሰፈር ትይዩ ከሆነ ቦታ ላይ ደርሶ የጠላትን ሠራዊት ብዛት አይቶ አልደነገጠም። ካስከተላቸው ጥቂት ወታደሮች መሀል ገሚሶቹ ነጋሪት እንዲጎስሙ ከፊሎቹ ጥሩንባ እንዲነፉ ሌሎች ደግሞ እንዲፎክሩና እንዲያቅራሩ ስለአደረገ ጦርነቱን ከመጀመሩ በፊት አሸነፈ። ጠላቶቹን አስበረገገ። ጦርነቱ የተጠናቀቀው ራሱ ዘርዓ ያዕቆብ አርዌ በድላይን አንገቱን ቀልቶ ከገደለው በኋላ ነበር። ዘርዓ ያዕቆብ ይህን ያህል ድፍረት ያገኘበት ምስጢር ቅድም በነገርኩህ ነገር ነው። ባሰራው ረቂቅ ጥበብ ምክንያት ማንኛውም የጦር መሣሪያ እንደማይመታው እርግጠኛ ነበር።....... አሁን የዘርዓ ያዕቆብ አፅም የተቀመጠው በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ውስጥ ነው።»

«ይህን ልትነግረኝ ነው ስንት ወንዝ ተሻግረህ የመጣኸው? ይህ ነው የምትነግረኝ ምስጢር?» ዲምላ እርር ትክን አለ።

«ይህን ብቻ አይደለም። በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ውስጥ የተቀመጠው የንጉስ ዘርዓ ያዕቆብ ዓፅም ሙሉ አይደለም። ከአፅሙ መካከል ጥቂት አጥንቶች ተሰብረው ተወስደዋል፤ በውድ ዋጋም ተቸብቸብዋል። ምክንያቱም የንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ አፅም የጦር መሣሪያ አያስመታም ተብሎ ስለሚታመን ነው። ከንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ አፅም ትንሽዬ ቅንጣቢ በአንገቱ አሥሮ የነበረው በላይ ዘለቀ ወራሪውን የጣሊያን ጦር በኢትዮጵያ ተራሮች ላይ ቆሞ ሲዋጋ አንድም ጥይት ሊገድለው አልቻለም። እመነኝ። እኔ ለጥቂት ቀናት ከበላይ ዘለቀ ጋ ተሰልፌ ጣሊያንን ስዋጋ ይህን አይቻለሁ። በላይ ዘለቀ የንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብን አፅም ሸራፊ በአንገቱ አሥሮ ነበር። ያለምንም ምሽግ ያለምንም ተገን ተራራ ላይ ቆሞ ዘመናዊ መሣሪያ እስከ አፍንጫው የታጠቀውን የጣሊያንን ጦር መድረሻ ያሳጣበት ምክንያት ይህ ነው። በዳጋ ቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም የሚገኘውን

የንጉሥ አፄ ዘርዓ ያዕቆብን አጥም ሄደህ ማየት ትችላለህ። አጥሙ ጎደሎ ነው። ቁጠርና ውሸታም በለኝ።»

«ባክህ! በላይ ዘለቀ ሲፈጠርም ጀግና ሆኖ ስለተፈጠረ ነው።»

«ጀግና አይደለም አላልኩህም እኮ። ጀግናማ ጀግና ነው። ይህን ማድረጉ እኮ ጀግንነቱን የሚያጉላ እንጂ የሚያደበዝዝ አይደለም። ጥበበኛ መሆን በራሱ ጀግንነት ነው። ይህንን ጥበብ ለግል ጥቅሙና ለዝርፊያ አለመጠቀሙ ነው የበለጠ ጀግና የሚያደርገው። ጀግና ነው። አፅሙን ለምን እንዳሰረው ጠንቅቄ አውቃለሁ። የቅርብ ጓደኛውም ነበርኩ። እሱ ጫካ ውስጥ ጣሊያንን ሲዋጋ እኔ የጣሊያንን የጦርና የዕቃ መርከቦች በጣና ሐይቅ ላይ እነዳ ነበር። የጣሊያን መርከብ ካፒቴን ሆኜ የጣሊያንን ውስጠ ምስጢር ለአርበኞች የማቀብል የውስጥ አርበኛ ነበርኩ። ከበላይ ዘለቀ ጋርም የተገናኘው በዚህ ወቅት ነበር። እንዲያውም የዘርዓ ያዕቆብን አፅም የሚያገኝበትን መንገድ ያመቻቸሁለት እኔ ነበርኩ።»

«እስቲ እንግዲያ ለእኔም ስጠኝና ያንን ፊንሐስ የሚባል አንጥረኛ እናቴን እንዳነደዳት ከአለበት ፈልጌ ላንድደው?» ዲምላ ድንገት ደሙ ሲፈላ ታወቀው።

«አስጨርሰኝ ይልቅ እሱን ለእኔ ተወው። እንዳልኩህ በላይ ዘለቀ ያንን ጥበብ ስለተጠቀመ ንጉሡ ከስደት ተመልሰው አለመግባባት ሲፈጠርም በንጉሡ ጦር በተከፈተበት ተኩስ አልወደቀም። ታስሮ የእስር ቤቱን ባለጠመንጃ ዘቦች ባዶ እጁን ገድሎ ሲወጣ ማንም በጥይት ሊያስቆመው አልቻለም። በመጨረሻ በስቅላት አንገቱ በገመድ ታንቆ ባደባባይ የተገደለበት ምስጢርም በጥይት መሞት ስለማይችል ነው።»

«ለእኔም ስጠኝ አልኩህ! አለበለዚያ አትዘብዝብብኝ!»

«ላንተማ ልብ የለህም እንጂ ልብ ካለህ የምሰጥህ ከዚህ የበለጠውን ምስጢር ነበር። ግን ልብ የለህም። ልበ ቢስ!»

በሌላ ቀን አለቃ አያሌው ለዘመናት ደብቀውት የኖሩትን ምስጢር ጫፍጫፉን ነገሩት። ከ1933 ዓ.ም ጀምሮ ሲሰደዱለት የኖሩትን ምስጢር! በተለይ በ1961ዓ.ም ማንም እንዳያገኘው አደርገው የቀለፉትን ምስጢር ቁጢት ሲያስይዙት ዘሎ ተጠመጠመባቸው። «አባቴ የሆንከው ገና አሁን ነው። እስከ አሁን እጠላህ ነበር አሁን ግን! ...ግን ለማንም ከእኔ በቀር እንደማትናገር ቃል ግባልኝ!» ሲል ዲምላ ሙቤ ረገጠ።

ዲምላ አባቱ አለቃ አያሌው ወደ ጣልያኖች የኤሌክትሪክ ሱቅ መምጣት ከሚያዘወትረው ሻጊዝ እጅጉ ጋር አፍ ለአፍ ገጥመው የሚያወሩት ነገር አላስደሰተውም። እንዲያውም ምስጢሩን ለሻጊዝ ይነግሩብኛል ብሎ ከተጠራጠረ ሰንብቷል። አለቃ አያሌውና



ሻጊዝ እጅጉ አብረው በተቀመጡ ቁጥር መብገን ጀመረ። የውስጡ ቃጠሎ እየነደደ መጣ። ሻጊዝን አንቆ ለመጣል ተመኘ። ግን ሻጊዝን አንቆ ቢጥል አባቱ ለሌላ ሰው ምስጢሩን ላለማሳለፋቸው ዋስትና የለውም። ስለዚህ ዋናው አማራጭ የምስጢሩን ባለቤት ማጥፋት ሆኖ አገኘው። አባቱን ማስወገድ! .....ወሰነ። ይህ ታላቅ ምስጢር የግሉ ሆኖ የሚቀረው አባቱን ሲያስወግድ ብቻ እንደሆነ አመነ። አለበለዚያ ከአባቱ ጋር ቁጭ ብሎ ያወራውን ሁሉ ዕድሜ ልኩን ሲገድል መኖር አለበት። ስንቱን ገድሉ ይጨርሳል? አለቃ አያሌውን ለመግደል ሲወስን ያለማቅማማት ነበር።

በአንድ ምሽት አለቃ አያሌው ወደተኙበት ደሳሳ ጉጆ ሲገባ የሞርሞርዲኖን ሽጉጥ አቀባብሎ ነበር። በደሳሳዋ ጉጆ ውስጥ በኩራዝ መብራት የሚያነቡትን መፅሐፍ ሳያጥፉ ከጉጆዋ ወደ ገባው ልጃቸው ዞር አሉ አለቃ አያሌው። ፈገግ አሉ ።

«ልጄ መጣህልኝ!?» ልቡ ወደ እሳቸው እንደተመለሰ ተስፋ አድርገው። «ልጄ ያላንተ እኮ ማንም የለኝ! እስቲ ተቀመጥና አጫውተኝ እኔም የማጫውትህ ጉዳይ አለኝ።»

«ምን ታጫውተኛለህ ....ለእኔ የምታጫውተኝን ለሌላም ሄደህ ቱሽ ትላለህ።....አንተ ሆድ ውስጥ ምን ምስጢር ይቀመጥና!» ሽጉጡን መኸርጦ በግንባራቸው ላይ አነጣጠረባቸው። ዲምላ።

«ምነው ልጄ? ኧረ በስመአብ በል! ም....ምም.....ምን ነካህ ልጄ .... ም.......ም»

«በስማም? .....ሃ!ሃ!ሃ! ዳቦ ነህ አንተ በስማም ብዬ የምቆርስህ? ወይስ የፋሲካ በግ? ሰው በስማም ተብሎ አይታረድም የፋሲካ በግ እንጂ! ይህ ለፍላፊ ልሳንህ ካልተዘጋ ገና ብዙ ትለፈልፋለህ።»

«ተው እንጂ ልጄ.....ተ....ተ.ተ.ተ.....ተተተ........»

«ለኔ ያወረስከኝ አንዳች ነገር የለህም! ከዚህች ከነገርከኝ ነገር በቀር። እስኪ ምን ወረስኩ ከአንተ አባትነት? እ? ወይኔ ከርታታው ዲምላ! ከዚህች ከነገርከኝ ምስጢር በቀር ምን አወረስከኝ? እሷን ባይሆን የእኔ ማድረግ ያለብኝ አይመስልህም? እሷን ባይሆን....እሷን!..... ግን አፍህ ወንፊት ነው። አፍህ እንደወንፊት አይቋጥርም። እንደ ወንፊት የሚያፈስ አፍ ካለህ የተናገርከው ምስጢር መልሶ ያጠፋሃል። ሃ! ሃ! ሃ! ይቅርታህን አለምንም። ከአንተ የምፈልገውን አግኝቻለሁ። እንድትረግመኝም እንድትመርቀኝም አልፈልግም።» በሽጉጡ ውስጥ ተቀባብለው የነበሩትን ጥይቶች በሙሉ ጭንቅላታቸው ላይ አርከፈከፈባቸው። የሆነ ነገር ሊናገሩ አፋቸውን እንደከፈቱ ገልጠው ከሚያነቡት መጽሐፍ ገፅ መሀል በደም ተጨማልቀው ከንብል አሉ።

ዲምላ ምስጢሩን ለሌላ እንዳይነግሩብኝ ብሎ አባቱን በገደለ ማግስት ተፀፀተ። መጠየቅ የሚገባውን ጥያቄ ጨርሶ ሳይጠይቃቸው ቸኩሎ ነበር እንደ ገደላቸው የገባው በኋላ ነው። የምስጢሩን ጫፍ ነገሩት እንጂ ሙሉ በሙሉ እንዳልነገሩት ቆይቶ የገባው። በንዴት ተቃጠለ።በይደር ሲነግሩት ያስቀመጡት ነገር ነበር። የተከፈተው መንገድ መልሶ ተዘጋበት። አባቱን በመግደል ወንጀል ተከሶም ወህኒ ተወረወረ።

በሞርሞርዲኖ ቡስኪ እገዛ ከአሰቃቂው እስር ቤት አምልጦ ከሞርሞርዲኖ ቡስኪ ቤተሰብ ጋር ወደ ጣሊያን ኮበለለ።ሲሲሊ እስከ ጥልፍልፏ ተቀበለችው። እስከ አሁን የኖረውም የሞርሞርዲኖን ትከሻ ሲጠብቅ ነው። ዕድሜ ልኩን።

ከዘመናት በኋላ አባቱ ሲነግሩት ጫፍ ያስያዙት ምስጢር ከጣሊያን ወረራ በኋላ ኢትዮጵያ የቀረው የቡስኪ ቤተሰብ እርስ በእርሱ ሲገዳደል የኖረበት ምክንያት መሆኑ ገባው። ሞርሞርዲኖን ያህል የሲሲሊ ጌታ ለተራ ነገር ብለው ወደዚህች የዓለም ጭራ ወደሆነች ደሀ ሀገር እንደማይመጡም እርግጠኛ ነው።

በመሆኑም የዚህን ምስጢር ክር እንደገና ለመጨበጥ በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ውስጥ የቀበሮ ባህታዊ ሆኖ ጓዳ ጐድጓዳውን እያነፈነፈ ይገኛል። ቀለሙ እንጂ ችሎታው እንዳላስመረጠውም ያውቃል። ዶን ሞርሞርዲኖ ከስንት ነፍሰ በላ ማፍያዎቻቸው መሀል የመረጡት የሀገሩን ስርዶ በሀገሩ በሬ ለማረስ ነው። ባለ ጥቁር ቆዳው ዲምላ ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ብቻ ከኢትዮጵያውያን መነኮሳት ጋር በቀላሉ ተደባልቆ የሚፈልገውን ቋጠሮ ለመመንተፍ አማራጭ የሌለው ሰው ነው። አሁን ተልዕኮውን ለመፈፀም ራሱን አመንኩሶ በዳጋ ገዳም ውስጥ የበቃ መነኩሴ መስሏል። ነፍሰ በላው መነኩሴ አባ ዲምላ በቢጫው የምንኩስና ልብስ ተኮፍሰዋል።

አባ ዲምላ አባታቸውን በማጥፋታቸው ሳይሆን አባታቸውን ሳያናዝዙና የምስጢሩን ቁልፍ በእጃቸው ሳያስገቡ በመግደላቸው ፀፀት እንደ ፍላፃ ልባቸው ላይ ተተክሎ አልነቀል ብሏቸዋል። በሌላ በኩል ምስጢሩን ቢያገኙት እንኳ ለዶን ሞርሞርዲኖ አሳልፈው ከመስጠት ባለፈ የእርሳቸው እንደማያደርጉት ተሰማቸው። ዓይን የማያዞሩት የሞርሞርዲኖ ጋርዶች ምስጢሩ እንደ ተገኘ እንደ ጉንዳን እንደ ሚወሯቸው ጥርጥር የላቸውም። ደሞም አንድ ነገር ተገለጠላቸው። አባታቸው የነገሯቸውን ያስታወሱት የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ አፅም እቃ ቤቱ ውስጥ በመስታዎት ሳጥን በክብር ተቀምጦ ያዩት ዕለት ነው። አባታቸው እንዳሉትም ከአፅሞቹ መሀል የተወሰነ ነገር እንደጐደለ በጣም ወደ መስታውቱ ሳጥን ተጠግተው አረጋግጠዋል። በመሆኑም ከዚህ አፅም ትንሽ ሰባሪ ለማግኘት ዕቅድ አወጡ። ግን እንዴት አድርገው? በገዳሙ ውስጥ ያሉትን የዋህ



መስለው ጠቢብ የሆኑ መነኮሳትን እንዴት መጋፈጥ ይችላሉ? እንደ ዓይን ብሌን ወደሚጠበቀው ዕቃ ቤትስ ማን ያስደርሳቸዋል? ከንጉሥ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ አፅም ትንሽ ስባሪ ቢያገኙማ የእሳቸው ህልም ብዙ ነበር።

ይህንን አፅም በአንገታቸው ካሰሩ የፈለገ ዓይነት ጥይት ቢተኮስባቸው ገላቸው ላይ እንደውሃ እየፈሰሰ ሲወርድ በሀሳባቸው ታያቸው። የጥይት እርሳሶችን እንደዝንብ እንኳ ሳይቆጥሩአቸው ዝም ብለው ሥራቸውን ሲሰሩ።ወላ መትረዬስ ወላ ክላሽንኮቭ ወላ ዲሞትፈር ወላ ዲሽቃ ሚሳዬልም ቢሆን ቢተኮስባቸው ዝንባቸውን እንኳ ማስነሳት እንደማይችል እርግጠኛ ሆኑ። በጉልበታቸው ደግሞ ይተማመኑበታል። እንኳን መነኩሴ መልአክ አድቅቆ የሚጥል ክንድ ባለቤት መሆናቸውን መጐናፀፊያቸውን ሰብስበው ጡንቻውን ቁጥር አድርገው አዩት። የተከመረ ጡንቻቸውን ሳሙት። ይህ ከሆነ ለዘመናት የተቀበረውን ምስጢር ፈልፍሎ ለማግኘት ማንም እንደማያስቆማቸው አሰቡ።ይህንን ምስጢር እንዳገኙም ሞርሞርዲኖ ቡስኪን እፍንጫህን ላስ ይሉታል። ምክንያቱም የሞርሞርዲኖን ጋርዶች በሲሲሊ ተራራዎች ላይ ቆመው ዓይቀጡ ቅጣት እንደሚሰጧቸው በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ አፅም እርግጠኛ ናቸው። ከዛም በእልም ዙሪያ ያሉት የሞርሞርዲኖ ካምፓኒዎች ባለቤት ለመሆን ማንም ምንም አያግዳቸውም። በዚህ ገዳም ውስጥ የሚፈልጉት ምስጢር ብቸኛ ባለቤትም ይሆናሉ። ይህ ካልሆነ የሞርሞርዲኖ ዘላለማዊ ባሪያ ከመሆንና ከመበዝበዝ የሚታደጋቸው መተማመኛ የላቸውም። በዛ ላይ ጉልበታቸው ከደከመ ተመልሶ ድህነት ሽምጥ እንደማይጋልባቸው በምን እርግጠኛ ይሆናሉ? አፅሙን የሚያገኙበትና ምስጢሩንም የሚፈልጉበትን መንገድ እያሰላሰሉ ወደ ዕቃቤቱ ተነስተው ገሰገሱ።

# ፲፯

የፀደዩ አበባዎች በኢትዮጵያ ተራራዎች ላይ ከስመዋል። የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ደሴት ዛፎች ግን በልምላሜ እንዳሸበረቁ ናቸው። 1997 ዓ.ም። እንደ ገና የክረምቱ ወራት መጣ። ሰኔም ብቶ ነበር። ወቅቱም በኢትዮጵያ ገዳማት ውስጥ ከመቼውም ጊዜ በላይ ፀሎት በዝቶበት ነበር። በሀገሪቷ ውስጥ የተደረገውን ምርጫ ተከትሎ በተቀሰቀሰው ግርግር ሀገሪቷ ወደመጠፋፋት እንዳታመራ መነኮሳቱ ተንበርክከው እያለቀሱ ነበር።

በዚህ ገዳም ውስጥ ሬዲዮ ማዳመጥ ክልክል ቢሆንም አንድ መነኩሴ ግን አሻፈረኝ ብለው ባህር ዳር ከተማ በመሄድ ሬዲዮ ገዝተው መጡ። ትንሿን ሬድዮ ከበው የሚያመሹ መነኮሣትም ተበራክተው ነበር። በየቀኑ ጥሩ ዜና አይሰሙም ። መነኮሳቱ ዘመናዊ ትምህርት የቀሰሙ መሆናቸው ከመቼውም ጊዜ በላይ የተሳበቀባቸውም በዚህ ጊዜ ነበር። የውጭ ሀገር ሬድዮዎች የሚያስተላልፉትን ዘገባ በእንግሊዝኛ እና በሌሎች ቋንቋዎች ያደምጡ ነበር። የጀርመን ድምፅ እና የአሜሪካ ድምፅ ሬድዮ ዜናዎች የማይታለፉ ነበሩ። «ከ1997ቱ የኢትዮጵያ ምርጫ በኋላ በተፈጠረው አለመግባባት ይህን ያህል ሰዎች ሞቱ። ይህን ያህል ቆሰሉ።»

«አልቅሱ መነኮሳት... ወጣት አለቀ!» ይላል አንዱ።

«ወጣት እንደ አይጥ ኮርኒስ ውስጥ እያደረ ነው ፀልዩ!» ይላል ሌላኛው።

«አባ ይህ ነገር ተገቢ አይደለም። ዝም ይበሉ። ወይ ለምን ሄደው ምርጫ አልተወዳደሩም? ልጠድቅ መጥቼ ኩነኔ ሊያስገቡኝ ነው እርስዎ ሰውዬ! ይተውኝ ሁለተኛ ፖለቲካ ሊያወሩኝ እንዳይመጡ። እሱን ራዲዎን ይዘውብኝ አይምጡ ብያለሁ እርስዎ ሰውየ....»

«መነኮሳት ለምን ድምጣቸውን እንዲሰጡ አልተደረገም?»

«መነኩሴ ምን ድምጥ አለው! ከውዳሴ ማርያም በቀር።»

«ድምጥዎትን ለማን ሰጡ አባ?»

«ለእግዜር» .........ሳቅ።

«ኧረ መነኮሣት ተዉ ይህ ነገር ገደል እንዳይከታችሁ? ይህ ሬዲዮ በምን ቀን መጣ? ማነው ያመጣው ግን? ይዞልን ይሂድ ይህን ሬዲዮ! አለበለዚያ ወደ ጣና ሐይቅ ነው የምወረውረው!» አንድ



የተበሳጨ መነኩሴ። «ቦለቲከኛ መሆን የፈለገ መነኩሴ ሂዶ ምርጫ መወዳደር ይችላል። እዚህ የመጣነው ልንጠድቅ ነው። ወቼ ጉድ!...ወይ እመብርሃን! መነኩሴው ሁሉ ቦለቲከኛ ሆነልሽኮ።»

«ዛሬ ጠዋት ፀሎት ሳላደረስኩም ማለት ይቀላል። የምርጫው ነገር መጥቶ ይሰነቀርብኛል። እባካችሁ ይህ ሬዲዮ ይሰበር......» በሬዲዮው ላይ ግን ማንም ለመስበር የጨከነበት አልነበረም።

«አባ ገብረ እግዚዕ.... ያኔ የኢትዮጵያና የኤርትራ ጦርነት ጊዜ የኢትዮጵያ ቦንብ ጣይ አውሮፕላኖች ጣና ሐይቅን በክንፋቸው እዩሰነጠቁ ወደ ሰሜን ሲወነጨፉ ከዳጋ አናት ላይ ካለው ዋርካ ወጥተው "ገደሏቸው! ፈጇቸው!" ሲሉ የነበር... ኤርትራዊነታቸው አለቀቃቸውም እንዴ? ምነው እንግዲያ አሁን ዝም አሉ.... የኢትዮጵያ ጉዳይ አያገባቸውም?»

«ኧረ ዝም በል! እርሳቸው በኤርትራዊነት አያምኑም። የእርስ በእርሱ ጦርነት አሳስቧቸው ይሆናል እንጂ። ይኸው ኢትዮጵያን ሙጥኝ ብለው.. ኢትዮጵያ ናት ሀገሬ እያሉ አይደል እንዴ እዚህ የቀሩት!? እነ ዘርዓይ ደረስ የሞቱላት ሀገር ኢትዮጵያ ናት ኤርትራ አይደለችም! እነ ራስ አሉላ ...አሉላ አባነጋ የምፅዋው የእሳት በር ....የኢትዮጵያው አጥር.... ሲጠብቃት የኖረችው ሀገር ኢትዮጵያ አይደለችም ወይ? ደቡብም ተወለድ ሰሜን ምስራቅም ተወለድ ምዕራብ ግድ የለኝም። ዘርህን እዚህ ገዳም ውስጥ የጠየቀህ ካለ ንገረኝ። ማንም ዘርህን አልጠየቀህም። ኤርትራ ውስጥ ብትወለድና እትብትህ እዛ ቢቀበር እትብትህን የበላው ምስጥ ግን ደቡብ ኢትዮጵያ ላለመገኘቱ እርግጠኛ አትሁን። ጋምቤላ ተወለድ። እትብትህን ጋምቤላ ውስጥ የበላው ምስጥ ግን አፋር ላለመድረሱ እርግጠኛ አትሁን። ለምን ከምስጡ ለመሻል አትሻም? ለምን ትጠባለህ?.......ሰፊ አገር እያለህ ለምን ጠባብ ክልል አገርህ እንዲሆን ትመኛለህ?...አህያ እንኳ ጋጣው ሲጠበው ይራገጣል። አትጥበብ። የማያሳፍርህ ነገር ቢኖር በኢትዮጵያዊነትህ ማመንህ ብቻ ነው። በቃ።»

«ዘርንና ጐሣን ተመርኩዘው የሚመሠረቱ የፖለቲካ ፓርቲዎችን መምታት ነው... በቃ። የአገሌ ዘር ፓርቲ የዕገሌ ዘር ፓርቲ እያሉ ህዝቡን የከፋፈሉት እነሱ ናቸው። ኢትዮጵያ ውስጥ እኮ ስድስት ሰዎች ብቻ ያሉት ብሔረሰብ አለ። እስኪ ይታዩዎት አባ? ከእነዚህ ስድስት ሰዎች ብቻ ካሉት ብሔረሰብ መሀል ኢትዮጵያን ለመምራት የሚችል አእምሮ ያለው ሰው ቢነሣና ቢመራት ምንድነው ችግሩ? ምንም። እኔ እቀበላዋለሁ። ኢትዮጵያን ለመምራት ዘር ሳይሆን ጭንቅላት መመረጥ አለበት! ....ጥሩ መሪ ሁልጊዜም ጥሩ ተከታይ አለው።»

ቃል ጕን ፃፉት፡፡ *«ዳጋ ከቤተ ልሔም ኮረብታ.........»* ፈገግ አሉ፡፡ «እህ?» ሌላ ስንኝ ነቀሱ፡፡ 10ኛውን፡፡

$10_{6}$.....10ኛው ስንኝ 6ኛው ቃል፡፡

*«ቀና ብላ እውነት እንዳታይ አንገቷን ቁልቁል ጠምዝዟት»* ስድስተኛውን ቃል ወሰዱት፡፡

"*ቁልቁል*" የሚለውን፡፡ *«ዳጋ ከቤተልሔም ኮረብታ ቁልቁል.......»* ስደራው ቀጠለ፡፡ ካርታው ነፍስ እየዘራበት መጣ፡፡ ቀጠሉ፡፡ የነብሩን ጅራት ይዘው እንዴት ሊለቁ ይችላሉ?

$29_{23}$........29ነኛው ስንኝ 2ኛውና 3ኛው ቃል፡፡ *«በጋው የእረኛ አደባባይ፤ ክረምት እንደወንዙ ፍሳሽ »* ሁለተኛውና ሶስተኛው ቃል«የእረኛ አደባባይ» ባንድ ላይ ነው፡፡ ከሚደረድሩት ቃላዊ ካርታ ጐን ፃፉት፡፡ *«ዳጋ ከቤተልሔም ኮረብታ ቁልቁል የእረኛ አደባባይ........»* ካርታው እየረዘመ መጣ፡፡

$77_{5}$........77ኛው ስንኝ 5ኛው ቃል፡፡ *«ቺጋር ከጐጆዋ ገፍቶ አግፏ ግርጌ ሲጥላት»* ከሚለው ስንኝ ውስጥ *«ግርጌ»* የሚለው 5ኛ ቃል ካርታው ጋር ሲፃፍ *«ዳጋ ከቤተልሔም ኮረብታ ቁልቁል የእረኛ አደባባይ ግርጌ........»* ይሆናል፡፡

$38_{456}$....30ኛው ስንኝ 4ኛው፣5ኛውና 6ኛው ቃል፡፡ 38ኛውን ስንኝ አነበቡት፡፡ *«በገጠር የደመና ዳስ፤ በገደል ሽለቆ አዳራሼ»* ይላል፡፡ ከዚህ ስንኝ ውስጥ 4ኛው 5ኛውና 6ኛው ቃላት «በገደል፣ ሸለቆ፣ አዳራሽ» የሚሉት ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት ካርታው «ዳጋ ከቤተልሔም ኮረብታ ቁልቁል የእረኛ አደባባይ ግርጌ በገደል ሸለቆ አዳራሽ.......»ሆኖ ተሰጠጠ፡፡

$52_{7}$...52ኛው ስንኝ 7ኛው ቃል፡፡ *«ከዜማ ቤት እቅኔ ቤት ከድጓ ቤት እመፃሕፍት»* 7ኛው ቃል እዚህ ስንኝ ውስጥ *«እመፃሕፍት»* የሚለው ነው፡፡ አባ ሚራዥ ተፍነከነኩ፡፡

*«ዳጋ ከቤተልሔም ኮረብታ ቁልቁል የእረኛ አደባባይ ግርጌ በገደል ሸለቆ አዳራሽ እመፃሕፍት.....»* ካርታቸውን ሰድረው ወደሚቀጥለው ቁጥር ተመለከቱ፡፡

$33_{2}$.......33ኛው ስንኝ፡፡ *«ከፍልፈል ጋር ሩጫ ስገጥም ከቀበሮ ድብብቆሽ»* ይላል፡፡ ከዚህ ስንኝ ውስጥ 2ኛው ቃል *«ጋር»* የሚለው ነው፡፡ ካርታው ጋር አዋቀሩት፡፡

*«ዳጋ ከቤተልሔም ኮረብታ ቁልቁል የእረኛ አደባባይ ግርጌ በገደል ሸለቆ አዳራሽ እመፃሕፍት ጋር.......»* እዚህ ላይ ግር አላቸው፡፡ ፮፮፮ የሚሉት ቁጥሮች ትርጉም ምንድን ነው፡፡ ለጥቂት ደቂቃዎች እነዚህ ቁጥሮች ላይ አትኩረው ሲመለከቱ ቆይተው ምንም ፍንጭ ስላላገኙ ቁጥሮችን ወስደው ከካርታው ጐን ፃፏቸው፡፡



*«ዳጋ ከቤተልሔም ኮረብታ ቁልቁል የእረኛ አደባባይ ግርጌ በገደል ሸለቆ አዳራሽ እመፃሕፍት ጋር ፮፮፮......»* ወደ ሚቀጥለው ቁጥር ተሻገሩ፡፡

975...... 97ኛው ስንኝ ምን ይላል?..............*«ኩርትም ብዬ እችልበት፤ እሸሸግበት አይጠፋም፡፡»* እዚህ ስንኝ ውስጥ 5ኛው ቃል *«አይጠፋም»* የሚለውን ወስደው ከካርታው ጋር ደረደሩት፡፡

*«ዳጋ ከቤተልሔም ኮረብታ ቁልቁል የእረኛ አደባባይ ግርጌ በገደል ሸለቆ አዳራሽ እመፃሕፍት ጋር ፮፮፮ አይጠፋም፡፡»* ካርታው ክርችም ብሎ ሞላ፡፡ ...አባ ሚራዥ እመር ብለው ተነስተው ዘለሉ፡፡ እነዚህ የተጠቀሱት ቃላት ሁሉ የተቀመጡበትን የዳጋ እስጢፋኖስን ደሴት የሚገልፁ ቃላት ናቸው፡፡......እኒህ ሁሉ ቃላት «ሰቆቃወ ጴጥሮስ» ከሚለው የሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን ግጥም ውስጥ ተፈልቅቀው የወጡ ናቸው፡፡ ‹አስገራሚ ምስጢር፡ አስገራሚ ቅኔ፡ ዘይገርም ካርታ....› አባ ሚራዥ ተደነቁ፡፡ ‹ይህን ምስጢር ነበር ለካ ከጀርባየ ተሸክሜው የኖርኩት! ይህን ምስጢር ነበር ለካ ይህን ቅኔ ነበር ለካ ሳልፈታው የኖርኩት! አሁንም ግን ቅኔውን ሙሉ በሙሉ አልፈታሁትም፡፡ ጂራቱን ነው ገና የያዝኩት› ዳጋ የተቀመጡበት ደሴት ነው፡፡ ከቤተ ክርስቲያኑ በስተምሥራቅ ኮረብታው ላይ የተሰራውን ቤተልሔም ያውቁታል፡፡ ቁልቁለቱም ሲመላለሱበት የከረሙበት ቁልቁለት ነው፡፡ የእረኛ አደባባይ እየተባለ በድሮ ጊዜ የሚጠራው ደግሞ የዕቃ ቤቱ ጠባቂ የሚቀመጡበት የመጠበቂያ ቤት እየተባለ የሚጠራው ነው፡፡ ‹በካርታው መሰረት እንግዲህ ከዚህ የመጠበቂያ ቤት ወይም በድሮ ጊዜ የእረኛ አደባባይ ተብሎ ከሚጠራው ቤት በታች የገደል ሸለቆ አለ ማለት ነው፡፡ በሸለቆው ውስጥም አዳራሽ፡፡ በዚህ አዳራሽ ውስጥ ከሚገኙ መፃህፍት ጋር ፮፮፮ አይጠፋም ማለት ነው› ሲሉ አሰቡ፡፡ ፮፮፮ ምን እንደሆነ ባያውቁትም ፡፡

በደረቀው ሌሊት ከበአታቸው ወጥተው ሽቅብ ወደኮረብታው እየተጣደፉ ወጡ፡፡ ከዕቃ ቤቱ የግንብ አጥር በር አጠገብ ቆመው በበሩ ማጮለቂያ ወደ ውስጥ ተመለከቱ፡፡ የዕቃ ቤቱ ጠባቂ ከእረኛ አደባባዩ ቤት ውስጥ አይታዩም፡፡

ከኋላቸው የሰው እጅ ትከሻቸውን ሲነካቸው ተርበትብተው ዞር አሉ፡፡ የዕቃ ቤቱ ጠባቂው ናቸው፡፡ እዩተከታተሉአቸው ነበር፡፡ የዕቃቤቱን ግቢ በር ከፍተው ወደ ውስጥ ይዘዋቸው ገቡ፡፡ «እንኳን ደስ አለህ ዶ/ር ሚራዥ» አሉ የዕቃ ቤት ጠባቂው ወደ መጠበቂያ ቤቱ ይዘዋቸው እየገቡ፡፡ «ፈተናውን በብቃት አልፈሀል» ሚራዥ ደነቀው፡፡ የዕቃ ቤቱ መጠበቂያ ቤት ውስጥ የሚንቦገቦጉት የመቅረዙ መብራቶች የወለሉን ቀይ ምንጣፍ አመድ አልባ ፍም አስመስለውታል፡፡

በእውኑ እንዲሆን በልቡ ፀለየ። በእንቅልፍ ልቡ ከሆነም ከእንቅልፉ እንዳይነቃ ፈጣሪውን ተማጠነ።

ተዘጋግተው የነበሩት ሁሉም በሮች ተከፍተው ከየክፍሉ በወጡት ብዙ ሰዎች በመሀል የሚያልፈው ሰፊ የአስፋልት መንገድ ተጥለቀለቀ። ሁሉም በጭብጨባ ዋሻውን አደመቁት። ሁሉም ሰዎች አንድ ዓይነት ቀይ ቀሚስ ለብሰዋል። ሁሉም በአንድ ድምፅ «ዴርቶጋዳ!» አሉ። «ዶ/ር ሚራዥ እንኳን ደህና መጣህ» ድምጻቸው በዋሻው ውስጥ የገደል ማሚቶ ደጋግሞ አስተጋባ። «ዴርቶጋዳ...ዴርቶጋዳ....ዴርቶጋዳ....ዴርቶጋዳ....»

ጭብጨባው ጋብ ሲል አንድ በር ተከፍቶ ረጅም ጢም ያላቸው ሽማግሌ ወጥተው ወደ አደባባዩ አመሩ። «ወንድማችን ዶ/ር ሚራዥን በደስታ ስለተቀበላችሁት እናመሰግናለን.....» ድምፃቸው ይንቀጠቀጣል። ከደስታቸው ብዛት እንደ ህፃን እየተፍለቀለቁ ነበር። ሽማግሌው መነኩሴ አባ ዠንበሩ መሆናቸውን ለመለየት አፍታ አልፈጀበትም። አባ ዠንበሩ ከአደባበዩ ወርደው በቀዩ ቀሚስ ውስጥ ቦርሰስ ቦርሰስ እያሉ ወደ እሱ ሲመጡ ከየክፍሉ ወጥተው የነበሩት ሰዎች ተመልሰው ገቡ። አንድ ሰው ግን ከመግባቱ በፊት እጅን አውለበለበለትና ወደእሱ መጥቶ አቀፈው። ዶ/ር ዠንጊዳ ነበር። ተጠመጠመበት። «ሚራዥ እንደገና በመገናኘታችን ደስ ብሎኛል።» አባ ዠንበሩም አቅፈው ከሳሙት በኋላ ዶ/ር ዠንጊዳ የምድር ውስጡን ምስጢራዊ ከተማ እንዲያስጎበኘው ነግረውት ወደ ቢሮአቸው ገቡ።

ሚራዥ በዠንጊዳ ገለፃ እየተመራ የዋሻውን የምድር ውስጥ ከተማ መጎብኘት ጀመረ። «ዴርቶጋዳ የትምህርትና ስልጠና ክፍል» የሚል ጽሑፍ ወደ ተሰቀለበት በር ሲደርሱ በሩን ዶ/ር ዠንጊዳ የኮድ ቀጥሮቹን ነክቶ ከፈተው።

«ይህ ክፍል.....» አለ ዶ/ር ዠንጊዳ ማብራሪያውን ሲጀምር። «ዴርቶጋዳ ትምህርትና ስልጠና የሚሰጥበት ክፍል ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ በምህንድስና በህክምና እና በሌሎች የትምህርት ዘርፎች ስልጠና የሚሰጥበት ነው። በውስጡ ባሉት ልዩ ልዩ የትምህርት ክፍሎች የሚሰለጥኑ ብዙ አባላት አሉ» እየተዟዟሩ ሲያስጎበኘው ቆይቶ ሰፊውን ክፍል ለቀው ሲወጡ በሩ ተመልሶ በራሱ ተዘጋ።

«ዴርቶጋዳ የጥናትና ምርምር ክፍል» የሚል ጽሑፍ ወደ ተሰቀለበት ክፍል ገብተው ዘመናዊ ኮምፒውተሮችና ረቂቅ የምርምር መሣሪያዎች የታጨቁበትን ማዕከል አስጎበኘው። በልዩ ልዩ ምርምር ላይ የተጠመዱትን ተመራማሪዎችም በየክፍሉ እየወሰደ አስተዋወቀው።



ከዚህ ክፍል ወጥተው የህክምና ማዕከሉን ሲያስጎበኘው ደግሞ የበለጠ ተደመመ። ዓይቷቸው በማያውቅ የህክምና መሣሪያዎች የተጨናነቀውን ሆስፒታል ሲመለከት እጅግ ተገረመ። ውስጡ በነጭ ቀለም የተቀባው የህክምና ማዕከል ሁሉም ነገር የተሟላለት ነው። ከቀላል እስከ ከባድ ቀዶ ጥገና የሚሰጥበትን የቀዶ ጥገና ክፍል እየተዘዋወረ ጎብኝቶ የሚቀጥለውን በጉጉት ለማየት ወጣ።

የመረጃና ደህንነት ክፍል መምሪያ ውስጥ ሲገቡ «ኮሎኔል ፍስሐ የዴርቶጋዳ የመረጃና ደህንነት ክፍል መምሪያ ሀላፊ» በማለት ሽበት ጣልጣል ያደረገባቸው ቆፍጣና ሰውዬ እጁን ጠበቅ አድርገው ጨበጡት። «እንኳን ደህና መጣህ ዶ/ር ሚራዥ» .....ሰውዬውን ከዚህ ቀደም አይቷቸው ያውቃል።.... አስታወሳቸው። አሜሪካ ውስጥ እያለ በሎሳንጀለስ የፓስፊክ ውቅያኖስ ዳርቻ ጊታሩን የሰጡት ሰውዬ ናቸው። «ኮሎኔል ፍስሐ ይባላሉ። የሚሳየል ሳይንቲስት ሲሆኑ አሜሪካ ውስጥ የጀመሩትን የረጅም ርቀት ተምዘግዛጊ ሚሳየል ፎርሙላ ጠረጴዛው ላይ ጥለው የመጡ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ናቸው። ኢትዮጵያ በሚለው ቅጽል ስማቸው ብትጠራቸውም ቅር አይላቸውም። እንዳንተና እንደ ሌሎቹ ብዙ ሳይንቲስቶች በኢንጂነር ሻጊዝ ተመልምለው የተላኩ ናቸው። ይህ ሁሉ የሆነው በሻጊዝ ነው። ገና እዛ የሚሠራ ጉዳይ ስላለ እንጂ በመጨረሻው ሰዓት እሱም ይመጣል» ባድናቆት ራሱን ነቅንቆ እንደገና ጨበጣቸው።

«ይህ ሁሉ ገና ጅማሮ ነው» ብለው ፈገግ አሉ ኮ/ል ፍስሐ። ክፍሉ ግዙፍ በሆኑ ኮምፒውተሮች የተሞላ ነው። ትላልቅ ስክሪኖች ላይ በዓለም ዙሪያ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ምስል ብልጭ ድርግም ይላል። ከወደ ውስጥ አንድ ሌላ ግርማቸው የሚባል ወጣት መጥቶ ተዋወቀው።

ወደ ሚቀጥለው ክፍል ሲገቡ ሙሉ በሙሉ ሽበት የወረራቸው ፊታቸው ግን ወጣት የሚመስል ሰውዬ ከወንበራቸው ተነስተው «ጀነራል አጥናፉ ታዬ.... የዴርቶጋዳ መከላከያ ጉዳይ ዋና ሐላፊ...» ብለው ራሳቸውን አስተዋወቁት። በእጃቸው ቀጥሎ ወደ ሚታየው በር አመለከቷቸው። በሩ ሳይነኩት ተከፈተ። ኸው ያለው ሰፊ ክፍል አረንጓዴ የስልጠና ልብስ በለበሱ ወታደር መሰል ወጣቶች ተሞልቷል።

«ዴርቶጋዳ የምህንድስና ማዕከል» ወደሚለው ክፍል ሲገቡ ጌራ የሚባል ወጣት ቱታ እንደለበሰ ወጥቶ ሚራዥን ተዋወቀው። ቱታው በግሪስና በሞተር ዘይት ተጨማልቋል። ፊቱ ላይም ጥቋቁር የተፈነጣጠቁ ቀለሞች አርፈዋል። የብሎን መፍቻ በያዘበት እጁ ፊቱን ሞዥቆ ፈገግ ካለ በኋላ «.......ዶ/ር ሚራዥ ስለተቀላቀልከን

ልትደሰት ይገባል። ሁሉን ነገር የምትወደው ይመስለኛል። እርግጠኛ ነኝ ለዚህ ተልዕኮ በመመረጥህ ሳትደሰት አትቀርም»ሚራዥ ይህን ወጣት ለማስታወስ ጊዜ አልወሰደበትም። አባይ ማዶ የሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህንን ግጥም በቃሉ ያነበነበለትና «ገጣሚ» ነኝ ያለው ወጣት ነው። በፈገግታ ተግባቡ።

«ኢንጂነር ጌራ ይባላል። የጼርቶጋዳ የምህንድስና ክፍል አባል ነው።» ሲል ለሚራዥ አስተዋወቀው ዶ/ር ገነጊዳ።« በዚህ የምህንድስና ማዕከል ውስጥ ከብዙ ኢንጂነሮች ጋር በመሆን ጼC33 በመባል የሚጠሩ በራሪ ማሽኖችን የሰራ ባለብሩህ አእምሮ ወጣት ነው። ኢንጂነር ጌራ የአሜሪካ የጦር ኃይል አባል ነበረ።ምርጥ አብራሪም ጭምር። ከልዩ ልዩ የዓለማችን ሀገራት የምርመራ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ኢትዮጵያውያን ሳይንቲስቶችን ጼC33 በምትሰኘውና በጼርቶጋዳ ኢንጂነሮች ጥምረት በተሰራችው በራሪ ማሽን በማምጣት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረገ ፓይለት ነው።»

«እንግዲያውስ ጼC33ን በቅድሚያ ላስጎብኛችሁ» አለ ኢንጂነር ጌራ። «ጼC33...» ሲል ቀጠለ ገለፃውን። «ጼC33.... እንግዲህ ይህች የምታይዋት አውሮፕላን ናት። ይህች ማሽን፣ በኮምፒዩተር የሚታዘዙ ሆነው ወደ ውስጥ ወደ ውጭ የሚወጡና የሚገቡ ክንፎች ያሏት አውሮፕላን ናት። ክንፎቿ ወደ ውስጥ ሲገቡ የመኪና ቅርፅ ስለምትይዝ እንደ ሌሎች መኪናዎች በምድር ላይ ማሽከርከርና በከተሞች አውራ መንገዶች እንደልብ መጓዝ ትችላለች። የዚህችው ማሽን የመሽከርከሪያ ጎማዎች ወደውስጥ ሲገቡ ሙሉ አካሏ በአልሙኒየም ንጣፍ በቅጽበት ስለሚሸፈን ከአየር ወደ ውሃ ገብታ በውሃ ውስጥ መጓዝና ሰርጓጅ መርከብ መሆን ትችላለች። ስለዚህ ይህች ማሽን....... አውሮፕላን፣ መኪና እና ሰርጓጅ መርከብ ናት ማለት ነው። ዲዛይኗን ያወጣት የናሳው ኢትዮጵያዊ ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝ እጅጉ ነው። አሁን የያዘችውን ቅርፅ እንድትይዝ ግን የጼርቶጋዳ ኢንጂነሮች ሌት ተቀን ሠርተዋል። ጼC33 አውሮፕላን በየትኛውም ሀገር ራዳር ውስጥ የማያስገባ ቅብ ስለተቀባች ወደየትኛውም ሀገር በመብረር ከጼርቶጋዳ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሳይንቲስቶች ለማምጣት ረድታናለች» ብሎ የትልቁን መጋዘን በር ከፍቶ ጼC33ን የሚመስሉ ሌሎች መለስተኛ አውሮፕላኖችን አሳያቸው።

«በዚህ በር...» አለ ኢንጂነር ጌራ። ወደ በሩ እየተራመደ። «በዚህ በር ነው እነዚህ ሰርጓጅ መርከቦች የሚወጡ የሚገቡት። ከባህር ዳር ከተማ በተሰራውና በሌላ ሰው ስም በተከፈተው ጋራዥ በኩል የሚገቡ ብረታ ብረቶች፣ የምግብና ሌሎች የጼርቶጋዳ ቁሳቁሶች የሚመላለሱት በእነዚህ በጣና ውስጥ ለውስጥ በሚጓዙ አነስተኛ ሰርጓጅ መርከቦች ነው። በዚህ ዋሻ ውስጥ ላሉ የጼርቶጋዳ



አባላት የሚገቡ ማንኛውም ነገሮች የሚመላለሱትም በእነዚህ ሰርጓጅ መርከብ፣ መኪና እና አውሮፕላን መሆን በሚችሉ መጓጓዣዎች ነው። ማንኛውም ወደዚህ ዋሻ የሚገባና የሚወጣ የጼርቶጋዳ ቁሳቁስም ሆነ ሰው በነዚህ አነስተኛ መርከቦች አማካኝነት ነው» አውሮፕላኖች ከቆሙበት መጋዘን ፊት ለፊት ያለውን ሰፊ አውቶማቲክ በር እያመለከተው አብራራለት።

ድምፅ አልባ ጀነሬተሮች የተተከሉበትንና ሰፊውን ቤተመፃሕፍት ጨምሮ ልዩ ልዩ የጼርቶጋዳ ክፍሎችን ካስጎበኘው በኋላ መልሶ ወደ አባ ዥንበሩ ቢሮ ሲወስደው ሚራዥ እጅግ ተገርሞ ነበር።

ከትልቁ ጠረጴዛ ኋላ ትልቅ ወንበር ላይ የተቀመጡት ሽማግሌው አባ ዥንበሩ ሐጫ በረዶ የሚመስል ጢማቸውን እያፍተለተሉ ከፊት ለፊት ካለው ምቹ ወንበር ላይ እንዲቀመጥ ጋበዙት። «ግራ የተጋባህ ትመስላለህ.... » አሉት ከትንሽ ፀጥታ በኋላ። ዶ/ር ገነጊዳ ወደ ሥራው ተመልሶ ነበር።

«አዎን» አለ ዶ/ር ሚራዥ።

«ግራ ቢገባህ አልደነቅም። ብዙ አዲስ ምልምሎችም ግራ ስለሚጋቡ። .... ይህን የመሰለ ዘመናዊ የምርምር ማዕከል ከዚህ ኋላቀር ሀገር ውስጥ ማን ይጠብቃል? ለዚያውም በዚህ አልባሌ ደሴት ! ......» በረጅሙ ተነፈሱና ቀጠሉ።

«በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1933 ዓመተ ምህረት። በዚህ ወቅት የኢጣሊያ ወራሪ ጦር በኢትዮጵያና በእንግሊዝ ጥምር ጦር ከኢትዮጵያ ተባረረ።የኢጣሊያ ጦር ወደ አፍሪቃ ሲዘምት ግን አፍሪካን በሙሉ መቆጣጠር እንደሚችል እርግጠኛ ነበር። ለዚህም ከ40 ዓመት ዝግጅት በኋላ ኢትዮጵያን ዋና የቅኝ ግዛቱ ማዕከል ለማድረግ ጓዙን ጠቅሎ መጣ።» ዘመናዊዉ ጠረጴዛ ላይ ያለውን ኮምፒውተር ቁልፎች ሲጫኑ የኢጣሊያ ጦር ሲገባ የሚያሳዩ ፎቶዎች ግድግዳው ላይ ካለው ትልቅ ስክሪን ላይ መታየት ጀመሩ። «ኢጣሊያ በምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ ጦርነት ስትጀምር ሶስት መቶ ሃያ አምስት ሺህ ወታደሮች ነበሯት። ከነዚህ ውስጥ ሁለት መቶ ሺህ ያህል ወታደሮቿ አፍሪካውያን ባንዳዎች ነበሩ» ስክሪኑ ላይ የጣሊያንን ጦር ወታደሮች የሚያሳዩትን ፎቶ ግራፎች ቀና ብለው ተመለከተ።

ጥቋቁር ወታደሮች ከነጭ ወታደሮች ጋር ነፍጥ ይዘው ሲጓዙ የሚያመለክቱ ፎቶ ግራፎችን ትኩረት ሰጥቶ አያቸው። አባ ዥንበሩ ቀጠሉ።

«የኢጣሊያ መንግሥት ሀገራችንን ሲወር ከንጉሡ ስደት በኋላ አንዳንዱ በቁጭት ጫካ ገብቶ በአርበኝነት ተዋጋ። አንዳንዱ

ከጣሊያን ጦር ጋር ተቀላቅሎ ሀገሩን በዘበዘ። ባንዳዎች የኢጣሊያን ጦር እየመሩ አርበኞችን እያሳደዱ ሀገራቸውን አጥንቷ እስኪቀር አስጋጧት። ይህን ለማየት ችያለሁ። እኔ በዚያን ወቅት ጫካ አልገባሁም። አካኪ ዘራፍም አላልኩም። ዝም በዬ የጣሊያንን ጦር ተቀላቀልኩ። ተላላኪያቸውም ሆንኩ። ታማኝነትን ለማግኘት ጊዜ አልወሰደብኝም። ወዲያው በሜዲትራኒያን ባህር ላይ የመርከብ ትምህርት ሊያስተምሩኝ ወደጣሊያን ወሰዱኝ። መርከብ መንዳት ተማርኩ። ካፕቴን ሆኜ ወደ ኢትዮጵያ ተመለስኩ» የካፕቴንነት ማዕረግ ሲሰጡ የተነሱትን ፎቶ ግራፍ ስክሪኑ ላይ ተመለከተ።

«ወራሪው የኢጣሊያ ጦር ከሰሜን ኢትዮጵያ ወደ መሃል አገር በሚያደርገው ግስጋሴ የሰሜን ምዕራብ አካባቢዎችን በተለይም ጐጃምንና ጎንደርን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ያመቸው ዘንድ የማዘዣ ጣቢያውን ጐርጐራ ላይ አደረገ። በጣና ሐይቅ ሰሜናዊ ዳርቻ። መቀመጫውን ጐርጐራ ያደረገበትን ምስጢር ብዙ ሰዎች አያውቁም። ጐርጎራ ሆኖ ጐጃም ውስጥና በባህር ዳር አካባቢዎች ወደ ሚገኙ ጦር ሰፈሮች ስንቅና ትጥቅ ለማጓጓዝ በርካታ ጀልባዎችን በጣና ሐይቅ ላይ አሰማርቶ ይንቀሳቀስ ነበር። እኔንም የአንድ ትልቅ ጀልባ ካፕቴን አድርጐ ሾመኝ። ይህ ጀልባ በጣና ሐይቅ ላይ ይንሳፈፉ ከነበሩበት ጀልባዎች ሁሉ ግዙፉ ነበር። ጀልባ ከማለት ይልቅ መርከብ ብንለው ሳይሻል አይቀርም። በዕርግጥ ይህ መርከብ የመጣው በ1932 ዓመተ ምህረት ነበር። በጣና ሐይቅ ላይ የቆየውም ለጥቂት ጊዜያት ነው። በዛ ወቅት ሳኒኮላ፣ ሳንጆርጅ እና ሳንታማሪያ ከሚባሉት ጀልባዎች ሁሉ ግዙፍ የነበረው መርከብ እኔ እነዳው የነበረው ይህ መርከብ ነበር»

በ1932 ዓ.ም አካባቢ በጣና ሐይቅ ላይ ይታዩ የነበሩት ጀልባዎች ፎቶ ግራፎች ስክሪኑ ላይ ብቅ ብቅ አሉ። አባ ዠንበሩ ይነዱት ከነበረው መርከብ ላይ ከሁለት ሌላ ሐበሾች ጋር ቆመው የተነሱት ፎቶ ግራፍም ስክሪኑን ሞላው።

«እነዚህ ከእኔ ጋር ቆመው የምታያቸው ሰዎች አንዱ አለቃ አያሌው ነው አባ ዲዲሞስ። ሁለተኛውንም ታውቃቸዋለህ። አባ ፊንሐስ ናቸው። በ1933ዓ.ም የኢጣሊያ ጦር ከኢትዮጵያ ተባሮ በሚወጣበት ወቅት ብዙ ጉድ ተከስቷል። የኢጣሊያ ጦር ለወታደራዊ አገልግሎት ሲጠቀምባቸው የነበሩትን ሁሉንም ጀልባዎች ተባሮ ሲወጣ ጐርጐራ ወደብ አጠገብ በሚገኘውና ከፍተኛ ጥልቀት ባለው የሐይቁ ክፍል በአንጋራ ደሴት አስጥሟቸው ሄደ። እንዲያውም ጣሊያን ከኢትዮጵያ ከወጣ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ የቀረው ጣሊያናዊ ቤተሰብ ዋና አንቀሳቃሽ የነበረ ቡስኪ የሚባል ጣሊያናዊ በ1940 ዓመተ ምህረት ሳንጆርጅ፣ ሳንታ ማሪያና ሳኒኮላ የሚባሉትን ጀልባዎች ከተቀበሩበት የአንጋራ ደሴት አውጥቶ «ናቢጋ



ጣና» የሚባል ድርጅት አቋቁሞ ነበር። በኋላ የጀልባዎቹ ስምም ተቀየረ። ሳንታ ማሪያ- ሊማሊሞ፣ ሳኒኮላ-አንድነት፣ ሳንጆርጅ ደግሞ ታጠቅ በሚል ስም ተቀየሩ። ይህንን ታሪክ ማንኛውም የአካባቢው ሰው ያውቃል። የቡስኪን ማንነት ግን ማንም አያውቅም። ለምን «ናቢጋ ጣና» የሚባል ድርጅት እንደከፈተም ለማንም ግልፅ አልነበረም። በ1967 ወታደራዊው የደርግ አስተዳደር ሥልጣን ሲይዝ ናቢጋ ጣና ከቡስኪ እጅ ወጣ። ቡስኪ መንቀሳቀስ ሲያቅተው ሁሉን ነገር ትቶ ሸሸ። የቡስኪ አላማ ግን በጣና ሐይቅ ላይ የትራንስፖርት አገልግሎትን ለማስፋፋት አልነበረም። ኢትዮጵያ የቀረው የጣሊያን ቤተሰብ ኢትዮጵያ ከጣልያን የተሻለ ለኑሮ የተመቸች ሀገር በመሆንዋ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። የቡስኪ ቤተሰብ ለረጅም አመታት ሲገዳደልበት የኖረ ሌላ ከፍተኛ ምስጢር አለ» ከወንበራቸው ተነስተው እስክሪኑን የሞላውንና እርሳቸው ያንቀሳቅሱት የነበረውን መርከብ ፎቶ ግራፍ በብዕራቸው መታመታ አድርገው ተመልሰው ተቀመጡ።

«ጣሊያን በ1933 ዓመተ ምህረት ተባሮ ሲወጣ በጥድፊያ ካሰጠማቸውና በኋላ ቡስኪ የተባለው ጣሊያናዊ በ1940 ዓ.ም ከአንጋራ ደሴት አጠገብ አውጥቷቸው እስከ አሁን በጣና ሐይቅ ላይ አገልግሎት ከሚሰጡት ጀልባዎች ሌላ እኔ እነዳው የነበረው መርከብ እስክ አሁን የት እንደደረሰ አልታወቀም። ይህ መርከብ የት እንደደረሰ ታውቃለህ?» ተነስተው ተንጐራደዱና መልሰው ተቀመጡ።

«ይህ መርከብ የሰጠመው እዚሁ ጣና ሐይቅ ውስጥ ነው። እ....ዚ.....ሁ!.... በአሁኑ ወቅት ብቸኛው በህይወት ያለሁ ምስክር እኔ ብቻ ነኝ። በጣና ሐይቅ ውስጥ ደብዛው ስለጠፋው መርከብ ከእኔ በቀር የሚያውቅ አንድም ኢትዮጵያዊ የለም።» አሁንም ተነስተው ተንቆራጠጡ።

«በከባድ ጥንቃቄና በጥልቀት የሰጠመው ይህ መርከብ ሃምሳ ዘጠኝ በርሜል የጠገራ ብር፤ ሰላሳ ስምንት በርሜል ወርቅ እና በዲያመንድ የተሞሉ የብረት ሳጥኖችን ተሞልቶ ነበር።........ ከዚህም በላይ በሌሎች ምን እንደያዙ ባለወኳቸው የብረት ሳጥኖች ተሞልቶ ነበር የሰጠመው። ይህ ሁሉ ሀብት የተቃረመው በጎንደር ቤተ መንግሥታት ሥር በሚገኙ የገንዘብ ማጠራቀሚያ ገደሎች እና በመላው ኢትዮጵያ ገንዘባቸውንና ወርቃቸውን በምድር ውስጥ የመቅበር ልማድ ካላቸው ኢትዮጵያውያን የተዘረፈ ነው። የእኛው የራሳችን ውድ ሀብት! ይህ መርከብ በድቅድቅ ጨለማ በጣና ሐይቅ ጠልቆ በተቆፈረ አዘቅት ውስጥ ሲቀበር ከቀባሪዎቹ መካከል እኔ፣ አያሌው እና ፊንሐስ ነበርንበት። በዚህ መርከብ ውስጥ እንሰራ ስለነበር። መርከቡ ከሰጠመ በኋላ የጣሊያን ጀነራሎች ካርታውን

በደንብ አንስተው ዓይኖቻችንን በጥቁር ጨርቅ ተሸፍነን በሌላ አነስተኛ ጀልባተጫንን። መሣሪያ ተወድሮብን ወደ ዳጋ እስጢፋኖስ ደሴት ካመጡን በኋላ በዚሁ ደሴት በሚገኝ አንድ ትልቅ ዋርካ ሥር ከሌሎች ሃያ አራት ጣሊያናውያን ወታደሮች ጋር የጥይት ናዳ አርከፈከፉብን። ጣሊያናውያን ወታደሮችን ጨምሮ ሌሎች የመርከቡ ዕቃ አውራጅና ጫኚ ኢትዮጵያንም ተረሸኑ። እኔ ባቴ ላይ በጥይት ቆስዬ ወደኩ። ከስድስት በላይ ሰዎች ከላየ ላይ ተነባብረውብኝ ሲወድቁ እኔ ከአስከሬኖች በታች በደም ተጨማልቁ የሚሆነውን ማዬት ጀመርኩ። እኛን የረሸኑን የኢጣሊያ ጀነራሎች ደግሞ እርስ በእርስ ተፋጠጡ። መርከቡን ያሰጠሙበትን ቦታ የሚጠቁመውን ካርታ ሽሚያ እርስ በእርስ መታኮስ ጀመሩ። ካርታውን የያዘው ጀኔራል እኔ ላይ ከወዳደቁት አስከሬኖች በላይ ተመትቶ ወደቀ። እንደምንም እጄን ከኪሱ ስሰድ ከርታውን አገኘሁት። በደም በተጨማለቀ እጄ ከወደኩበት መሬት ጥግ ካለ ድንጋይ ሥር ተስቤ ቀበርኩት። ጀኔራሎች ተገዳድለው ሲያልቁ በመጨረሻ የቀረው ጀኔራል የሁሉንም ጀኔራሎች ኪስ መፈተሽ ጀመረ። ካርታውን ሲያገኘው ግን አልቻለም። ዕብድ ሆነ። የወዳደቁትን ወታደሮች ኪስ ሁሉ እየፈተሸ አድሮ ሌሊቱ ሲነጋበት የእኛን ዓይኖች አስረው በመጡበት ሞተር ጀልባ ሄደ።

ይህ ጀኔራል በኋላ ወደ ኢጣሊያ ተጉዞ ከተመለሰ በኋላ ቤተሰቦቹን ይዞ ኢትዮጵያ ውስጥ መኖር ጀመረ። ስሙን ቡስኪ ብሎ ቀይሮ በ1940 ዓ.ም ናቢጋ ጣና የሚባል ድርጅት ሲከፍት ማንም የቀድሞ የኢጣሊያ ጀኔራል መሆኑን አላወቀም።»

«እሺ ካርታውስ የት ደረሰ..... » ሚራዥ በተመስጦ ሲያደምጧቸው ከቆየ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥያቄ አነሳ።

«ካርታውን አሸሸሁት። ከእኔ ጋር ተረሽነው የነበሩት አያሌውና ፊንሐስ ቆስለው በህይወት አገኘኋቸው። እኔ ግን ባቴን ጨርፎኝ ካለፈ ጥይት በቀር የጠነከረ ቁስለት አልነበረብኝም። ልብስ እየቀደድኩ ቁስላቸውን ካሰርኩላቸው በኋላ የገዳሙ መነኮሳት ወታደሮችን በመቅበር እንዲተባበሩን ወደገዳሙ ወርጄ ተማፀንኳቸው። በዛ ወቅት በነበሩ መነኮሳት አሁን ደረስ ለታሪክ መዘክርነት ቆሞ ባለው በዛወቅት የጣሊያን ጀልባዎች በጣና ሐይቅ ላይ ሲተላለፉ ምልክት እንዲሆን በተተከለው የመብራት ማማ አቅራቢያ በዚሁ ደሴት ላይ ከሰሩት ወደብ አካባቢ ጥልቅ ጉድጓድ ተቆፍሮ ጣሊያናውያኑ ወታደሮችና የሞቱት ኢትዮጵያን ወዝ አደሮችም ተቀበሩ። እኛም በገዳሙ ውስጥ ከሰነበትን በኋላ ወደ ባህር ዳር ከተማ ሄድን። በዛ ወቅት ንጉሡ ወደ ሃገራቸው ተመልሰው ስለነበር ወደየቤተሰቦቻችን ስንመለስ አያሌው እኔ እና ፊንሐስ በባንዳነት ተከሰን ወደ ወህኒ ተወረወርን። በ1955 ዓ.ም



ሶስታችንም ከእሥር ቤት አመለጥን። ፊንሐስ ወደ ሰሜን ተራራ ሸሸ። ቤተ እስራኤላዊ ስለነበር በሰሜን ተራራ በአንጥረኝነት ከተሰማሩ ዘመዶቹ ጋር ተጉራብቶ ትዳር መሰረተ። አያሌውና እኔ በባህር ዳር ከተማ አቅራቢያ በምትገኝ መንደር ውስጥ መኖር ጀመርን። እኔ በ1959 አንተ ከተወለድክ ሶስት ዓመት ገደማ ሲሆንህ እንደገና የንጉሡ ወታደሮች ስላሳደዱኝ ወደ ዚሁ ወደ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም አንተን ይዤ ሸሸሁ። በኋላም ፊንሐስ ሲጳራ የምትባል ህፃን ልጁን ይዞ ወደዚሁ ገዳም መጣ። በዚህ ገዳም ሴቶች ስለማይገቡ አንተ እና እሷ ወዳደ.ጋችሁበት ለእስጦንስ የሴቶች ገዳም አስረከብናችሁ።

«የሥጋ አባትህ ነኝ እያሉኝ ነው?»። ሲል አቋረጣቸው ዶ/ር ሚራዥ።

«አዎ። አባትህ ነኝ። እናትህ እኔ ያለሁበትን እንድትናገር ስትደበደብ አረፈች። ገደሏት።»

«ለምን እስካሁን አባቴ እንደሆኑ አልነገሩኝም?»

«ጊዜውን እየጠበኩ ነበር። በኋላ ከዳጋ ወደ ክብራን ገዳም ልነግርህና ይህንንም ምስጢር ላካፍልህ ስመጣ ከገዳሙ ጠፍተህ መሄድህን ሰማሁ። ፍለጋዬም ከንቱ ሆነ። ይኸው ከስንት አመት በኋላ ታሪክ መልሶ አገናኘን።»

«የሲጳራ አባትስ አባ ፊንሐስ ነበሩ እንዴ?»

«እርሳቸው ነበሩ» አሉና አባ ዠንበሩ ስለ ሰጠመው መርከብ የጀመሩለትን ወግ ቀጠሉለት።

«የእኛን ወደዚህ ገዳም መምጣት ተከትሎ አሰቃ አያሌውም መጣ። ካርታው በእኔ እጅ እንደሚገኝ ነገርኳቸውና በአንድ ነገር ተስማማን። የሰጠመውን መርከብ አውጥተን በውስጡ ያለው ሀብት እኩል ለመካፈል። ይህን ለማድረግ ግን አቅማችንም ዘመኑም አይፈቅድም ነበር። የሰጠመውን መርከብ ለማውጣት ኃይል ያስፈልገን ነበር። ምክንያቱም መርከቡ ከሐይቁ ወለል በታች በከፍተኛ ጥልቀት ተቆፍሮ ነበር የተቀበረው። ይህን መርከብ ለማውጣት ምንም አይነት አቅም አልነበረንም ነበር። በኋላ ሶስታችንም ይህንን ዋሻ መቆፈር ጀመርን። ዋሻውን መቆፈር ስንጀምር አላማችን ለራሳችን መደበቂያነት ለመጠቀም ነበር። በኋላ የሀገሪቷን ውድ ሀብቶችና የብራና መፃህፍቶች ከጥፋት መከላከያ ሆኖ አገለገለ። እኔም በዚህ ወቅት በገዳሙ ውስጥ በማነባቸው መፃሕፍት እየተለወጥኩ መጣሁ። ራዕዬን ከግለሰብነት ወደ ሀገራዊነት ቀየርኩት። ራሴን ብቻ ለማበልፀግ ቀን ተሌት የሰጠመውን መርከብ ስመኝ ነበር። በኋላ ሁሉም ነገር አዕምሮዬ ውስጥ ሲቀያየር ታወቀኝ። ወደ ጣሊያን ለመርከብ ነጅነት ሥልጠና ልወስድ በሄድኩበት ወቅት ያየሁት የአውሮፓ ስልጣኔ አስቀናኝ።

ላይ እንደጥይት የሚወነጨፉ ባቡሮች ህብረተሰቡን በፍጥነት ሲያቀራርቡት ነው። ባቡሮቹ የሚተነፍሱት የተለያዩ ክልል አየር የአንድነት እስትንፋስ ይሆናል። መንገድብዙዎችን ያገናኛል። ጉንዳኖች ተያይዘው በሚሠሩት መንገድ ታላቅ ወንዝ ይሻገራሉ። ጉንዳኖች ተያይዘው ዓባይን ሲሻገሩ ዓይቻለሁ። እኛም ተያይዘን በምንሠራው መንገድ ወደስልጣኔ እንሸጋገራለን። የኢትዮጵያን እውናዊ አንድነት ከቃል የምናሸጋግረው ህዝቡን በኢኮኖሚና በብዙ ማህበራዊ መስተጋብሮች ስናስተሳስረው ነው። መንገድ የኢትዮጵያ አንድነት ደም ሥር ይሆናል። ኢትዮጵያን አንድ ማድረግና ወደታላቅ ስልጣኔ ማምጠቅ የሚቻለው ከሰሜን እስከ ደቡብ …ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ በተዘረጉ የባቡር ሀዲዶች ላይ እንደጥይት በሚወነጨፉ ባቡሮች ሲኖሩን ነው። ከዛም አንድ ሰው ከደቡብ ጫፍ ተነስቶ ከሰሜኑ ጫፍ ለመድረስ የሚያባክነው ጊዜ እና ብዙ ገንዘብ አይኖርም። ሁሉም ነገር ይፋጠናል። በሀገሪቷ ጠረፋማ አካባቢ ስትሠራ ውለህ ዋና ከተማዋ ውስጥ ካሉ ቤተሰቦችህ ሄደህ ማደር ትችላለህ። የትም ቦታ ለሥራ ብትመደብ አታቅማማም። ምክንያቱም የፈለከውን ጭነህ ቤትህ በቡሌት ባቡር ለመመለስ ጊዜ ስለማይጨርስብህ።

የኢትዮጵያ መሪዎች ራሳቸውን ወንበሩ ላይ ለማቆዬት…. ለፖለቲካ … ለስብሰባ…. ለፕሮፖጋንዳ መንዣ ….ለካድሬ ክፍያ እንኳ የሚያወጡት ገንዘብ በሀገሪቷ ሙሉ የባቡር ሀዲዶችን ለመዘርጋት ቢያውሉት እስከ አሁን ሀገሪቷ በድህነት አትማቅቅም ነበር። ይህን ማድረግ ግን አይፈልጉም። ለግል ብልጽግና የሚራኮቱ ቅጥረኞች በመሆናቸው። መንገዶች ከበዙም መንግስትን ለመገልበጥ የሚሞክር ማንኛውም ሀይል በቀላሉ ሊሳካለት ስለሚችል። መሪዎቻችን እነማንም ይሁኑ እነማን እኛ በግላችን በዬትኛውም ጊዜ በዬትኛውም ፈተና ውስጥ ሆነን ሀገራችንን መገንባት አለብን። እስከ መቼ ጥሩ መሪ እንጠብቃለን?…..ለሀገር ብልጽግና የምትቆረቆር ከሆነ ይህን አላማ ትደግፋለህ። የሰጠመው መርከብ ሀብት ደግሞ ከነገርኩህ በላይ ማድረግ የሚችል ሀብት ነው። የባቡር ሀዲዱን ለመዘርጋት በቂ ኢንጂነሮች አሉን። የመንገድ ተቋራጭ ድርጅት እናቋርብና……………እንዲያውም አንተን በባለሀብት ሽፋን ከመንግስት ጋር አደራድረን የባቡሩን ሐዲድ በሰጠመው መርከብ ሃብት ለሀገራችን እንዘረጋላታለን። የባቡር ሀዲዱም የሀገራችን አንድነትና ህልውና ደም መዘዋወሪያ የደም ሥር ይሆናል። እስኪ በከተሞች ውስጥ የምድር ውስጥ የኤሌክትሪክ ባቡሮች ሲወነጨፉ…..በምድር ላይ ደግሞ አገር አቋራጭ ተወንጫፊ ባቡሮች በባቡር ሀዲዶች ላይ በተቦረቦሩና በተበሱ ተራሮች ውስጥ እያቆራረጡ ሽው እልም ሲሉ የሚመጣውን ብልጽግና አስብ።



ይታይህ ያኔ የሚኖረው አንድነት! ይታይህ ያኔ የሚኖረው መፈቃቀር… ይታይህ ያኔ የሚፈጠረው መቀራረብ ….ይታይህ የተሰባበረው የኢትዮጵያ የአንድነት መንፈስ ሲጠገን… ይሄ ነው እውናዊ አንድነት። አለበለዚያ ዝም ብሎ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ማለት የውሸት ይመስላል። ይህኛው ትውልድ ሠራሁት የሚለውና ለእናት ሀገሩ የፍቅር መግለጫ ስጦታ እንዲሆን የባቡሩን ሀዲድ በዚህ ትውልድ ስም ልንገነባለት ይገባል። ቃል በተግባር ሲታይ የጋራ ህልሙም እውን ሲሆን ያኔ ተለያይ ብትለው እንኳ የሚለያይ ህዝብ አይኖርም። እንዲያውም ኢትዮጵያዊነት ወደ አፍሪካዊነት እየተለወጠ ኢትዮጵያ ላይ የተለኮሰው ችቦ ከጽንፍ እስከ አጽናፍ እየበራ ይመጣል። አፍሪካም ታብባለች። ለዚህ ነው ቁልፉን ስጠኝ የምልህ። ባለጉጡን ግማደ መስቀል…..እድሜ ልኬን ስፋለም የኖርኩለትን ምስጢር መፍቻ…..ስ..ጠ…ኝ…»

«መስቀሉን እኮ….. » ሚራዥ አቀረቀረ። በዓይኑ ዕንባ ሞላ። መጥፋቱን ሊያረዳቸው አልደፈረም። «ዝም ብሎ መስቀል መስሎኝ ለሲጳራ አስሬላት ……ያ…ያ…… ያኔ …እ…እ…እነ አባ ፊንሐስ ይዘዋት ሲሄዱ…….. ይዘውት….ወይኔ……..» ተንተባተበ።

«እ?» በድንጋጤ ቱግ አሉ አባ ገርንበሩ። ተንደርድረው በጥፊ ድርግም አደረጉት።

አባ ፊንሐስ ሲጳራን ይዘው የሸሹበት ምክንያት ገና ዛሬ ተገለጠላቸው። ከሲጳራ አንገት ላይ በቶ ቅርጽ የተሰራውን ባለጉጥ መስቀል በማየታቸው ይዘዋት እንደኮበለሉ ተረዱ። በንዴት ጦፉ። መናገር እንኳ አልቻሉም። ከንፈራቸው ተንቀጠቀጠ።

ሚራዥ ለአንድ ሳምንት ያህል በባዶነት ስሜት ነፍዞ ሰነበተ። በኋላ ግን ህይወቱን በሙሉ ከኢትዮያውያን ወገኖቹ ጋር ተባብሮ የባቡሩን ሀዲድ ለመስራት «ዶርቶጋዳ» የሚል ፕሮጀክት ነደፈ። በዚህ ፕሮጀክት መሠረት በጥቂት አመታት ውስጥ ኢትጵያን በባቡር ሀዲድ ለማገናኘት የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ዘረዘረ። እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ በገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች ላይ በማሳተፍ ይህን ፕሮጀክት የህብረተሰቡ ራዕይ ለማድረግ የሚከተለውን እቅድ ነድፎ ሲጨርስ ከዘቀጠበት ባዶነት ነቃ። ለፕሮጀክቱ መሳካት ቆርጦ ተነሳ። ከላሊቱን ከመሸጥ ጀምሮ የማይሞክረው ጥረት እንደማይኖርም ወሰኗል። የኢትዮጵያ ህዝብ በራሱ ጥረት ሀገሩን የሚገነባበት ብቸኛው እድል መቃረቡን አወቀ። «ይዘገይ ይሆናል እንጂ የማይሳካ ህልም የለም» ሲል ህልሙ እውን እንደሚሆን አረጋገጠ። በዓይነ ህሊናው በኢትዮጵያ ተራራዎችና ሸለቆዎች እያቋረጡ እንደ ጥይት የሚወነጨፉ ባቡሮች ታዩት።

በኋላ ደግሞ አባ ዝንበሩ መልሰው አጽናኑት፡፡ «የሰው ልጅ ትልቁ ሀብቱ ጭንቅላቱ ነው፡፡ የምድራችን ትልቁ ሀብትም ጭንቅላት ነው፡፡ ስለዚህ አሁን ወዳለን ነገር ፊታችንን እናዙር፡፡ ከሰጠመው መርከብ ሃብት ይልቅ ያንተ ጭንቅላት ለሀገርህና ለወገንህ ይጠቅማል፡፡ ስሜታዊ ሆኜ ነገሩን አከረርኩት እንጂ፡፡ ስለዚህ ይህችን ሀገር በእውቀትህ አገልግላት» አሉት፡፡ «ይልቅ በዚህ ወቅት የምናከናውነው አንድ ታላቅ ተልእኮ ስላለ በዛ ላይ በመሳተፍ እርዳን፡፡ ከነገ ወዲያ ወደ አሜሪካ ትጓዛለህ፡፡»

ሚራዥም ኢትዮጵያን ለሚጠቅም ማንኛውም ተልእኮ ራሱን ከመስጠት ወደ ኋላ እንደማይል ገለፀላቸው፡፡

በታህሣሥ ወር መገባደጃ በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1998 ዓ.ም አንድ ሌሊት ሚራዥና ዝንጊዳ ኢንጂነር ጌራ በሚያበራት ዴር33 ልዩ ድምጽ አልባ አውሮፕላን ለልዩ ተልዕኮ ከዳጋ ደሴት የምድር ውስጥ ዋሻ በጣና ሐይቅ ውስጥ ለውስጥ ወጥተው ወደ አሜሪካ በረሩ፡፡

ዴር33 ጣና ውስጥ ሰርጓጅ መርከብ፡፡ አየር ላይ ልዩ አውሮፕላን፡፡ አሜሪካ ውስጥ የቤት አውቶሞቢል ሆና ለልዩው ተልዕኮ ተሰማራች፡፡



# ፲፯

**ኒውዮርክ፡አሜሪካ**
**1998 ዓ.ም**
**ታህሣስ 28……ከምሽቱ 5፡46**

የቤቷ በር በሀይል ሲንኳኳ ቀና ብላ ግዳግዳው ላይ ትር…ትር.. ትር….የሚለውን የግድግዳ ሰዓት ተመለከተችው፡፡ 5፡46፡፡ ደግሞ ተንኳ፡፡ ትንፋሽዋን ዋጥ አድርጋ ወደ ሽጉጧ እጇን ላከችው፡፡ ተስልሶ በሩ ተሰለቀ፡፡

«ማነው?» አለች ሜሮዳ ጉሮሮዋን ጠራርጋ ፡፡

«እኔ ነኝ» አለ ጎርነን ያለ ደምፅ ከውጭ፡፡

«ማን ልበል ?»

«ይህን ደምፅ አታውቂውም?» አለ ከውጭ የሚመጣው ድምፅ፡፡ «ሚራዥ ነኝ»

በሩን ስትበረግደው በማጮለቂያው ለማየት እንኳ ጊዜ አልነበራትም፡፡ ሶስት ሰዎች በሩ ከመከፈቱ በችኮላ ተንደርድረው ገቡ፡፡ ሌሎችን የሚያይ ዓይን አልነበራትም፡፡ ሚራዥን አንቃ ሳመችው፡፡ ሰውነቷ ሲንዘፈዘፍባት እየታወቃት ነበር፡፡ መርበትበቷን ለማስቆም ግን አቅም አጣች፡፡

«ሚራዥ………?» ለመናገር ብላ ከንፈሯ ሲንቀጠቀጥባት መልሳ ገጠመችው፡፡

«ሜሮዳ ደህና ነሽ…?»

«አይደለሁም ደህና ነሽ አትበለኝ… ሚራዥ….ጎድተኸኛል፡፡ ቢያንስ እንኳን የሄድክበትን ብትነግረኝ ምናለ…?» ወደ ሶፋው በዝግታ ሄዶ ሲቀመጥ በዓይኗ እየተከተለችው፡፡

«ኢትዮጵያ ውስጥ ነበርኩ…….»

«እናም እኔን ልታየኝ ተመልሰህ መጣህልኝ፡፡ ….»

«አይደለም ሜሮዳ ሰው ላድን ነው የመጣሁት ሻጊዝን ላድን ነው የመጣሁት….» አለ ሚራዥ የግንባሩን ላብ እየጠረገ፡፡ ሊዋሻት አልፈለገም፡፡ «አስቸኳይ ጉዳይ ነው፡፡»

«እኮ! ለእኔማ ምንም ግድ የለህም፡፡ አውቃለሁ ፡፡ ግን መልሼ ጨቅላ እሆናለሁ፡፡ ደደብ ነኝ» አለች ሜሮዳ በሽቃ፡፡ «እና ታዲያ ከእኔ ምን ፈለክ? አሁንም ተጠቅመኸኝ ጥለኸኝ ልትሄድ…..»

«እንድትረጅን እንፈልጋለን፡፡ ህይወቱን እናድነው እባክሽ….»

«እኛ አንታይሽም አይደል…. » ዝንጊዳ እጁን ለሰላምታ ዘረጋላት፡፡

«ኦው ዶ/ር ዝንጊዳ ተለውጠህብኛል….» አለች፡፡ እጁን ጠበቅ አድርጋ ጨበጣ፡፡ «…ብዙ ተለውጠሃል፡፡»

በኋላ ደግሞ አባ ዠንበሩ መልሰው አጽናኑት፡፡ «የሰው ልጅ ትልቁ ሀብቱ ጭንቀላቱ ነው፡፡ የምድራችን ትልቁ ሀብትም ጭንቅላት ነው፡፡ ስለዚህ አሁን ወዳለን ነገር ፊታችንን እናዙር፡፡ ከሰጠመው መርከብ ሃብት ይልቅ ያንተ ጭንቅላት ለሀገርህና ለወገንህ ይጠቅማል፡፡ ስሜታዊ ሆኜ ነገሩን አከረርኩት እንጂ፡፡ ስለዚህ ይህችን ሀገር በእውቀትህ አገልግላት» አሉት፡፡ «ይልቅ በዚህ ወቅት የምናከናውነው አንድ ታላቅ ተልእኮ ስላለ በዛ ላይ በመሳተፍ እርዳን፡፡ ከነገ ወዲያ ወደ አሜሪካ ትጓዛለህ፡፡»

ሚራዥም ኢትዮጵያን ለሚጠቅም ማንኛውም ተልእኮ ራሱን ከመስጠት ወደ ኋላ እንደማይል ገለፀላቸው፡፡

በታህሣሥ ወር መገባደጃ በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1998 ዓ.ም አንድ ሌሊት ሚራዥና ዠንጊዳ ኢንጂነር ጌራ በሚያበራት ዱር33 ልዩ ድምጽ አልባ አውሮፕላን ለልዩ ተልዕኮ ከዳጋ ደሴት የምድር ውስጥ ዋሻ በጣና ሐይቅ ውስጥ ለውስጥ ወጥተው ወደ አሜሪካ በረሩ፡፡

ዱር33 ጣና ውስጥ ሰርጓጅ መርከብ፡፡ አየር ላይ ልዩ አውሮፕላን፡፡ አሜሪካ ውስጥ የቤት አውቶሞቢል ሆና ለልዩው ተልዕኮ ተሰማራች፡፡



# ፲፯

## ኒውዮርክ፡አሜሪካ
1998 ዓ.ም
ታህሣስ 28......ከምሽቱ 5፡46

የቤቷ በር በሀይል ሲንኳኳ ቀና ብላ ግዳግዳው ላይ ትር...ትር.. ትር....የሚለውን የግድግዳ ሰዓት ተመለከተችው፡፡ 5፡46፡፡ ደግሞ ተንኳ፡፡ ትንፋሸዋን ዋጥ አድርጋ ወደ ሽጉጧ እጇን ላከችው፡፡ ተሰልሶ በሩ ተሰለቀ፡፡

«ማነው?» አለች ሜሮዳ ጉሮሮዋን ጠራርጋ ፡፡

«እኔ ነኝ» አለ ጎርነን ያለ ደምፅ ከውጭ፡፡

«ማን ልበል ?»

«ይህን ደምፅ አታውቂውም?» አለ ከውጭ የሚመጣው ድምፅ፡፡ «ሚራዥ ነኝ»

በሩን ስትበረግደው በማጮለቂያው ለማየት እንኳ ጊዜ አልነበራትም፡፡ ሶስት ሰዎች በሩ ከመከፈቱ በችኮላ ተንደርድረው ገቡ፡፡ ሌሎችን የሚያይ ዓይን አልነበራትም፡፡ ሚራዥን አንቃ ሳመችው፡፡ ሰውነቷ ሲንዘፈዘፍባት እየታወቃት ነበር፡፡ መርበትበቷን ለማስቆም ግን አቅም አጣች፡፡

«ሚራዥ.........?» ለመናገር ብላ ከንፈሯ ሲንቀጠቀጥባት መልሳ ገጠመችው፡፡

«ሜሮዳ ደህና ነሽ...?»

«አይደለሁም ደህና ነሽ አትበለኝ... ሚራዥ....ጎድተኸኛል፡፡ ቢያንስ እንኳን የሄድክበትን ብትነግረኝ ምናለ...?» ወደ ሶፋው በዝግታ ሄዶ ሲቀመጥ በዓይኗ እየተከተለችው፡፡

«ኢትዮጵያ ውስጥ ነበርኩ.......»

«እናም እኔን ልታየኝ ተመልሰህ መጣህልኝ፡፡ ....»

«አይደለም ሜሮዳ ሰው ላድን ነው የመጣሁት ሻጊዝን ላድን ነው የመጣሁት....» አለ ሚራዥ የግንባሩን ላብ እየጠረገ፡፡ ሊዋሻት አልፈለገም፡፡ «አስቸኳይ ጉዳይ ነው፡፡»

«እኮ! ለእኔማ ምንም ግድ የለህም፡፡ አውቃለሁ ፡፡ ግን መልሺ ጨቅላ እሆናለሁ፡፡ ደደብ ነኝ» አለች ሜሮዳ በሽቃ፡፡ «እና ;ታዲያ ከእኔ ምን ፈለክ? አሁንም ተጠቅመኸኝ ጥለኸኝ ልትሄድ.....»

«እንድትረጅን እንፈልጋለን፡፡ ህይወቱን እናድነው እባክሽ....»

«እኛ አንታይሽም አይደል.... » ዠንጊዳ እጁን ለሰላምታ ዘረጋላት፡፡

«አው ዶ/ር ዠንጊዳ ተለውጠህብኛል....» አለች፡፡ እጁን ጠበቅ አድርጋ ጨብጣ፡፡ «...ብዙ ተለውጠሃል፡፡»

ይገባል። ያስከፍለውን መስዋዕትነት ከፍለን ማዳን አለብን» ዶ/ር ሚራዥ ተፈናጥሮ ተነሣ።

«እኔ ግን.....» አለች ሜሮዳ። «ከአሁን በኋላ ለማንም ለምንም ብዬ የምከፍለው መስዋዕትነት አይኖርም። ሰው ማድረግ የሚችለውንና ማድረግ የማይችለውን ለይቶ ማወቅ አለበት። ወደ ማትችሉት ውስብስብ ነገር ውስጥ እየገባችሁ ነው። ይህ አሜሪካ ነው። በሲ. አይ. ኤ ግዛት ውስጥ ነው ያላችሁት። ኢንጂነር ሻጊዝን ይቅርና ኢንጂነር ሻጊዝ ከተሳጨው የፀጉር ዘለላ ላይ አንዲት ቅንጣት እንኳ ይዛችሁ መሄድ አትችሉም። አሜሪካ እንኳንስ ለናሳው እውቅ ሳይንቲስትና ለአለማችን ቁንጮ የህዋ ተመራማሪ ኢንጂነር ሻጊዝ ይቅርና ለአንድ ተራ ዜጋዋ እንኳ የማታነሣው በትር አይኖርም። ትሰሙኛላችሁ? አርፋችሁ ወደመጣችሁበት ተመለሱ። ይህን ነው ልመክራችሁም ልረዳችሁም የምችለው.......አሜሪካ ለዚህ ሰው ስትል ማንኛውንም ጦርነት ለማድረግ ዝግጁ ናት። ሶስተኛው የአለም ጦርነት ቢነሳ እንኳ ይህን ሳይንቲስት ከአሜሪካ እጅ ፈልቅቆ መውሰድ የሚችል አይኖርም። ጃፓን፣ ቻይና፣ በቅርቡ ወደ ህዋ መንኮራኩር ለማምጠቅ ደፋ ቀና የምትለው ህንድ፣ሰሜን ኮርያ፣ እስራኤል፣ ሩሲያ፣ ኢራን፣ ሶርያ.......እነዚህ ሀገራት ሁሉ ሲባዝኑለት ኑረው ያላገኙትን ሰው  እናንተ ልትወስዱት? ምናልባት በገዳማዊው ሚራዥ በኩል መለኮት ጣልቃ ካልገባ ወይም ሞት ጠምቷችሁ ካልሆነ በቀር እንዲህ ማሰባችሁ በራሱ የምዕት ዓመቱ ምርጥ ቀልድ ነው። እኔ በበኩሌ በዚህ ሰውዬ ጉዳይ ውስጥ ብሞት አልገባም።እኔ ሜሮዳ ነኝ። የምችለውንና የማልችለውን ለይቼ አውቃለሁ።» አለች ወደ ፊታቸው አንገቷን ከደረቷ መዛ።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ዶ/ር ሉስ ካን እየተንቀጠቀጠ የመርፌውን ስሪንጅ እስከ ደንደሱ በኢንሱሊን ሞላው። «አ! አምላኬ .....» በጭንቀት ተንፍሶ። «ጲላጦስን እጄን ማነው ያስታጠበው? እኔ ልታጠብ ብል ግን ውሃ የሚጨምርልኝ የለም። እጄን ይቆርጡኛል እንጂ። አ! ያልታደልኩት ጲላጦስ!......»

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ሁሉም አቀርቅረው በፀጥታ ማሰላሰል ጀመሩ። አማራጭ እንዳለ።........................................

«አንቺ የምታደርጊልን እኮ .....ዶ/ር ሉስ ካንን ማጥመድ ብቻ እኮ ነው» አለ ሚራዥ እስከ ተቀመጠችበት ጥግ ተንፉዋቆ ተቀምጦ። ለትንሽ ሴኮንዶች አይኖቹን ትኩር ብላ ተመለከተቻው። ናፍቆቱ ሲያርመጠምጣት የኖረችውን ያህል።



«እወድሃለሁ ሚራ!....» አለችው ፈጣሪ ከፅርሃ አርያም ከዋክብት መሀል ነቅሎ የተከለላት የሚመስሉ ዓይኖቿዋን አስለምልማ።

«እኔም.....»እወድሻለሁ ሲላት ቃሉ ከከንፈሩ ሲደርስ መልሶ ዋጠው። አንድ ነገር ውስጡ እንዳለ ይሰማዋል። የውስጠኛው ውስጡን ማሸነፍ ግን አልቻለም። ውስተ ውሳጤውን።እንዲያውም እሷን ሲያይ ትዝ የምትለው ሲጻራ ናት። የሜሮዳን አካል አካሷ አድርጋ በሜሮዳ ቃል የምትናገረው ሲጻራ ትመስለዋለች።

«ስለማፈቅርህ ግን ከማትችለው ነገር ውስጥ ስትገባ ይዘኸኝ አትግባ። ላፈቅርህ እንጂ ልታፈቅረኝ የተፈጠርኩ አይመስለኝም በእርግጥ። ውለታ ውዬልህ እንድታፈቅረኝም አልፈልግም። ፍቅር የውለታ ምላሽ አይደለም። እሺ ይህንን ነገር ከሀገርህ አንፃር እንየው ብንል ኢንጂነር ሻጊዝ ለኢትዮጵያ የሚገባት ሰው አይደለም። እንዲያውም አንተን ብዬ እንጂ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ታስጠላኛለች። እንዴት እንዳደኩ እኔ ነኝ የማውቅ። የእናቴ ገላ ለርካሽ ሸርሙጥና የተሸጠባት ሀገር ናት ኢትዮጵያ። አሁን ኢትዮጵያ ምኗ ይወደዳል ! ቁንጫዋ? ትኋኗ? እከኳ ? መሪዎቿ ? እስኪ ከምኗ ነው ፍቅር የያዛችሁ?......»

«እከካም ያደረግናት እኛው ራሳችን እንጂ ኢትዮጵያ ለችጋርና ለጉስቁልና  አልተፈጠረችም» ኢንጂነር ጌራ ጣልቃ ገባ።

«ያም ሆነ ይህ ያችን ቀፋፊ ሀገር የምወድበት ምክንያት የለኝም። ለኢትዮጵያ ብዬ ደግሞ የማንቆረቁረው ላብ የማፈሰው ደም የለኝም። ሚራዥ..... » አለች እስከ አፉ ተጠግታ።« በዚህ ጉዳይ ልተባበርህ ስላልቻልኩ ይቅርታህን እለምናለሁ። በዛ ላይ ደግሞ ዘግይታችኋል። በዚህ ሰአት በኢንጂነሩ ላይ ያፈጠጡ አንድ ሺህ አንድ ዓይኖች እንደሚኖሩ አትጠራጠሩ። ኬጂቢ፣ ሞሳድ፣ ሲ..አይ.ኤ፣ የኢትዮጵያ የደህንነት ሰዎች ወዘተ ወዘተ። ይህኔ በእነዚህ ኃይሎች የሰሜን አስቲን የህክምና ማዕከል እንደታጠረ መጠራጠር ቂልነት ነው። ኢትዮጵያን ሳይጨምር መላው ዓለም ይህን ሳይንቲስት በእጁ ለማስገባት በሚስገበገብበት ሰአት መምጣታችሁ በራሱ ያረፈዳችሁ መሆኑን ሳይሆን የሚያሳየው የቀራችሁ መሆኑን ነው።»

«እንንቀሳቀስ።» አለ ዶ/ር ሚራዥ ቱግ ብሎ ተነስቶ። «ህ!...ኢትዮጵያ ውስጥ ችጋር ያልወቀጠው የለም። ሁላችንም በሰቆቃ ውስጥ ነው ያደግነው። እኔን የሚገርመኝ ....ኢትዮጵያ እንደ የውስጥና የውጭ ጠላቶቿ ብዛት እስከ አሁን ከምድረ ገፅ አለመጥፋቷ ነው። የኢትዮጵያ እስከ አሁን መቆየት በራሱ ለዚህ ትውልድ ታላቅ ነገር ነው። እስኪ አስቢ ኢትዮጵያ እንደ እስራኤል ጠፍታ ቢሆን ኖሮ መልሰን እንመሠርታት ነበር? አሁን በዚህች

ብቻዋን በቆመች ሀገር ቂም ይያዛል ? ሜሮዳ ...አዎ እዚህ ...አሜርካ ውስጥ ለእያንዳንዱ ችግር መፍትሔ አለ። ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ ለእያንዳንዱ ችግር ሌላ ችግር አለ። ግን ሁኔታዎች በዚህ አይቀጥሉም። ኢትዮጵያ የምታብበበት ጊዜ ሩቅ እንዳይመስልሽ። ትናንት ደሀ ስንላት የነበረችው ሀንድ ዛሬ የህዋ ምርምር ተቋም ሳይቀር ገንብታለች። አስቢ.... ሻጊዝ ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ መቶ ሰው ቢያስለጥን እንኳ የሚመጣውን ለውጥ ማሰብ ቀላል ነው! ኢትዮጵያ የአዕምሮ እንጂ የጥሬ ሀብት ደሀ አይደለችም። እመኚኝ የኢትዮጵያ ትንሣኤ ሩቅ አይደለም። ከኢትዮጵያ የህዋ ምርምር ተቀዋም መንኮራኩሮች የሚመጥቁበት ጊዜ ሩቅ አይደለም። ይዘገይ ይሆናል እንጂ የማይሳካ ህልም የለም። ጉንዳኖች ማዕበል እንደ ቅቤ እዬናጣቸው ተያይዘው ወንዝ ይሻገራሉ።....ስለ ኢትዮጵያ አናቅማማም አናፈገፍግም። ላስከ መጨረሻዋ የደም ጠብታ.....» በሩን እስኪገነጠል በርግዶት ወጣ። ዶ/ር ዣንጊዳ እና ኢንጂነር ጌራም ተከትለውት ወጡ።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ዶ/ር ሉስ ካን ጫን ጫን እየተነፈሰ ታካሚውን በብዥታ ውስጥ ተመለከተው። ጆሮው ላይ በተተከለለት ረቂቅ ስልክ ውስጥ «ምን ትጠብቃለህ?!» ጎርናና ትዛዛዊ ቃና ያለው ድምፅ ታምቡሩን የቀደደው መሰለው። «አሁኑኑ!» በቀዶ ጥገናው ክፍል ውስጥ የተገጠመውን ስውር ካሜራ ቀና ብሎ ተመለከተው። እንደሚከታተሉት አውቆ በእሽታ ራሱን አወዛወዘ። መርፌውን ከጋወኑ ኪስ አውጥቶ በጭካኔና በቁርጠኝነት አልጋው ላይ ወደተኛው ታካሚ ተመለከተ። በኢንጂነሩ ዙሪያ ይተራመሱ የነበሩትን ነርሶችና የህክምና ቡድኑ አባላት እንዲወጡ ትእዛዝ በመስጠቱ ወጥተዋል። ትክክለኛው ሰአት ላይ መሆኑን ተገንዝቦ መርፌውን የያዘበት እጁ እየተንቀጠቀጠ ወደ ኢንጂነሩ ተራመደ።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ከሜሮዳ ቤት ታዛ ወደ ቆመችው መኪና መሰሏ ጼር33 ልዩ ትንሽ አውሮፕላን ሲገቡ ሲሉ ልብሷን በፍጥነት ለባብሳ ተከተለቻቸው። ሶስቱም ዞረው አዩአት።

ዶ/ር ሚራዥ ፈገግ ሲል ውብ ነጫጭ ጥርሶቹ በመብራቱ ሀዳል ሲፈልቁ ታዩት።

«ለአንተ ስል ገሃነምም ቢሆን እገባለሁ» አለችው ልዩ ወደ ሆነችው መኪና ተከትላቸው እየገባች። እጇን ስቦ ፈገግ እንዳለ ከጥጉ አስቀመጣት።ሙሉ ጥቁር ለብሳ እስከ ወኔዋ ወታደር መስላለች ።

ኢንጅነር ጌራ ልዩዋን ጼር33 ጼርቶጋዳ ልዩ ማሽን በፍጥነት እየነዳ የኒው ዮርክን ከተማ ጉዳና ጨርሰው ወደ



ገጠራማው ግዛት እንደገቡ ከመኪናዋ መሪ ጥግ የተገጠሙ ቁልፎችዋን ሲጫን መኪናዋ ከሆድ እቃዋ የወጡ ክንፎችዋን እንደ አሞራ ዘረጋጋች። ቀስ በቀስ ወደላይ ከፍ ከፍ ብላ እንደጀት አውሮፕላን እየሩን እየሰነጠቀች ሰማይ ላይ በከፍተኛ ፍጥነት ስትበር ሜሮዳ አይኗን አፍጥጣ አፏን እንደከፈተች ወደ ሚራዥ ዞረች።

«አሁንስ አታምኝም? ብትሰሚ ኑሮ አዎ አታምኝም። እያየሽም አለማመን መብትሽ ነው። ማንንም ለማሳመን አይደለም የምንሠራው። ጭንቅላትን ያህል አካል ይዘን የተፈጠርነው ውሃ እንድናሞቅበት አይደለም።»

«እኔ አላምንም ከሰማይ የወረደችላችሁ አውሮፕላን መሆን አለባት» አለች ሜሮዳ ተደንቃ።

«ይልቅ ቀበቶሽን ጠበቅ አድርጊ ኦውስቲን ልንደርስ ስለሆነ ከገጠራማው መንገድ ላይ ነው የምናርፍ»አለ ኢንጂነር ጌራ በከፍተኛ ፍጥነት እያበረረ። «ሁላችሁም ቀበቷችሁን በደንብ አጥብቁ»

ቀስ በቀስ መኪና መንገዱ ላይ ካሳረፋት በኋላ ሌሎች ቁልፎችን ሲጫን ክንፎቿ ወደ ውስጥ ገብተው ፍፁም መኪና መሰለች። የታርጋ ቁጥሮቿን መሪው ጥግ ባለ ቦርድ ላይ ያሉ ቁጥሮችን ነካክቶ ካስተካከለ በኋላ ወደ ሰሜን ኦስቲን የህክምና ማዕከል የሚያደርሰውን አውራ መንገድ አሳብሮ ገብቶ በፍጥነት ነዳት።

«በእውነት ኢትዮጵያ ውስጥ ነው የሰራችኋት!?...» አለች ሜሮዳ በአግራሞት አፏን እንደ ከፈተች።:::

«..ነው እንዳልልሽ ውሸት ይመስልሻል፣ አይደለም እንዳልልሽ እነውት ይመስልሻል» አላት ዶ/ር ሚራዥ እየሳቀ።

ጌራ የሚራዥ መልስ ገርሞት ወደነሱ ዙሮ ሲስቅ ሜሮዳ ካይኖቹ ጋር ተጋጨች። ከውስጡ የፈለቀ እንዳች የማታውቀው ወላፈን ልብዋን ሲጠብሳት ታወቃት። «አይደረግም!» አለች በውስጥዋ። «ምን አይነት ስስ ልብ ነው ያለኝ በኔ ሞት? ለስንቱ ደንግጬ እዘልቀዋለሁ...... ደሞ እንደ.ት ያምራል! በርግጥም ይህ ሰው በልጅነት ልቤ ለፍቅር እስለው የነበረው ሰው ነው......» የልብ ምትዋን ያረግብላት ይመስል የሚራዥን ክንድ ጥብቅ አርጋ ያዘችው። ከጌራ ማጅራት ላይ አይንዋን ሳትነቅል።

# ፲፰

### ቴክሳስ ፡ አሜሪካ
### 9፡05
### ሰሜን አውስቲን የህክምና ማእከል

ታዋቂው የሰሜን አውስቲን የህክምና ማዕከል ግርግር በዝቶበታል። ጆሮአቸውን ቢቆርጧቸው የማይሰሙ የሚመስሉት ነጫጭ ጋወን የለበሱ ዶክተሮች ይራወጣሉ። የተደገመባቸው የሚመስሉት ነርሶችም ይቅበዘበዛሉ። አያሌ የቡድን ረዳቶችና የቴክኒክ ሰራተኞች እንደ ነሐሴ አሸን ብር ብር ሲሉ ርዕደ መሬት የተከሰተ ይመስላል። የቀዶ ጥገና ክፍሎች በዶክተሮችና በነርሶች ተጨናንቀዋል። የድንገተኛ ክፍሎችም በሚያጣጥሩ በሽተኞች የስቃይ ድምጾች ምድራዊ ሲኦል መስለዋል።

ከዶክተሮች መልበሻ ክፍል ነጭ ጋወን ለብሶ ከዋናው መተላለፊያ በስተቀኝ በኩል ያለውን የቀዶ ጥገና ክፍል በርግዶት ሲገባ ዶ/ር ሉስ ካን በቅጽበት ፊቱን በሩን በርግዶ ወደ ገባው ሰው አዙሮ አፈጠጠበት። «አው! ....ዶክተር ዣንጊዳ ....በስንት ጊዜህ ተመልሰህ መጣህ? ከረጅም ጊዜ በኋላ.....» አለ ዶ/ር ሉስ ካን ጆሮ በሚበሳ ቀጭን ድምጽ። ቀጭን ድምጹ ፈጣንም ስለሆነ እንግሊዝኛው ከማሽን የወጣ እንጂ ከሰብአዊ ፍጡር ልሳን የወጣ አይመስልም። አፍንጫው ላይ ያደረገውን የሽታ መከላከያ አረንጓዴ ጓንት ባጠለቀ እጁ ወደ ላይ እያስጠጋ «እንኳን ደህና መጣህ ለማንኛውም።» መርፌውን በግድግዳው በኩል ሸፍኖ ወደ ኪሱ ከተተው።

«እንኳን ደህና ቆየኸኝ ዶክተር ሉስ ካን።» አለ ዶ/ር ዣንጊዳ ጠረጴዛው ላይ ወደተጋደመውና በቀዶ ጥገና መሣሪያዎች ገመድ ጭንቅላቱ ላይ ወደተተበተቡበት ጥቁር ታካሚ እየተጠጋ። «ታካሚህ እንዴት ነው በጣም ተጐድቷል?»

«በጣም እንጂ በጣም ነው የተጐዳው። ከቀዶ ጥገናውም በኋላ ወደ ጭንቅላቱ የሚፈሰውን ደም ማስቆም አልቻልንም። ይህን ቀዶ ጥገና ለማድረግ በኦፕሬሽኑ የተሰማራውን የህክምና ቡድን እንደመምራቴና በሪፖርቱም ላይ እንደገለጽኩት ወደ ጭንቅላቱ የሚፈሰውን ደም ማቆም አልቻልንም» አለ ዶ/ር ሉስ ካን በብሽቀት ተንፍሶ። ጆሮው ላይ የተተከለለትን ረቂቅ ስልክ ለጊዜው ግንኙነቱ እንዲቋረጥ አድርጎ የመከታተያ ካሜራውንም በፍጥነት ዘጋው።

ዣንጊዳ ድምጹን ዝቅ አድርጐ «ይህን ኦፕሬሽን ለምን እኔ አልጨርሰውም?» አለው።



«ምን!?» አለ ዶ/ር ሉስ ካን በመጠየፍ እየተመለከተው።

«በደቂቃዎች ውስጥ የታካሚህን ደም ማስቆም እችላለሁ» አሰው የበለጠ ተጠግቶ። «እጄን ላውስህ።»

«....እያልከኝ ያለኸው ከአንተ የበለጠ ችሎታ አለኝ ነው?!» የዶ/ር ሉስ ካን ነጭ ቆዳ በቅፅበት ቀላ።

«.....አይደለም። ላግዝህ ማለት ችሎታ የለህም ማለት ነው? ....አብረን ሰርተን አናውቅም እንዴ ዶ/ር ሉስካን? .....ተጋግዘን አናውቅም እንዴት?.....ይህን ነገር እንዴት በሌላ ትመነዝረዋለህ...? እኔ ያልኩህ ሌላ አንተ ያልከኝ ሌላ። ምናልባት ለአንተ ያልታየህ ለእኔ ሊታየኝ ይችላል። እያከምከው ያለኸው ሰው ደግሞ በጣም አስፈላጊ ሰው ነው። የዓለማችን ምርጡ ሳይንቲስት።»

«የማያስፈልግ ሰው አለ እንዴ ዶ/ር ዣንጊዳ?»

«የማያስፈልግ ሰው የለም። አስፈላጊ ሰው ነው ማለት አስፈላጊ ሰው የለም ማለት ነው ዶ/ር ሉስ ካን?»

«አሁን ሥራዬን ልስራበት ያለ ምድብህ መጥተህ አትበጥብጠኝ!» ረጅም አፍንጫው እስኪንቀጠቀጥ ተቆጣ ዶ/ር ሉስ ካን። «አለበለዚያ ለህክምና ማእከሉ ፕሬዝዳንት ለማመልከት እያስገደድከኝ ነው። ውጣልኝ አሁን። ከባድ ጥፋት እያጠፋህ ነው። ውጣልኝ። ለፕሬዝዳንቱ ከማመልከቴ በፊት ውጣልኝ።....ውጣልኝ» አለ ሉስ ካን አመልካች ጣቱን ወደ በሩ ቀስሮ እያንዳንዱን ቃላት አጥብቆ እየጠራ። ‹ዲቃላ!› አለ በውስጡ

«እሺ እወጣለሁ። ግን ስለሚደረገው ነገር የማላውቅ እንዳይመስልህ። don't forget what we have done before.... ታስታውሳለህ ሉስ....» አለ ዶ/ር ዣንጊዳ ክፍሉ ውስጥ አቀርቅሮ እየተንጐራደደ። «ከዘጠኝ ታካሚዎች ዘጠኝ ጉበት፣ ከሌላ ሶስት ሴት ታካሚዎች ደግሞ ሶሶት ኩላሊት፣ እዚሁ የህክምና ማዕከል ውስጥ ከሞተ ከአንድ ታዋቂ ሴናተር ደግሞ ልብ አውጥተህ በመሸጥህ የእነዚህ ሁሉ ሰዎች ደም በእጅህ እንዳለ አታውቅም?»

«ምንድን ነው የምታወራው?» ዶ/ር ሉስ ካን ደሙ ሞቀ።

«የእነዚህ ሰዎች ደም በእጅህ እንዳለ ሁሉ ይህንና ሌሎች ዘግናኝ ወንጀሎችን ስትፈጽም በስውር የተቀረጸው ቪዲዮ ካሴት ደግሞ በእኔ እጅ ነው። አሁን ወጥቼ መሄድ እችላለሁ።..... »ዶ/ር ዣንጊዳ ወደ በሩ ሲራመድ የሜሮዳ እቅድ እንዲሰራ እየጸለዬ ነበር።

«ቆይ!» አለ ሉስ። «መነጋገር ሳይኖርብን አይቀርም።»

«ከዚህ ኦፕሬሽን ጀርባ ያለውን ሻጥር በሙሉ አውቀዋለሁ። ሞሳድም በለው ሲ.አይ.ኤ የግል ገመናህን ሊሸፍኑልህ አይችሉም። ምናልባት እኔን እዚህ ብታስቀረኝ እንኳ ገመናህን ሊያጋልጥ የሚችል አጋር እውጭ አቁሜ መምጣቴን ልታውቅ ይገባል። መደራደር ካለብን ግን ከዚህም በላይ ጥሩ ወደ ሆነ ነገር

will continue to be a remarkable role model for many generation of Ethiopia As well as for many youths of the world. The tales of his achievements in the field **of** aerospace will inspire many would be Ethiopia scientists.» **ሲል በሳይንቲስቱ ህይወት ዙሪያ ሰፊ ዘገባ ያስነበበው** «the scientist» **የሚባለውና ሳይንሣዊ ዘገባዎችንና የሳይንቲስቶችን ህይወት በመዳሰስ የሚያቀርበው ታዋቂው ጋዜጣ ነው፡፡**

«The former NASA chief of spacecraft and satellite systems engineer and Ethiopian patriot, scientist shagiz died an hour past midnight on January 13, 2006 four days after he under went surgery at north Austin Medical center in Austin, Texas.

In 1978, he invented two a aerospace mechanisms and patented under NASA's new technologies programs while working with other NASA scientists and the Apollo astronaut BUZ Aldrin, second man to walk on the Moon. In several advanced technology application research effort on mars missions, shagiz managed martin Marietta's research team and produced outstanding scientific results.

Shagiz joined Rockwell informational (builder of the space shuttle orbiter), space systems Division in 1986. He becomes a principal investigator and chief research engineer for several advanced space systems projects at Rockwell. He had a long dispute with his former American Jewish wife because of his children. He over saw the development of advanced technologies for kinetic energy weapons systems. He was also a program manager for a lunar mars-rover research and development effort in support of NASA's future exploration missions.

He then turned his attention to Africa and his beloved Ethiopia hoping to introduce and advance technology based development. Ethiopia as well as the whole world has missed one great man on earth. He will be truly missed.» የሚለውን የጠዋቱን ጋዜጣ ሥርአቶ ቀብሩ ከሚፈፀምበት መካነ መቃብር ውጭ መኪናው ውስጥ ሆኖ እያነበበ እያለ ፈገግ አለ ዶ/ር ሉስ ካን፡፡ የጋዜጦችና የመገናኛ ብዙሃኑ ዘገባ እንኳንስ ለዚህ ምስጢር ባዳ የሆነውን ህዝብ እሱን እንኳን መሞቱን ሊያሳምነው ዳር ዳር ብሎ ነበር፡፡ ከሀገሩ ከኢትዮጵያ



የመንግስት ብዙሀን መገናኛ ጣቢያዎች በቀር የመላው ዓለም የመገናኛ አውታሮች ዜና ዕረፍቱን በፍጥነት አራገቡት፡፡ የሞቱን ዜና በኢንተርኔት የሰሙ ‹ምናለ ሞቱን እንኳ ባይሆን ቢያረዱን....ጠላታችን የሚሉትን ሰው ሞቱን ማርዳት እንዲህ ይከብዳል?.....› ሲሉ በኢትዮጵያ ሚዲያ ላይ ብዙዎች አጉረመረሙ፡፡

ዶ/ር ሉስ ካን ከሞሳድ ማዕከላዊ ቢሮ ጋር ግንኙነት የፈጠረውና ኢንጂነሩ በምስጢራዊው የሬሣ ሣጥን ውስጥ በህይወት የመኖሩን ምስጢር በማቀበል ከሥርዓተ ቀብሩ በኋላ በአስደናቂው የሬሣ ሣጥን ውስጥ ረቂቅ የኦክስጅን መስጫ መሣሪያዎችና ሕይወቱን የሚመግብ ግሉኮስ የተተከለለትን ሳይንቲስት እስከ ሳጥኑ ለማስረከብ መደራደር የጀመረው የኢንጂነር ሻጊዝ የቀብር ጉዞ ከመጀመሩ በፊት ነበር፡፡

ሉስ ካን መኪናው ውስጥ ከመካነ መቃብሩ ፊት ለፊት ተቀምጦ የሚያነበውን ጋዜጣ ካስቀመጠ በኋላ ላፕቶፕ ኮምፒውተሩን ጭኑ ላይ አድርጐ ከሬሣ ሣጥኑ ውስጥ እንዲያስቀምጥ ከሞሳድ የተላከለትን ረቂቅ ካሜራ ከኮምፒውተሩ ጋር ግንኙነት መፍጠሩን ለማረጋገጥ ቁልፎችን ተጫናቸው፡፡

«እም፡፡....» አለ ዶ/ር ሉስ ካን በኮምፒውተሩ ስክሪን ላይ የሬሳ ሳጥኑ ያለበትን አካባቢ የሚጠቁመው ቀዩ ጠቋሚ መብራት ሲበራ፡፡ ቀጥሎ ደግሞ የውስጥኛው ካሜራ ከውስጥ የተኛውን አስከሬን ቁልጭ አድረጎ አሳየው፡፡ ምስጢራዊው የሬሳ ሳጥን በረቀቁ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ተሞልቷል፡፡ ከአስከሬኑ አፍንጫ ላይ የኦክስጅን መስጫ መሳሪያ ተተክሎለታል፡፡በክንዶቹ ላይም የግሉኮስና የማይክሮ ፍሉድ ምግብ መስጫ መሳሪያዎች ተገጥመውለታል፡፡ በድንገም እንዳይንቀሳቀስ ተደርጎ ከሬሳ ሳጥኑ ውስጣዊ ክፍል ጋር በቀያይ ቀበቶዎች ተጠፋፍሯል፡፡ ጭንቅላቱ ከብረት የተሠራቆብ ተገጥሞለታል፡፡ ድንገታዊ ተኩስ ቢከፈት በህይዎት ያለውን አስከሬን ከጥፋት ለማዳንም የሬሳ ሳጥኑ ውስጣዊ ክፍል ጥይት በማይበሳው ብረት ተለብጧል፡፡

በሬሣ ሳጥኑ ውስጥ በረቀቁ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች የታበተውን ህያው አስከሬን ሲመለከት ፈገግ አለ ዶ/ር ሉስ ካን ፡፡ «የህይወት ታሪክህን እያዳምጥክ ይሆናል ይኼኔ፡፡ ልብ ወለድ በሚመስለው የህይዎት ታሪክህ እንደተመሰጥክ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ በሬሣ ሣጥንህ ውስጥ ሆነህ ማን በደንብ እንደሚያለቅስልህና ማን እንደማያለቅስልህ ለመለየት የቻልክ ብቸኛው የዓለማችን ሰው ሆደ ለእኔም ኪሴን የሚያወፍር ገንዘብ ባለቤት ስላደረከኝ

አመሰግናለሁ።....እንዴት ነው የቀድሞዋ እስራኤል አሜርካዊት ሚስትህ ስታለቅስ ያምርባታል? ተከራክራ የወሰደችብህ ሶስቱ የምትወዳቸው ልጆችህስ?......ባለቀ ሰዓት ሲሳይ ስለሆንከኝ አመሰግናለሁ። ከአንተዎቹ የሐበሻ ሰዎች አርባ ሚሊዮን ዶላር ልቀበል የቀረኝ ሥርዓተ ቀብርህ እስኪፈፀም መታገሥ ብቻ ነው። ከሞሳድ ደግሞ ሃምሳ ስድስት ሚሊዮን ዶላር ዛሬ ማታ ኪሴ ውስጥ ይገባል። ቪቫ!....አመሰግናለሁ አንተ ህያው አስክሬን! ....ነፍስ ይማር። ከአሁን በኋላ ማንንም በሽተኛ ቀዶ መስፋት አከተመ» እያለ ባለሆሳስ ብቻውን ኮምፒውተሩ ላይ እንዳፈጠጠ የመኪናው የመስታወት በር ተንኳኳ። ብንን ብሎ ሲያይ የሞሳድ መታወቂያ እያሳየችው አንዲት ጠይም ሴት ጥቁር ሳምሶናይት ከፍ አድርጋ አሳየችው።

ከሞሳድ ማዕከላዊ ቢሮ ከእሷ ጋር ግንኙነት እንዲያደርግ ተነግሮታል። እንዲያገኛት የተነገረችው ሴት ፎቶ ግራፍና ስም በግል የኢሜል አድራሻው ስለተላከለት ትክክለኛዋ ሴት ለመሆኗ መታወቂያዋንና ፊቷን የመኪናውን በር ከመክፈቱ በፊት አነጻጸረው። መታወቂያዋ ላይ ያለው ስም ‹‹ሲጻራ ፊንሐስ›› ይላል። መታዋቂያዋ ላይ የሞሳድ ኤጀንት መሆኗን አመሳከረ። ‹እሷ ናት› ብሎ በውስጡ የመኪናውን መስኮት ከፈተላት። ምንም ቃል ሳትተነፍስ በገንዘብ የተምላውን ሳምሶናይት ሰጠችው።

ሳምሶናይቱን በፍጥነት ሲከፍት ለመቁጠር የሚያታክት «IN GOD WE TRUST» የሚል ጽሑፍ ያለበት የአሜሪካ ዶላር ታስሮ ታስሮ ተቀምጦለት አየ። «we trust in gold too.» ብሎ ፈገግ አለ። «በእግዚአብሔርም እናምናለን፤ በወርቅም እናምናለን።»

በስምምነቱ መሠረት ከሬሳ ሳጥኑ ጋር የተያያዘውንና የረቂቁ የሬሣ ሳጥን ውስጣዊ ክፍል ካሜራ መቆጣጠሪያ የሆነውን ላፕቶፕ ኮምፒውተር ሰጥቷት መኪናውን አስነስቶ በፍጥነት ከአካባቢው ሲሰወር ሥርዓተ ቀብሩን የፈፀሙት ሀዘንተኞች ኢንጂነራቸውን ቀብረው እየተመለሱ ነበር።

ዶ/ር ሉስ ካን ከነ ዶ/ር ሚራዥ ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ሰሜን አስቲን የህክምና ማዕከል በር ላይ ደርሶ እስከ ምሽት መኪናው ውስጥ ሆኖ ቢጠብቅም ብቅ ያለለት ማንም አልነበረም።

«እነዚህ ከሀዲዎች ተጫውቱብኝ ማለት ነው።...ግዴለም እኔም እጫወትባቸዋለሁ» እያለ ሲያጉረመርም ጥቁር አውቶሞቢል



መኪና እየፈጠነች መጣች። ሜሮዳ ወርዳ ትልቅ ቦርሳ ሰጥታው ተመልሳ በጥቁሯ አቶሞቢል ከአካባቢው እልም አለች።

ቦርሳውን በፍጥነት ከፍቶ ሲያይ በውስጡ ከአንዲት ብጣሽ ወረቀት በቀር ያገኘው ሰባራ ሳንቲም አልነበረም። «ዘግናኙን ወንጀል ስትፈጽምም ሆነ ልብና ኩላሊት እያወጣህ ስትሸጥ በስውር የተቀረፀው ቪደዮ ፊልም የሚሰጥህና የተቀበረው ፈንጂ የሚከሽፈው ሁሉም ነገር በእጃችን ከገባ በኋላ ነው። ገንዘቡም ያኔ ይከፈላል» ይላል ጽሁፉ። ወረቀቱ ላይ ተፍቶበት እንኳ ንዴቱን መቆጣጠር አልቻለም። ወረቀቱን በጥርሱ ቦጫጭቆ ጥሎት የመኪናውን መሪ በቡጢ ነርቶት በረረ። «የውሻ ልጆች!»

ቋሚ ድርጅት ያስፈልጋታል፡፡ ለዚህም ነው ዴርቶጋዳ የተቋቋመው፡ አስፈላጊ ሴት መሆንሽን ዴርቶጋዳ ተረድቷል፡፡››

‹‹ላስብበት›› አለች ሜሮዳ፡፡ ‹‹ስለድርጅቱ አላማም በደንብ ማወቅ ይኖርብኛል፡፡ ሲ.አይ.ኤ ተጠቅሞብኛል፡፡ ሌላ ድርጅት ደግሞ እንዲጠቀምብኝ አልፈልግም፡፡ የማሰቢያ ጊዜ ይሰጠኝና አስብበታለሁ፡፡

«ግዴለም አስቢበት፡፡ ሁሉን ነገር ልንነግርሽም ዝግጁዎች ነን፡፡ እስከአሁን ያደረግሽልን ለዚህ የከበረ አላማ እንድንመርጥሽ አበገድዶናል፡፡»

ሚራዥ ባቱ ላይ የመታችው ጥይት ወጥታ እግሩ በፋሻ ተጠቀለለት፡፡ ጠረጴዛው ላይ እንደተንጋለለ ሜሮዳን ትኩር ብሎ አያት፡፡ «አመሰግናለሁ» አላት፡፡

«ምንም አይደል፡፡ ላንተ ስል፡፡ .......» አለችው ፈገግ ብላ፡፡

«የራሣ ሣጥኑ ተከፈተ?» አላት በጉጉት፡፡

«እየተከፈተ ነው፡፡»

«ማየት አለብኝ»አለ ሚራዥ......እየተነሳ፡፡ «ወደዚያው ውሰዱኝ፡፡ ኢንጅነር ሻጊዝን ማየት እፈልጋለሁ፡፡ እንኳን ደህና መጣህ ብዬ ደስታየን ልግለጽለት ውሰዱኝ፡፡»

ክራንች ተሰጥቶት በሳይንቲስቶችና በዴርቶጋዳ አባላት ወደ ተከበበው ምስጢራዊ የሬሣ ሣጥን እያነከሰ ቀረበ ምስጢራዊው የሬሣ ሣጥን ተከፍቷል፡፡

የሬሣ ሳጥኑ ውስጥ በረቂቅ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች የተተበተበው አስከሬን ዙሪያውን የከበቡትን ቀያይ ጋዋን የለበሱ ሳይንቲስቶችና ባደስታ የተዋጡ የዴርቶጋዳ አባላትን ተመልክቶ ፈገግ አለ፡፡ ራሱ ላይ የተገጠመው የብረት ቆብ ወልቆለታል፡፡ ጭንቅላቱ በፋሻ ተጠቅልሏል፡፡ እንዳይነቃነቅ ከሳጥኑ ጋር በታሰረ አካሉ ዙሪያ የግሉኮስና የኦክስጅን መስጫ መሣሪያዎች ተተብትበዋል፡፡ የተገጠሙለት መሣሪያዎች በሙሉ ተፈታተው ተሽከርካሪው የህክምና አልጋ ላይ ተደርጐ ወደ ህክምና ክፍሉ ሲገባ ቀያይ ጋወን የለበሱት የዴርቶጋዳ አባላት በጭብጨባ አጀቡት፡፡ እጁን በቀስታ አንስቶ በደስታ አወዛወዛቸው፡፡



# ፳፪

## ቴልአቪቭ ፡ እስራኤል

ሲጳራ ከሞሳድ መስሪያ ቤት በታች በተሰራው የቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ ፊቷ በአባቷ ፊት ከተቀየረ ከሳምንት በኋላም በቁሙ መስታወት ውስጥ ፊቷ ላይ የተገጠመውን የአባቷን ፊት ማየቷን አላቆመችም፡፡ ረጅም ጊዜ ከፈጀው ቀዶ ጥገና በኋላ ፊቷ በፋሻ ታጅሎ ነበር የሰነበተው፡፡ ፊቷ በቀዶ ጥገና በአባቷ ፊት ሲተካ አልተቃወመችም፡፡ ድምፅዋም የአባቷን የአባ ፊንሐስን ድምጽ እንዲመስል ሆኖ በኮምፒውተር ተስተካክሏል፡፡

ኢንጅነር ሻጊዝን ለእስራኤል ካስረከበች በኋላ የተፈጥሮ ፊቷ እንደሚመለስላት ተነግሯታል፡፡ፊትዋን በመስታውት እየተመለከተች ሞሳድ የእሷን ፊት የለወጠበት ጥበብና ምስጢር ድንቅ ግርም ብሏታል፡፡

በዘመቻ ሙሴ ወደ እስራኤል ስትመጣ የሱዳን በረሃ ሲሳይ ሆነው የቀሩት አባቷ አባ ፊንሐስ ከመሞታቸው በፊት በሞሳድ የተነሱት ፎቶ ግራፍ በሞሳድ የዶክመንተሪ ክምችት ውስጥ ተገኘ፡፡ በፎቶ ግራፍ የነበረው የአባ ፊንሐስ ፊት በልዩ ቀዶ ጥገና ፊቷ እንዲሆን ተደረገ፡፡ አባቷ ከመሞታቸው በፊት ስለ ኢትዮጵያ የኑሮ ሁኔታና በኢትዮጵያ ፈላሻዎች እንዴት ይኖሩ እንደነበር በረሃ ውስጥ ለሞሳድ ቃለምልልስ ከሰጡት የቴፕ ድምጽ ላይ ድምፃቸው ተጠንቶ የሲጳራ ድምጽ እንደ አባቷ ሆኖ ተስተካከለ፡፡
በመሆኑም ከአንገቷ በላይ ፍፁም አባቷን መስላለች፡፡ ድምጿም ከአባቷ ድምጽ አይለይም፡፡

ከቀዶ ጥገናው በኋላ መስታወት ላይ ፊቷን ስታይ አባቷ ድቅን አሉባት፡፡ ከሚራዥ ስለለያዩዋትና ትርጉም አልባ ህይወት እንድትመራ ስላደረጓት በውስጧ ሳትረግማቸው አልቀረችም፡፡ መስተዋቱ ፊት ለፊት ቆማ አዲስ የተገጠመላትን የአባቷን ፊት ስታይ ከቆየች በኋላ አባቷ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ውስጥ ይለብሱት የነበረውን የምንኩስና ልብስ አይነት ስትለብስ ሙሉ በሙሉ እርሳቸውን መሰለች፡፡

እንደ ሞሳድ ውሳኔ ጭራሽ ደረቷንም የወንድ ደረት ለማስመሰል ጡቷም በሰርጀሪ ሊመጠጥ ነበር፡፡ እሷ ግን አጥብቃ ተቃወመች፡፡ ከአንገቷ በታች የሚፈትሻት እንደሌለ እርግጠኛ ናት፡፡ ደረቷ ላይ የተከመሩትን ትላልቅ ጡቶቿን በወፍራም ልብስ አጅላቸዋለች፡፡ የመናኙ ደበሎዋም ሴትነቷን ውጦታል፡፡ አስፈላጊ

የፀሎት መጻሕፍትንና የመነኩሴ ዝክንትሎችንም አንግታለች። የእሷን አባ ፊንሐስነት የሚጠራጠር ከእሷ በቀር ማንም አይኖርም።

በምስጢራዊው ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ደሴት ውስጥ የተሰወረውን ሳይንቲስት ከገባበት ገብታ ለማነቅ ያደረገችው ውሳኔ ትክክለኛ ለመሆኑ እርግጠኛ ናት። ወደ ኢትዮጵያ የምትገባበት አውሮፕላንም ተዘጋጅቶላታል። ወደ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ደሴት የምትገባበትና አድርሷት የሚመለስ ጀልባም ቀደም ብሎ ወደ ኢትዮጵያ በገባው የሞሳድ የሰላዮች ቡድን ተመቻችቶላታል። አባ ፊንሐስን ሆና አባቷ ወደ ነበሩበት የወንዶች ገዳም ልትገባ አንድ ቀን ብቻ ነው የቀራት። ወደዛ ገዳም እንኳን የሰው የእራዊትም ሴት እንደማይገባ ታውቃለች።

ያንን ህግ ጥሳ የምትገባበት ቀን ላይ ናት። እንዲያውም በዚህ ህግ ላይ ያደረ ቂም አለባት። ፍቅሯን የከለከላትን የወንዶችን ገዳም ህግም እገረ መንገዷን ለመበቀል ቋምጣለች።

የሬሳ ሳጥኑን የሚያመለክተው ካሜራ የተገጠመለት ኮምፒውተር ሻንጣዋ ውስጥ ከመፅሐፍ ቅዱስና ከሽጉጧ ጋር ተቀምጦላታል። ልዩ ልዩ የመገናኛ መሥሪያዎችም ተሰጥተዋታል። ይህ ሁሉ ጉድ የታጨቀበት ሻንጣዋ ግን የኢትዮጵያ መነኮሳት የሚይዙት አይነት ላዩ ላይ ቡትቶ የተሰፋለት ከረጢት ነው።

«ሲጳራ...... »አሉ የሞሳዱ ዋና ዳይሬክተር ወደስዋ በፍጥነት እየተራመዱ። ከረጢት መሰል ሻንጣዋን እንደተሸከመች ዘወር አለች። «በዶ/C ሉስ ካን ሪፖርት ላይ እንደተገለፀልን በኢንጅነሩ ጭንቅላት ውስጥ በቀዶ ጥገናው ወቅት ረቂቅ ማይክሮ ፈንጂ ተጠምዷል። ካልያዝነው ይፈነዳል ከያዝነው ደግሞ በሰርጀሪ እናወጣለታለን። ኢንጅነሩን መያዝና ማምጣት ያለብሽ ቦንቡ ከመፈንዳቱ በፊት መሆኑን አትዘንጊ። ቦንቡ መውጣት የሚችለው እዚህ ሲመጣ በምናደርግለት ቀዶ ጥገና ብቻ ነው። መፍጠን አለብሽ። ቦንቡ ሊፈነዳ የቀረው ጊዜ እጅግ በጣም ጥቂት ነው። አሥራ አምስት ቀናት ብቻ። ከአሥራ አምስት ቀናት በፊት ኢንጅነሩ ቴልአቪብ ካልደረሰ ሁሉም ነገር አከተመለት ማለት ነው። ትሰሚኛለሽ?!.... ከኢንጅነሩ ጭንቅላት ውስጥ የተጠመደው ፈንጂ ሊፈነዳ የቀሩት አሥራ አምስት ቀናት ብቻ ናቸው። ያንቺን ጥሪ የሚጠባበቅ ድጋፍ ሰጪ አካል ከሁዋላ ይከተልሻል።» ይህንን ተናግረው ዳይሬክተሩ ወደ ቢሯቸው ሲገቡ የአውሮፕላኑ ሞተር እያጓራ ነበር።

ወዲያው ዶ/C አናንያ የሆነ ነገር አንጠልጥሎ እየሮጠ ደረሰባት። «አንተ!.....ም....ምም.... ምን እያደረክ ነው!?» አለች ሲጳራ በድንጋጤ። በእጁ እንደቀላል እቃ አንጠልጥሎ የያዘው የእሷን ፊት ነው። በዝልግልግ ፈሳሽ ወስጥ ህዋሳቱ እንዳይሞቱ



ተደርጎ የተቀመጠበት ባለ መስተወት ጃር ነው። ፊቷ በዝልግልጉ ፈሳሽ ውስጥ ታያት።

«ፊትሽን አየሽው?! ህ!......ይህ ነው ስትኩራሪበት የነበረው ፊትሽ ያምራል አይደል?....አሁን መሳም እችላለሁ። መልሶ ባይስመኝም እስመዋለሁ። እምጱዋ!» በጃሩ ጠርሙስ ውስጥ በዝልግልጉ ፈሳሽ ላይ የሚንሳፈፈውን የፊትዋን ቆዳ ምጥምጥ አድርጎ ሳመው። ዶ/C አናንያ ከሸንጡ የመዠረጠውን ሽጉጥ በጃሩ ላይ ደቀነው።

«what the hell are you doing!?» ሲጳራ አፏ ተሳሰረ።

«ከአሁን በኋላ ይህን ስትኩራሪበት የነበረውን ፊትሽን አታይውም። ትዝ ይበልሽ ወንዱን ልጅ እንደ ሴት አስደፍረሽኛል» የሽጉጡን ምላጭ ሳበው። ፊቷ የተቀመጠበትን ጃር በጥይት በሳሳው። ፊቷን ከገደለው በኋላ «ሃ! ሃ! ሃ! ሃ! »ብሎ በብሽቀት ስቆ የራሱን ሽጉጥ ጠጥቶ ወደቀ። እሷን ያፈቀረበት ራሱንም አስወገደው።

እንደነብር ተወርውራ አስከሬኑን እነቀችው። ሞቷል። የራሷን ሽጉጥ አውጥታ በድኑን ቦተራረፈችው።

«ፊቴን! ፊቴን! ፊቴን!....» ተንሰቅስቃ እያለቀሰች የጥይት ናዳ በድኑ ላይ ብታወርድበትም አልጠቀማትም። ነፍሱን ተከትላ መልሳ ብትገላትም አትረካም።

የሞሳድ ዋና ዳይሬክተርና ሌሎች ኤጀንቶች ቢያጽናኗትም ለቅሶዋ ሊበርድ አልቻለም።

በኋላ ደግሞ እንደምንም ለመሄድ ወሰነች። ፈንጁ ሳይፈነዳ............።

# ፳፫

## ዳጋ እስጢፋኖስ፡ ኢትዮጵያ

አባ ፊንሐስ በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ውስጥ ጥሩ መስተንግዶ ተደርጎላቸዋል። ሌሊቱን ግን በማያውቁት ጉዳይ ለእስር ተዳረጉ። የሽሪሪቶች መናሃሪያ በሆነው ቀፋፊ ጎጆ ውስጥ ባለው ሽንቁር ግንድ ታሰሩ። ግንዱ ሊጎተት የማይችል ገንደፊላ ነው። በሁለቱ የግንዱ ቀደዳዎች እግራቸውን እንዲከቱ ከተደረጉ በሁዋላ በሁለቱ ሽንቁሮች ያለፉት እግሮቻቸው በእግረ ሙቅ ተጠረነፉና ተቆለፈባቸው። መተኛትም መደገፍም አልቻሉም። ሰውነታቸው ተቅመደመደ።

በዛው ሌሊት አባ ዝንበሩ ወደ ታሰሩበት ጎጆ ገቡና " አባ ፊንሐስ!" አሉአቸው። "በአራት ነገሮች ተከሰሃል። ሶስቱን እነግርሃለሁ አራተኛውን ግን ስለምታውቀው አልነግርህም። አንደኛ ከእኔ ጋር አብረህ ጓደኛ መስለህ ዋሻውን ስታቋፍረኝ ኑረህ ወደ ዋሻ ካሸሸናቸው ቅርሶች መኃል የንጉሡን ዘውድ ሰርቀህ በአንጥረኝነት ሙያህ ቀጥቅጠህ ሸጥከው። ሁለተኛ አባ ዲዲሞስን ወይም አለቃ እያሌውን አሳደህ ሚስቱንና ቤቱን በእሣት አቃጠልክ።ካርታውን በጥበብ መውሰድ ስንችል አንተ ግን በጉልበትህ ብዙ ነገር አበላሸህ። ሶስተኛ በእንጦንስ የሴቶች ገዳም ውስጥ የኖረችውን ልጅህን ያሳደግሃት ይመስል የገዳምዋን ልጅ ልክ እንደወንበዴ እፍነህ ከመወሰድህ በላይ የዚህን ገዳም ጀልባ ይዘህ ጠፋህ። የተከሰስከው እንግዴህ በክህደት፣ በስርቆትና በነፍስ ማጥፋት ወንጀል ነው ማለት ነው። አራተኛውን ወንጀልህን አንተው ታውቀዋለህ። መነኩሴ ነኝ እንጂ የሞት ቅጣት እፈርድብህ ነበር። ለነገሩ....የሚገድልም የሚያድንም እግዚአብሔር ነው። ሙዋች የሆነ ሰው የሞት ፍርድ መፍረድ አይችልም። የሞት ቅጣት እንዳልፈርድብህ የሞት ቅጣትን እቃወማለሁ። ቅጣት ጠባይን ማረሚያ ነው። ብዬ አምናለሁ። ከሞት በሁዋላ የሚታረም ነገር የለም። በገሃነም ወይም በመንግስተ ሰማያት ውስጥ የምትገባን ነፍስ ጠባይ የማያርም ቅጣት ነው የሞት ቅጣት። መልሰን ልንሰራው የማንችለውን ህይወት ማፍረስ ታላቅ ወንጀል ነው ። ያልሰራነውን የማፍረስ መብት የለንም። በዚህ ባላምን ግን የሞት ፍርድ እበይንብህ ነበር። አዎ.... አባ ፊንሐስ ወንጀልህ ልክ የለውም" አባ ዝንበሩ ይህን ተናግረው የአባ ፊንሐስን መልስ ሳይሰሙ እየተበሳጩ ተነስተው ሄዱ።



አባ ፊንሐስ በድንጋጤ ተርበተበቱ። ሲጳራ አባቱዋን እስከ ወንጀላቸው ነው ለካ የለበሰቻቸው....የተሸከመቻቸው። በአባቷ ፊት የአባቷን ቅጣት ተቀበለች። ሲጳራን ፀፀት ሰነጣጠቃት። ይህንን የአባትዋን ወንጀል ብታውቅ ኖሮ በቀዶ ጥገና ፊቷን በአባቷ ፊት ባልቀየረችም ነበር። መቀየር እንዳልነበረባት ተረዳች።

በዚሁ ሌሊት ደሞ አባ ዲምላ አባ ፊንሐስ ወደ ታሰሩበት ቀፋፊ ጎጆ መጡ። "አንጥረኛው ፊንሐስ?" አሉ አባ ዲምላ። "እንኳ ቆብ ብረት ብትደፋ እንኳ የምረሣህ እንዳይመስልህ። ልብህ ካልመነኮሰ ራስህ ብቻ ቆብ ቢደፋ ምን ዋጋ አለው?! ከቆብህ በታች የአንተ ገመና ብዙ ነው። ...........ትዝ ይልሃል? ትዝ ይለሃል እንጂ! እናቴን ከአልጋዋ ጋር አስረህ እሳት ያነደድክባት ትዝ ይልሃል? እኔ ግን ልረሳው አልችልም። የእናቴ የሰቆቃ ዋይታና ኡኡታ እስከ አሁን ደረስ በጆሮዬ ይሰማኛል። ሲገርፏት የነበረው የእሳት ነበልባል እስከ አሁን ድረስ ህሊናዬን ይገርፈኛል። ይለበልበኛል። ያቃጥለኛል። አዎ! ያ..ቃ..ጥ..ለ..ኛ..ል። ያንን ሁሉ ሐጢአት በተሸከምክበት ጭንቅላትህ ላይ ደሞ ቆብ ደፋህበት። አይ አንጥረኛው ፊንሐስ !! አይ ወንጀለኛው ፊንሐስ ! ጉድ ነው! ጉድ እንጂ የጉድ ጉድ። ቂቂቂቂ...ሃ!ሃ!ሃ!...." አባ ዲምላ በሹፈት ሲገለፍጡ በጎጆው ቀዳዳ በገባው የጨረቃዋ ወገግታ ባዶ ድዳቸው ግልጥጥ አለ። የጃርት ጉድጓድ የመሰለው አፋቸውን ስታይ ሲጳራ የሲኦል ደጅ ላይ የቆመች መሰላት። አባ ፊንሐስ ወከክ አሉ። ሲጳራ ራደች።

"አባ ፊንሐስ -አንጥረኛው ፊንሐስ! ወንጀለኛው ፊንሐስ!" አሉ አባ ዲምላ። "ልትፀድቅ ነው መንኩስህ የመጣሃው? እውነት እልሃለሁ ወንጀለኛው ፊንሐስ አንተ ከፀደክ እኔ የመንግስተ ሰማያት መግቢያ ቁልፍ ያዥ እሆናለሁ ማለት ነው። የእናቴን አሰቃቂ አሟሟት እግዚአብሔር ይበቀልልኝ ብዬ የምተውህ እንዳይመስልህ። ገሀነመ እሣትና ሲኦል ለፈፀምከው በደል ለሠራሃው ኃጢአት በቂ መቀጮዎች አይደሉም። ስለዚህ እኔ በጥሩ ሁኔታ እቀጣሃለሁ። አዎ..........................መጀመሪያ በጉጠት ጥፍሮችህን ቀስ በቀስ እነቃቅላቸዋለሁ። ቀጥዬ ጣቶችህን በመጥረቢያ እቀረጥፋቸዋለሁ። ከዛም እጆችህን እጎነድሻቸዋለሁ። ቀጥዬ እግሮችህን አንድ በአንድ እቆራርጣቸዋለሁ። ከዛም ጥርሶችህን አወላልቄ የራስህን ሥጋ በድድህ እያኘክ እንደትበላ አደርግሀለሁ። ይህ ሁሉ ሲሆን እንድታይ ዓይኖችህን ቀድሜ አላጠፋቸውም። አዎ! ውይ! ረስቼው። ብልትህን ቆርጬ አበላሀለሁ። አዎ ከዛም እንደ እንቁራሪት ሆድህ እስኪነፋ በእሳት እለበልብሃለሁ። ይህ ሁሉ እስኪሆን ግን እንድትሞት ስለማፈልግ ነፍስህን ከሥጋህ ጋር የማሥርበት ዘዴ አላጣም። አይዞህ! ቶሎ አልገድልህም።" አባ

ዲዎላ ይህን ብለው እየዛቱ ተነስተው ሄዱ። ሲጳራ ፍርሃትና ጭንቀት ሲወራት ተሰማት። አባ ፊንሐስ ተርበተበቱ። "አባ ፊንሐስ አይደለሁም!" ሲሉ እሰቡ አባ ፊንሐስ። ሲጳራ። ግን ይህን ካሉ የመጡበት አላማ እክል ይገጥመዋል።

ከሰው እስከ እንስሳ ሴት የሆነ ሁሉ ወደዚህ ገዳም እንዲገባ አይፈቀድለትም። ምናልባት ከአዕዋፍ እስከ ትንኝ ያሉ በራሪ ነፍሳትም ሴትና ወንድነታቸው ስለማይለይ እንጂ የእነሱም ሴቶች ተለይተው አይገቡም ነበር። ሲጳራ ይህንን የወንዶች ገዳም ህግ በልጅነትዋ ትቃወም ነበር። በወንዶች ገዳም ውስጥ የነበረውን ፍቅርዋን ሚራዥን ለማየት የከለከላት የማትወደው ህግ ነው። እንዲያውም በዚህ ገዳም ውስጥ የተፈፀመ አንድ አገር ያወቀው ታሪክ መኖሩን ታውቃለች። እቴጌ ምንትዋብ ተጎንደር መጥተው እዚሁ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ለመግባት ከጅለው ሲከለከሉ ከወደቡ ኮረብታው ላይ እስካለው ቤተ ክርስቲያን ምንጣፍ አስነጥፈው እኔ ምንጣፌን እንጂ መሬታችሁን አልረገጥኩም ብለው ሲጉዋዙ መሀል ላይ ደም በደም ሆነው ተመልሰዋል ይባላል። በዚህም ምክንያት ደቅ ደሴት ላይ የሚገኘውን ናርጋ ስላሴ ቤተ ክርስቲያንን እንዳስገነቡ ሲጳራ በልጅነትዋ ያነበበችውን ታስታውሳለች። ለዚህም ነው ፊትዋን በቀዶ ጥገና የወንድ ፊት አልብሳ ወደዚህ ገዳም የመጣችው። ታዲያ ምን ያደርጋል የአባትዋ ፊት የአባትዋን ሐጢአትና ወንጀል አሸከማት። ድምፅዋም ፊትዋም ቁርጥ ጣል እንደ አባትዋ ነው።

ቀኑም እየነጎደ ነው። ከኢንጂነሩ ጭንቅላት ውስጥ በቀዶ ጥገናው ወቅት የተጠመደው ፈንጅ ሲፈነዳ የቀሩት አሥር ቀናት ብቻ ናቸው። ፈንጁ ሳይፈነዳ ኢንጂነሩን መውሰድ አለባት። ግን እንዴት አድርጋ? ይባስ ብሎ ያልጠበቀችው እስራትና ህይወትዋን የምትነጠቅበት እጣ ፋንታ ደረሳት። የአባ ዲዎላ ዛቻና አስፈሪ ፊት በአእምሮዋ ተመላለሰ። ቅዱስ ሚካኤል የደበደበውን ሰይጣን የሚመስሉት አባ ዲዎላ አርበተበቷት።

በሁለተኛው ሌሊት አባ ዝንበሩ አባ ፊንሐስ ወደ ታሰሩበት ደሳሳ ጎጆ ለሁለተኛ ጊዜ ገቡ።

"አባ ፊንሐስ !" አሉ አባ ዝንበሩ። "ልጅህ የት ናት?"

"ልጂ ደግሞ ምን ሠራች?" አሉ አባ ፊንሐስ ።

"ልጅህ አሥራው በነበረው ነገር ምክንያት እንደ ወሰድካት አታውቅምና ነው መልሰህ የምትጠይቀኝ?"

"አይ አባ ........" አሉ አባ ፊንሐስ። "ልጂ የት እንዳለች በምን አውቃለሁ? እኔ እንደሁ ያ ምድራዊ ምኞቴ አሁን ከእኔ ጋር የለም። ሁሉም ነገር ከንቱ መሆኑ ገብቶኛል። ወደ ኢየሩሳሌም ከሄድኩ በሁዋላ በጌታችን መቃብር፣ በጎልጎታ፣ በቀራንዮ፣ በዶሮሱልጣን እየዞርኩ ንስሐ ስገባ ስለ ሐጢአቴ ሳለቅስ ኑሬ ነው



የመጣሁት። .....አሁን እዚህ የመጣሁበት ምክንያትም ይህ ቦታ ቅዱስ በመሆኑ እዚሁ አረፍተ ሞቴ እንዲሆን ተመኝቼ ነው። በዚህ ቅዱስ አፈር ላይ ለማረፍ። ቢያስሩኝ ቢገርፉኝ ቢደፉኝ ምንም አይመስለኝም!"

"አትዋሽ! አንተ በፍፁም እንዲህ ዓይነት ሰው አይደለህም። እስከዛሬ የዋሸኸኝ ይበቃሃል" አባ ዝንበሩ በጣም ተጠጉ። ሲጳራ የታሰረችበት እግረ ሙቅ ቁልፍ ከቢጫው ቀሚሳቸው ኪስ ጫፍ ላይ እየተንዘላዘለ ነው። "አንተን እግዚአብሔር ይቅር አይልህም።"
"ብሉኛል እንጂ! ይቅር ብሉኛል። እግዚአብሔር እንደ ሰዎች አይደለም! ሰዎች በራሳቸው አምሳል መልሰው ፈጥረውት ነው እንጂ። ይቅር ብሉኛል። ይቅር እንዳለኝም ተገልጦ ነግሮኛል። እንባዬን አብሶልኛል። ይልቅስ በመስቀልዎት ይባርኩኝማ። ያሳልሙኝ። መስቀሉን መሣም እፈልጋለሁ።"አባ ፊንሐስ እንቁላል እንደታቀፈች ዶሮ ጎጆ ቤት መስለው እንደታሰሩ ፊታቸውን ለቡራኬ አዘነበሉ። ወደ አባ ዝንበሩ። የእግር ብረቱ ቁልፍ ከኪሳቸው ጫፍ ላይ ተንጠልጥሎ ስላዩ።

አባ ዝንበሩ ካሳለሙአቸው በሁውላ "ለመሆኑ ልጅህ ወዴት ናት?" አሉ።

"እስራኤል ሀገር ውስጥ ናት።"

"የት ቦታ?"

«ስሙን አላውቀውም። ቦታውን ግን በዓይን ባየው አውቀው ይሆናል። በጣም አስፈላጊ ከሆነም ሄደን እናመጣታለን። ግን ልጂ ምንድን ነበር ያሠረችው?»

«አታውቅምና ነው? ለዛ ስትል አይደል እንዴ አንቀህ የወሰድካት»

«ሸረ ወላዲተ አምላክን! እመአምላክን ምን እንደያዘች አላውቅም።»

«በል ወደዚያው ትወስደኝና የያዘችውን አብረን እናያለን» ተነስተው ሄዱ ።

«ይፍቱኝ እንጂ አባ? ይፍቱኝ እንጂ! ተነጋግረን አይደል እንዴ? እግዚአብሔር ይቅር ያለኝን እርስዎ ሊያስሩኝ? ወይ ሰው! ወይ መነኩሴ!» አባ ፊንሐስ ይህን ቢለፈልፉም አባ ዝንበሩ ግን ዞር ብለው እንኳ አላዩአቸውም።

አባ ፊንሐስ በታሰሩ በሁለተኛው ሌሊት ኮረብታው ላይ በሚገኘው የእስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተንበርክከው ሲፀልዩ ተያዙ፣ አባ ዝንበሩ "ማን ፈታህ አንተ መናጢ?" አሉ እርሳቸውም እንደ ሚፀልይ ሰው ከጥጋቸው ተንበርክከው በለሆሳስ።

"አልነገርኩዎትም አባ? እግዚአብሔር ይቅር ብሉኛል ብዬዎት አልነበረም? ይኸው እግዚአብሔር ቅዱስ ሚካኤልን ልኮ

ከእስራቴ ፈታኝ። እግዚአብሔር የፈታውን ማን ያስረዋል? ይልቅስ ቁልፉን እነሆ። ቅዱስ ሚካኤል ከኪስዎ ወስዶ እኔን ሲፈታኝ ለምን ቁልፉን ሲወስድ አላዩትም? ብዬ አልጠይቅዎትም" አሉ አባ ፊንሐስ። "ቁልፉን መልስላቸው ብሎኛል ይልቅ። ቁልፉን ይውሰዱ"

"ይከተሉኝ" አሉ አባ ዠንበሩ። አባ ፊንሐስ እስከ ገዳሙ ተከተሏቸው።

"ይኸው ቤትዎ። የግል በአትዎ ይኸውና። ከሳምንት በሁዋላ ወደ እስራኤል አብረን እንሄድና ከልጅዎት ጋር ያገናኙኛል" የግል የፀሎት ቤት ሰጥትተዋቸው ሲሄዱ አባ ፊንሐስ እንግዳ ቤት ያስቀመጡት ጓዛቸውን ወደ ግል ቤታቸው አምጥተው አስገቡ።

በኢንጂነሩ አንጎል ውስጥ የተቀበረው ረቂቅ ፈንጅ ሊፈነዳ ስምንት ቀናት ብቻ ቀርታውታል። በዚሁ ሌሊት ከረጢታቸው ውስጥ ያለውን ኮምፒውተር አውጥተው በደሴቱ ምድራዊ ክፍል የሬሣ ሳጥኑን የሚያመለክተውን ቀይ ምልክት ተመለከቱ። በሬሣ ሳጥኑ ውስጥ የነበረው ህያው አስከሬን የለም። የሬሣ ሣጥኑም ተከፍቷል። ኢንጂነሩ በዚህ ዋሻ ውስጥ እንደሆነ ግን ጥርጥር የላቸውም። ኮምፒውተሩን ከፍተው ከመመልከታቸው በፊት ለብሰውት የሰነበቱትን የምንኩስና ልብስ አወላልቀው በመጎናፀፊያው ብቻ ጡቶቻቸውን ሸፍነው ነበር። ሸጉጣቸውንም ከኮምፒውተሩ ጀርባ ካለው መፅሐፍ ቅዱስ ላይ አስቀምጠውት ነበር።

በዚህ ቅፅበት አባ ዲምላ በሩን በርግደው ገቡ። አባ ፊንሐስ በቅፅበት ሽጉጣቸውን በአባ ዲምላ እናት ላይ በደመ ነፍስ ሲያነጣጥሩ ራቁታቸውን የተጋለጡ ጡቶቻቸውን ረስተዋቸው ነበር።

አባ ዲምላ ከሲጻራ ካቦ ካቦ የሚያካክሉ ጡቶች ጋር ሲፋጠጡ "አሃ!" አሉ ጥርስ አልባ አፋቸውን እንደከፈቱ። ከመጥፋት የተረፈችው አንዲት ዓይናቸው የአባ ፊንሐስን እንስታዊ አካል እንደሸንኩርት ከታች እስከ ላይ ላጠችው። ግራ ተጋቡ-አባ ዲምላ። ከአንገት በላይ ዕድሜ ጠገብ ጢማም ሽማግሌ ወንድ! ከአንገት በታች የወሲብ እሳት ጭን ውስጥ የምትለኩስ አማላይ ሴት!

«ወይ ጉ....ድ! » አሉ አባ ዲምላ። «ሰውን ገልጦ ነው ማየት! ላይ ላዩን እያዩሁ እንስት ነው ተባዕት ስል መኖሬ ከንቱ ነበር ለካ። እግዜር እንስትና ተባዕት አርጎ ፈጥሮዎት ነው ለካ ተንከለዎትን እንዲህ ያበዛው። እንዲህ አይነት ፍጡር አይቼም ሰምቼም አላውቅ» ሽጉጡን ረስተው በሚያዩት ትንግርት ትንፋሻቸው ቆመ። "ሴትና ወንድ ነዎት እንዴ ለካ አንጥረኛው ፊንሐስ?"

"አፍህን ዝጋ!" አለች ሲጻራ። "አባ ፊንሐስ አይደለሁም። ወደ ውስጥ ግባና በሩን የሁዋሊት ዝጋው!" አባ ዲምላ በሩን



የኋሊት ጠረቀሙት። አንዲቷ ዓይናቸው በአባ ፊንሐስ ትላልቅ ጡቶች መካካል አፍጥጣለች። በሰንሰለት ታስሮ በአባ ፊንሐስ ጡቶች መካካል ወርዶ የተንጠለጠለውን ባለጉጥ ግማደ መስቀል በአንዲት ዓይናቸው ጠቡት።

አባታቸው አለቃ አያሌው አባታቸው አባ ዲዲሞስ የዚህን መስቀል ቅርፅ በመጽሐፍ ቅዱሳቸው መሃል ስለውት አይተው ነበር። ይህን ባለጉጥ ግማደ መስቀል ፍለጋ አይደል እንዴ የቀበሮ ባህታዊ ሆነው ወደዚህ ገዳም የዝቡት? ለረጅም ጊዜ መስቀሉ ላይ ሲያፈጡ ሲጻራ ግራ ገባት። አባቷ አባ ፊንሐስም ሱዳን በረሃ ውስጥ ከመሞታቸው በፊት እንዲህ ያፈጡበት ነበር። አሁን ደግሞ አባ ዲምላ።

‹ምንድን ነው ምስጢሩ?› ይህ ባለጉጥ ግማደ መስቀል የምንጊዜም ፍቅሯን ሚራዥን ከማስታወስ ባለፈ ለእሷ ሌላ ምስጢር የለውም። ሚራዥ ካሰረላት ጊዜ ጀምሮ ከአንገቷ ወልቆ የማያውቀው ይህ መስቀል ዘወትር እንደ ጅረት ውሃ ቁልቁል ለሚያፈሳት ትዝታዋ የመፈለቂያ ምንጭ ነው። ከዚህ በቀር ሌላ ምስጢር አስራው የኖረችው መስቀል እንደያዘ አታውቅም። ስለዚህ መስቀል !ምታውቀው ምስጢር ቢኖር በሀሰቧ ከሚራዥ ጋር የምትገናኝበት የፍቅር ስጦታ መሆኑን ብቻ ነው።

"ወይ አባ ፊንሐስ!" አሉ አባ ዲምላ እጃቸውን ወደ ላይ እንደተማረከ ወታደር እንዳንጨባረሩ። "ይህን ምስጢረኛ መስቀል ማስረዎትን ባውቅ ኖሮ እሰግድልዎት ነበር እንጂ መች እንደዛ እዝትብዎት ነበር። ይበሉ ይቅር ይበሉኝ አሁን። ይቅር ይበሉኝ" በግንባራቸው ወለሉ ላይ ተደፉ። "ይቅር ይበሉኝ!" በውስጣቸው ቀጥለው ስለሚያደርጉት ነገር እያሰላሰሉ። መስቀሉን የሚቀሙበትን ዘዴ። ቀስ ብለው እየተሳቡ ከሲጻራ እግር ሲደርሱ ከአባ ፊንሐስ እግር ላይ የተደፉ መስለው ስበው ለመጣል እያሰቡም ነው። ግን ሽጉጡስ? ቀና ብለው አፈ ሙዙን ተመለከቱት።

"ተነሳ!" አሉ አባ ፊንሐስ። "ተነሳ!"
አባ ዲምላ ተነስተው ቆሙ።

"እሱ ዘንድ ተቀመጥ!" ሲጻራ ሽጉጧን በአባ ዲምላ እናት ላይ እንደነጣጠረች ታናዝዛቸው ጀመር።

"መስቀሉን ለምንድን ነው ይህን ያህል ያፈጠጥክበት?....ስለ መስቀሉ ምን የምታውቀው ነገር አለ?"

"እያውቁም መቼም አልልም። ሳያውቁትማ አያስሩትም መቼም። መስቀሉን! ይህን! ከእኔ የበለጠ እርስዎ ሳውቁት ቀርተው ነው?" በዚህ መስቀል ምስጢር ምክንያት አባታቸውን እንደ ገደሉ ትዝ አላቸው አባ ዲምላ።

"ይበሉ አባ ፊንሐስ ሽጉጡን ይመልሱትና እንነጋገር።"

"እሺ እንነጋገር" አለች ሲጻራ። ስለዚህ መስቀል ምስጢር የማወቅ ጉጉቷ እየናረ መጣ። ይህን ሰው በመጀመሪያ በኃይል ሳይሆን በጥበብ የመስቀሉን ምስጢር ለማውጣጣት ወሰነች።

"ሴት ነዎት ወንድ ግን ?"

"ሴትም ወንድም አይደለሁም። አሁን ሁለት ምርጫ ልስጥህ። ያየኸውን ነገር ለማንም መናገር አትችልም።የእኔ ሴትነት ወይም ወንድነት አያገባህም። ከተናገርክ ደሞ በህይዎትህ ፈርደህ መሆን አለበት።"

"የኖርኩት ሲሲሊ ውስጥ ነው። በኦሜርታ ህግ ስር ነው ዕድሜዬን የገፋሁት"

"ምን ለማለት ነው........"

«ኦሜርታ አይቶም ሰምቶም ዝም የማለት ህግ ነው። ይህን በልቤ እይዘዋለሁ። የእርስዎ ሴትነት ወይም ወንድነት ለእኔ እያስጨንቀኝም። ይልቅ በአንድ ነገር እንስማማ። የመበቀሉን ምስጢር ለጋራ እናድርግ እኔም የእርስዎን ሴትነት ወይም ወንድነት ለማንም አልናገርም። አንድ ነገር ተረድቻለሁ። ይህን መስቀል ከያዙ ወደዚህ ገዳም የመጡበት ምስጢር ግን አልገባኝም። እኔም እርሰዎም እዚህ ገዳም የመጣነው ፅድቅን ፍለጋ እንደላሆነ ተረድቻለሁ። አሁን እዚህ ገዳም ውስጥ ምን እፈልግ ይመስልዎታል? ፅድቅ? አይደለም። እኔ መፅደቅ አልፈልግም። ልፅደቅ ብል እንኳ የምፀድቅበት ምክንያት የለም። እዚህ ገዳም ውስጥ የምፈልገው ነገር ቢኖር ይህን መስቀልና የንጉሥ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ አፅም ብቻ ነው፡ መስቀሉን በእርስዎ እጅ ገባ በእኔ ምንም ማለት አይደለም። እርሰዎ መስቀሉን ይዘዋል። እኔ ደግሞ በውሃው ውስጥ ጠልቆ የሚቆፍርና በኮምፒውተር ትዕዛዝ ብቻ የሚቆፍር ጠላቂ ኤክስካቤተር-ዶዘር አለኝ። የሰጠመውን መርከብ በዚህ አይነት ትብብር ለሁለታችን ብቻ ማድረግ እንችላለን።" በዚህ ስምምነት የሰጠመውን መርከብ ካወጡ በኋላ ሴትም ትሁን ወንድ በአፍጢሟ እንደሚደፋት እርግጠኛ ነው።

ሲጻራ ምንም ሊገባት የቻለ ነገር የለም። አለማዎቋ እንዲንፀባረቅባት ግን አልፈለገችም። "የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ አፅም ደግሞ ለምንህ ነው?" አለች ገርሟት። ከመስቀሉ ጋር የሚያያይዘው ነገር ይኖር ይሆን? መጠየቅ እንደለባት ወስናለች።

"መጀመሪያ በደንብ እንተዋወቅ። እኔ ዲዎላ እባላለሁ። እርስዎስ አባ ፊንሐስ አይደሉም ግን? አባ ፊንሐስ ቢሆኑም ምንም ማለት አይደለም በእርግጥ። እኔ ቂመኛ ሰው አይደለሁም። ያለፈው አልፎአል። ካለፈ በደል ያሁኑ ይቅር መባባል ይበልጣል። ቂም ያጠቀረው ደም ሲጠራ ብኸርታ ያጨለመው የጋራ ራዕይም አብሮ ይጠራል። ሰዎችን በጠላን ቁጥር ራሳችንም በዛው ልክ



እንጠላለን።........ ቂም ቁዋጥረን ከኖርነው መቶ ዓመት በፍቅር የዋልነው አንድ ቀን ይበልጣል። ይቅር ከመባባል የሚገኘውን ትርፍ የሚተካ የለም። አባ ፊንሐስ። ይቅርታ ልብ ላይ እንጂ መሬት ላይ አይወድቅም። ይቅርታ ያድርጉልኝ አባ ፊንሐስ? "

"አባ ፊንሐስ አይደለሁም አልኩህ እኮ።"

"እንግዲያ ማን ነዎት?" ወለሉ ላይ ወደ ወደቀው የሴት መታዎቂያ ተመለከተ። እስከ አሁን ልብ አላለውም ነበር። "ሲጻራ ፊንሐስ" የሚል ስም ተፅፏል። መታወቂያው ላይ የአንጥረኛው ፊንሐስ ልጅ መሆንዋን ተረዳ። ግን በቀሉን ወደ ውስጥ ለጊዜው መዋጥ እንዳለበት ወሰነ። የአባቷን ፊት ገፍፋ ፊትዋ ላይ እንዳጠለቀችው ገብቶታል። እሷም እንደሱ ለዚህ መስቀል ብላ አባቷን እንዳረደች ጠረጠረ። ግዴለም እሱም የሚፈልገውን ከወሰደ በሁዋላ እንደሚያርዳት አረጋገጠ። እስከዚያ ግን ታማኝ ለመምሰል መጣር እንዳለበት አምኗል። ፈገግ አለ አይኑን ከመታወቂያዋ ላይ ነቅሎ።

"አብረን ብዙ ነገር መሥራት አለብን ማለት ነው። አባቶቻችን ለቂም ተፈላልገው ይሆናል እኛ ለፍቅር ብንፈላለግስ?" አለ ዲዎላ። "ሁሉን ነገር በምስጢር ይዘን ወደፊት እንጓዛለን። የኋላውን ወደኋላ ትተን። የአባትሽንና የአባቴን ነገር ወደኋላ ትተን እኔና አንቺ አብረን ለዚህ ነገር መስራት እንችላለን።"

"የጠየኩህን መልስልኝ ። የንጉሥ አፄ ዘርዓ ያዕቆብን አፅም ለምንህ ነው የምትፈልገው?"ዲዎላ ሁሉንም ነገር ተራ በተራ ተረከላት። ስለ ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ አፅም ምስጢርና ስለ ግማደ መስቀሉ ውስጣዊ ካርታ ሁሉን ዘረዘረላት። አንድ ጥያቄ ስትጠይቀው ግን ክው አለ ዲዎላ። ደነገጠ።

"የንጉሡን አፅምስ አገኘህ እንበል። ግን ጥይት እንደ ማያስመታ በምን ላይ ትሞክረዋለህ? ከአፅሙ ቅንጣቢ በአንገትህ ከአሠርክ በኋላ አፅሙ ጥይት እንደማያስመታ መሞከር አለብህ። አለበለዚያ ..... ማን ነበር ያልከኝ? የማፍያውን ስም?"

"ዶን ሞርሞርዲኖ።"

"የሞርሞርዲኖን ሰዎች ጥይት እንደማይመታህ እርግጠኛ ሆነህ እንዴት ትፋለማቸዋለህ?"

"መጀመሪያ አፅሙን ላግኝ።"

"ከዛስ?"

"በአንገቴ አስረዋለሁ።"

"ከዛስ?"

"አንቺ በሽጉጥ......"

"እሞክርሃለሁ። ከሞትክ ግን የለሁበትም።"

“ውይ!....... .......ይህማ የማይሆን ነገር ነው፡፡ መሞትማ አልፈልግም”

“ታዲያ በምን እናረጋግጣለን?”

“በእንስሳ እንሞክረዋለና!”

“እ..ህ! ለሰው ብቻ የሚሠራ ከሆንስ?”

“ውይ! ልክ ነሽ፡፡ ይህ ነገር ቢቀርብኝ ይሻላል፡፡”

“እዎ ይቅርብህ፡፡ ይልቅ አብረን ከሠራን ሁሉንም ነገር በእኛ ቁጥጥር ሥር እናደርገዋለን፡፡ ጥይት እተኩዋኮስ አለማምድሀለሁ፡፡ ጭንቅላትህን ካለማመድከው ከአስማትም በላይ ነው፡፡”

“እና እቅዱን ንገሪኛ! አንቺ ለምንድን ነው ወደዚህ ወደ ወንዶች ገዳም የመጣሽው?”

“እየውልህ መጀመሪያ በዚህ ደሴት ውስጥ ወደ ሚገኘው ዋሻ የምንገባበትን መንገድ እንፈልጋለን፡፡ ከዛ ዋሻውንና በዋሻው ውስጥ ያለውን በቁጥጥር ሥር ካደረግን በሁዋላ ወደሰጠመው መርከብ ፊታችንን እናዞራለን፡፡ ካርታው በእጃችን ነው፡፡ ይልቅ መጠንቀቅ ያለብህ ይህ ምስጢር ከአፍህ እንዳይወጣ ነው፡፡ ሴት መሆኔን ካወቁ በአንድ ደቂቃ ውስጥ ከዚህ ገዳም እንደሚያስወጡኝ አስብ፡፡ ከዚህ የበለጠ አደጋም አለው!”

“ተያቸው ባክሽ!” አለ ዲምላ ባዶ ድዱን ግልጢጥ አርጎ፡፡ “በወንዶች ገዳም ውስጥ የሚኖሩ መነኩሳት ልባቸው በሴቶች ገዳም ውስጥ ነው፡፡ ወሲብን ሽሽት! ዝሙትን ሽሽት! ግን....ወሲብን በመሸሽ ማምለጥ አይቻልም፡፡ ወሲብ አብሮን የተጠፈጠረ ነገር ነው፡፡ ወሲብን በሸሽነው ቁጥር የበለጠ ይቀርበናል፡፡ ወሲብ ሁሌም ከብልታችን ጋር ተጣብቆ በሄድንበት ሁሉ ይከተለናል፡፡”

“እሱ ራስ ምታቴ አይደለም” አለች ሲጳራ፡፡ “መፍጠን አለብን፡፡ ከሥድስት ቀናት በፊት ሁሉም አፕሬሽን መጠናቀቅ አለበት፡፡ ጭንቅላቱ ሳይፈነዳ......”

«የምኑ ጭንቅላት?»

«ተወው....ረጅም ታሪክ ነው,...»



# ፳፬

የኢንጅነሩ ህያው አስከሬን ወደ ዴርቶጋዳ ከገባ ከስምንት ቀናት በኋላ የሞቀው የአቀባበል ሥነ ሥርዓት ተዘጋጀለት፡፡ በዋናው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ የዴርቶጋዳ አባላት በሙሉ ቦታ ቦታቸውን ይዘዋል፡፡ ቲያትር ቤት የሚመስለው የመሰብሰቢያ አዳራሽ የመድረኩ ቀያይ መጋረጃዎች ሲገለጡ በነጩ ስክሪን ላይ ሳይንቲስት ኢንጅነር ሻጊዝ የሰራቸው ሥራዎች በፊልም መታየት ሲጀምሩ አባ ዠንበሩ ወደ መነጋገሪያው ሳጥን እያመሩ ነበር፡፡ ከኢንጅነር ሻጊዝ ሥራዎች መካከል በናሳ ውስጥ የፈጠራ ባለቤትነት ያስገኙለት ሁለት መንኮራኩሮች እና በናሳ የማምጠቂያ ማማ ወደ ህዋ የሚመጥቁ መንኮራኩሮችን የሚያሳየው ፊልም ቆሞ አባ ዠንበሩ ንግግራቸውን ቀጠሉ፡፡

«የተከበራችሁ የዴርቶጋዳ አባላት ከ፡አመታት በፊት ይህን ዋሻ መቆፈር ስንጀምር ይህን ያህል ዘመናዊ የምርምር ማዕከልና የኢትዮጵያ ምርጥ ምርጥ ሳይንቲስቶች የሚሰባሰቡበት ተቋም ይሆናል የሚል ህልም የለንም ነበር፡፡ ግን አንድ ጥሩ ነገር ለማድረግ ለሀገራችን ተመኝተንላት ነበር፡፡ ቀስ በቀስ ይህን ለማየት ታደልኩ፡፡ ዋሻውን ስቆፍር እየተጋረጡ ያስቸገሩኝ አለቶች ለካ አንድ ነገር እያስተማሩኝ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ አለት የምትሆንዋትን እናንተን በነዚህ አለቶች ላይ እንደማቆም እየስተማሩኝ ነበር፡፡ ተመኘሁ፤ አገኘሁ፡፡ ከዚህ በላይ የምመኘው ነገር የለኝም ፡፡ በአለም ዙሪያ እውቀታችሁንና ጉልበታችሁን ወዳችሁ ሳይሆን ተገዳችሁ ስትበዘበዙ የነበራችሁ ውድ የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ! ኢትዮጵያን ለኢትዮጵያውያን በቴክኖሎጂ ገንብታችሁ እንደምታስረክቧቸው አንዳችም ጥርጥር የለኝም፡፡» ጭብጨባው አስተጋባ፡፡

«ከኢራቅ፣ ከኢራን፣ ከራሺያ፣ ከጃፓን፣ ከእስራኤል፣ ከቻይና፣ ከኩባ፣ ከአሜሪካና ከግብጽ ምስጢራዊ የምርምር ጣቢያዎች የምታገኙትን እንክብካቤና ገንዘብ ትታችሁ ኋላቀር ሀገራችሁን ለመርዳት ከአለም ዙሪያ የተሰበሰባችሁ የዴርቶጋዳ ሳይንቲስቶች ዛሬ ደግሞ እናንተ ከመጣችሁበት አመጣጥ ለየት ባለና በረቀቀ መንገድ ከጐናችሁ ሆኖ ሀገሩን ለመገንባት ለመጣውና እስከ አሁንም በገንዘቡ የዴርቶጋዳን ዘመናዊ መሣሪያዎችና የረቀቁ የቴክኖሎጂ ማሽኖች ሲያስገባልን ለቆየው ለእውቁ የአለማችን የህዋ ሳይንቲስት ለናሳው የእኛ ሰው ኢንጅነር ሻጊዝ እጅጉ አክብሮታችሁን ትገልጹለት ዘንድ ንግግር እንዲያደርግ ጋብዙልኝ አመሰግናለሁ፡፡»

ጭብጫባው ጋብ ሲል ወደ መነጋገሪያ መድረኩ የወጣው ኢንጅነር ሻጊዝ ንግግሩን ቀጠለ፡፡ «.....እስከ አሁን ከሞት ላንቃ

ወጥቼ ከመካከላችሁ ለመገኘቴ እርግጠኛ አይደለሁም ነበር፡፡ አሁን ግን እርግጠኛ ሆኛለሁ፡፡» አለ በደስታ ተፍለቅልቆ፡፡

«እ....እኔን ለማዳን ያደረጋችሁት ጥረት አንድ ነገር እንድናገር እየገፋፋኝ ነው፡፡ ከአሁን በኋላ መዋሸት እንደሌለብኝ ይሰማኛል፡፡ እውነቱን ስነግራችሁም የምታደርጉብኝን ሁሉ ለመቋቋም ተዘጋጅቼ ነው፡፡» አቀረቀረ፡፡

በትካዜ የተዋጠ ፊቱን ሲያዩ ሁሉም ቀጥሎ የሚናገረውን ለመስማት ቋመጡ፡፡

«እኔ ኢንጅነር ሻጊዝ አይደለሁም፡፡» መልሶ አቀረቀረ፡፡ ከባድ ድንጋጤ በአዳራሹ ላይ ወደቀ፡፡ ሁሉም እርስ በእርስ በብዥታና በድንጋጤ ተያዩ፡፡

«እና አንተ ማን ነህ?......» ዶ/ር ሚራዥ ወደ መድረኩ በክራንቹ እየተመረኮዘ ወጣ፡፡

«እኔ......» ድምፁ በዕንባ ታነቀ፡፡

«እኔ.....ኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ እጦት ስንከራተት ኑሬ በኋላ በብዙ መከራ ወደ አሜሪካ የሄድኩ አንድ ተራ ሰው ነኝ፡፡ እንደ ኢንጀነር ሻጊዝ ታዋቂ ሳይንቲስትም አልነበርኩም» ግንባሩ ላይ ጭርር ያለ ላቡን ጠርጎ ንግግሩን ቀጠለ፡፡ «አሜሪካ ውስጥ በገባሁ በአምስተኛው አመት ሲ.አይ.ኤ መለመለኝ፡፡ ሰፊ ስልጠና ከወሰድኩ በኋላም በሰርጀሪ የኢንጅነር ሻጊዝን ፊትና መልክ እንድመስል ተደረገ፡፡ ድምፄም የእሱን እንዲመስል በቀዶ ጥገና ተስተካከለ፡፡ ከዛ በኋላ ለስድስት አመታት የኢንጅነሩን ታሪክ፣ ሥነ ልቦና እና ከቤተሰቦቹና ካንዳንድ ከሚያውቃቸው ሰዎች ጋር የሚያደርጋቸውን ውይይቶች ሳጠና ኖርኩ፡፡ በተለይ በ1998 ዓመተ ምህረት ኢንጅነሩ ሙሉ በሙሉ ወደ ኢትዮጵያ እና ወደ ፖለቲካዋ መስመጡን ተከትሎ ኢትዮጵያን ጨምሮ ብዙ ሀገሮች ስላጠመዱት ለመሰወር ሲባል እኔን በመግደል ሞቷል ለማለት ወሰኑ፡፡ እኔም በገና ዋዜማ ወደ ቤተሰቦቹ ሄጄ ከልጆቹ ጋር የቅርጫት ኳስ እየተጫወትኩ እንድወድቅ ተደረኩ፡፡ ተዝለፍልፌ ከወደኩም በኋላ ወደ ሰሜን አውስቲን የህክምና ማዕከል ተወሰድኩ፡፡ ለቤተሰቦቹ ብዙ ገንዘብ በባንክ ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ የተስማማሁት ለመሞት ነበር፡፡ ከቀዶ ጥገናው በኋላ እኔን በማያሰቃይ መልኩ እንደምገደል ቃል ተገብቶልኝ ነበር፡፡ በኋላ ግን መጥታችሁ አዳናችሁኝ፡፡ ወይ ፈጣሪ!....እኔን ሊያድን ማን ይመጣ ነበር!? ዳንኩ! አመለጥኩ!....ከሞት መንጋጋ አወጣችሁኝ፡፡ ሁሁ!....How can I believe it!?...ዳንኩ!.....አመለጥኩ...» መቀባጠርና መድረኩ ላይ በደስታ መዝለል ጀመረ፡፡ እንደ ህፃን እረገው፡፡ ፈነጠዘ፡፡

«......እርግጠኛ ነህ ኢንጅነር ሻጊዝ አይደለህም?!......» ዶ/ር ሚራዥ በንዴት ጡፎ የለበሰውን ሸሚዝ አወለቀበትና ጀርባውን



ገልጦ ማየት ጀመረ፡፡ ከጀርባው «ዴርቶጋዳ» የሚለው ንቅሳት እንደ ሌለ በማስተዋሉ በእርግጥም ኢንጅነር ሻጊዝ እንዳይደለ አመነ፡፡ ፊቱና ቁመናው በተለይም የራሱ ላይ በራ ቁርጥ ጣል ኢንጅነር ሻጊዝን ስለሚመስል' ማንም ሰው ኢንጅነር ሻጊዝ አይደለም የማለት ድፍረት አይኖረውም፡፡

«አዎን፡፡ ይህ ሰው ኢንጅነር ሻጊዝ አለመሆኑን አረጋግጫለሁ፡፡ኢንጅነር ሻጊዝ አይደለም፡፡»አለ ዶ/ር ሚራዥ ተሰፋው በሰለለ ድምፅ፡፡

«አልነገርኳችሁም እኔ ኢንጅነር ሻጊዝ አይደለሁም፡፡ እኔ ማታያስ ማሞ ነኝ፡፡ ዘመዶቼን በተለይም በችጋር ስትጠበስ የኖረችውን እናቴን ከድህነት ለማላቀቅ ራሴን ለሞት አሳልፌ ሰጥቼ ነበር፡፡ አሁን ግን ከሞት አዳናችሁኝ፡፡ ስለዚህ ባሪያችሁ አድርጋችሁ ልታሰሩኝ ወይም ይህን የሚያህል ሌላ ዋሻ ልታስቆፍሩኝ ትችላላችሁ፡፡ መንኮራኩር ዲዛይን የሚያደርግና እንደ ኢንጅነር ሻጊዝ በቴክኖሎጂ የበለፀገ ጭንቅላት ግን የለኝም፡፡ ፊቴ እንጂ ጭንቅላቴ የእሱን አይደለም፡፡ ቅጂው ሻጊዝ ነኝ፡፡ ከሻጊዝ ላይ የተቀዳሁ፡፡ ፎርጅዱ ሻጊዝ!......ግን አንድ ነገር ልንገራችሁ፡፡ ከታሪካችን ጠባሳዎች አንዱን አስታውሱ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ በረሀብ ምክንያት እናት የልጇን ሥጋ በልታለች፡፡ ረሀብ ክፉ ነው፡፡ ያበላላል፡፡እንኳንስ አንድ ሰው ሀገር ያሸጣል፡፡ እኔም እንደናንተ ሀገሬን እወዳታለሁ፡፡ ግን ድህነቷ ራሴን ለሞት አሳልፌ እንድሰጥ አደረገኝ፡፡ አሁን ግን አዳናችሁኝ፡፡ ባትፈርዱብኝ የምለምናችሁ አንድ ነገር ብቻ ነው፡፡ ሀገሬን እንድረዳት እድል ስጡኝ፡፡ ከእናንተ ጋር ለለውጥ ሳልደክም እሰራለሁ፡፡ ተራራም ቢሆን ለመናድ ዝግጁ ነኝ!»

«ኢንጅነሩ የት ነው ያለው አሁን?» አባ ዝ'ንበሩ ወደ መድረኩ እየተንገዳገዱ ወጥተው በቁጭት አንባረቁበት፡፡

«ኢንጅነሩ የት ነው?!....ሻጊዝ የት ነው?!......» አዳራሹ በሙሉ ተንጫጫ፡፡

«ኢንጅነር ሻጊዝ በናሳ ዋና መስሪያ ቤት አቅራቢያ በሚገኝ የምድር ውስጥ የምርምር ጣቢያ የሆነ ነገር እንዲሰራ በግዴታ ታግቶ ሳለ እኔ እየሄድኩ ስለቤተሰቦቹ፣ ከቀድሞዋ እስራኤል አሜሪካዊት ሚስቱና ከልጆቹ ጋር የምግባባበትን መንገድ በግዴታ እየተጠየቀ ሳጠና እዛ ውስጥ አይቼው ነበር፡፡ በኋላ ግን ከዛ አውጥተው የት እንዳደረሱት አላውቅም፡፡ » ሁሉም በሃዘን ኩምሽሽ ብለው ተመለከቱት፡፡ ታላቅ ሀዘን ወደቀ፡፡ ዝምዝምታ፡፡ ከዚያ ደግሞ ....ጉምጉምታ......

# ፳፫

በድቅድቁ የጨለማ ግሣት ውስጥ ወደ ዕቃ ቤቱ ግቢ በግንቡ ላይ ተንጠላጥለው ሲገቡ የዕቃ ቤት ጠባቂው የመጠበቂየ ቤት በር ተከፍቶ ነበር። የመቅረዙ ብርሃን ዕቃ ቤት ጠባቂውን አጋልጧቸዋል። ትልቅ የብራና መፅሐፍ ዘርገተው አፋቸውን ሳያንቀሣቅሱ እያነበቡ ነው።

ጨለማው ውስጥ ተወሽቀው የመነኩሴውን እንቅስቃሴ የሚከታተሉት ዲምላና ሲጻራ በሹክሹክታ እየተነጋገሩ ነው። "እየሽ አላልኩሽም!?" አላ ዲምላ።

«አንቺ አትበል አላኩህም? እርስዎ በል እኮ ብዬህ ነበር። አሁንም ደግሜ አስጠነቅቅሃለሁ አባ ፊንሐስ እንጂ ሲጻራ ብለህ እንዳትጠራኝ። አባ ፊንሐስ ነኝ በቃ።"

"እሺ አባ ፊንሐስ። አላልኩዎትም? መነኩሴው የያዛቸው መዓት ቁልፎች ይታዩዎታል? ብዙ ቁልፎች ናቸው። እዚህ ገዳም ውስጥ የሚከፈቱ በሮች ግን በጣም ጥቂት ናቸው። ስለዚህ እኒህን መነኩሴ....." ንግግሩን አቋረጠ መነኩሴው የሚያደርጉትን ተመለከተ።

መነኩሴው የወለሉን ቀያይ ምንጣፎች ገልጠው ወለሉን ማጭድ በመሰለ ቁልፍ ከፈቱት። ወለሉ ላይ በከፈቱት በር ቁልቁል ገቡ። አባ ፊንሐስ የሩቁን አቅርቦ በሚያሳየው መነፅራቸው የዕቃ ቤቱ ጠባቂ ከወለሉ በታች የገቡበትን በር ሲያዩ በረጅሙ ተንፍሰው አባ ዲምላን ጎሰሙአቸው። ሁለቱም እንደነበር ተስፈንጥረው ወደ መጠበቂያው ቤት ገቡ። የመቅረዙን መብራቶች አጥፍተው ጠባቧ ቤት ውስጥ ትንፋሻቸውን አጥፍተው ተቀመጡ።

ወለሉ ላይ በተከፈተው በር ቁልቁል የወረዱት መነኩሴ ተመልሰው ወደ መጠበቂያው ቤት ወለል ብቅ ሲሉ የመቅረዙ መብራቶች በመጥፋታው ሊያዩ ያቻሉት ነገር የለም። ወዲያው አንገታቸውን የሆነ ጠንካራ እጅ ፈጠረቃቸው። አፋቸው ውስጥ ደግሞ ወፍራም ጨርቅ ተጎደጎደ። መተንፈስ ያቻሉበት ቅፅበት የለም ነበር። ተዝለፈለፉ።

አባ ዲምላ የዕቃ ቤት ጠባቂውን ሞት እንዳረጋገጡ የመነኩሴውን አንገት የፈጠረቁበት ጠንካራ ክንደቸውን ከመነኩሴው አንገት ላይ አነሱ። ህይዎታቸው የተጠናቀቀውን መነኩሴ በቀዩ የወለሉ ምንጣፍ ጠቅልለው ወደ ጎን በድናቸውን ካስቀመጡት በሁዋላ የመጠበቂያውን ቤት በር ከውስጥ ጠርቅመው ዘግተው የመቅረዙን ሻማዎች ለኮሱአቸው። ከመነኩሴው እጅ በመከራ



ከተፈለቀቀው የቁልፍ መያዣ ማዕተብ ውስጥ ያሉትን ቁልፎች በእጃቸው ካስገቡ በሁዋላ በተከፈተው የወለሉ በር ቁልቁል ወረዱ።

"መመለስ አለብህ።" አለች ሲጻራ ቱቦ በሚመስለው የዋሻው ውስጥ መንገድ ላይ ቆም ብላ። " እንዴት?" አለ ዲምላ እርምጃውን ገታ አድርጎ።

"የዕቃ ቤት ጠባቂውን እኮ ገድለናቸዋል።"

"እኮ?"

"ማሸሽ አለብህ።"

"ምን? "

"ተመለስና በድናቸውን አሽሽ።"

"አንቺስ?"

"እኔ ወደ ዋሻው እገባለሁ።"

"ወደየት ነው የማሸሸው?"

"ቅበራቸው አለበለዚያ.........?"

"እሺ ቁልፉን አምጭው!"

"የትኛውን ቁልፍ?"

"መስቀሉን... የሰጠመውን መርከብ ቁልፍ።"

"እሱንማ አልሰጥህም። እንደተነጋገርነው ፊታችንን ወደ ሰጠመው መርከብ ለመመለስ መጀመሪያ ሰው አልባዋ ደሴት ላይ ተቀምጦ የላከህን ጣሊያናዊ ልታስወግደው እንደሚገባ ተነጋግረናል። ሁለት ተልእኮዎችን ማጠናቀቅ አለብህ በመጀመሪያ። የመነኩሴውን በድን አጥፋ-- አንድ። ሞርሞርዲኖን ደምስስ-ሁለት። እኔም እዚህ ዋሻ ውስጥ ሥራዬን ልጨርስ። ከዛም ተገናኝተን የሰጠመው መርከብና በውስጡ ያለው የእኛ ይሆናል።"

ዲምላ ወደ መጣበት ተመለሰ። የወለሉን በር ዘግቶ በቀዩ ምንጣፍ የተጠቀለለውን የመነኩሴውን በድን ተሸክም ከወጣ በሁዋላ የመጠበቂያው ቤት በር ቆልፎ የዕቃ ቤቱን ግቢ ለቆ ወጣ።

ሲጻራ ማጭድ በመሣሠሉት ቁልፎች የዋሻ ውስጡን በሮች እየበረገደች ስትገባ ዋሻው በአደጋ ጊዜ ጥሪ ድብልቅልቅ አለ። ወዲያው አውቶማቲክ መሣሪያ የታጠቁ ሰዎች ዙሪያውን ከበቧት ሁሉም ጭንቅላቷ ላይ አነጣጥረዋል። ሁለት እጆችዋን ወደ ላይ አንጨፍርራ እጇን ሰጠች። እጆችዋን በሰንሰለት የፍጥኝ አሰሯትና እያዳፉ ቁልቁል ወደ ሚያወርደው አሳንሰር አስገቧት።

የአሳንሰሩ በር ተከፍቶ ካስወጧት በሁዋላ ወደ አንድ ጨለማ ክፍል አስገብተው ዘጉባት።

ከቆይታ በሁዋላ ሁለት ሰዎች ወደ ጨለማው ክፍል እንደገቡ ጨለማው ክፍል በብርሃን ተሞላ። የሁዋሊት እጆችዋ ታስረው ወለሉ ላይ እንደተቀመጠች የገቡትን ሁለት ሰዎች አፈራርቃ ተመለከተቻቸው። አንደኛውን ወዲያው አወቀቻቸው። አባ

ዝንበሩ ናቸው። ሁለተኛው ግር አላት። አዲስ ፊት አልሆነባትም። በጣም አፍጣ ተመለከተችው። የምታውቀው ይመስላታል። ‹የት ነበር ያየሁት?› በፍጥነት ማሰብ ጀመረች። አዕምሮዋ ወደሁዋላ ተፍጠነጠነ። እንዴት ሊሆን ይችላል? ለዘመናት ስትፈልገው የኖረችው ሰው እዚህ ዋሻ ውስጥ ምን ሊሰራ መጣ? ሚራዥ ሊሆን ይችል ይሆን እንዴ? በፍፁም ሊሆን አይችልም። ከፊቷ የቆመው ጎልማሳ በውስጧ ለዘላለም የኖረው ሚራዥ ምስላቸው ይቀራረባል። በዚህ ሰው ውስጥ ልቧን በፍቅር ሲያደማ የኖረው ሚራዥን አየችው ።

አባ ዝንበሩ ክፍሉ ውስጥ እየተንጎራደዱ ሲዞሩአት እሷ ግን ዓይኗን ካየችው ጎልማሳ ላይ ለመንቀል ተስኗታል።

"አባ ፊንሐስ!" አሉ አባ ዝንበሩ ለረጂም ዲቂቃዎች እየተንጎራደዱ ከቆዩ በሁዋላ "ወንጀልህ ሁልቆ መሳፍርት ሊኖረው አልቻለም። የተለወጥክና ንስሐ የገባህ መስሎኝ በዚህ ገዳም እንድትኖር ፈቅጄልህ ነበር። አሁን ግን ሳይፈቀድልህ በጉልበት ወደዚህ ዋሻ ሰብረህ ገባህ!"

«አባ ፊንሐስ ናቸው እንዴ?» ሚራዥ እጁን ወደ ሽንጡ ላከው።

«አዎ ናቸው። አባ ፊንሐስ!» ሽጉጡን ከሽንጡ ልጦ ግንባራቸው ላይ አነጣጠረው። "ሲጻራ የት ናት?" እንባራቀባቸው።አባ ፊንሐስ ግን ምላሽ ሳይሰጡት እስከአሁን አፍጥጠው እየተመለከቱት ነው።

"አባ ፊንሐስ ...... ትዝ አልኩዎት? እኔ ሚራዥ ነኝ። ሲጻራን የት አደረሷት?"

ሚራዥ ከንፈሩ ተንቀጠቀጠበት። "ምላጬን ከመሳቤ በፊት ያለችበትን ይንገሩኝ።"

አባ ፊንሐስ ቡዝዝ ብለው እያዩት በዚያው ከዓይናቸው ዕንባ ፈሰሰ። "ሚ.......ሚ...ሚራዥ በህይዎት አለህ? የኔ ፍቅር አለህልኝ እውነት? ይህን ያህል ዘመን ስፈልግህ ነበር እኮ የኖርኩት።"

"የምጠይቅዎትን ብቻ ይናገሩ። ሲጻራ የት ናት?"

"አይ.... እንዲህ ናቸው ድሮም። የተጠየቁትን ሳይሆን.... መናገር የሚፈልጉትን ነበር ድሮም የሚመልሱት። ያ ጠባያቸው ተጠናክሮ ቀጥሏል። አጭበርባሪነታቸውም ንሯል። እንዲህ ናቸው አባ ፊንሐስ" አባ ዝንበሩ በመሰላቸት መንፈስ ተወራጩ።

"እኔ አላምንም! ሚራዥ ብዙ ጊዜ ተስፋ ቆርጬ ነበር። በውስጤ ያረገዝኩትን ምስልህንና ፍቅርህን ተሸክሜ እኖራለሁ ብዬ እንጂ በአካል አንተን የማግኘት ተስፋዬ ተሟጦ ነበር።"

"ምንድን ነው እያወሩ ያሉት?"



"ሲጻራ ነኝ። ሚራዥ.... እኔ ነኝ ሲጻራ። እያየውህ ነው። አንተ ግን ልታየኝ አትችልም። በአባቴ ፊትና በአባቴ ወንጀል ተሸፍኛለሁ" ሲጻራ ይህን ስትናገር አባ ፊንሐስነቷን ዘንግታው ነበር። ድምፅዋ እንደተቀየረ ታውቃለች። ፊቷም ድምፅዋም የአባቷ ነው። በምን ሊለያት ይችላል? እሷነቷን በምን ሊያረጋግጥ ነው? አንድ ሀሳብ መጣለት።

"እመነኝ ሚራዥ። እኔ ሲጻራ ነኝ!.......... እኔን ብትረሳኝ ስጦታህን አትረሳውም። የኸውና መስቀሉ በልጅነታችን ደሴት ላይ ያሰርክልኝ ባለጉጥ መስቀል ይኸውና። የእጄን ሰንሰለት ፍታልኝና ላሳይህ።"

የኒሊት የተጠፈነጉ እጆችዋን ከሰንሰሉቱ ነፃ ሲያደርግላት የለበሰችውን የምንኩስና ቆሚስና መደረቢያ አወላልቃ ዕርቃኗን ቆመች። በጡቶቿ መሃል በወረደው ሃብል ላይ የተንጠለጠለውን ባለጉጥ መስቀል ሲያይ ቅፅበታዊው ትዝታው እንደ መብረቅ ብልጭ አለለት...መስቀሉን ሲያሰርላት...አባ ፊንሐስ እያስሙሁ ሲወስዷት...

ከላይ ፊቷን አየ። የጢማም መነኩሴ ፊት። የወንድ ፊት። ከአንገቷ በታች ደግሞ የተዋበች እንስት። ዕድሜ ልኩን ሲፈልጋትና ሲያስባት የኖረችው ሲጻራ ልትሆን? ግራ ተጋባ።

# ፳፯

ዲምላ የዕቃ ቤቱን ጠባቂ አስከሬን ተሸክሞ የዳጋን ደሴት ቁልቁለት ከወረደ በሁዋላ ወደቡ ላይ ቆሞ ጥቂት አሰላሰለ፡፡ የጣና ሐይቅ ማዕበል ከወደቡ ጋር ወደ ሚያጋጨው አሮጌ ታንኳ በድኑን እንደተሸከመ ገብቶ እየቀዘፈ ወደ ደሴቱ ምዕራባዊ አቅጣጫ አመራ፡፡ ከደሴቱ ምዕራባዊ አቅጣጫ አምስት መቶ ሜትር ያህል እንደቀዘፈ ታንኳው ላይ የጫነውን አስከሬን ወደ ሐይቁ ገፈተረው፡፡

በደቅ ደሴትና በዳጋ እስጢፋኖስ ደሴት መካከል በጉረር ወደብ አቅራቢያ ባለችውና የደሀ ሰው መዳፍ ወደምታህለው ሚጢጢ ደሴት አሮጌውን ታንኳ እየቀዘፈ ሲደርስ ትንሽዋ ደሴት ሞቅ ደመቅ ብላ ነበር፡፡ ጨረቃዋ በደሴትዋ አናት ላይ ቆማ ቁልቁል ለደሴትዋ ብቻ የምታበራ ይመስላል፡፡ ከደሴትዋ ወደብ ጥግ ትልቁ የሞርሞርዲኖ ጀልባ እንደቆመ ነው፡፡ ዲምላ በዚህ ጀልባ ያለውን ጠላቂ ኤክስካባተር-ዶዘር ሲያስታውስ ጠላቂውን ኤክስካባተር-ዶዘር ለመንዳት በፓሌርሞ ወደብ አቅራቢያ ሲያደርገው የነበረው ልምምድ ትውስ አለው፡፡ ይህንን ጠላቂ ኤክስካባተር-ዶዘር ለማሰራት ሞርሞርዲኖ ያወጡት ወጪ እና የፈጁት ጊዜም ትዝ አለው፡፡ ወደቡን አልፎ ወደ ደሴትዋ ሲገባ በድንኳኖች ውስጥ ሳቅ ደምቋል፡፡ የሚንደቀደቀው ጀነሬተር ድንኳኖች ውስጥ ብርሃን ለሚፈነጥቁት አምፑሎች የብርሃን ምንጭ ከመሆኑ በቀር በዚህች ደሴት ሌላ የሚሠራ ነገር የለም ፡፡

ሞርሞርዲኖ የሚጠባበቁት ነገር ቢኖር ዲምላንና ካርታውን ብቻ ነው፡፡ ካርታውን ብቻ እንጂ፡፡ በዘቦች ተፈትሾ ዲምላ መሆኑ ከተረጋገጠ በሁዋላ ሞርሞርዲኖ ወዳሉበት ድንኩዋን ተወሰደ፡፡ ጠባቂዎቹ አውቶማቲክ መሣሪያ ታጥቀው በተጠንቀቅ ይጠብቁታል፡፡ በሰፊው ጠረጴዛ ላይ በውድ የጣላያን መጠጦች የተሞሉ ብርጭቆዎች ተሸኮትኩተዋል፡፡ ከአሥር የሚበልጡ ሰዎች በጠረጴዛው ዙሪያ ተቀምጠው አልኮሉን እየተጎነጩ ይሳሳቃሉ፡፡

ዲምላ ወደዚህ ድንኩዋን እንደገባ ሞርሞርዲኖ ከተቀመጡበት ተነስተው በደስታ ተቀበሉት ፡፡ በጠረጴዛው ዙሪያ ከተቀመጡት ሰዎች መሀል በዚህ ምሽት የመጣውን ባለስልጣን አስተዋወቁት፡፡ በጥቁዋቁር መነፅራቸው ውስጥ ሚመለከቱት የሚኒስትሩን የግል ጠባቂዎች በየተራ ገረመማቸው፡፡

"ክቡር ሚኒስትር......" ብለው ሲያስተዋውቁት በውስጡ "ሚኒስትር ወይስ መንጥር?" ሲል አንሾካሾከ፡፡ «ይህ ሁሉ ተባይ እዚህች ደሴት ላይ አሰፍስፎ እየጠበቀ ያለው እኔን አይደል?



ለመቀራመት! ህ! አሳይሀለሁ እያንዳንድህ! ባሪያ ሆኜ መኖር ካልፈለኩ በቀር ለዚህ ሁሉ ወፈሰማይ የሰጠመውን መርከብና በውስጡ ያለውን ሀብት ዓይኔ እያዩ አልሰጠውም፡፡» በውስጡ ከራሱ ጋር ተማከረ፡፡

ሞርሞርዲኖ በጠረጴዛው ዙሪያ ያሉትን ሰዎች ከሚኒስትሩ በቀር በምልክት እንዲወጡ ካደረጉ በሁዋላ "ባሪያው! ስራህን ጨርሰህ መጣህ አይደል?" አሉት የተጎነጩትን ወይን እያጣጣሙ፡፡ ምላሳቸውን ከላይኛው ላንቃቸው ላይ ሲያላቅቁት እንደ ጅራፍ አጩኸው፡፡

"አልጨረስኩም" አለ ዲምላ፡፡ "አንድ ነገር ይቀረኛል፡፡ አውቶማቲክ መሣሪያ፡፡"

"ለምን?" አሉ ሚኒስትሩ ፡፡ "ለእሱ አትጨነቅ እሳት የሚተፉ መትረዬስ እሰጥሃለሁ፡፡"

"አሁን ነው የምፈልገው፡፡ አሁን!" አለ ዲምላ እየተነሳ፡፡ "ጊዜ መፍጀት የለብንም፡፡"

ሚኒስትሩም ተከትለውት ተነሱ፡፡ ሚኒስትሩ እየመሩ ደሴቷ ላይ ከመሼ ወዳረፈችው አነስተኛ ሄሊኮፍተር ወሰዱት፡፡ ሄሊኮፍተሯ ውስጥ የተቀመጠውን አውቶማቲክ መሣሪያ እያወረዱ "ይሄውልህ፡፡" አሉት፡፡ "ምስጢሩን ጠብቀህ ልትጠቀምበት ትችላለህ፡፡"

"የእጅ ቦንቦችም ያስፈልጉኛል፡፡" አለ ዲምላ፡፡

"ለምንህ?" አሉ ሚኒስትሩ፡፡ "ሶስተኛውን የዓለም ጦርነት ለመጀመር አስበሃል እንዴ?"

"የተከበሩ ሚኒስትር!?" አለ ዲምላ አውቶማቲኩን ጠመንጃ እያስተካከለ፡፡ "ይህ ለእኛ አራተኛው ወይም አንደኛው የዓለም ጦርነት ቢሆን አይደንቀኝም፡፡"

ዶን ሞርሞርዲኖ ቡስኪ የጣና ሐይቋን ብጣቂ ደሴት በኢንቨስትመንት ሥም ሲሰፍሩባት የሰጠመውን መርከብ ምስጢር ለዚህ ሚኒስትር ለመንገርና እገዛ ለማግኘት ለምን እንደፈለጉ ዲምላ ያውቃል፡፡ ይህ ጉዳይ ወደ አራት ኪሎ ቤተ መንግሥት ያልደረሰበት ምክንያት ለዲምላ ግልፅ ነው፡፡ በቤተ መንግሥቱ ዙሪያ የተጠመዱ እሳት የሚተፉ ከባድ መሣሪያዎች ይህ ምስጢር እዛ ቢደርስ ኖር ሞርሞርዲኖ ላይ ላለመርከፍከፋቸው ማንም እርግጠኛ አይሆንም፡፡ ግን...ሞርሞርዲኖ ሁሌም የሚሠሩትን ያውቃሉ፡፡ ከማን ጋር ምን መሥራት እንዳለባቸውም ጠንቅቀው የሚያውቁ ሰው ናቸው፡፡ ይህን ሚኒስትር ለሸፋን የተጠቀሙት አቅመ ቢስ መሆኑን ስለሚያውቁ ነው፡፡ አቅመ ቢስ በመሆኑ ብቻም አይደለም ቅንጣት ታህል ሀገራዊ ፍቅር ስላላዩበት ነው፡፡ አቅመቢስና ቅንጣት ታህል ሀገራዊ ፍቅር ስላላዩበት ብቻም ሳይሆን በቀላሉ ሊጠመዘዝ የሚችል ሰው በመሆኑም ነው፡፡ ይህ ምስጢር

ካራት ኪሎው ሰውየ ዘንድ ደርሶ ቢሆን ኖሮ እንኳንስ እርሳቸው ወፎችና ዓሣ ጠልቀው የሚያወጡ አሞራዎች እንኳ ጣና ሐይቅ ላይ ማረፍ እንደማይችሉ አስቀድመው ያውቃሉ። እሳት የሚተፉት የአራት ኪሎ ከባድ መሳሪያዎች ጣና ሐይቅን ከበው እንደሚጠብቁ በባህርዳር የባህር ትራንዚት ወደብ ጥግ እስከ አሁን ሥራ ላይ ሳትውል የተቀመጠችው የመንግስት ጠላቂ መርከብ የጣናን ሆድ እቃ እንደምታስስ እርግጠኛ ነበሩ። እንዲያውም በባህር ዳር ወደብ አቅራቢያ ያለሥራ የቆመችውን ጠላቂ መርከብ ያዩ ጊዜ ልባቸው በአፋቸው ቁር ብላ እስክትወጣ ደንግጠው ነበር። ምስጢሩ የተደረሰበት መስሏቸው። ሲሰሊ ብዙ ያስተማረቻቸው ሞርሞርዲኖ ግን ይህ ሚኒስትር ለእነሱ ብዙም አስጊ እንዳልሆነ ለዲምላ ነግረውታል።

ዲምላ በእጅ ቦንቦች የተሞላውን ዝናር ከታጠቀና ዘመናዊውን አውቶማቲክ መሣሪያ ጥይት ካቃመው በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሰማይ አንጋጦ ጨረቃዋን ተመለከተ። ሌሊቱ ከመገባደዱ በፊት ይህንን ለመጀመሪያ ጊዜ የግሉ የሆነውን ተልዕኮ ማጠናቀቅ እንዳለበት ወስኗል።አውቶማቲክ መሣሪያዎች የታጠቁትን የሞርሞርዲኖን ጠባቂዎችና የሚኒስትሩን አጃቢዎች በየቦታው በዝግታ ቃኛቸው። ሁሉም በተጠንቀቅ ቆመዋል። እንዴት ሊጋፈጣቸው ይችላል? የልብ ምቱ ፈጠነ። የደም ዝውውሩ የቆመ መሰለው። አንዲት ጥይት ሳይተኩስ ጭንቅላቱን እንደሚበሳሱት እርግጠኛ ነው።

ወደ ዶን ሞርሞርዲኖ ቀርቦ "ሰዓቱ እየደረሰ ነው" አላቸው ባዶ ድዱን ግልጢጥ አድርጎ።

"የትኛው ሰዓት?"

"ሁሉምን ነገር በእጃችን የምናስገባበት። ይህ ሚኒስትር ግን......" አለ ዲምላ በለሆሳሳ። ሚኒስትሩን ዞሮ ለአፍታ በቆረጣ ተመልክቶ። ጣልያንኛ እንደማይሰማም ያውቃል። እያማጠ ከሚናገረው ሰበርባራ እንግሊዝኛ በቀር። "ባክህ ተወው!" አሉት ሞርሞርዲኖ "ስለዚህ ገርሼ ሚኒስትር አትጨነቅ። ብቻ ካርታውን በእጃችን እናስገባ። ሚኒስትሩ ጠመንጃ እንጂ ጭንቅላት የለውም። እዚህ አገር ጭንቅላት ያለው ሰው አይሾምም አላልኩህም? ያለነው አፍሪካ ውስጥ ነው። ሊያውም ከአፍሪካዊቷ መናኛ ሀገር ኢትዮጵያ ውስጥ። ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገዛህ ሕግ ሳይሆን ጠመንጃ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ማንኛውም ሰው ከጠመንጃ በታች እንጂ ከህግ በታች አይደለም። የሲሲሊ ማፍያዎችና ካፖዲካፒዎች ሲሲሊን የሚገዟት ባልተፃፈና በማይገረሰስ ህግ ሲሆን የኢትዮጵያ መሪዎች ደግሞ ኢትዮጵያን የሚመሯት በተፃፈና መሪዎችን በማያካትት ህግ ነው። ማንም እረኛ ሚኒስትር ቢሆን ግዴለኝም እኔ



ሞርሞርዲኖ! እንኳንስ ከዚህ ነፈዝ ሚኒስትር ከስንት ጅቦች መንጋጋ ውስጥ ስንት ነገር እንደነጠቅን ሲሲሊ ትመስክር።" ሞርሞርዲኖ በሹክሹክታ ሲናገሩ ቆይተው ሚኒስትሩ ወደነሱ ሲመጣ የዲምላን ትከሻ ቸብቸብ አደረጉና ፀጥ አሉ። ዲምላ መሬት ላይ እቃ የጣለ ይመስል አቀርቅሮ ሲያስላስል ከቆዩ በኋላ ወደ ሞርሞርዲኖ ቀና ብሎ "በዚህች ደሴት ላይ ያለ ሁሉም ሰው ድንኳኑ ውስጥ ለስብሰባ እንዲጠራ እፈልጋለሁ" አለ።

"ችግር የለም!" አጨበጨቡ ሞርሞርዲኖ። "ሁላችሁም ወደ ድንኳኑ ግቡ!" ሁሉም ድንኳኑ ውስጥ ገቡ። ሚኒስትሩና ሞርሞርዲኖ ብርጭቆአቸውን እንደገና ሞልተው ወይናቸውን መጎንጨት ጀመሩ። በዚህ ስብሰባ ለመካፈል በጠረጴዛው ዙሪያ ከተቀመጡት የቆሙት ብዙ ናቸው። ተሰበሰቡ እንጂ የሚነጋገሩበት ጉዳይ ምን እንደሆነ ማንም አያውቅም። ስብሰባው የተጠራበት ምክንያት ምን እንደሆነ የሚያውቅ ዲምላ ብቻ ነው። ዲምላ ጉሮሮውን ጠራረገ። ብቸኛዋ አንዲት ዓይኑ የተጨቀጨቀ በርበሬ መስላ ቀልታለች። አፉን ደም ደም አለው።

"አሁን የተሰበሰብንበት ምክንያት ........"

ጉሮሮውን አሁንም ጠራረገ። "ያልታደለች ትንኝ! ..እእእ!... ያልታደለች ትንኝ በተከፈተ አፍ ትገባለች!....... እእእ!......"

ሞርሞርዲኖ ከት ብለው ሳቁ። ሚኒስትሩም ሳቁን ለመጋራት ተንፈቀፈቀ። ዲምላም ደሴቱን የሚያናጋ ሳቅ አመለጠው። ቀይ ባዶ ድዱን ሲያዩ ድንኩዋኑ ውስጥ ያሉት ሁሉም ሳቅ በሳቅ ሆኑ። ወዲያው ደግሞ ድርቅ አለ ዲምላ። ሳቁን ገታው። "ይቅርታ ..... እእእእ! ......." ዲምላ ጉሮሮው እስኪሰነጠቅ እየጠራረገ ሲወጣ የሚኒስትሩና የሞርሞርዲኖ ሳቅ አላባራም ነበር። የወይኑ ዱቅዱቅታና የብርጭቆዎች ግጭት "ችርስ!" ከሚለው ቃል ተደባልቀው እየተሰሙት ራቅ ብሎ ወደ ድንኳኑ ዞሮ ቆመ።

ወዲያው ደሴቷ በከፍተኛ ፍንዳታ ተናወጠች። ዲምላ የታጠቃቸውን ቦንቦች እየፈታ ወደ ድንኳኑ ወረወራቸው ከመሸገበት ቋጥኝ አድፍጦ የተቀባበለውን አውቶማቲክ መሣሪያ በእሳት ከሚጋየው ድንኳን ላይ አርከፈከፈው። ሞርሞርዲኖና ሚኒስትሩ ከጠባቂዎቻቸው ጋር የተሰበሰቡበት ድንኳን በእሳት ሲጋይ በእሳት ተያይዘው የሚወጡትን በጥይት መልቀም ጀመረ።

በዚሁ ቅፅበት ሚኒስትሩና ሶስት ሰዎች በአቅራቢያው ወደ ቆመችው ሄሊ ኮፕተር ሲሮጡ የሚኒስትሩ ኮት በእሳት ነበልባል ተያይዞ ነበር። ዲምላ ከኋላቸው ከተኮሳቸው ጥይቶች መካከል አንዷ ከሚንስትሩ ኋላ ከሚሮጡት አንዱን አስቀረችው። እቃስቶ ሲወድቅ ሚኒስትሩ በእሳት የተያያዘ ኮታቸውን ላዩ ላይ ወርውረውበት ወደ ሄሊኮፍተሯ ገቡ። ዲምላ በሚተኩሳቸው ጥይቶች የምትበሳሳው

ሄሊኮፍተር ተነሣችና ከአከባቢው ሸሸች። ካፍታ በኋላ ተመልሳ መጥታ ትንሽዋ ደሴት ላይ ጥይት መዝራት ጀመረች። ዲምላ ቋጥኞቹ ውስጥ አድፍጦ ኢላማው ውስጥ እስክትገባ ጠበቃት። ኢላማው ውስጥ ግን ልትገባለት አልቻለችም። ወዲያውኑ ከሄሊኮፍተሯ የተተኮሰ ጥይት ግራ እጁን ሲቦተርፈው አቃስቶ ወደ ቋጥኙ ውስጥ ተንሸራቶ ገባ። በቀኝ እጁ ብቻ የያዘው አውቶማቲክ መሳሪያ በደመነፍስ ቋጥኙ ውስጥ ተንጣጣ። ሂሊኮፍተሯ ርቃ ከመሄዷ አንድ ገላው እንደግንድ የተለበለበ ሰው ምድር ለምድር እየተሳበ ዲምላ ወደ መሸገበት ቋጥኝ መጣ። ዲምላ አውቶማቲኩን መሣሪያ እየተሳበ ከመጣው ሰው ጭንቅላት ላይ አፈሙዙን ለገተው። በእሳት ተለብልቦና የተጠበሰ ሥጋ መስሎ የመጣው ሰው ዶን ሞርምርዲኖ መሆኑን የለየው በመጀመሪያው ቃል ነው።

“ከዳሀኝ አንተ ጥንብ ባሪያ!” ጥርሱን እንደሚናከስ ውሻ አገጠጠ። የተለበለበ ግንድ የመሰለው ሰውዬ ። “አንተ አህያ .... ከአፌ ቀምቼ እንዳላጎረስኩህ ..... ከ... ከ .. ከዳሀኝ!.... ከ.... ከ..ከ ከዳሀኝ ! አ.....አ አንተ ጥንብ ባሪያ!” ጥርሶቹን አፋጫቸው።

“ሁልጊዜ ጌትነት ዘለአለምም ባርነት የለም። ለተረኞች መልቀቅ ግዴታ ነው። ሃ! ሃ! ሃ!” ዲምላ ተሳለቀ።

“እበላሀለሁ!.. አንተ ባሪያ! እበላሀለሁ!” ዶን ሞርሞርዲኖ ተስበው በጥይት የተመታውን የዲምላን ግራ እጅ ነከሱት ።

“የጥቁር ሰው ሥጋ ይበላሉ እንዴ እርስዎ? ይቅርብዎት ያስታውክዎታል።” ጥርሳቸው እስከ አጥንቱ ዘልቆ ተሰማው። “አ......አአአ!”አቃሰተ። አውቶማቲኩን መሣሪያ ጭንቅላታቸው ላይ መልሶ አፈ ሙዝን እበኪያስጠጋ የእጁን ሥጋ ቦተረፉት። የመሣሪያውን አፈሙዝ ከብዙ ትንቅንቅ በኋላ ጭንቅላታቸው ላይ አነጣጥሮ ምላጩን ሲስብ ራስ ቅላቸው ብትንትን አለ። ሄሊኮፍተሯ ርቃ ከተንዘች በኋላ ተመልሳ መጥታ ደሴቷን እየተሽከረከረች አይናማ ድንጋዮችንና የወደዳቁ አስከሬኖችን ሳይቀር ጥይት አዘነበችባቸው። ሄሊኮፍተሯ ለአፍታ ደሴቷን ተሽከርክራ ዞራ እስክትመጣ ዲምላ ከተሸጎጠባቸው ቋጥኞች ጠባብቅ ወጥቶ ከደሴቷ ጥግ መልህቁን ወደ ጣለውና ጠላቂው ኤክስካባተር- ዶዘር ወደ ተጫነበት መርከብ ሮጦ ገባ። ወዲያው ዲምላ የገባበትን መርከብ ሄሊኮፍተሯ ደሴቱዋን ተሽከርክራ መጥታ በቦንብ አጋየችው።



# ፳፯

## ዳጋ እስጢፋኖስ + ምድር ውስጥ

“አወከኝ አይደል ሚራ...አውቀኸኛል አይደል እንዴት ልትረሳኝ ትችላላህ? እወቀኝ የኔ ጌታ..... እወቀኝ እነጂ! ሲጻራ እኮ ነኝ።” እርቃኗን ተንሰፍስፋ አቀፈችው። በአባቷ ፊትና በአባቷ ረጅም ሽበቶ ጢም ፊቷ መሸፈኑን ረስታዋለች። ዕርቃን ገላዋን ከላይ እስከታች ሲያይ ቀፈፈው... ሚራኸ። ፊቷ ዘገነነው። ጢማም ሽማግሌ። ወንድ ያቀፈው መሰለው። ከወደ ደረቱ የሚጎሥሙት ጡቶቿን ሲመለከት ከትላልቅ ጡቶቿና በልጅነቱ ከሰጣት ባለጉጥ መስቀል ጋር ተፋጠጠ።

“ሚራ.... እወቀኝ እነጂ ! እኔ እኮ ነኝ! ...ሲጻራ እኮ ነኝ!.. እሺ እንድታስታውሰኝ .... ትዝ ይልህ እንደሆነ እንዲያውም... አንሶላዬን ቀድጄ ደብዳቤ ፅፌልህ ... አጠበው ብዬህ... እየዋኘህ መጥተህ ... መቃብሩ ቤት ውስጥ ...ስንሳሳም... መቃብር ቆፋሪዎች መጥተውብን....” ጩኸቃት። በምን ታስረዳው? “ትዝ አይልህም እንዴ? ሚራ... እወድሀለሁ እኮ! እስከዛሬ ....አንተን ስፈልግ...” ዕንባዋ አነቃት። ባያውቃትስ?

ወዲያው ሲጻራ የታሰረችበት እሥር ቤት ተበርግዶ አንድ ሰው እየተደበደበ ገባ። ሲጻራ ተገፍትሮ ወደ ታሰረችበት የገባውን ሰው ዓይኖቿን ከሚራኸ ላይ ነቅላ አየችው ...ዲምላ ነው።

ዲምላ ከሁለት ሰዎች ጋር ተፋጣ ርቃኗን ወደ ቆመችው ሲጻራ እጁን ቀስሮ “አዎ! አ...አዎ ከእሷ ጋር ነኝ። አላልኋችሁም.... ከእሷ ጋር ነኝ!” አለ እያቃሰተ። ሰውነቱ በደም ተጨማልቋል። “ወደ ውስጥ ሰብሮ ሲገባ ተይዞ ነው! የእቃ ቤቱን ጠባቂ ገድሎ። በመጠበቂያው ቤት በኩል ወርዶ ሲጋባ ይዘነው ነው!” ዲምላን እያዳፉ ከመጡት ሰዎች መሀል አንዱ ወደ አባ ዠንበሩ ዞሮ። የእሥር ቤቱን የኋሊት ዘግተውት ተመለሱ ዲምላን ያመጡት ሰዎች።

ዲምላ ወለሉ ላይ እያለከለከ ኧ ብሎ ወደቀ። እነ ሞርሞርዲኖን ትንሽዋ ደሴት ላይ ደምስሶ ወደ መርከቡ ሮጦ ሲገባ ሄሊኮፍተሯ መርከቡን አጋይታው ነበር። ዲምላ ግን መርከቧ እየተቀጣጣለች ባለችበት ቅፅበት በመርከቧ ሆድ ሥር ወደተቀመጠው ጠላቂ ኤክስካባተር -ዶዘር ገብቶ አስቀድሞ ሲያጠናው የከረመውን ጥበብ መጠቀም ጀመረ። ኤክስካባተር-ዶዘሩ ከመርከቧ ሆድጋር የታሰረባቸውን ወፋፍራም ሰንሰለቶች የሚታዘዙበትን ቁልፍ ሲጫን የመርከቧ ሆድ ተከፍቶ ኤክስካባተር-ዶዘሩ ወደ ሐይቁ ውስጥ ሲገባ

ሞተሩን አስነስቶ በሐይቁ ውስጥ ለውስጥ ሽመጠጠ። ሄሊኮፍተሯ መርከቡን ሙሉ በሙሉ በቦንብ አጋይታ ዲምላ እንደተቃጠለ አስባ ስትሄድ ዲምላ ወደ ዳጋ ደሴት ለመድረስ ስምንት መቶ ሜትር ያህል ቀርቶት ነበር። ጠላቂው ኤክስካባተር- ዶዘር ብረት ለበስ ሆኖ የጠላቂ መርከብ ቅርፅ ያለው ሲሆን በመሪው ዙሪያ ያሉት ቁልፎቹ ሲነካኩ መቆፈሪያው እንደ አንቴና ተመዞ ይወጣል። ጠልቆ መቆፈር እንዲችል፣ ቋጥኝ የመፈንቀል አቅም እንዲኖረውና ወደ ውስጥ ውሃ እንዳያስገባ ተደርጎ በብዙ ወጪ የተሰራ ነው።ይህንን ልዩ ኤክስካባተር-ዶዘር በሞርሞርዲኖ ልዩ ትእዛዝ የሠሩት መሐንዲሶች ሙከራው ከተሳካና ዲምላ ማሽኑን ከተለማመደው በኋላ እዛው በፓሌርሞ ወደብ አቅራቢያ ሜዲትራኒያን ባህር ውስጥ ሲገደሉ ከሶስቱ መሐንዲሶች ጭንቅላት ላይ ቃታውን የሳበው ራሱ ዲምላ ነው።

ዲምላ ጠላቂውን ኤክስካባተር- ዶዘር በዳጋ ደሴት ሰሜናዊ ዳርቻ ገባ ብሎ ሐይቁ ውስጥ ባሉ ቋጥኞች ጠባብቅ ሰጥሞ እንዲቀመጥ መልህቁን ከቋጥኞች ሥር ካያያዘው በኋላ በዋና ወጥቶ ወደ ደሴቱ ኮረብታ አመራ። የእረኛ አደባባይ ተብሎ በሚታወቀው የመጠበቂያ ቤት ገብቶ የወለሉን ቀያይ ምንጣፎች ገላልጦ ወደውስጥ ሲገባ የምድር ውስጡ የአደጋ ጊዜ መጥሪያ ማሽኖች መንጫጫት ጀመሩ። ወዲያው በታጠቁ ጋርዶች ተይዞ አሁን ወዳለበትና ከሲጳራ ጋር ወደ ተገናኙበት የምድር ውስጥ እሥር ቤት እየተደበደበ ተወረወረ። ሲጳራ “እወቀኝ!” እያለች በጥያቄ የምታጣድፈው ሰው ዲምላ ወደ ገዳሙ ሲገባ በእንግዳ ቤት ውስጥ አብሮት ያደረው ሰው ነው። ዲምላ እንኳን ከሲጳራ ደረት ላይ ያለውን መስቀል በደህና አገኘው እንጂ የሚጨቃጨቁት ነገር ግድ አይሰጠውም። እንደገና በተኛበት ቀና ብሎ ዕርቃኗን ከሚራዥ ጋር የምትሟገተውን ሲጳራን ትቶ ደረቷን ተመለከተ። ደረቷ ላይ ያለውን ባለጉጥ መስቀል። ራቅ ብለው ቆመው ሚራዥንና ሲጳራን በትንግርት የሚመለከቱት አባ ዢንበሩን ትኩረት ሰጥቶ አላያቸውም። ዕረፍት ማድረግ አለበት። ትንሽ ዕረፍት አማረው። በረጅሙ ተነፈሰ- በተንጋለለበት።

“አወከኝ አይደል?” ሲጳራ የሚራዥን ዓይኖች በዓይኖቿ እየተማፀነች። ሚራዥ ሳያስበው ዕንባው ተናነቀው።

“ፎቶ ግራፍ ይዘሻል?” አላት።

“ፎ...ፎ...ፎቶ.....ግ..ግ... ግራፍ...ፎቶግራፍ...” አፏ ተሳሰረ፡ “አዎ ይዣለሁ። እ...እ.. ...እዚህ ግን አይደለም ከበእቴ ውስጥ ነው። ሻንጣዬ እዛው ነው... ገዳሙ ውስጥ.....”

“ሻንጣሽ እኔ ዘንድ ነው” አለ ዲምላ። እንደተንጋለለ እያዳመጣቸው ነበር። “ከፈለግሽ አብረን ሄደን ማምጣት እንችላለን።”



ሆን ብሎ ነበር ሻንጣዋን የደበቀባት መረጃዋን ሁሉ የያዘውን ሻንጣ ሲደብቅ ለመያዥነት ብሎ ነው።

“እንሂድ!” አለ ሚራዥ። “ፎቶ ግራፍሽን እፈልገዋለሁ”

“ተነስ!” አለች ሲጳራ ወለሉ ላይ ወደ ተንጋለለው ዲምላ አዘቅዝቃ።

“ሻንጣዬን ስጠኝ።”

“ግዴለም እሰጥሻለሁ።” ቀኝ እጁን ሰጣትና ተውተርትሮ ቆመ።

“የመጀመሪያውን ተልዕኮዬን ፈፅሜአለሁ። ትንሽዋን ደሴት አፅድቻታለሁ። ሞርሞርዲኖን እስከ ሰዎቹ ጨርሼ ወደ ገሃነም ልኬዋለሁ። ሚኒስትሩም ሁሉን ነገር አጥቶ ተመልሷል። አሁን ደሴቷ ብቻዋን ቀርታለች። ትልቁን ጀልባም ሚኒስትሩ አጋይቶታል። እኔን ያገኘ መስሎት። እኔ ግን አልሞትኩም ጠላቂውን ዶዘር በሐይቁ ውስጥ እያበረርኩ ወደዚህ መጣሁ።” አባ ዢንበሩና ሚራዥ ዲምላ የሚያወራው ተኣምር መሰላቸው። ስለዚህ ጉዳይ የሚያውቁት ነገር የለም። ከዳጋው የምድር ውስጡ ዶርቶጋዳ ዋሻ እየወጡ የፈፀመውን ጀብዱ ተረከላቸው። በጥይት የቆሰለውን ግራ እጁን በጨርቅ ግጥም አድርጎ ቢያስረውም ደሙ ጨርቁን ዘልቆ እየተንጠባጠበ ነበር። ሚራዥ ሲጳራ አውልቃ የጣለችውን ልብስ መልሶ አልብሶ እያስተካከላትና አባትዋን አባ ፊንሐስን እያስመሰላት ዲምላ የሚያውራውን ጀብዱ እያዳመጠ ነው።

በደሴቷ ላይኛው ክፍል እንደወጡ ሲጳራ “ጣላቂውን ዶዘር ታዲያ የት አደረከው?” አለችው።

«ተከተሉኝ»አለ ዲምላ። በውስጡ የሚፈልገውን እስኪያገኝ ወዳጅነት ፈጥሮ ኋላ አሳይቶ እንደ ሚነሳቸው እያምሰለሰለ።

ከደሴቱ ከረብታ ወርደው በሰሜኑ አቅጣጫ ሐይቁ ዳር እንደደረሱ “እኔ እጄን ውሃው ስለሚቆጠቁጠኝ መዋኘት አልችልም። ከፈለግሽ ውስጥ ለውስጥ ዋኝና እይው። እዛጋ አለለሽ” አላት አገጩን ዶዘሩን ወዳስቀመጠበት አቅጣጫ አሹሎ።

ሲጳራ ውስጥ ለውስጥ ጠልቃ ከዋኘች በኋላ ከቋጥኞች መሃል ተጣብቆ መልህቁ የታሰረውን ዶዘር ስታይ ተገረመች።

“እሺ አሁን ፎቶ ግራፌ ያለበት ሻንጣዬን ስጠኝ” አለችው ሲጳራ ከሐይቁ ውስጥ ጠላቂውን ዶዘር አይታ ከወጣች በኋላ።

“ከዛ በፊት እኔም አንድ ነገር እፈልጋለሁ” አለ ዲምላ ወደ ገዳሙ በር እያመሩ እያለ።

“ምን?” አለችው ሲጳራ።

“መያዣ እንዲሆነኝ መስቀሉን ስጪኝ።”

“መ... መ... መስቀሉን ነው ያልከኝ?”

“አዎ። መስቀሉን።”

"እሱንማ አልሰጥህም።"

"እንግዲያውስ..... እኔም ሻንጣውን አልሰጥሽም።"

"ወደህ ትሰጠኛለህ!?" ሲጳራ የቆሰለ እጁን ወደ ኋላ ጎተተችው።

"አ......አአአ!"

"ገና እጅህን እነቅለዋለሁ።"

"እየከዳሽኝ ነው?"

"አይደለም። ፎቶዬን እፈልገዋለሁ።"

"እሺ ዋሻው ውስጥ ግቡ ሻንጣሽን እዛ አመጣልሻለሁ።"

"እንደምታመጣልኝ በምን እርግጠኛ እሆናለሁ?"

"መስቀሉን ይዘሽ አይደል እንዴ? ያንቺ ፎቶ ለእኔ ምን ይሠራኛል? አመጣልሻለሁ። ግን እዛው ዋሻው ውስጥ።" ሚራዥና ሲጳራ ተያዩ።

"ተስማምተናል" አለችው ሲጳራ። "ፍጠን!"



# ፳፰

## ዴርቶጋዳ ፤ የቀዶ ጥገና ክፍል

ረጂም ሰዓታት የወሰደው የፊትዋ ቀዶ ጥገና ከተደረገላት በሁዋላ ለቀናት አልነቃችም ነበር። አሁን ሙሉ በሙሉ እንግማ ተነስታ የምታየውን ማመን አቃታት። ህልም መሰላት። "ፊቴን ከየት አገኘኸው?" አለች ሲጳራ በቀዶ ጥገና ወደ ቀድሞው፤ ወደ ራሷ ፊት የተመለሰላት ፊቷን በመስታውት ቆማ እየተመለከተች። "ወይኔ አምላኬ ፊቴን ወደ ድሮው መልሰህልኛልኮ።"

"ፎቶሽን የፈለኩት ለዚህ ነበር" አለ ዶ/ር ሚራዥ ጋወኑን እንደለበሰ ከኋለዋ ቆሞ። ሌሎች የዴርቶጋዳ ዶክተሮችም ረጅም ጊዜ የፈጀው ቀዶ ጥገና በመሣካቱ ተደስተው ሲያይዋት ቆይተው ነበር ወደ መሰብሰቢያ አዳራሽ ወጥተው የሄዱት። በደስታ ሰክራ ሚራዥን ግጥም አርጋ ሳመችው።

"እሄውልሽ ቃሌን ጠብቄ ፎቶሽን መልሻለሁ። ፎቶሽን አምጥቼ ሻንጣውን ሰጠኋቸው። ከዛም የአባትሽን ፊት ከፊትሽ ላይ ገፈው የራስሽን ፊት ፎቶሽን እያዩ ሰሩልሽ። አየሽ እኔ ፎቶሽን ባላመጣልሽ ኖሮ ጢማም ሆነሽ ትቀሪ ነበር ማለት ነው። ይህ ሁሉ ሲሆን አንቺ በሰመመመን ውስጥ ስለነበርሽ አታውቂም።" ዲምላ ውለታ እንደዋለላት ለመናገር ቃል አጠረው።

"በስንት ቀን ነበር ይህ ሁሉ የሆነው?"ሲጳራ በፍጥነት ጭንቀት ወረራት። "ስ...ስ...ስ.. ስንት......."

"ከስድስት ቀናት በላይ ሳይሆን ይቀራል?"

"ከስድስት ቀናት በላይ?! እስቲ ላፕቶፑን አቀብለኝ። ሻንጣውን አምጣልኝ! ቶሎ በል! የፈጣሪ ያለህ! ዲምላ ፍጠን!"

"ምንድን ነው?...ም...ምም...ምን ተፈጠረ?!" አለ ሚራዥ በድንጋጤዋ ተደናግጦ። ዲምላ ሻንጣዋ ውስጥ ያለውን ላፕቶፕ በፍጥነት አውጥቶ ሰጣት። ላፕቶፑን ተጣድፋ ከፈተችው። በቀዩ ምልክት ከኢንጂነሩ ጭንቅላት ውስጥ የተጠመደው ፈንጂ የሚፈነዳበትን ጊዜ የሚጠቁመው ሰዓት አመልካች እየቆጠረ ነው። ፈንጁ ሊፈነዳ የቀሩት ሃምሳ ዘጠኝ ሴኮንዶች ብቻ መሆናቸውን ያመለክታል። 00:59................

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

የዴርቶጋዳን ወርሃዊ ጉባኤ ምክንያት በማድረግ በስብሰባ ላይ ያሉት የዴርቶጋዳ አባላት የኮሎኔል ፍስሐን ስሜት ቆንጥጦ የሚይዝ ንግግር በተመስጦ በማዳመጥ ላይ ናቸው። ማትያስ ማሞ ከስብሰባው አዳራሽ መሀል ጭንቅላቱን ከምሰሶው አስደግፎ ቆዝሞ ተቀምጦ ንግግሩን እያዳመጠ ነው። ኮ/ል ፍስሐ የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ ባንድጃቸው ከፍ አድርገው ይዘው ያንገታቸው ጡንቻ እየተግተረተረ ይናገራሉ።«.....ይህች ሀገር.........እናት ሀገር ኢትዮጵያ የምንላት ለጥቂቶች አንጉዋች ለብዙዎቻችን ደግሞ የእንጀራ እናት ሆናለች። ኢትዮጵያን ለኢትዮጵያውያን መመለስ የሚቻለው በዴርቶጋዳ ነው። ዴርቶጋዳ ለጥቂቶች ብቻ የሚያደገድግ ድርጅት አይደለም። ለየትኛውም.....ሃይማኖት፣ ዘር፣ ጎሳ፣ የፖለቲካ ድርጅት...ጥበቃ ለማድረግ የተቋቋቋመ ድርጅት አይደለም። ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ በአመለካከቱ ምክንያት በጠላትነት አይፈርጅም። የኢትዮጵያን ችግር ሳይንስ እንጂ ፕሮፖጋንዳ አይፈታውም። ዴርቶጋዳ ኢትዮጵያን በሳይንስ ወደ ቀደመ ክብሯ ይመልሳታል።» ጭብጨባው አስተጋባ። ማትያስ ማሞ ቆሞ አጨብጭቦ መልሶ ተቀመጠ። ጭንቅላቱን ለጉባኤው ሽብረቃ ብዙ ጌጣጌጦች ከተንጠለጠሉበት ምሰሶ አስደገፈ።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

"ኢንጂነሩ የት ነው!?" ሲጻራ አንባረቀች። 00:44....ክንፈሯ ተንቀጠቀጠባት። "ኢ....ኢንጂነሩ የት ነው? ሳ...ሳሳ...ሳይንቲስቱ! ሻ...ሻ.... ሻጊዝ" ሁሉም ተደናግጠው ዝም አሏት።

"ሚራዥ! ኢንጂነሩ ዬት ነው? ለምን አትነግረኝም!......"

"የቱ ኢንጂነር?" አለ ሚራዥ ድምፁን ከፍ አርጎ።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

«የኢትዮጵያን ችግር መፍታት የሚችሉት ኢትዮጵያውን ሳይቲስቶች ናቸው። ነዳጅዋን ማውጣት፣ ዩራኒዩሟን ማበልፀግ፣ የህዋ ምርምር ተቅዋሟን መመሥረት ያለባቸው የራስዋ ታማኝ ልጆች እንጂ ቅጥረኞችና ወሮበሎች አይደሉም። ዴርቶጋዳ ይሄን ማድረግ የሚያስችለው ደረጃ ላይ ደርሷል። ዴርቶጋዳ አያወራም ይሠራል እንጂ። ለዚህም ነው እስከዛሬ ድምጡን አጥፍቶ የሚሠራው.....» ድምጻቸው በጭብጨባው ተዋጠ።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖



"ኢንጂነር ሻጊዝ። እዚህ ዋሻ ውስጥ .... የትኛው ክፍል ውስጥ ነው ያለው?" አለች ሲጻራ ከህክምና ክፍሉ እየወጣች ላፕቶፑ ላይ ያለው ሰዓት ይቆጥራል።........... 00:23

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ጭብጨባው ጋብ ሲል ንግግራቸውን ቀጠሉ። «እስከ ዛሬ ድረስ ኢትዮጵያ የገዢ መደቦች ጥቅም አስከባሪ ሰላዮች እንጂ መንግስታት በተቀያዩሩ ቁጥር የማይቀያዩር ቋሚ የደህንነት ተቅዋም የላትም። ለዚህም ነው ቋሚ ራዕይና ዘላቂ ሕልም አልባ ሀገር ሆና የመጣው ሁሉ ወደፈለገው የሚያሽከረክራት። ዴርቶጋዳ ከምስጢራዊ የሳይንስ ምርምር ተቋምነቱ በተጓዳኝ የኢትዮጵያ ጠበቃ በመሆንም ያገለግላል። ዴርቶጋዳ መንግስታት በተቀያዩሩ ቁጥር የማይቀያዩር ቋሚ የኢትዮጵያ የደህንነት ተቋም ነው። የኢትዮጵያ ዳግም ትንሣኤና ህዳሴ ምልክትም በ«ቶ» ቅርፅ የተሠራው ይህ ልዩ መስቀል ነው።..........»

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

"የትነው እኮ ነው የምልህ? ምን ሆነሃል! "..... 00:05። "ኢንጂነር ሻጊዝ አይደለም" አለ ሚራዥ ቆዝሞ ቆይቶ። "እሱን የሚመስል ሰው በሰርጀሪ ሰርተው .........."

"ምን?" ...

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ማንንም የሚነሽጠውን የድርጅቱን መዝሙር አዝማች ለንግግራቸው ማጣፈጫ ድምጻቸውን ቀስ አርገው ሲጀምሩት ሁሉም ተቀበሉአቸው።..........

ማንም ሰው ላይመጣ እኛን ለመለወጥ
አናፈገፍግም አናቅማማም ለለውጥ።
ዴርቶጋዳ .... ዴርቶጋዳ.... ዴርቶጋዳ
እንነጠቃለን ከተጫነን ፍዳ።
ያቀረቀርክበት አንገት ያስደፋህ ቀን
ነግቷል ብለህ ተነስ ፍዳና ሰቀቀን።
..............................

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

"...ሻጊዝ አሁንም እዛው ነው» አለ ሚራዥ ከወደላይ በኩል ከጆሮው ጥልቅ ያለውን ዝማሬ ላፍታ አዳምጦ። «በአንድ ምስጢራዊ የቴክኖሎጂ ምርምር ጣቢያ ውስጥ ታግቶ እየሰራ ነው።".......00:01.......

"ጭንቅላቱ ውስጥ..." ተናግራ ሳትጨርስ ዋሻው ውስጥ ከፍተኛ ፍንዳታ ተሰማ፡፡

ዋሻውን ያናወጠውን ፍንዳታ ተከትሎ የእሳት ነበልባል በዋሻው ውስጥ መጥመልመል ጀመረ፡፡ በዶርቶጋዳ ዋሻ ውስጥ የተተካከሉት ድምጽ አልባ ጀኔሬተሮች በእሳት ተያያዙ፡፡ የነዳጅ ጀሪካኖችና በርሜሎች የእሳቱን ላንቃ አስፋፉት፡፡

ዋይታ.....ጩኸት፡፡ የላብራቶሪ ዕቃዎችና የኤሌክትሪክ ገመዶች ተንጣጡ፡፡ በዋሻው ውስጥ ያሉ ክፍሎች በሙሉ ወደ ነበልባልነት ተቀየሩ፡፡

የማትያስ ጭንቅላት እንደ ፈነዳ ወዲያውኑ ተደግፎት የነበረው ምሰሶ ተደርምሶ ከጥጉ ያለው ነገር ሁሉ እሳት መትፋት ጀመረ፡፡ አንዱ አንዱን ሊያድን ሲተረማመስ ኮ/ል ፍስሐ የተያያዘባቸውን ሰንደቅ አላማ እሳት እያጠፉ አባ ዠንበሩን ለማዳን ሲጣደፉ የርሳቸው ልብስ በሙሉ በእሳት ተያይዞ ነበር፡፡ ወዲያው ከላይ የወደቀ መርግ ሲአዳፍናቸው መተንፈስ አቅቶአቸው ወደቁ፡፡ ሁሉም ተጣደፈ፡፡ እሳቱን የቀደመ ግን ማንም አልነበረም፡፡ ማንም ማንንም ማዳንም አልቻለም፡፡

አባ ዠንበሩ የሚይዙትን አጥተው ሲንበጀበጁ ዶ/ር ዣንጊዳ ከእሳቱ ውስጥ ነጥቆ ተሸክሟቸው ቁልቁል መሮጥ ጀመረ፡፡ በአደጋ ጊዜ መውጫው በር ሲደርስ አስር ሜትር ያህል ሲቀረው አባ ዠንበሩን እንደተሸከመ በእሳቱ ተዋጠ፡፡ ፀጉሩ፣ ልብሱ ገላው ፣ሁሉ ተለበለበ፡፡ "ጣለኝና አምልጥ!" አሉት አባ ዠንበሩ እያጣጣሩ፡፡ "አ....አምልጥ እባክህ ሌሎቹ እንዲድኑ ንገራቸው አምልጥ፡፡ ወደ .....እኔን ጣለኝ፡፡"

ኢንጂነር ጌራ እና ሜሮዳ ወደ ህክምና ክፍሉ እየሮጡ ሲሄዱ እሳቱ ከኋላቸው በከፍተኛ ፍጥነት እየተከተላቸው ነበር፡፡ ኢንጂነር ጌራ የሜሮዳን እጅ ይዞ እየጎተተ ወደ ዶ.ር 33 አስገባት፡፡ ከዛም ወደ ሐይቁ የሚያስገባውን ትልቅ በር ከፍቶ የዶ.ር33ን ሞተር አስነሳ፡፡ ሜሮዳ እንደገና ተመልሳ የህክምና ክፍሉን በርግዳ ገብታ "ተከተሉኝ! ፍጠኑ!" አለቻቸው እነ ሚራዥን በጭንቀት፡፡ "ውጡ! ራሳቸውን አድኑ......ሩጡ ! ሚራዥ !"

"ዣንጊዳ ወዴት ነው?" አለ ሚራዥ በሩጫ ሜሮዳን እየተከተለ "አባ ዠንበሩስ?!"

"እሳቱ ደርሶባቸዋል፡፡ ዝም ብለህ ና ! ራስህን አድን፡፡...."
"አልመጣም ጥያቸው አላመልጥም፡፡" ሚራዥ እየተጥመለመለ ወደ ሚከተላቸው እሳት ሮጠ፡፡ ሲጻራ ተከትላው እጁን እየጎተተች ጌራ ሞተሯን ወደስነሳት ሰርጓጅ መርከብ ይዛው ለመግባት ተጣደፈች፡፡ "እኔ ደግሞ አንተን ጥየሀ አልሄድም፡፡"



"ነይ ነው ምልሽ!" አላት ዲምላ ሲጻራን፡፡ ከሚራዥ ላይ መንጭቆ ተሸክሞ ወደ ሰርጓጇ መርከብ አስገባት፡፡ "በአንገትሽ ያሰርሽውን መስቀል የዘነጋሽው ይመስላል፡፡ ወይ ስጭኝና እኔ ልያዝው ......"

ሚራዥ በእሳቱ ውስጥ ሰው ተሸክሞ የሚመጣ ሰው ሲያይ ተመልሶ ወደ እሳቱ ሮጠ፡፡ "ዣንጊዳ!" ዣንጊዳ ወደ ሚራዥ አባ ዠንበሩን እንደተሸከመ ሲደርስ ሁሉ ነገሩ በእሳት ተያይዞ ነበር፡፡ "በሩን ዝጉት!" አለ ጌራ ፡፡ "ዝጉት!" ከኋላቸው ትልቁን በር ዘግተው ወደ ሰርጓጇ መርከብ ሲቃረቡ ዣንጊዳ አባ ዥንሩን እንደተሸከመ ወደቀ፡፡

"እሷቱን አጥፉለት፡፡ እሳቱን.... ኮቱን አውልቅለት፡፡" ጌራ መርከቧን እያንቀሳቀሰ አንባረቀ፡፡ ዣንጊዳ እንደ ግንድ ተሰብልቧል፡፡ ሰውነቱ በሙሉ በእሳት ተንጨቅጭቋል አባ ዠንበሩ ለዘለአለሙ አሸልበዋል፡፡ ሁሉም በሃዘን ተኮራመቱ፡፡ ሚራዥ አባ ዠንበሩን እያገላበጠ ተንሰቅስቆ አለቀሰ፡፡

"እሳቱ በሩን ሳያልፍ ኑ ቶሎ ግቡ!" አለ ጌራ፡፡ "ቶሎ በሉ በሩ ተያይዟል ፍጠኑ፡፡" ሚራዥ ዣንጊዳን ወደ ዶ.ር33 ተሸክሞት ገባ፡፡...........

ዶ.ር33 እንደ ጠላቂ መርከብ ሆና የጣና ሐይቅን ውስጥ ለውስጥ እየሰነጠቀች ወደ ባህር ዳር አቅጣጫ ገሠገሠች፡፡ በዳጋ እስጢፋኖስ ደሴት ውስጥ ለዘመናት ሲገነባ የኖረው የምድር ውስጥ የምርምር ተቋም በቅጽበት እንደልነበረ ከሆነ በሁዋላ፡፡ ትልልቅ አለቶች እየተሰነጣጠቁ የጣናን ውሃ ወደ ዋሻው አስገቡት፡፡ እሳቱን ተከትሎ ውሃው የቀረውን ክፍተት ሞላው፡፡ ዋሻው በሁሉም አቅጣጫ ተዘጋጋ፡፡...........

# ፳፱

## ባህር ዳርተ ግዮን ሆቴል

በዴር33ቷ ልዩ ሰርጓጅ መርከብ ከዳጋ ደሴት የምድር ውስጥ እሳት በጣና ሐይቅ ውስጥ ለውስጥ አምልጠው ሲወጡ መሽቶ ነበር። ትንሿን ጠላቂ መርከብ ከጣና ሐይቅ ትራንስፖርት ድርጅት ወደብ ዝቅ አርገው ሐይቁ ውስጥ መልህቋን ጥለው እንደ ወጡ ቀጥታ ወደ ግዮን ሆቴል ገቡ።

ዶ/ር ሚራዥ ከአንድ መድኃኒት ቤት ማስታገሻ ነገሮችን ገዝቶ የዶ/ር ዣንጊዳን ቁስል ካከመለት በኋላ ህመሙ ታግሶለታል።

በጣና ሐይቅ ዳርቻ ባለው ግዮን ሆቴል ሽር ብትን በሚሉ የውጭ ሀገር ዜጎች ተሞልቷል። የሚበዙት ቻይናዎች ሲሆኑ በቻይንኛ ቋንቋ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ይነጋገራሉ። ከሆቴሉ ፊት ለፊት ከተገተረው ዋርካ ሥርቻ ጋር የሐይቁን ማዕበል የሚያጋጨው ቀዝቃዛ ነፋስ የሆቴሉ አበባዎችን ያወዛውዛቸዋል። የማዕበሉንና የቀዝቃዛውን አየር ተፈጥሮአዊ ሙዚቃ እያዳመጡ በካምፋየሩ ዙሪያ የተሰበሰቡት ቱሪስቶች የተመቻቸው ይመስላሉ።ይሳሳቃሉ፤ ካምፋየሩን እየዞሩ ይጨፍራሉ። ባህር ዳር እንደዚህ የሚያመርባት ምሽት ላይ ነው።በጥቁሩ አስፋልት ላይ ብርሃናቸውን የሚረጩት የመንገድ ዳር አምፑሎች ጎዳናውን ሞልተው የሚጓዙትን የውባውብ ልጃገረዶችንና ጎረምሶችን ውበት ለማሳየት የተተከሉ ይመስል በስራቸው የሚተላለፉትን ሁሉ ወርቃማ ብርሃናቸውን ያፈሱባቸዋል። በዘምባባዎች ላይ እያፏጨ የሚነፍሰው ለስለስ ያለ አየር የዘምባባዎችን ቅርንጫፎች ሙዚቃ ያጫውታቸዋል፤ ያውረገርጋቸዋል፤ ያዘምራቸዋል፤ ያስደንሳቸዋል።

ባህር ዳር በምሽት ለአፍታ ሞቅ ትልና ምሽቱ ገፋ ሲል ወዲያው ታንቀላፋለች። ሁሉም ነገር ይዘጋጋል። ከባህል ጭፈራ ቤቶች የማሲንቆ ድምጾችና የባለገር ዘፈኖች ብቻ መሰማት ይጀምራሉ። ምሽቱ ሲገፋ ባህር ዳር ውስጥ የማይተኙት ዘምባባዎች ብቻ ናቸው። የከተማዋ ጠባቂ መላእክት መስለው ቅርንጫፎቻቸውን እንደ ክንፍ ዘርግተው ያሸበሽባሉ።

እነ ሚራዥ ግን ይህን ሁሉ የባህር ዳር ውበት የሚያዩ ዓይኖች አልነበሩዋቸውም። ግዮን ሆቴል ውስጥ በተለኮሰው ካምፋዬር አቅራቢያ ተቀምጠው ቆዝመዋል። የሚንቦገቦገው እሳት አልሞቃቸውም። የሚነፍሰው ቀዝቃዛ አየርም አልቀዘቀዛቸውም ። ሀዘን ረጃጅም ጥላውን ጥሎባቸዋል። ቃላት አይለዋወጡም።



ሚራዥ አንገቱን ደፍቶ መሬቱን በዓይኑ ይቆረቁራል። ሲጻራ ጭንቅላቷን ከሚራዥ ትካሻ ላይ ጥላ ከጥጉ ተቀምጣለች። ሜሮዳና ኢንጂነር ጌራ ጥግ ለጥግ ቢቀመጡም የሜሮዳ አይን ግን የተተከለው ተደጋግፈው ከተቀመጡት ከሚራዥና ከሲጻራ ላይ ነው። ዶ/ር ዣንጊዳ የሚለበልበው ቁስሉ ትንሽ ቢታገስለትም በተፈጠረው ነገር የውስጡ ቁስል ብሶበታል። ዲምላ ደግሞ ሲጻራ ካሰረችው ባለጉጥ መስቀል ላይ ዓይኖቹን እንደተከለ ነው። በጥይት የተመታውና በሞርሞርዲኖ ንክሻ የተተለተለው የእጁ ቁስል ይቆጠቁጠዋል።

ያዘዙት ራት መጥቶ ባንድነት ከተመገቡ በኋላ ሚራዥ ሲጻራ ያሰረችውን ባለጉጥ ግማደ መስቀል ሲያገላብጥ ቆይቶ በ«ቶ»ቀለበት ላይ ከሰፈሩት ቁጥሮች መካከል ባለፈው ያልፈታቸውን ቁጥሮች ተመለከታቸው። “$98_{123}9_{6}10_{67}40_{567}88_{123456}$” ቁጥሮቹ የ«ሰቆቃወ ጴጥሮስ» ግጥም ሚስጥሮች መሆናቸውን ቢያውቅም ግጥሙ የተፃፈበትና ባለፈው ምስጢሩን መፍታት የጀመረበት ብራና እስከጊታሩ በዳጋ ደሴት የምድር ውስጥ እሳት ጋይቷል።

“ጌራ?” አለ ዶ/ር ሚራዥ ሲያሰላስል ከቆየ በኋላ። አባይ ማዶ ገጣሚ ነኝ ብሎ ሰቆቃወ ጴጥሮስን በቃሉ እንዳነበነበለት ትውስ አለው ። “ያንን ግጥም እስኪ በልልኝ?” አለው።

“የቱን?” አለ ጌራ ከሰመጠበት የሀዘን እንቅልፍ ባኖ።

“ሰቆቃወ ጴጥሮስን።”

“አስታውሰዋለሁ ብለህ ነው? ያኔም እኮ በስንት ትግል ነበር የያዝኩት። አባ ዥንበሩ በመከራ ነበር ያስጠኑኝ።”

“እስቲ ግድ የለም ሞክር... ”

“ እስቲ ልሞክር. ” ጉሮሮውን ጠራርጎ ሁለት ስንኞችን እንዳነበነበ ቀጥ አለ። ጠፋበት።

“አዬ፣ ምነው እመብርሃን? ኢትዮጵያን ጨከንሽባት?

ምነው ቀኝሽን ረሳሽት? ውይ! ሙልጭ ብሎ ጠፍቶብኛል . . እ. . .”

“አይዞህ አስታውስ . . . .. ሶስተኛውን ስንኝ እኔ ላግዝህ እሺ.....”

“እስቲ እስቲ. . .”

“እስከ መቼ ድረስ እንዲህ መቀነትሽን ታጠብቂባት?”

“አዎ !.. እስከመቼ ድረስ እንዲህ መቀነትሽን ታጠብቂባት?”

ልቦናሽን ታዞሪባት?

ፊቱናዋን ሰቀቀንዋን ጣርዋን ይበቃል ሳትያት?

አሳንቺ እኮ ማንም የላት . . . ” እያማጠ ስንኞቹን መደርደር ጀመረ። ከዛም ሚራዥ ስንኞቹንና ቃላቱን ከቁጥሮቹ ጋር ማዛመድ ጀመረ።

ጽሁፍ የተቀረጸበትን ጫፍ አሽከርክሮ ሲፈታው መስቀሉ ብትንትን ብሎ ከውስጡ የተጠቀለለ ብራና ወረቀት ወጣ።

ሁሉም ከመስቀሉ ውስጥ የወጣውን ጥቅል ብራና እና በላዩ ላይ የሰፈሩትን ቁጥሮች በመደመም ተመለከቷቸው።

$32_{12}$ $20_4$ $32_3$ $101_3$ $101_5$ $30_{23}$ $32_6$ $21_3$ $68_6$ $63_6$ $102_2$ $17_2$ $63_1$ $95_3$ $60_7$ $71_{45}$ $82_2$ [illegible] $98_5$!

ዲምላ ቁጥሮቹን በሙሉ ጭኑ ላይ በምላጩ ጥርሱን ነክሶ ፃፋቸው። ደሙ ልብሱን እያበሰበሰው ነው።

ቁጥሮቹን ወደቃል ለውጦ ምስጢሩን የግሉ ለማድረግ አንድ ነገር እንደሚያስፈልገው ያውቃል። ያንን ነገር የት እንደሚያገኘውም አላጣውም። እስከ አሁን መጻሕፍት ቤቶች እንደሚከፈቱ እርግጠኛ ነው! ረፍዷል። ከመጻሐፍት ቤቶች ባንዱም «እሳት ወይ አበባ»ን እንደማያጣው እርግጠኛ ነው። ቁጥሮቹን በሙሉ መጻፉን ካረጋገጠ በኋላ ከተቀመጠበት እመድረፍ ብሎ ተነሳ። ከጭኑ የፈሰሰው ደም ከቀመበት መሬት ላይ ሲንጠባጠብ ሁሉም ደሙ ያረፈበት መሬት ላይ ሲያፈጡ ዲምላ ወደ ሆቴሉ በር ተፈተለከ።

ደሙን እያዘራ በሩጫ ከአካባቢያቸው ሲርቅ "እንዴ ! ሰውዬው የወር አበባ ማየት ጀመረ እንዴት?"ብሎ ጌራ ሲናገር ሁሉም ከት ብለው ሳቁ።

ዲምላ አስፋልቱን ይዞ ወደ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አቅጣጫ ሲሮጥ ቆይቶ አንድ መንገድ ዳር አሮጌ መጻህፍት ዘርግቶ የሚሸጥ ወጣት ሲያይ ቆመ።

መጻሕፍቱ ላይ ዓይኑን ቢያንከባልልም "እሳት ወይ አበባ" የሚለውን መጽሐፍ ሊያየው አልቻለም።

"እሳት ወይ አበባ የሚለው መጽሐፍ አለህ?" ዲምላ እያለከለከ ነበር።

"የለኝም" አለው ወጣቱ መጽሐፍ ሻጭ ።

"እንዴት አይኖርህም?"

"እሃ?"

"እሺ የት ነው ማግኘት የምችለው?"

"የትም አታገኘውም።"

"ሰውዬ! ....ደም እኮ እየፈሰሰህ ነው !" አለ መጽሐፍ ሻጩ የዲምላን የሚንጠባጠብ ደም አስፋልቱ ላይ እየተመለከተ።

"ዝም ብለህ መጽሐፉን ስለማገኝበት መንገድ ንገረኝ"

"እየሀ . . . መጽሐፉ የታተመው በ1966 ዓ.ም ነው። ከ1966 እስከ 1998 ስንት አመት ነው? 32። 32 አመታት። አዎ ከታተመ 32 አመቱ ነው። . . . የመጽሐፉ ደራሲ ዘንድሮ መሞቱን አልሰማህም? ያ . . . ማነው ? ማን ነበር? አዎ የናሳው ሳይንቲስት



ከሞተ ጥቂት ቆየት ብሎ ደግሞ ሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህን ሞተ። ሁለት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ይህቺ ሀገር ሁለት ታላላቅ ሰዎች አጣች።"

"እባክህ!" አለ ዲምላ። "ዝም ብለህ መጽሐፉን የማገኝበትን መንገድ ንገረኝ።"

"ነገርኩህ እኮ! ሎሬቱ ሙቷል። መጽሐፉም ከታተመ 32 አመታት አልፎታል! የት ታገኘዋለህ?"

"በቃ አላገኘውም?"

"ማግኘትማ ታገኘዋለህ ግን በጣም በውድ ዋጋ!"

"የት?"

"ስንት ትገዛለህ?"

"መጽሐፉ አለህ እንዴ?"

"መጀመሪያ የጠየኩህን ንገረኝ ስንት ትገዛለህ?"

"በፈለከው ዋጋ!"

"መቶ ብር ትከፍላለህ?"

"ሁለት መቶ ብር አደርግልሃለሁ።"

"አይበቃም።"

"እሺ ሶስት መቶ!"

"እንካ!" አለ መጽሐፍ ሻጩ በድሮ ጋዜጣ የተለበደ አጭር መጽሐፍ ካስቀመጣቸው አሮጌ መፃሕፍት መሃል ጎርጉሮ አውጥቶ።

ዲምላ መጽሐፉን ቶሎ ገልጦ "ሰቆቃወ ጴጥሮስ" የሚለውን ግጥም ፍለጋ ገፆቹን ማተረማመስ ጀመረ።

"ሰቆቃወ ጴጥሮስ የሚለው ግጥም አለበት?"

"አዎ! ምን ሰቆቃወ ጴጥሮስ ብቻ! የቴዎድሮስ ስንብት ከመቅደላ፣ እሳት አመድ ወለደ፣ አብረን ዝም እንበል፣ ደህና ዋይ እማማ፣ ቃል ቃተተ . . ."

"በቃ !በቃ! በቃ! አገኘሁት . . . "

"በል .... ሶስት መቶ ብሩን ወዲህ በል! እንግዲያውስ . . ."

"ያ መጽሐፍ ስለ ምንድን ነበር የሚያወራዉ?" አለ ዲምላ ወደ አንድ አሮጌ መጽሐፍ ጣቶቹን ቀስሮ ።

መጽሐፍ ሻጩ ጎንበስ ብሎ መጽሐፉን አንስቶ ቀና ሲል ዲምላ እሳት ወይ አበባ የሚለውን መጽሐፍ ይዞ ዋጋውን ሳይከፍል ሲፈተለክ ተመለከተው።

መጽሐፍ ሻጩ ዲምላን በሩጫ እየተከተለ "መጽሐፌን! መጽሐፌን! ...መጽሐፌን! አስቁመው.... ሌባ ነው!...... ሌባ !ሌባ!ሌባ! .....ሶስት መቶ ብሬ! ....ያዘው ! ያዘው!.... ያዥው!... ሌባ!ሌባ!..." ቢልም ዲምላን ማንም ሮጦ ሊይዘው የቻለ የለም። ከኋላው የሚከተሉት ሰዎች እየበረከቱ "ሌባ !ሌባ!"የሚለው ድምጽም እየበዛ መጣ። ከፊቱ ቆሞ ዲምላን ለመያዝ ግን ማንም አልደፈረም።

ማየት የዘወትር አስገራሚ ትዕይንት ነው..." የሚለውን ጽሑፍ እንብባላቸው ስትጨርስ ቀና አለች።

"ታዲያ.......... እንዴት ነው መሄድ የምንችለው?"ሚራዥ የኢንጂነር ጌራን አይኖች እየተመለከተ ጠየቀው።

"ዶር33ን መጠቀም እንችላለን" አለ ጌራ። "ጢስ አባይ ፏፏቴ ከባህር ዳር በስተምስራቅ 30 ኪሎ ሜትር ላይ ከጢስ አባይ ከተማ አጠገብ ነው የሚገኘው። ከባህር ዳር ጢስ አባይ ከተማ ለመድረስ የመኪና መንገድ አለ። ከከተማዋ ወደ ፏፏቴው ለመሄድ ከጢስ አባይ ከተማ 1.5 ኪሎ ሜትር ያህል በመኪና መጓዝ ይቻላል። ....ከዚህ በታች ባለው የአባይ ሸለቆ ውስጥ ቁልቁል በመጓዝ ነው ሰባራ ድልድይን የምናገኘው።........ዶር33ን ባየር ላይ ስለምንጠቀም የአባይን ወንዝ ቁልቁል ስንከተል እናገኘዋለን ግዶለም።"

"እም..... አሁን ስለ ድልድዩ ያነበብኩት ትዝ አለኝ"አለች ሜሮዳ።

"እንዲያውም ሰባራ ድልድይ በአባይ ወንዝ ላይ የተሰራው የመጀሪያው ድልድይ እንደሆነ አንብቤያለሁ። በጥንተ ስሙ የሉስ ድልድይ በመባልም ይታወቃል።"

"በቃ እንንቀሳቀስ።"

ዶር33 መልህቋን ጥላ ወደተደበቀችበት ሲደርሱ የጣና ሐይቅ ፀጥ ረጭ ብሎ ነበር። ማዕበሉ ሰክኖ።

ኢንጂነር ጌራ ሞተሯን ካስነሳ በኋላ በሐይቁ ውስጥ ለውስጥ ነድቶ ወደ ላይኛው የሐይቁ ክፍል አወጣት። ከዛም ሁሌም እንደሚያደርገው መሪዋ ጥግ ያሉትን ቁልፎች ሲጫን ከሆዷ ውስጥ ሁለት ክንፎች ወጡ። በጣና ሐይቅ ላይ ክንፏን እንደዘረጋች ካኮበኮባት በኋላ ወደ አየር አወጣት።

በአባይ ሸለቆ ውስጥ ዓባይን ቁልቁል እየተመለከቱ ወደ ጢስ አባይ ከተማ ጥምዝምዙን የአባይን ውሃ ጉዞ ተያያዙት።



# ፴

## ሰባራ ድልድይ፡ አባይ

ዲምላ ከሰባራ ድልድይ ለመደረስ ብዙ ኪሎ ሜትሮች ሲቀሩት መኪና መንገድ ስላጣ በብስጭት ከርካሳዋን መኪና ከቋጥኝ ጋር አጋጭቷት ወርዶ ሸጥ ለሸጥ በሩጫ ይፈተለክ ጀመር- አቀበት ቁልቁለቱን። ምናልባት የሚቆፈር ነገር ይኖራል ብሎ በመገመቱ የሽማግሌውን ዶማና ማጭድ ይዞአል።

ሰባራ ድልድይ ላይ ሲደርስ ልቡ በአፉ ቱር ብላ እስክትወጣ ከመጠን በላይ በመሮጡ እያለከለከ ነበር። ከሰባራው ድልድይ ወዲህ ማዶ ቆሞ ወዲያኛው ማዶ ያለውን የድልድዩን ምሰሶ ተመለከተ። ይህ ምሰሶ ጥንት «የሎስ ምሰሶ»ተብሎ የሚታወቀው መሆኑን አልረሳውም።ድልድዩ የተያያዘው በቀጭን ገመድ ነው።ይህቺ ቀጭን ገመድ ነበረች ኢትዮጵያን አያይዛት የኖረች። በዚህች ገመድ ላይ ነበር ህይወት ስትውተረተር የኖረችው። በዚህች ቀጭን ገመድ ላይ እንዴት ተንጠላጥሎ ከወዲያኛው ማዶ እንደሚደርስ ግራ ገባው።

ሰባራው ድልድይ ጫፍ ላይ ቆሞ ቁልቁል ሲመለከት አዞረው። በሰፊው ሸለቆ ውስጥ የሚጥመለመለው የአባይ ወንዝ ጭንቅላቱን ይዞበት የሄደ ይመስል ተንገዳግዶ ወደ ኋላ ተመለሰ። ተንፏቆ ተቀመጠ - ስላዞረው።

ከማዶ ካለው የድልድዩ ምሰሶ ወገብ አካባቢ የ«ቶ» ቅርፅ መስቀልና ööö የተቀረፀበትን ድንጋይ ከህንፃው ላይ ሲያይ ቅጭም ብሎ ተመለከተው። ገመዱን በጥርሱ ነክሶ ቢሆንም መሻገር እንዳለበት ወሰነ። በገመዱ ላይ መንጠላጠል ጀመረ።

በገመዱ እየተንጠላጠለ ቁልቁል የሚጥመለመለውን የአባይን ውሃ አዘቅዝቆ ሲያይ ሰውነቱ ተንዘፈዘፈበት። ገመዱ አምልጦት ቢወድቅ ከሥር ያገጠጡት ሹል ሹል የአባይ ቋጥኞች አናቱን ሲበጠርቁት በሀሳቡ ታየው። ትንፋሹን ዋጠ። ላብ ከብብቱና ከግንባሩ ጭርር ሲል በአባይ ሸለቆ አናት ካለችው ፀሐይ ይልቅ የውስጡ ትኩሳት ብሶ ነበር። ከወንዙ መሃል ላይ ወደ ቆመው የሉስ ምሰሶ በመከራ እየተንፏቀቀ ደረሰ። የመስቀሉን ምልክትና ööö'ን እስካየበት ድንጋይ በምሰሰው ላይ እየተንሸራተተ ወረደ። ከድልድዩ ምሰሶ ህንፃ ድንጋዮች ላይ በዶማ መቆፈር ጀመረ። ጥብቁን የህንፃ ድንጋይ ለመቦርቦር ብዙ ደቂቃ ፈጀበት። ጠንካራ ክንዱ ከጥንታዊው ጠንካራ ህንፃ ጋር ሲፋለም ቆይቶ መስቀልና ööö የተሳለበት ድንጋይ ከሕንፃው ላይ ተፈንቅሎ ወደ ውሃ ተምዘግዝጎ ድንቡቅ አለ።

ድንጋዩ ወደተፈነቀለበት ሽንቁር እጁን ሲከት ትንሽ ቀይ የብረት ሳጥን ይዞ ወጣ ። ሳጥኗ ላይ “ዴርቶጋዳ” የሚል ጽሑፍ ተቀርጾበታል። “ዋው! ይሄ ነው ዲያላ!” ብሎ በፉከራ ሲጮህ የአባይ ሸለቆ የገደል ማሚቶ መልሶ ፉከራውን አስተጋባለት። “ዘጠና አምስት በመቶ የምድራችን ሀብት አምስት በመቶ በሚሆኑ ሰዎች እጅ ብቻ ነው ያለው” አለ ዲያላ ለራሱ። ከሰባራው ድልድይ ምሰሶ ላይ ሽቅብ ለመውጣት ትንሿን ሳጥን ይዞ እየተንፏቀቀ።

«እኔ ዲያላ ደግሞ የበይ ተመልካች ሆኜ መሞት አልፈልግም። ሕይወት ትግል ናት። በትግሉ የሚሸነፉ ይበዘበዛሉ። እኔ ዲያላ እስካሁን ተበዝባዥ ነበርኩ። አሁን ግን የብዝበዛ ዘመኔ አክትሟል። ......................የሰጠመው መርከብ ካርታ በእጄ ነው። የሰጠመውን መርከብ ካወጣሁት በሁዋላ በመጀመሪያ...ጣሊያን ውስጥ ከዛም ፈረንሳይ...አሜሪካ...እንግሊዝ...ታላላቅ ኩባንያዎችን እገዛለሁ...ከዛም...ፈልሰስ ብየ” እየተንፏቀቀ ድልድዩ ላይ እንደወጣ ጭኑ ላይ በምላጭ የሸነሸነውን የመስቀሉን ካርታ ቁጥሮች ቁስል ተመለከተ። ጭኑ ላይ የፈሰሰው ደም ገግሯል።

«ብዙ ጊዜ!» አለ ትንሿን ሳጥን በእጁ ጠበቅ አድርጎ ይዞ እየተመለከተ። “አዎ..... ብዙ ጊዜ ፈጀሽብኝ። ይገባኛል አይደል?” ሳጥኗ ታናግረው ይመስል ይበልጥ ወደ አንዲት ዓይኑ አስጠግቶ ጠየቃት። «ይገባኛል። የሰጠመው መርከብና በውስጡ ያለው የትየለሌ ሀብት ለእኔ ይገባል። ለእኔ! ምንም ነገር በምድር ላይ ለሌለኝ።” ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። ቀና ሲል ሚራዥ በገመዱ ላይ እየተንጠላጠለ ወደ እሱ እየገሠገሠ ተመለከተው።

“አታገኘውም!” አለ ዲያላ በሹፈት እየሳቀ። “ይልቅ እንዳትከሰከስ። ተመለስ።” ድልድዩ ላይ ድንጋይ አንስቶ በገመዱ ላይ እየተንጠላጠለ ወደ እርሱ የሚገሰግሰው ሚራዥን ጭንቅላቱን ፈጠፈጠው። የሚራዥ ፊት በደም ተሸፈነ።ዲያላ ሳጥኗን ከድልድዩ ጫፍ ላይ አስቀምጦ ሚራዥ የሚንጠላጠልበትን ገመድ በማጭዱ ቆረጠው። ሚራዥ ዲያላ ከቆመበት የድልድዩ ጫፍ ሊደርስ ሲንጠራራ ገመዱ ተቆረጠ። «አአአአ.....» ብሎ እየተምዘገዘገ በተቆረጠው ገመድ ጫፍ ላይ ተንጠልጥሎ ውሃው ውስጥ ተደነቀ። የገመዱ ጫፍ ትንሿን ሳጥን ጠርጎ ከድልድዩ ላይ ሲያንሸራትታት ቁልቁል ወደ አባይ ወንዝ ተምዘግዝጋ ወደቀች። በውሃው ላይ እየተንሳፈፈች ቁልቁል ከውሃው ሞገድ ጋር ስትጓዝ በተቆረጠው ገመድ ላይ ተንጠልጥሎ ውሃው ውስጥ የተዘፈቀው ሚራዥ ገመዱን ለቆ በዋና ሳጥኗን መከተል ጀመረ። ዲያላ በሰባራው ድልድይ ላይ ዘሎ ወደ ውሃው ተወርውሮ ገባ። ሚራዥንና ሳጥኗን በዋና ተከተላቸው። ሚራዥ እንደምንም በፍጥነት ዋኝቶ ሳጥኗን እንደ ጨበጠ የዲያላ ፈርጣማ ክንድ



ከኋላው ጭንቅላቱን የሚያናጋ ምት አሳረፈበት። ዲያላ ሚራዥን ውሃው ውስጥ ትንፋሹ እስኪቆም ደፈቀው። ውሃው በደም ቀላ። ሚራዥ የዲያላን ጠንካራ ምቶች መቋቋም አልቻለም። ትንፋሽ አጥሮት እያቃሰተ ሳጥኗን ለቀቃት። ዲያላ ሳጥኗን በእጁ እንዳስገባ ሚራዥን ውሃው ውስጥ ደፍቆ ያዘው።

ወዲያው ዲያላ ከኋላው ከባድ ነጎድጉዋዳማ ድምፅ ያለው አቅል የሚያስት ምት ጭንቅላቱ ላይ ሲያርፍበት እንደምንም ተንገታግቶ ወደኋላ ዞሮ አየ። ሲጻራ ደጋግማ የሸጉጧን ምላጭ ሳበችው። ግምባሩ በጥይት ሲበረቃቀስ ደም በአፉና በአፍንጫው እኩል ቡልቅ አለ። የዛለ እጁ ሳጥኗን ሊይዝለት አልቻለም። ሳጥኗን ለቆ ውሃው ውስጥ ወደቀ። መናገር አልቻለም። አፉን እንደከፈተ ከአባይ ውሃ ጋር ቁልቁል ወረደ።

ሚራዥ ተንገዳግዶ ሳጥኗን እንደያዘ ከሚፈሰው ውሃ በተቃራኒ ሽቅብ እየዋኘ ወደ ሲጻራ ገሠገሠ። እሱዋም እየዋኘች ወደ ሚራዥ ፈጠነች። በውሃው የተኛው ፀጉሯን ከፊቷ ላይ ገልጦ ቡዝዝ ቅዝዝ ብሎ ተመለከታት። ፊቱ በደም እንደቀላ። እሰዋም ፍዝዝ ብላ ተመለከተችው።ከንፈሮቿ እንደድሮውናቸው። የጎመራ የሮማን ፍሬ እንደመሰሉ ናቸው። ጎረሳቸው።

ሜሮዳ ከወንዙ ገንብ ዳር ከጌራ ጋር ቆማ ቁልቁል ሲጻራንና ሚራዥን ስታይ ውስጧ ተፈረካከሰ። ቅናትና ፍቅር። ሚራዥን የግሉዋ እንደምታደርገው እርግጠኛ ሆና ስትኖር ሲጻራ የምትባል መንፈስ በህይወት ትኖራለች ብላ አልገመተችም ነበር።

ጌራ ትክሻዋን መታ መታ አደረጋትና “ሚራዥ ለአንቺ አልተፈጠረም”አላት።

“እኔ ግን የተፈጠርኩት ለእሱ ነበር!” አለች ሜሮዳ።

“ትወጅዋለሽ አይደል ?” አላት ጌራ መልሶ።

“ምን ጥያቄ አለው!”

“እንግዲያውስ እሱ የሚወደውን እንዲያደርግ ተይው። ምናልባት ለአንቺ የተፈጠረ ሌላ ይኖራል። እየሽ ... የሰው ልጅ ትልቁ ፍላጎቱ መፈለጉን ማወቁ ነው። እንደምትፈልጊው ያውቃል። እንደምታስፈልጊውም እንዲሁ። እሱን ሆነሽ አስቢው እሰቲ...ዕድሜ ልኩን ሲፈልጋት ኑሮአል ሲጻራም ስትፈልገው ኖራለች።...”

“የምትለው ይገባኛል ጌራ። ........... እንዳልከው ውስጤን መመርመር ሳይኖርብኝ አይቀርም። ከዚህ በኋላ ግን ያለ ፍቅር መኖር አልችልም። ፍቅር አልባ ሰው እና ክንፍ የሌለው አሞራ አንድ ናቸው። ሁለቱም መብረሪያቸውን አጥተዋል። ታውቃለህ? እኔ ፍቅር እፈልጋለሁ። አበባ ቀጥፎ የሚሰጠኝ አበባ ቀጥፌ የምሰጠው ያስፈልገኛል። ፍቅርን ከቀንቀን ከዘመን ዘመን

ስጠብቅ....ጊዜየን ዕድሜየን ጨረስኩት፡፡ ግን....ግን ደሞ ....ፍቅር ጊዜ አይሰጥም፡፡ ያለ ፍቅር ከዚህ በኋላ አንድ ቀን እንኳዋ መዋል አልችልም፡፡ አበባ ቀጥፎ የሚሰጠኝ አበባ ቀጥፌ የምሰጠው ያስፈልገኛል" ዓይኗ ዕንባ አቀረረ፡፡

ጌራ እየሮጠ ሂዶ ዓባይ ዳር ፈንድታ አሽግሮ ያያትን አበባ ቀጥፎ ተመለሰ፡፡

"አበባ ቀጥፎ የሚሰጥሽ ተገኘ ማለት ነው" አለ ጌራ፡፡ "ይኸው አበባሽን ተቀበይኝ፡፡"

«እየቀለድክብኝ እንዳይሆን!» ፈገግ ብላ ተቀበለችው፡፡ "አየህ . . . እኔ በቀላሉ የሚያዝን ልብና በቀላሉ የሚደሰት መንፈስ ያለኝ ሴት ነኝ፡፡ በቀላሉ መደሰት እችላለሁ፡፡" እንባዋን ወደ ውስጧ አመቀችው፡፡ ፊቷ ላይ የወረዱትን የእንባ ዘለላዎቿን ሲያብስላት እቅፍ አደረገችው፡፡ «ምናልባት ለእኔ የተፈጠርከው አንተ እንደሆንክ ማን ያውቃል?» አለች በውስጧ፡፡

"አመሰግናለሁ፡፡ ጌራ . . . እኔ ያለፍቅር መኖር አልችለም፡፡ ደግሞም በቀላሉ ማፍቀር የምችል ሴት ስለሆንኩኝ ፍቅሬን ወደ ዚህች ምስኪን ሀገሬ ማዞር እችላለሁ፡፡ ይህች ሀገር እንደኔ ሁሉም ተጠቅሞ የሚጥላት ናት፡፡ እሷን ማፍቀርና ቀሪ ህይወቴን ለእሷ መስጠት እችላለሁ፡፡ እንዲያውም ሀገር ሆኖ ስላላገኘኋት እሷን ሀገር ለማድረግ ፍቅሬን ወደእስዋ ማዞር እችላለሁ፡፡ . . . አንተም . . ."

"እኔም ከጎንሽ ነኝ ሜሮዳ፡፡" ጌራ ሳያስበው ጥብቅ አድርጎ አቀፋት፡፡

ሚራኸና ሲጳራ ተያይዘው ከውሃው ሲውጡ ዶ/ር ዣንጊዳ ከቅርብ ከቆመችው ጄር33 ልዩ አውሮፕላን እያዘገመ ወጥቶ ተቃቅፌው የቆሙትን ጌራንና ሜሮዳን በፈገግታ ተመለከታቸው፡፡

ሚራኸ የባለጉጡን መስቀል የታችኛውን ጫፍና የቀይዋን ሳጥን ቁልፍ ሲያነፃጽር ከቆየ በኋላ የመስቀሉን ጫፍ በቀይዋ ሳጥን ቀዳዳ ከትቶ ሲያሽከረክረው ሳጥኗ በቅጽበት ከተፈተች፡፡ ቀይዋ ሳጥን ውስጥ ፬፻፬ የሚል የገጽ ቁጥር የተፃፈበት ከታላቁ መጽሐፍ ላይ የተገነጠለው ሰፊ የብራና ገጽ ተጣጥፎ ተቀምጧል፡፡ ስድስት ሜትር በአራት ሜትር የሆነውን የብራና ገጽ ታጋግዘዘው ሲዘርጉት በቀይ ቀለም የተሳለውንና የሰጠመው መርከብ ያለበትን ትክክለኛ የጣና ሐይቅ ከርሰ ምድር የሚያሳየውን ካርታ ሲያዩ ሁሉም በደስታ ፈነጠዙ ፡፡ የሰጠመው መርከብ ካርታ፡፡ ኢትዮጵያን የሚገነቡበት ካርታ፡፡

ቀና ብሎ ሁሉንም ተመለከታቸው ፡፡

"ዛሬ ሌሊት!" አለ ሚራኸ፡፡ "የሰጠመውን መርከብ እናወጣዋለን፡፡ በውስጡ ያለው ሀብትም . . ."



ጌራ ሀሳቡን ቀጠለለት፡፡ "የኢትዮጵያ ባቡር ሀዲዶች እንዲዘረጉ እናደርግበታለን፡፡ ሁሉም የኢትዮጵያ ግዛቶች በባቡር ሀዲድ ይገናኛሉ፡፡ የኢትዮጵያ ተራሮች እየተቦረቦሩ በውስጣቸው እንደጥይት የሚወነጨፉ ባቡሮች ያልፉባቸዋል፡፡ ከተሞች ከከተሞች በባቡር መስመር ይገናኛሉ፡፡ በኢትዮጵያ ገጠሮችም ባቡሮች እየተወነጨፉ ያልፋሉ፡፡ ................ያኔ የኢትዮጵያ የሕዝብ ለህዝብ ግንኙነትና ወንድማማችነት ወደ አንድነት ያመራል፡፡ ንግድ፣ ትምህርት፣ ነፃነት፣ ኢኮኖሚ፣ ሳይንስ፣..... ስልጣኔ ያብባል፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሁሉም ነገር ወደ መልካምነት ይቀየራል፡፡ ሳምንትና ከዚያ በላይ የሚጨርሰው ጉዞ በደቂቃዎች ውስጥ ይጠናቀቃል፡፡ ባቡሮችና የባቡር ሀዲዶች ብዙ ነገሮቻችንን ያስተሳስሩታል፡፡ ኢትዮጵያን ከአዝጋሚነት ወደ ተራማጅነት በፍጥነት እንለውጣታለን፡፡"

ሜሮዳ ፈገግ ብላ ወደ መሀላቸው ገባችና "ላፕቶፕሽን አንዴ ልታውሺኝ ትችያለሽ?" አለቻት ሲጳራን እጅዋን ይዛ፡፡ ሲጳራ ወደ አውሮፕላኗ እየሮጠች ሂዳ ላፕቶፕዋን ይዛ መጣችና ሰጠቻት፡፡

ሜሮዳ አንደኛውን የፊት ጥርሷን ይዛ ስትጎትት ከጥርሷ በላይ የተደረበ ሌላ ጥርስ የሚመስል ነገር ወለቀ፡፡ ሁሉም ባግራሞት ተመለከቷት፡፡ ያወለቀችው ጥርሷን ከላፕቶፑ ጋር አገናኘችውና ቁልፎቹን ስትጫን የኢንጂነር ሻጊዝ ፎቶ ግራፍ ስክሪኑ ላይ ወጣ፡፡ ቀጥሎ የትልቅ ህንፃ ፎቶ ተተካ፡፡ ከዛም በዘመናዊ መሳሪያዎች የተሞላ ሰፊ የምርምር ጣቢያ....በስራ የተጠመዱ ቢጫ መለዮ የለበሱ ሰዎች በቢጫ በርሜሎች የተሞሉ መተላለፊያዎች...አውቶማቲክ መሳሪያ የወደሩ ብረት ለበስ ሰዎች.....ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝ እጅጉ፡፡ ስክሪኑ ላይ ሻጊዝን ሲያዩ ሁሉም አፋቸውን ከፍተው ቀሩ፡፡

"ይህ ...ጥርስ አይደለም ስውር ካሜራ ነው" አለች ሜሮዳ፡፡

«እስከዛሬ ደረቅ ፈገግታ የምታሳይን ለዛ ነበር ለካ፡፡» ሚራኸ ራሱን እየነቀነቀ ተመለከታት፡፡

"ይህ የጥርስ ካሜራ ከኢንጂነር ሻጊዝ ጋር በቀጥታ የሚያገናኝ ሶፍት ዌር የተገጠመለት ነው፡፡ እንደምታዩት በየደቂቃው ኢንጂነሩ የት እንዳለ የሚጠቀሙ መረጃዎችን እየቀረጸ ይሰበስባል፡፡ ፍቅሬን ወደ ሀገሬ በማዞሬ ብቻ አሁን እነግራችኋለሁ፡፡ እስከ አሁን ተዋናይ ነበርኩ፡፡ ተውኔቱን በደንብ እንደተጫወትኩ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ኢንጂነሩን ከሚከታተሉት የሲአይኤ ኤጀንቶች መካከል አንዷ ነበርኩ፡፡ ይህ ካሜራ ተተክሎልኝ እሱን ሳጠምድ ኑሬአለሁ፡፡ አሁን ግን ለሀገሬ አጠምደዋለሁ፡፡ በዚህ የጥርስ ካሜራ እየተመራን ኢንጂነር ሻጊዝን ማምጣት እንችላለን፡፡" ጥርሷን ከላፕቶፑ ላይ ነቅላ መልሳ ከጥርሷ ላይ ሰካችው፡፡ ሁሉም እርስ በእርስ በትንግርት

ተያዩ፡፡ "አሁን ሙሉ ለሙሉ አብሬአችሁ ልሰራ ዝግጁ ነኝ፡፡ ምክንያቱም....." ጌራን ተመለከተችው፡፡ እሱም ፈገግ ብሎ በፍቅር ተመለከታት፡፡

"እኔ ደግሞ አንድ የምስራች ልነገራችሁ" አለ ጌራ ሁሉንም በፈካ ፊት እየቃኘ፡፡ "ከወደቀብን የሀዘን ጥላ ጀርባ ሌላ ብርሃን እንዳለ ልነገራችሁ ተዘጋጅቻለሁ፡፡ ከኢትዮጵያ ተራራዎች በአንዱ ውስጥ ቁጥር ሁለት ዶርቶጋዳ አለ፡፡ ቁጥር ሁለት ዶርቶጋዳ እየጠበቀን ነው፡፡ በዚያም በእሳት ከወደመብን ከቁጥር አንዱ ዶርቶጋዳ ውስጥ ይሰሩ ከነበሩ ሳይንቲስቶች በቁጥር የሚልቁ ሳይንቲስቶች ሥራቸውን እየሰሩ ነው፡፡ ወደዚያው በዶር 33 እንሄዳለን፡፡"

"አትቀልድ!" ሚራዥ ሀዘኑ እንደ ልብስ ወልቆ ሲወድቅ ተሰማው፡፡ ተስፋው መልሶ ሲያቆጠቁጥ ታወቀው፡፡

"ወደ ቁጥር ሁለት ዶርቶጋዳ ምናልባትም በዚህ ምሽት ስትገቡ የምታረጋግጡት ስለሆነ ያኔ ታምኑኛላችሁ፡፡ ምናልባት ዛሬ ማታ፡፡ አያችሁ....ዶርቶጋዳ ማለት ‹አናቅማማም አናፈገፍግም› ማለት ነው፡፡ ‹We never hesitate› ማለት ነው፡፡ ‹አናፈገፍግም› ማለት ነው፡፡ እንዲያውም የመዝሙሩ ሁለት ስንኞች ትርጉሙን የያዙ ናቸው......ልዘምርላችሁ....» አብረውት ባንድ ላይ እየዘመሩ ወደ ዶር33 ተከታትለው ገቡ፡፡...............

ዶርቶጋዳ
ዶርቶጋዳ..........................
ማንም ሰው ላይመጣ እኛን ለመለወጥ
አናፈገፍግም አናቅማማም ለለውጥ፡፡
ዶርቶጋዳ
ዶርቶጋዳ..........................
ያቀረቀርክበት አንገት ያስደፋህ ቀን
ነግቷል ብለህ ተነስ ፍዳና ሰቀቀን፡፡..............

ዶር33 አውሮፕላን ወደ ጣና ሐይቅ ስትበር የዓባይ ዳር ባለ ረጃጅም ክንፍ አሞራዎችም በህብረት መስመር ሠርተው ወደ ጣና እየተምዘገዘጉ ተከተሉአቸው፡፡

**@...በነሱ ውስጥ የሞቱት በኛ ውስጥ ህያዋን ናቸው፡፡.....@**



# ነፃ እይታ

እነሆ አንድ ምትሀታዊ ብዕር ከዚህ ትውልድ ሲመዘዝ ካላየ ላይ አንቀሳፍታ የቆየችው የስነ ፅሁፍ አድባር ከዱካኳ ነቃች፡፡ ይህን ስል ከዚህ በላይ የምልበት ቃል አጥቼ እንጂ ዶርቶጋዳ ከዚህም በላይ የሚባልለት ጉሩም ልብወለድ ነው፡፡ ስለዚህም ምትሀታዊ ብዕሩን ከመዘዘው ከይስማዕከ ይልቅ የፈራሁት አንባቢውን ነው፡፡ ምክንያቱም አንባቢው ይን ልብወለድ አንብቦ ሲጨርስ ለመጽሀፉ የማይመጥን የወረደ አስተያየት ሰጥተህል ብሎ እንዳያኮርፈኝ ሰግቼ ነው፡፡

ቢሆንም ስለ ዶርቶጋዳ ዝም አልልም፡፡ ጤነኛ አንባቢ ይህን ረዥም ልብወለድ አንብቦ ሲጨርስ ዝም አይልም፡፡ ወይ ተነስቶ ይሸልላል ወይም ለኢትዮጵያ የስነ ጽሁፍ አማልክት የምሥጋና መስዋዕት ያቀርባል፡፡ በዚህ ዘመን ይህን የመሰለ ጥምን ቆራጭ ልብወለድ ያነበበ ልበ ንጹህ ሰው በሀሴት መፍነክነኩ እሙን ነው፡፡ ለምን ቢባል ዶርቶጋዳ ለዚህ ዘመን ትውልድ ለሚቀጥለውም የተበረከተ እፁብ ድንቅ ገጸ በረከት ነው፡፡

ይህን ለማለት አፌን ያሞጠሞጥኩበትን ምክንያት መጽሀፉን አንብቦ አጣጥሞ የዘለቀ ሁሉ ይረዳልኛል፡፡ ስለ እውነት ተገድጄ እንጂ ለውዳሴ የሚፈጥን ልብ ኖሮኝም አይደለም፡፡ ይህን ልብወለድ ልዩ የሚያደርጉትን ብዙ ወርቃማ ባህርያት ለሰሉና እውነተኛ ለሆኑ ሃያስያን ትቼ አንዳንዶቹን ልጠቅስ፡፡ መሠረታዊዉ የዚህ ልብወለድ ስኬት እስካሁን ካነበብኳቸው የኢትዮጵያ ልብወለዶች በጭብጥ ልዩ ሆኖ መቅረቡ ነው፡፡ ከተነሳበት አቢይ ጭብጥ እስከ ንዑሳን ጭብጦቹ ስንወርድ እስካሁን ያልተነካን ድንግል ሃሣብ የያዘ ረቂቅ ሥራ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይዞት የተነሳውን ዓላማ በድል ተወጥቷል፡፡ ከገጸ ባህርያት ቀረፃ አንፃር ስናየው ደግሞ ፍንትው ብለው የሚታዩ፣ ነጥረው የተሳሉ፣ ከአእምሮ የማይጠፉ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ እንኳንስ አበይት ገጸ ባህርያት ሆነው የተሳሉት( ያን ሁላችንም የምናውቀውን ሰውዬ ጨምሮ) ታይተው የሚጠፉት አስተኔ ገጸ ባህርያቱ እንኳ ተቀርጸውብን የሚቀሩ ናቸው፡፡ ሚራዥ፣ሻጊዝ፣ጌራ፣ዠንጊዳ፣ሲዳራ፣ሜሮዳ፣አባ ዠንበሩ፣አናንያ...አባ ዲዲሞስ... ሞርሞርዲኖ፣ዲምላ......ሁሉም ልዩ ሆነው ለምክንያት የተቀረጹ ናቸው፡፡ አንድም በዘኣ( ሥራ አጥ) ገፀ ባህርይ አታገኙም፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የዚህ ልብወለድ ግሩም ጥንካሬው የገፀ ባህርያቱ ዲያሎግ ነው፡፡ ወመሽመጥ የሚቆርጡና ታሪኩን ወደፊት የሚያስወነጭፉ ንግግሮችን ከእያንዳንዱ ገፀ ባህርይ አፍ እናዳምጣለን፡፡ በትምህርተ ጥቅስ እየጨለፍን ማስታወሻችን ላይ

የምናስቀምጣቸው ልባችን ላይ የምንጽፋቸው ፍልስፍናዎች ከእያንዳንዱ ገጽ ላይ እናጣም። ከምንጠላቸው እኩይ ገፀ ባህርያት እንኳ የምንለቅመው ብዙ ቃል ይገኛል።

ሌላው ይስማዕከን ልዩ የሚያደርገው ፈጣን የአፃፃፍ ቴክኒኩ ነው። ገጸ ባህርያቱ ጎርደን እየተጎነጩ ቁጭ ብለው ነገር የሚጎነጉኑ ሳይሆኑ በዚህ የአፃፃፍ ፍጥነቱ እንደ አለላ ስፌት እያሰባጠረ የሚሰድራቸው ጠንካራ ሴራ-ሦቹ አንባቢን የሚያቁነጠንጡ ናቸው። በልዩ የሴራ አወቃቀር ጥበቡ የወዲያውን ከወዲህ እንደ ሽረሪት ድር ሸርቦ የአንባቢን አእምሮ ይፈትናል። ቆይቶ ደግሞ እራሱን አንባቢውን ሴራውን ይፈታ ዘንድ መረቡ ውስጥ ይዶለዋል። በእያንዳንዷ ሴራ ውስጥ የገባችው እያንዳንዷ ሰበዝ ያለ አንዳች ምክንያት አልተሰበዘችም።

ስለዚህም ይህን ልብወለድ የሚያነብ ሰው ወደሁዋላም ወደ ፊትም እየተንደረደረ ቋጠሮዎችን ሁሉ ለመፍታት ከገጸ ባህርያቱ ጋር ይወጣል ይወርዳል። ፈጠራ ይሏል ይሄ ነው! ምን ያህል እድለኞች ነን እናንተዬ!..... እነዚህ ሁሉ የጠቃቀስኳቸው መልካም ጎኖች የደራሲውንና የብዕሩን ምትሀተኛነት ብቻ አይደለም የሚያሳዩን። ይልቁንስ ዶርቶጋዳ ለነገም የሚሆን አንዣት የሚያርስ የፈጠራ ሥራ መሆኑን ነው።

ከነዚህ መሠረታዊ የልብወለዱ ባህርያት አለፍ ስንል የምናገኘው የደራሲውን ሳይንሳዊ የፈጠራ ክህሎት ነው። በዚህ ልብወለድ ውስጥ ከደራሲው ብሩህ አእምሮ የፈለቁት ሳይንሳዊ ግኝቶች በተጨባጭ ሊፈበረኩ፣ ሊደረጉ ሊከወኑ የሚችሉ ናቸው። በልዩ የአፃፃፍ ጥበቡ የፈጠረውን ሳይንሳዊ ጽንሰ ሀሳብ አንባቢን አስገድዶ ያሳምናል። ነገሬን ለመቋጨት ስጥር ሌላ ያላልኩት ሀሳብ እየተሰነቀረ እያስቸገረኝ ሳጠቃልለው.........ዶርቶጋዳ የሸፈተውን አንባቢ ልብ አማሎ ወደ ኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍ የሚዶል ድንቅ ሥራ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

ዶ/ር ዮፍታሄ ስዩም

ስለ መጽሐፉ ያለዎትን አስተያየት ከዚህ በታች በተጠቀሰው አድራሻ ቢልኩት ለደራሲው ይደርስልዎታል።

ይስማዕከ ወርቁ
ፖ.ሣ.ቁ 17486
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ